አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

[illegible]

[illegible]

[illegible] ትምህርት ክፍል [illegible] ምረቃ መርሃ ግብር

[illegible]

በ

[illegible]

[illegible]

[illegible]

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ቡዳ፣ ቡዳነትና ቡዳዊ ተረክ በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ

በ

ሙሉቀን ንጋቱ

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ቴዎድሮስ ገብሬ

ህዳር 2006 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ቡዳ፣ ቡዳነትና ቡዳዊ ተረክ በሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ


CLEARED FROM ILS LIBRARY

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ILS LIBRARY ADDIS ABABA

# የጥናቱ አካባቢ የካርታ መግለጫ

## የኢትዮጵያና የአማራ ክልል ካርታ




## የሰሜን ጎንደር ዞን ካርታ




ምንጭ፤ የሰሜን ጎንደር ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ


ምስጋና ........................................ ሀ
አጠቃሎ ........................................ ለ
1. መግቢያ ........................................ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 2
1.3. የጥናቱ አላማ ........................................ 3
1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ........................................ 4
1.5. የጥናቱ ወሰን ........................................ 4
1.6. የአጠናን ዘዴ ........................................ 4
1.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........................................ 5
1.6.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ........................................ 6
1.6.3. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ........................................ 6
1.7. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........................................ 8
2. የሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ ........................................ 10
2.1. የሰሜን ጎንደር መልክዓ ምድር፣ ቋንቋና ሐይማኖት ........................................ 10
2.2. ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ........................................ 10
2.3. ልማዳዊ እምነት ........................................ 10
2.4. ባህላዊ ጋብቻ ........................................ 13
3. የንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................................ 14
3.1. የንድፈ ሃሳብ ዳራ ........................................ 14
3.1.1. የቡዳ ምንነት ........................................ 14
3.1.2. የቡዳ ጥቃት ........................................ 15
3.1.3. የቡዳ ጥቃት የመከላከያ፣የመለያ፣ የመፈወሻ ዘዴዎች ........................................ 18
3.1.3.1. የቡዳ ጥቃት የመከላከያ ዘዴ ........................................ 18
3.1.3.2. የቡዳ ጥቃት የመለያ ዘዴዎች ........................................ 19
3.1.3.3. የቡዳ ጥቃት የመፈወሻ ዘዴዎች ........................................ 20
3.1.4. የቡዳ እምነት አጠናን ስልት ........................................ 22
3.1.5. የተረክ ምንነት ........................................ 23
3.1.6. የተረክ አጠናን ስልት ........................................ 24
3.1.7. ግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝ ተረኮች ........................................ 26
3.1.8. አውዳዊ የጥናት ፈለግ ........................................ 27
3.1.8.1. ባህላዊ አውድ ........................................ 28
3.1.8.2. ማህበራዊ አውድ ........................................ 29
3.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................................ 30
4. በሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ ቡዳ፣ ቡዳነትና ቡዳዊ ተረኮችን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................................ 33
4.1. ቡዳና ቡዳነት በሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ ........................................ 33
4.1.1. የቡዳ አገባባዊ ፍቺ በሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ ........................................ 33
4.1.2. የቡዳ ማህበረ-ባህላዊ ፍቺ በሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ ........................................ 34
4.1.3. የቡዳ ጥቃት በሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ ........................................ 35

4.1.3.1. በቡዳ የመጠቃት(የመበላት) ፅንሰ ሀሳብ በሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ. 36
4.1.3.2. የቡዳ ጥቃት ምንጭ በሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ ........................ 37
4.1.4. የቡዳ አይነቶች በሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ ........................ 40
4.1.4.1. የቡዳ አይነቶች ከቡዳነት አንጻር ........................ 40
4.1.4.1.1. የፅዕ ወይም የትምህርት ቡዳ ........................ 40
4.1.4.1.2. የዘር ቡዳ ........................ 42
4.1.4.1.3. የተፈጥሮ ቡዳ ........................ 45
4.1.4.2. የቡዳ አይነቶች ከሚያስከትሉት ጉዳት አንጻር ........................ 49
4.1.5. የቡዳ ጥቃት ተጋላጭነት ........................ 50
4.1.6. የቡዳ ጥቃት የመከላከያ ዘዴዎች ........................ 55
4.1.6.1. የቡዳ መድሃኒት ........................ 55
4.1.6.2. ክታብ (ጥፌት) ........................ 57
4.1.6.3. ጌጣጌጦችና ሌሎች ቁሶች ........................ 57
4.1.6.4. ጸሎት ........................ 60
4.1.6.5. አካላዊና ቃላዊ ገለጻ ........................ 61
4.1.7. የቡዳ ጥቃት የመለያ ዘዴ ........................ 64
4.1.8. የቡዳ ጥቃት የመፈወሻ ዘዴዎች ........................ 67
4.1.8.1. ልማዳዊ የቡዳ ጥቃት ፈዋሾችና የፈውስ ስርዓተ ክዋኔ ........................ 67
4.1.8.1.1. ልማዳዊ የቡዳ ጥቃት ፈዋሾች ........................ 67
4.1.8.1.2. ልማዳዊ የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ክዋኔ ........................ 69
4.1.8.2. ሐይማኖታዊ የቡዳ ጥቃት ፈዋሾችና የፈውስ ስርዓተ ክዋኔ ........................ 73
4.1.8.2.1. ሐይማኖታዊ የቡዳ ጥቃት ፈዋሾች ........................ 73
4.1.8.2.2. ሐይማኖታዊ የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓተ ክዋኔ ........................ 74
4.1.8.3. የማህበረሰባዊ እውቀት የቡዳ ጥቃት የፈውስ ዘዴ ........................ 78
4.2. ቡዳዊ ተረኮች በሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ ........................ 80
4.2.1. ግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝ ተረኮች በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ........................ 81
4.2.1.1. "በኔ የደረሰ" ተረኮች ........................ 81
4.2.1.2. "በአይኔ በብረቱ" ያየሁት ተረኮች ........................ 85
4.2.1.3. "ሲባል የሰማሁት" ተረኮች ........................ 86
4.2.1.4. "በተረት የማውቀው" ተረኮች ........................ 87
4.2.2. ቡዳዊ ተረኮች የሚቀርቡበት አውድ ........................ 88
4.2.3. ቡዳዊ ተረኮች የሚቀርቡበት ፋይዳ ........................ 89
4.3. የሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ በቡዳ እምነት እና ቡዳዊ ተረኮች ላይ ያለው አመለካከት ........................ 90
5. ማጠቃለያ ........................ 94
ዋቢ ፅሑፎች ........................ 96
አባሪዎች

# ምስጋና

ከሁሉም በላይ ያጋጠመኝን ችግር በመረዳትና ጊዜያቸውን በመሰዋት የፅሁፌን ረቂቅ በማረምና በማስተካከል ለተባበሩኝ አማካሪዬ እና አስተማሪዬ አቶ ቴዎድሮስ ገብሬ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። የአማካሪ ያህል በጥናቱ ዙሪያ በማወያየት፣ ለጥናቱ የሚያግዙ መጽሀፍትንና ጥናታዊ ጽሁፎችን በመስጠት የተባበሩኝ መምህሬን አቶ አብርሃም አለሙን አመሰግናለሁ

መረጃ ለማግኘት ይረዳኝ ዘንድ የትብብር ደብዳቤ የጻፉልኝን የዞንና የወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤቶች፣ የየወረዳዎቹ ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ሀላፊዎችን አመሰግናለሁ። የቡዳ ጥቃት የፈውስ ሥርዓተ ክዋኔ እንድመለከትና እንድቀርጽ አስፈላጊውን ትብብር ላደረጉልኝ ሊቀ ካህን መልአከ ሰላም ጌታሰው በላይ፣ አባ ፍስሀ አባተ፣ አቶ ወርቁ ታደሰ፣ አቶ ወንድማገኝ ጎሹ እና አቶ አደራጀው ባዬ እንዲሁም መረጃ አቀባዮቼን በሙሉ ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

በአጋጠመኝ የመኪና አደጋ ሳቢያ በተከሰተ ህመም የዚህን ጥናት ስራ ባቋረጥኩበት ጊዜ ደሞዜን በመክፈል በኋላም ውል እንዳድስ በማድረግ ጥናቱን እንዳጠናቅቅ ላደረገኝ ሰመራ ዩኒቨርሲቲን እንዲሁም ለህክምና የሚሆን የገንዘብ እገዛ ላደረጋችሁልኝ የዩኒቨርስቲው አስተዳደር ሰራተኞችና መምህራን አመሰግናለሁ። የእኔን ደህና መሆን በመመኘት ለስራዬ መቃናት በተለያዩ ነገሮች እገዛችሁ ላልተለየኝ ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ ተመስገን ታደሰ፣ ከድር ጋሻው፣ ታሪኩ ቦንሳ፣ እንዳለጌታ ከበደ፣ እንዱዓለም አባተ፣ በላይነህ ሀይሌ፣ አማረ ተሾመ፣ ኮማንደር ሙሃመድ  አመሰግናችኋለሁ።

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ የቡዳ እምነት እና ከእምነቱ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ተረኮችን መርምሮ መግለጽ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። ጥናቱ የፎክሎር የመስክ ምርምርን መሠረት አድርጎ የተካሄደ ነው። በዚህም የቡዳ ጥቃት ምንነት፣ የመከላከያ፣ የመፈወሻ ዘዴና ስርዓተ ክዋኔ እንዲሁም ቡዳዊ ተረክ ላይ እውቀትና ልምድ አላቸው ከተባሉ አዛውንቶች፣ ከቡዳ ጥቃት ፈዋሾችና ሰለባዎች፣ ከወጣቶች፣ ከተማሪዎች፣ ከሐይማኖት መሪዎችና ከባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊዎች በቃለመጠየቅ፣ በቡድን ውይይትና በአውዳዊ ምልከታ አማካይነት መረጃዎች ተሰብስበዋል። እነዚህ መረጃዎችም አውዳዊ ፈለግና የተረክ ትንታና ዘዴን በመከተል ተተንትነዋል። በጥናቱ የማኅበረሰቡ የቡዳ እምነትና ጥቃት ምንነት፣ የጥቃቱ አድራሾች እና ሰለባዎችን ማንነት፣ ምንጭና አይነት እንዲሁም የመከላከያ፣ የመለያ፣ የመፈወሻ ዘዴና ስርኣተ ክዋኔ ተተንትኖ ቀርቧል። ከዚህ በተጨማሪ የማህበረሰቡን ቡዳዊ ተረኮች አይነት፣ የሚቀርቡበት አውድና ፋይዳ ለመግለጽ ተሞክሯል።

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየውም በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት ቡዳ አንድ ሠው በስውር ጥበብ ወይም ሐይል አማካኝነት አይታው በሰው፣ በእንስሳ ወይም በግኡዝ ነገር ላይ ጥቃት ያስከትላል የሚል እምነት መሆኑ ታውቋል። በቡዳነት ተለይተው የሚታወቁ ግለሠቦችና ቡድኖች መኖሪያቸውና የቡዳነታቸው ምንጭም በዘር፣ በተፈጥሮና በእፅ የተገኘ እንደሆነ ታውቋል። ማህበረሰቡ ከቡዳ ጥቃት ራሱን ለመጠበቅና ለመፈወስ የተለያዩ ዘዴዎች የሚጠቀም ሲሆን የቡዳ መድሐኒት፣ ክታብ፣ ጉማጉጥና ቁስ፣ ፀሎት፣ አካላዊና ቃላዊ ገለጻ የቡዳ ጥቃት መከላከያ ዘዴዎች ሲሆኑ ሐይማኖታዊ፣ ልማዳዊ እና የማኅበረሰባዊ እውቀት የሚሉት ደግሞ የመፈወሻ ዘዴዎች ሆነው ተገኝተዋል።

ጥናቱ እንደሚያሳየው በማኅበረሰቡ ከቡዳ እምነት ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ተረኮች ግለሠባዊ ልምድና ገጠመኝ ያደረጉ "በኔ የደረሰ"፣ "በአይኔ በብረቱ ያየሁት"፣ "ሲባል የሰማሁት"ና "በተረት የማውቀው" በሚል የሚተረኩ መሆኑ ታውቋል። እነዚህ ተረኮችም በማኅበረሰቡ ዘንድ ልማዳዊ እምነቱን የማስረጽ፣ የቡዳ ጥቃትን የመከላከልና የመፈወስ ፋይዳ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል።

# 1. መግቢያ

ይህ ጥናት ዋቢዎችንና አባሪዎችን ሳይጨምር በአምስት ክፍሎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱን ዓላማ፣ የአጠናን ዘዴ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች በቅደም ተከተል የቀረበበት ነው። በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለ ሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ሐይማኖታዊ፣ ልማዳዊ እምነቶች፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች እንዲሁም የአካባቢው መልክዓ ምድራዊ ሁኔታዎች የተቃኙበት ነው።

በሦስተኛው ክፍል የቡዳ እምነትን እና ተረክን የተመለከቱ ፅንሰ ሐሳቦች እንዲሁም ከጥናቱ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው ጥናታዊ ፅሁፎች ተዳሰውበታል፡፡ በአራተኛው የጥናቱ ክፍል በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ በቡዳ፣ በቡዳነትና በቡዳዊ ተረኮች ላይ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል። በመጨረሻው ክፍል ደግሞ ጥናቱ ባለፈባቸው ሂደቶች ውስጥ የተገኙ ውጤቶችን በማጉላት ማጠቃለያ የቀረበበት ነው። በመጨረሻም ዋቢ መፃህፍትና አባሪዎች ቀርበዋል።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

"ሰዎች አጥብቀው የያዟቸው እምነቶችና ልማዶች መነሻ ምንጫቸው ምንድን ነው? ትርጉማቸውና ፍቻቸውስ ምን ይሆን? ሰዎች በአንድ ነገር ለምን ያምናሉ? የተወሰኑትንስ ለምን ይተዋሉ? ሳያምኑ መኖር ይችላሉ? ወዘተ የመሳሰሉ ጥያቄዎች በተለያዩ ፈላስፋዎች፣ ደራሲያን፣ ስነሰቦች (Anthropologists) እና ፎክሎሪኞች ጊዜ ወስደው የተመራመሩባቸውና ዛሬም የሚመራመሩባቸው ጥያቄዎች ናቸው" (ፈቃደ አዘዘ[1] 1991)፡፡ እምነት (እምነቶች) ደግሞ እምነቱን የምንፈጽማቸውን ድርጊቶችና ተግባራት ያጠቃልላል። በዚህም እምነት ለአንዳች ግብር ተብሎ ከሚከናወነው የሀገረሰባዊ እምነትና ልማዳዊ ድርጊት ወይም ባህርይ አንስቶ እስከ የልዕለ ሰብናና ልዕለ ተፈጥሮ እንዲሁም ሐይማኖታዊ አሳቤዎች ድረስ ያሉትን ያቅፋል ( Sims እና Martine, 2005: 54)።

[1] በዚህ ጥናት ውስጥ የሀገሬውሰዎ/ዋ ስም በአማርኛ ቋንቋ የተገለፀ ከሆነ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር የሚያሳይ ሲሆን በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈው ግን የአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር የሚያመለክት ነው። በጥናታዊ ፅሁፉ ውስጥ ስማቸው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጠቀሱ አጥኚዎች በሙሉ በእንግሊዝኛ ቀርበዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት በአብዛኛው የውጭ አጥኚዎችን በቃ ለይቶ ለማስቀመጥ ስለሚያስቸግር ነው።

እንደ ፈቃደ አዘዘ (1991) ገለጻ ሀገረሰባዊ እምነቶች ተለይተው በታወቁት የሐይማኖት መጽሐፍት ውስጥ ከታዘዘው ውጭ ሰዎች በራሳቸው (የሐይማኖቱ ተከታይ ሳይሆኑ ወይም መሆናቸው ሳይቋረጥ) የሚከተሏቸውን እምነቶችና የሚፈጽሟቸውን እምነታዊ ድርጊቶች ይመለከታል። ለምሳሌ በብዙዎቹ ሀገረሰባዊ እምነቶች ውስጥ አንዳች ሐይል አለው ተብሎ በሚታመን ሰው እይታ መጋለጥ ወይም የአይን ማረፊያ መሆን ጉዳት ያስከትላል በሚል ይታመናል (Dundes, 1992: vii, 258)። ይህ እምነት በተለያዩ ሀገራት ልማዳዊ እምነቶች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በተለያዩ ስያሜዎችም ይታወቃል። ከስያሜው በተጨማሪ የጉዳቱ አይነትና መንገድ፣ አድራሽና ተጋላጮች ማንነት እንዲሁም የመከላከያና የመፈወሻ ዘዴ እንደ ሀገራቱ ባህል፣ ልማድና እምነት ይለያያል። በቡዳ እምነት ላይ የሚካሄዱ ጥናቶች በቀጥታ ከነዚህ ጉዳዮች ጋር ይያያዛሉ።

እንደ Migliore (1981: 3) እና Ross (2010: 49) ጥናቶች ገለጻ እስካሁን በቡዳ እምነት ላይ የተካሄዱ የስነ ሰብዕና የፎክሎር ጥናቶች በአብዛኛው በቡዳ እምነት ስርዓት (belief system)፣ ባህላዊና ማህበራዊ ተግባር፣ ጥንተ-አመጣጥና የስርጭት መንገድ፣ታሪካዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ፣ ከሌሎች እምነቶችና ሚቶች (myths) [ተረኮች] ጋር ያለው ትስስር ላይ ያተኩራሉ ። ይህ ጥናትም የሰሜን ጉንደር ማኅበረሰብ ለቡዳ እምነት ያለውን አመለካከት፣ የቡዳ ጥቃት ምንነት፣ የመከላከያና የመፈወሻ ዘዴ እንዲሁም የቡዳ እምነትን አስመልክቶ በሚተረኩ ትረካዎች ላይ ያተኩራል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ተወልጄ ባደኩበት አካባቢ ስለ ቡዳ ብዙ ይባላል። በልጅነቴ በቡዳነት የተፈረጁና በቡዳ ተበሉ የተባሉ ሰዎችን ተመልክቻለሁ። ብዙ ጊዜ ታናሽ እህቴ ቡዳ በላት ተብሎ ሰዎች ጭንቅላቷ ላይ ውሃ እየደፉ፣ቢጋለ ብረት እያስፈራሩና የመኪና ጉማ እያጨሱ፣ በጭሱም እያፈኑ ሲያስለፈልፏት አስታውሳለሁ። እንዲሁም የመሰናዶ ትምህርት ቤትና የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪ በነበርኩበት ወቅት ለእረፍት ወደ ቤተሰብ በሄድኩ ቁጥር እናቴ ከቤት እንዳልወጣ ታደርገኝ ነበር። "አደራህን ልጄ ላብህ ሳይደርቅና አየሩን ሳትላመድ ከቤት እንዳትወጣ!" እያለች ታስጠነቅቀኛለች። "ዘንድሮ ሳር ቅጠሉ ሁሉ ቡዳ ሆኗል፤ እገሌን ሰላም እንዳትል፤ ከእገሌ ቤት እንዳትሄድ፣ ከእገሌ ልጆች ጋር እንዳትጫወት" በማለት ትመክረኝ ነበር። እኔም ትዕዛዟን አክብሬና ምክሯን ተቀብየ ከቤት ስቀመጥ በጥያቄ አጣድፋት ነበር። ትሰጠኝ ከነበሩት መልሶች ውስጥ "እገሊትን የበላት ቡዳ ነው

ምክንያቱም 'ለፍልፋለች'[2] እንቶኔ ለሃብት ሲል ቡዳ ሆኗል። እገሌም ቡዳ መሆኑ አገር ምድሩ ያውቃል ወደ ሃያ የሚሆን ሰው 'ለፍልፎበታል'" የሚሉ ነበሩ።

ከዚህ በተጨማሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር በምከታተልበት ወቅት በአጋጣሚ ክፍል ውስጥ ስለ ሀገረሰባዊ እምነት በተለይ ስለ ቡዳ ስንነጋገር አንዷ የክፍል ጓደኛዬ "አራት ወንድሞቼን በሞት ያጣሁት በቡዳ ነው! ቡዳ ስለመኖሩ በትክክል አምናለሁ" በማለት ስትናገር ሰማሁ። በወቅቱ እኔም ሆንኩ ሌሎች ተማሪዎች ቡዳን በተመለከተ ያለንን አመለካከት ተናገርን። በጊዜው ያስተምሩን የነበሩት መምህርም አንድ ማኅበረሰብ ለቡዳ እምነት ያለውን አመለካከት ማጥናት እንደሚቻል ጥቆማ ሰጡ። በዚህ ጊዜ ይህንን ጉዳይ ማጥናት እንደሚቻል ሃሳብ መጣልኝ። በኋላም ክፍል ውስጥ በተሰነዘረው ሃሳብ፣ ከልጅነቴ ጀምሮ እናቴ ስለቡዳ ትተርክልኝ በነበረውና እኔ በማውቀው መነሻነት ይህንን ጥናት ለመስራት ወሰንኩ። በዚህም የቡዳ እምነት ምንድን ነው? ቡዳስ ማን ነው? የቡዳ መከላከያና መፈወሻ መንገዶች ምንድን ናቸው? ቡዳ በተባለው ሰው ላይ የሚለፈለፍበትና ቡዳ የተበላ ሰው የሚለፈልፈው ነገር ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በተለይ "መለፍለፍ" የሚለው ጉዳይና ማኅበረሰቡ "የቡዳ ታሪክ" በሚል የሚታርኳቸው ትረካዎች ከእምነቱ በተጨማሪ ቡዳዊ ተረኮችን እንዳጠና ምክንያት ሆነውኛል።

## 1.3. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በተጠኚ ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ውስጥ የቡዳ እምነትና ከእምነቱ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ትረካዎችን መመርመር ነው። ይህን አብይ አላማ ለማሳካትም ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች አሉት።

- በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት ውስጥ የቡዳን እምነት ምንነት መግለጽ።
- በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት መሰረት በቡዳነት የሚጠረጠሩ ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን ማንነት ማስረዳት።
- በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት መሰረት የቡዳ ጥቃትና መከላከያ መንገዶችን መተንተን።
- በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት መሰረት የቡዳ ጥቃት መፈወሻ ዘዴዎችና ስርዓተ ከዋኒያቸውን መመርመር።

[2] በቡዳ የተበላ ሰው በቡዳው መንፈስ ሆኖ በቡዳ ፈዋሹ (በአስለፍላፊው) ወይም በጸበል አጥማቂው አማካኝነት ስለ በላው ቡዳ (ሰው) የሚጠየቀውን ሁሉ መናገር (መቶረክ)።

- ማኅበረሰቡ በቡዳ እምነት ላይ የሚያቀርባቸውን የተረክ አይነቶች ከማኅበረሰቡ ግላዊ ልምድና ገጠመኝ አኳያ መተንተን፡፡
- ማኅበረሰቡ በቡዳ እምነት ላይ የሚያቀርባቸውን ተረኮች አውድ፣ ስያሜና ፋይዳ መግለፅ፡፡

## 1.4. ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

- በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት ውስጥ ‹‹ቡዳ›› የሚለው አሳቤ እንዴት ይገለጻል?
- በማኅበረሰቡ በቡዳነት የሚጠረጠሩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እነማን ናቸው? ቡዳ ስለመሆናቸው የሚቀርቡ አስረጅዎችስ ምንድን ናቸው?
- ለማኅበረሰቡ "በቡዳ መበላት" ማለት ምን ማለት ነው? ቡዳውስ ማንን፣ ለምን፣ እንዴትና መቼ ይበላል?
- ማኅበረሰቡ የቡዳ ጥቃትን ለመከላከል፣ ለመለየትና ለመፈወስ የሚፈጽማቸው ስርዓተ ከዋኔዎች ምን ምን ናቸው?
- ማኅበረሰቡ የቡዳን እምነት በተመለከተ የሚተርካቸው ተረኮች አሉት ወይ? ካሉት ምን በማለት እና ለምን ፋይዳ ይተርካቸዋል?

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በሰሜን ጐንደር ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ውስጥ በቡዳ እምነትና ከእምነቱ ጋር ተያይዘው በሚተረኩ ተረኮች ላይ ያተኩራል፡፡ በሌላ በኩል የዚህ ጥናት የትኩረት ቦታ በሰሜን ጐንደር መስተዳደር ዞን በሚገኙ ሦስት ወረዳዎች ማለትም ጐንደር ዙሪያ፣ ደንቢያና ጣቁሳ ወረዳ ላይ ነው፡፡ እነዚህ ወረዳዎች የተመረጡበት ምክንያት ከዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ በተገኘ መረጃ መሰረት ስለ ቡዳ በብዛት የሚወራባቸውና ባህላዊና ሐይማኖታዊ የቡዳ መፈወሻ ተቋማት ያሉባቸው በመሆናቸው ነው፡፡

## 1.6. የአጠናን ዘዴ

በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና መሳሪያዎች እንዲሁም የመተንተኛ ንድፈ ሃሳብ ስልቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

የቤተ መዛግብት ፍተሻ፣ ምልከታ፣ ቃለመጠየቅና የቡድን ውይይት የዚህ ጥናት የመረጃ ማመንጫ ዘዴዎች ናቸው።

የመጀመሪያው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የቤተ መዛግብት ፍተሻ ነው። በቤተ መዛግብት ፍተሻና ትንተና አማካይነት ከመስክ በፊት፣ ጊዜና በኋላ ስለተጠኚ ማኅበረሰቡ አካባቢ ምንነት፣ የትነት እና አጠቃላይ ለጥናቱ አጋዥ የሆኑ መረጃዎች፣ ከጥናቱ ጋር የተያያዙ አሳቤዎችና የትንተና ማኄጃ ንድፈ ሃሳባዊ ዳራዎች ተዳሰዋል። እንዲሁም ልማዳዊ እምነቶችን በተለይም ቡዳን አስመልክተው የተደረጉ ጥናቶች፣ መፅሔቶችና መጽሐፎች ተቃኝተዋል።

የዚህ ጥናት ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ-መጠይቅ ነው። ቃለ-መጠይቅ ፎክሎረኛው የመረጃ አቀባዮችን ግለሰባዊ ታሪክና መረጃ፣ ለፎክሎራዊው ጉዳይ ያላቸው ዕውቀት፣ ስሜትና ፍቺ እንዲሁም የፎክሎሩን ጥበባዊ አቀራረብ፣ የአተራረክ መንገድ፣ የተስተላለፎት ሂደትና ሌሎች መረጃዎችን የማግኛ ዘዴ ነው (Goldstain, 1964: 106-107)። ይህንን ዘዴ በመጠቀም የቡዳን ልማዳዊ እምነት አስመልክቶ የተለያዩ የተጠኚ ማኅበረሰብ አባላት ያላቸውን እውቀት፣ አመለካከት፣ ስሜትና ፍቺ መረጃ ማግኘት ተችሏል።

ከዚህ በተጨማሪ ልምድና ገጠመኝ መሠረት በማድረግ *"በእኔ የደረሰ"*፣ *"በአይኔ በብረቱ ያየሁት"*፣ *"ሲባል የሰማሁት"* እና *"በተረት የማውቀው"* በሚል የሚተርኳቸውን "የቡዳ ታሪኮች"[3] በቃለ-መጠይቅ አማካይነት ተሰብስበዋል። የጥያቄው አይነትም ክፍት (open ended) ሲሆን የተከናወነውም ቀድመው ከተዘጋጁት ጥያቄዎች በተጨማሪ በትረካ ወቅት ሁነት በሚጠራቸው አገረ መንገዳዊ ጥያቄዎች አማካይነት አጠናክሮ በመጠየቅ ነው። ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብ መጠየቅ አስቸጋሪ በሆነበትም ጊዜ ከሰዎቹ ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር፣ ሲያወሩ አብሮ በማውራትና ጉዳዩን አስስልሶ በመጠየቅ[4] መረጃዎች ተገኝተዋል።

ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ምልከታ ሲሆን ምልከታ አጥኚው ፎክሎሩ በሚከወንበት አውድ በመገኘት የስሜት ህዋሳቶቹን በማስተሳሰር መረጃ የሚያገኝበት ዘዴ ነው። በዚህ መሠረትም በቡዳ የተበላ ሰው የሚያሳየውን ባህሪና የሚለፈልፋቸውን ጉዳዮች እንዲሁም ልማዳዊና

---

[3] የማኅበረሰቡ አባላት ስለቡዳ የሚተርኳትን ማንኛውንም ትረካ "የቡዳ ታሪክ" በማለት ይጠሩታል።

[4] የማኅበረሰቡ ዘገድ አንዳንድ ሰዎች ስለ ቡዳ ማውራትና በቡዳ ማመን ከኋላ ልማዳዊ ድርጊትና ከስም ማጥፋት ወንጀል ጋር የሚያያዙ የሚያስቀጣ በመሆኑ ስለ ቡዳ ለማውራት፣መረጃ ለመስጠትና ለመቀረፅ ፈቃደኝነታቸው አነስተኛ ነበር ።

ሃይማኖታዊ የቡዳ ጥቃት መፈወሻ ስርዓተ ክዋኔዎችን በፀበል ቦታ እና በየቡዳ ጥቃት ፈዋሹ ቤት በመገኘት ተፈጥሯዊውን አውድና ክዋኔ በመመልከት መረጃ ማግኘት ተችሏል።

አራተኛው የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የቡድን ውይይት ነው። ፎክሎር በሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ ያለውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እስካልዘነጋን ድረስ ማንኛውንም ሰው በፎክሎራዊ ጉዳዮች ላይ በመረጃ አቀባይነት ልንጠቀም እንችላለን። ነገር ግን ሰዎች ለፎክሎራዊ ጉዳዮች ካላቸው ቅርበት፣ ልምድና ገጠመኝ እንዲሁም የመከወንና የመግለፅ ብቃት መለያየት ምክንያት የተሻለውን መምረጥ እንደሚያስፈልግ Bartis (2002: 18) ይገልጻሉ። በመሆኑም በየወረዳዎቹ የባህልና ቱሪዝም እና አስተዳደር ጽህፈት ቤቶች በተገኘ መረጃ (ጥቆምታ) መሰረት የአካባቢውን ታሪክ፣ ባህልና እምነት ያውቃሉ ከተባሉ የሃገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና እናቶችና ሌሎች ሰዎች ጋር የቡድን ውይይት ተካሂዷል። በቡድን ውይይቱ አማካይነትም የቡዳን ምንነት፣ ጥንተ አመጣጥ፣ የመከላከያና የመፈወሻ ዘዴ፣ በቡዳ የተበላ ሰው የሚያሳየው ባህሪና የሚለፈልፈውን ጉዳይ በተመለከተ መረጃ ተሰብስቧል[5]።

### 1.6.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

እንደ Sims እና Martine (2005: 205) አገላለፅ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ዋናውና ጠቃሚው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የአጥኚው የስሜት ሕዋሳትና የማስታወስ ችሎታ ቢሆንም ከዚህ በተጨማሪ አጥኚው መረጃ የሚሰበስብባቸው መሳሪያዎች መኖራቸውን ይጠቅሳሉ። በመሆኑም በዚህ ጥናት የተገኙ መረጃዎች በቪዲዮ ካሜራ ተቀርጸው፣ በፎቶግራፍ ተነስተው፣ በመቅረጸ ድምጽ ተቀድተውና በማስታወሻ ተጽፈው እንዲሁም ተሰንደው ተይዘዋል።

### 1.6.3. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ይህ ጥናት በገላጭ-ተንታኝ (descriptive analysis) መንገድ የቀረበ ሲሆን አውዳዊ ፈለግ (contextual approach) እና ስነ ተረክ (narratology) የተሰኙ ንድፈ ሃሳቦችን ተከትሏል። ከነዚህ ንድፈ ሃሳቦች በተገኙ አውዳዊ ትንታኔ (contextual analysis) እና የተረክ ትንተና (narrative analysis) ዘዴዎች አማካይነት የጥናቱ መረጃዎች ተተንትነዋል።

---

[5] ከወረዳዎቹ የማህበረሰብ ሽማግሌዎች፣ የሐይማኖት አባቶችና እናቶች በተደረገው ውይይትም የቡዳ ጥቃት ፈውስ የሚያስገኙትን ቦታዎችንና ፈውስ የሚያስገኙትን ሰዎችን ለማወቅ ተችሏል። በዚህም በቦታዎቹ በመገኘትና ፈዋሽና ተፈዋሽ ሰዎችን በማናገር በምልከታና በቃለ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል።

Bauman (1986) እና Ben Amos (1993) እንደ የፎክሎር አጥኚ ከመስክ የሰበሰባቸውን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ከበቀሉበት ማህበራዊና ባህላዊ ገፅታ አኳያ ለመመርመር አውዳዊ ፈለግ የጥናት አቅጣጫ መከተል ጠቃሚነት እንዳለው ይገልፃሉ። በተለይ Bauman (1983, 263) አጥኚው ከመስክ ያገኛቸውን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ሊያደራጅባቸውና ስርዓት ሊያስይዝባቸው የሚችሉ ባህላዊ አውድ (cultural context) እና ማህበራዊ አውድ (social context) የተባሉ ሁለት ሰፋፊና በስራቸው ሌሎች ንዑሳን ክፍሎችን ያቀፉ የአውዳዊ ጥናትና ትንታኔ ስልቶች መኖራቸውን ይገልጻሉ። በመሆኑም Bauman የገለጹዋቸው ሁለት ሰፋፊ ክፍሎችና በውስጣቸው የቀረቡ ንዑሳን ምድቦች በዚህ ጥናት ለተሰበሰቡ መረጃዎች መተንተኛ መንገድ ሆነዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ በማኅበረሰቡ በቡዳ ላይ የሚቀርቡ ተረኮች ቅርፅና ይዘት፣ የሚተረኩበት አውድ፣ ምክንያትና ተግባር ለመተንተን የተረክ ትንተና ስልትን ተከትሏል። Ben Amos (1975) የአፍሪካ ፎክሎር ቀድመው ከተጻፉ ንድፈ ሃሳቦች ይልቅ ፎክሎሩ በበቀለበት ማህበራዊና ባህላዊ ገጽታ አንጻር መጠናት እንዳለበት ይገልጻሉ። እኚህ ምሁር ተመራማሪዎች ከመስክ መረጃዎችን ሲሰበስቡ (ሲያደራጁና ሲተነትኑ) ቀዩአዊ ዘውጎችን[6] ማጤን እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ። እንዲሁም የፎክሎሩ ባለቤት የሆነው ማኅበረሰብ ለፎክሎራዊ ጉዳዩ ካለው አእምሯዊ ግንዛቤ (cognitive)፣ አንጓለጽ (expressive) እና ማህበራዊ ገጽታ (social feature) አኳያ መመርመር አለበት ይላሉ።

በመሆኑም በ Ben Amos (1975) የምደባ መስፈርት አገራዊ ስያሜዎችንና ክፍፍሎሽን (local terminologies and taxonomies) መሰረት በማድረግ በቡዳ ላይ የሚቀርቡ ተረኮች ከተጠኚው ማኅበረሰብ ግላዊ ልምድና ገጠመኝ (personal experience narrative) አንጻር ተከፋፍለው ተተንትነዋል።

---

[6] ቀደሞ በውን የቋንቋው ተናጋሪዎች ወይም የፎክሎሩ ባለቤቶች ልዩ ልዩ ፎክሎራዊ አይነቶችን (አንዱን ፎክሎራዊ ቅርጽ ወይም አይነት ከሌላው ለይተው) የሚጠሩበትን፣ የሚገልጹበትን፣ የሚበይኑበትን፣ የሚያደራጁበትንና የሚሰይሙበትን አገርኛ (አካባቢያዊ) የእውቀት ስርዓት ይመለከታል።

## 1.7. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

"ቡዳ፣ ቡዳነትና ቡዳዊ ተረክ በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ" የሚለውን ጥናት ሳጠና በዋናነት ሁለት ችግሮች አጋጥመውኝ ነበር፡፡ እነዚህም መረጃ አቀባዮቼ በግልም ሆነ በቡድን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን እና ጥናቱን በታቀደለት ጊዜ አለመጨረስ ናቸው፡፡

በማኅበረሰቡ ዘንድ የቡዳ እምነት ከማህበረ- ባህላዊ በተጨማሪ አስተዳደራዊ (ፖለቲካዊ) ችግር የሚንጸባረቅበት ነው፡፡ በመንግስት ደረጃ የቡዳ እምነት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በዚህም አንድ ሰው ሌላን ሰው በቡዳነት መጠርጠር፣ ቡዳ ማለትና አንድን ሰው ከቡዳነት ጋር አያይዞ ማውራት ከስም ማጥፋት ወንጀል ጋር ይያያዛል፡፡ ይህንን ሲያደርግ የተገኘም በህግ ይጠየቃል፡፡ ማኅበረሰቡ ደግሞ በቡዳ ያምናል፡፡ ቡዳ የሚባሉት ሰዎች ልጆቻችንን ይበላሉ፣ ሀብት ንብረታችንን በስውር ጥበብ ወይም አስማታዊ ሀይል ያወድማሉ የሚል እምነት አለው፡፡ በዚህ የተነሳ ማኅበረሰቡ በቡዳነት የሚጠረጠሩ ሰዎችን ያገላል፣ "ቡዳም" ይላቸዋል፡፡

ከዚህ በተቃራኒ መንግስት ሰው ሰውን አይበላም፣ ይህ ስም ማጥፋት ነው በማለት ቡዳ የሚሉና በቡዳነት የሚጠረጠሩ ሰዎችን የሚያገሉ፣ የሚሳደቡ፣ የሚያስፈራሩ ሰዎችን በህግ ይጠይቃል፡፡ በዚህ የተነሳም በማኅበረሰቡና በመንግስታዊ አካላት መካከል ሁልጊዜ አለመግባባት እንደሚፈጠር በሰሜን ጎንደር ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የባህል ጥናትና ልማት አጠቃላይ የስራ ሂደት ሃላፊ የሆኑት አቶ ያለው አዲስ ይገልጻሉ፡፡[1]

እኔም በቡዳ እምነት ላይ ጥናት ለማካሄድ መምጣቴን የሚያመለክት ህጋዊ ደብዳቤ በማሳይበት ጊዜ አብዛኛዎቹ የማኅበረሰቡ አባላት እንደ አንድ የመንግስት አካል በመቁጠርና በመፍራት መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ የማኅበረሰቡ ሽማግሌዎችም አካባቢውን ለጥናት መምረጤ አካባቢያቸው እንደ "የቡዳ አገር" የተቆጠረና አካባቢያዊ ማንነታቸውም ዝቅ እንዳለ አስበው ነበር፡፡

በተለይ በጣቁሳ ወረዳ ከአካባቢው ሽማግሌዎች ጋር በነበረኝ ውይይት አንድ በአካባቢው የታወቁ ሽማግሌ "በመጀመሪያ ደረጃ እንዴት ጎጃምን አልፈህ ጎንደር ጣቁሳ ላይ ስለ ቡዳ ለመጠየቅና

---

[1] በመስክ ቆይታዩ ከማኅበረሰቡ የተለያዩ አባላት ጋር ባደረኩት ወይይትና ቃለመጠይቅ መረዳት እንደቻልኩት አንዳንድ በቡዳነት የሚጠረጠሩ ሰዎች በውስጥ የሚጠረጥሯቸውን ሰዎች በስም ማጥፋት ወንጀል የሚከሱ እንዳሉና ችግሩንም በሽማግሌ እንደሚፈታ ነግረውኛል። እንዲሁም በየወረዳዎቹ በተለያዩ ሃላፊነት የሰሩና እየሰሩ ያሉ የማህበረሰቡ አባላት እንደሚገልጹት ማህበረሰቡ በውስጥ የሚጠረጠሩ ሰዎች ጥቃት አደረሰብን በሚል በሚያስኗቸው አንዳንዶም ጥቃት በሚያደርሱባቸው ግዜ ተጠርጣሪዎችን ወደ ሌላ ቦታ ወይም ሀገር የሚያባርሯቸውን መሆኑን የተለያዩ የእብነት (አስረጅ) ትረካዎችን በማቅረብ ይገልጻሉ።

ለማጥናት መጣህ?" የሚል ሞጋች የማንነት ጥያቄ አቅርበውልኝ ነበር።[8] ሌሎች የማኅበረሰቡ አባላት ደግሞ በማኅበረሰቡ የተከሰተውን የቡዳ ችግር ለመፍታት እንደመጣሁ ገምተው ነበር። በዚህ ሳቢያ ለጥናቱ የሚያግዘኝን የተሟላ መረጃ እንዳላገኝ አግዶኝ ነበር።

በኋላም ማኅበረሰቡ ለቡዳ እምነት ያለውን አመለካከት በመመርመር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ለመስራት የመጣሁ መሆኔን ለማኅበረሰቡ አባላትና ለሽማግሌዎች በውይይት ለማሳመን ሞከርኩ። በውይይቱም ቡዳ መኖር አለመኖሩን አረጋግጬ ለመንግስትም ሆነ ለማኅበረሰቡ ለማሳወቅ፤ ቡዳ እያሉ የሚሳደቡ ወይም የቡዳ ጥቃት የሚያደርሱ ሰዎችን ለማጋለጥና ለፍርድ ለማቅረብ አለመምጣቴን በማስገንዘብና በማግባባት መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ። አካባቢውም ለጥናት የተመረጠበት ምክንያት ስለቡዳ ብዙ የሚወራበት፤ ሀይማኖታዊና ልማዳዊ የቡዳ ጥቃት መፈወሻ ተቋማት ያሉበት፤ እኔም የማውቀውና የኖርኩበት መሆኑን በመግለጽ የተከሰተውን ችግር ለመፍታት ችያለሁ።

ሁለተኛው በዚህ ጥናት ወቅት ያጋጠመኝ ችግር ጥናቱን በታቀደለት ጊዜ አለማጠናቀቄ ነው። የጥናቱ ርዕስ የፀደቀው ሚያዝያ 2003 ዓ.ም ነበር። በወቅቱ ባጋጠመኝ የጊዜ እጥረትና የመረጃ ክፍተት ምክንያት ለ2004 ዓ.ም የመጀመሪያ ሴሚስተር መረጃዎችን አጠናክሬ ለመስራት ተመዝግቤ ነበር። ይሁን እንጂ በመኪና አደጋ ሳቢያ በተከሰተብኝ የጀርባ ህመም ጥናቱን እንዳቋርጥ ተገድጃለሁ። ከረጅም ጊዜ ህክምና በኋላም ጥናቱን ለማጠናቀቅ ችያለሁ።

---

[8] በተለምዶ በአካባቢው ማኅበረሰብ ነቾም "የቡዳ አገር" ነው ተብሎ ይወራል። ይህንን የሚያመለክቱ ቃላዊ ግጥሞችም በአካባቢው ይዜማሉ። ከነዚህ ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፤

1. [illegible]
2. [illegible]
3. [illegible]

## 2. የሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ስለ ሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ሐይማኖታዊ፣ ልማዳዊ እምነቶች፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች እንዲሁም የአካባቢው መልክዓ ምድራዊ ሁኔታዎች ተዳሰዋል።

### 2.1. የሰሜን ጎንደር መልክዓ ምድር፣ ቋንቋና ሐይማኖት

የሰሜን ጎንደር ዞን በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሚገኝ ሲሆን በሰሜን የትግራይ ክልል በደቡብ የቤንሻንጉል ክልል፣ በምዕራብ ሱዳን፣ በምስራቅ ዋግ ህምራ ዞን ያዋስኑታል። የዞኑ አጠቃላይ ስፋትም 45,946.63 ስ.ኪ.ሜ ይሸፍናል። ዞኑ በ23 ወረዳዎች እና በ579 ቀበሌዎች የተከፋፈለ ነው። ዞኑ ከአዲስ አበባ 732 ኪሎ ሜትር ከክልሉ ዋና ከተማ ከባህር ዳር ደግሞ 180 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል (የሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ዓመታዊ ስታስቲካል መጽሄት 2004)።

ሰሜን ጎንደር በአመዛኙ የአማራ ብሄረሰብ ተወላጆች የሚገኙበት ሲሆን ሌሎች ብሄረሰቦችም ይኖሩበታል። የዞኑ መግባቢያና የስራ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን አልፎ አልፎ በዞኑ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ትግርኛ ይነገራል።

በዞኑ 95.38% ህዝብ የክርስትና እምነት ተከታይ ሲሆን 4.54% ህዝብ ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታይ ነው።

### 2.2. ኢኮኖሚያዊ ገጽታ

የሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ ዓመታዊ ስታስቲካል መጽሄት (2004፣3) እንደሚያመለክተው የዞኑ ህዝብ ዋና መተዳደሪያ ግብርና እና ንግድ ነው። ይህም በመቶኛ ሲሰላ ግብርና ዘጠና ከመቶ ሲይዝ ንግድ አስር በመቶ ይሸፍናል። በግብርናው መስክ የእርሻና የእንስሳት ሃብት ልማት ይከናወናል፡፡

### 2.3. ልማዳዊ እምነት

በሰሜን ጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ውስጥ ደብተራዎች፣ የባህል ህክምና አዋቂዎችና ፀበል አጥማቂዎች ማንም ሠው ሊያከናውናቸው የማይችሉ ልዩ ልዩ ተአምራትንና ተግባራትን በመለኮታዊ ወይም በአስማታዊ ሀይል እገዛ ያከናውናሉ ተብሎ ይታመናል። እነዚህ

አካላት የሚፈፅሟቸው ተአምራትና ተግባራት በማኅበረሰቡ ለሚጠቀሱ ሀገረሰባዊ እምነቶች ምንጭም ተደርገው ይቆጠራሉ። እነዚህ አካላት የሚያከናውኗቸውን ተግባራትም በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

አንደኛው ተግባር ለሰዎች ሀይልንና ጥበብን መስጠት እና በሰዎች ላይ ጉዳት ማድረስ ነው። በተጠኚ ማኅበረሰብ ዘንድ ደብተራዎችና መድሃኒት አዋቂዎች ለአንድ ሠው ያሻውን ሀይል የመስጠትና በሰው ወይም በራሳቸው ፈቃድና ትዕዛዝ ጉዳት የማድረስ ሀይል አላቸው ተብሎ ይታመናል።

እንደማኅበረሰቡ የእምነት አተያይ አንድ ሠው በአቋራጭ ለመክበር፣ ተወዳጅና ዝነኛ ለመሆን፣ ለመሾምና በቀላሉ ተሟግቶ ለመርታት፣ አንጣጥሮ ለመተኮስ፣ ያሻውን ሴት እንድታፈቅረውና እንድታገባው ለማማለል[9]፣ ትምህርት እንዲገባው፣ የሠው አይን እንዳይፈራ (እንዳያፍር) ወዘተ...ለማድረግ ከደብተራዎችና ከባህል መድሃኒት አዋቂዎች ይሄዳል። እነዚህ አካላት የሚጠይቁትን ክፍያ ወይም ስጦታ በመስጠትም የፈለገውን ሀይል ያገኛል፣ ስኬታማም ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

ከዚህ በተቃራኒ እነዚህ አካላት ለአንድ ሠው ስኬትን ከማጎናፀፍ ባለፈ ስኬት አልባ ማድረግ ይችላሉ በሚል ማኅበረሰቡ ያምናል። ይህም አንድ ሰው የተቀናቀኑ ሀብት እንዲቀንስ፣ ትዳሩ እንዲናጋ፣ ተሟግቶ እንዳይረታ፣ አዕምሮው ለትምህርት እንዳይሰላ፣ ቡዳ እንዲሆን ከፍ ሲልም ለእብደትና ለሞት እንዲዳረግ ከላይ ለተጠቀሱት አካላት ገንዘብም ሆነ ስጦታ በመስጠት ያሰበውን ጉዳት ወይም ጥቃት ማድረስ ይችላል ተብሎ ይታመናል።

ይህ በደብተራዎችና በባህላዊ መድሐኒት አዋቂዎች እርዳታና ትዕዛዝ የሚፈጸም ስኬትንና ህልውናን የማሳጣት ተግባር እፅ ማጠጣት፣ ውለሽና ድግምት[10] ይባላል። በማኅበረሰቡም የዚህ ሰለባ የሆነ ሰው "የተቋሰበት"፣ "የተደገመበት"፣ "እፅ" ወይም "መተት" የተደረገበት ይባላል። ከዚህ ጋር ተይይዞ በተለይ በደብተራዎች አማካይነት ለስኬት ተብለው የሚወሰዱ መድሐኒቶችና እፆች ወይም የሚፈፀሙ ድግምቶች ከስኬቱ ጋር ተያይዞ ቡዳነትን አብረው ያመጣሉ፣ ቡዳም ያስሆናሉ ይባላል። በመሆኑም አንድ ሠው ለጀግንነት፣ ለዝነኛነት፣ ለሀብት፣ ለሹመት፣ አዕምሮን

[9] ሴቷም ልትሆን ትችላለች። ነገር ግን በሴቶች ብዙ ጊዜ የተለመደ አይደለም።

[10] ውለሽ በአካባቢው ማኅበረሰብ አጠራር መተት ማለት ነው። መተት ሲባልም በአንድ ሰው ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም መተት አድራጊው የሚፈልገው ነገር እንዲፈጸምለት መተት በሚደረግበት ሰው ልብስ፣ ምግብ፣ መጠጥ፣ የቤት ቁሳቁሶች እና በመገልገያ ነገሮች ላይ የሚደረግ ድግምት ነው። ድግምት ማለት ደግሞ ምስጢራዊ የሆኑ የአጋንንት ወይም የአስማት ስሞችን መድገም፣ ማንበብ፣ ማነብነብ፣ መናገር፣ መለፍለፍ፣ መጸለይ ማለት ነው (ደስታ ተክለወልድ፣ 1964፣ 340- 341)።

ለማስላት ወዘተ. ፈልጎ የወሰደው መድሐኒት ወይም እፅ በአጋጣሚ የቡዳ መንፈስ ባለቤት (ቡዳ) ሊያደርገው ይችላል ተብሎ ይታመናል።

ሁለተኛው የደብተራዎች፣ የባህል መድሃኒት አዋቂዎችና የፀበል አጥማቂዎች ተግባር እርኩሳን መናፍስትን ማውጣትና መፈወስ ነው። በማኅበረሰቡ በዘር ወይም በደብተራዎች አስማታዊ ድግምት፣ እፅና መድሃኒት አማካይነት የሚመጡ እንደ ቡዳ፣ ጋኔን፣ ውለሽ እና የመሳሰሉ እምነቶችና እምነታዊ ተግባራት እርኩስ መንፈስ ተደርገው ይቆጠራሉ። እነዚህ መናፍስት በአንድ ሠው ላይ ባደሩ ጊዜም አቅልን በመሰወር የማሳበድ፣ እንቅልፍ የማሳጣት፣ እረፍት የመንሳትና ስራን በአግባቡ እንዳይሰራ የማድረግ ሀይል አላቸው ተብሎ ይታመናል። ደብተራዎች፣ የባህል መድሃኒት አዋቂዎችና ፀበል አጥማቂዎች እነዚህን እርኩሳን መናፍስት ከሰዎች የማራቅ፣ በሰዎች ላይ አድረው ከተገኙም የማውጣትና የመፈወስ ስራዎችን ያከናውናሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ደብተራዎች በአንድ ሠው ላይ የተደረጉ ውለሾችንና ድግምቶችን የማፍረስና የማርከስ እንዲሁም የቡዳ ጥቃት የደረሰበትን (በቡዳ የተበላን ሰው) የመፈወስ ሀይል አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የማኅበረሰቡ አባላት ፀበል አጥማቂዎች ከአምላክ በተሰጣቸው ፀጋ በመታገዝ ቡዳንና ሌሎች እርኩስ መናፍስትን ፀሎት በማድረግ ፣ በመፆምና በማስፆም፣ ፀበል በመርጨትና በማጠጣት ከተጠቂው ላይ ማስለቀቅ ይችላሉ የሚል እምነት አላቸው፡፡ ይህንም እምነታቸውን፣ ልምድና ገጠመኞቻቸውን መሰረት በማድረግ አስረጅ ትረካዎችን በማቅረብ ያጠናክራሉ፡፡

ሶስተኛው ተግባር በሽታዎች (ደዌዎችን) መፈወስ ነው። የአካባቢው ማኅበረሰብ ከተለያዩ በሽታዎች በፀበልና በባህል ህክምና አዋቂዎች አማካይነት ፈውስ ማግኘት ወይም መዳን ይቻላል ብሎ ያምናል። በዚህም በሰው ልጅ ላይ የሚከሰቱ አካላዊም ሆኑ ስነልቦናዊ ጉዳዮች ማለትም አይነ አፋርነት፣ ፍርሃትና ጭንቀት፣ ቡዳነትና በቡዳ መበላት፣ ማየትና መስማት አለመቻል፣ "ሸባነት" እና ሌሎች በሽታዎች የባህል መድሃኒት አዋቂዎችና ደብተራዎች በሚሰጧቸው ባህላዊ መድሃኒቶችና በሚያከናውኗቸው ድርጊቶች እንዲሁም በፀበል የሚድኑ መሆናቸውን የማኅበረሰቡ አባላት ይገልጻሉ፤ የአብነት ትረካዎችንም ያቀርባሉ።

### 2.4. ባህላዊ ጋብቻ

የሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ የእርስ በርስ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮችን ከሚያጠናክርበት ባህላዊ እሴቶች መካከል ጋብቻ አንዱ ነው። በማኅበረሰቡ ባህልም "የማደጎ" እና "ገላጥቦሽ" የተሰኙ የጋብቻ አይነቶች አሉ።

ሁለት ተጋቢዎች በህፃንነታቸው በቤተሰቦቻቸው ፈቃድ የሚፈፀም የጋብቻ አይነት በማኅበረሰቡ ባህል የማደጎ ጋብቻ ይባላል። ይህ ጋብቻ በተጋቢ ቤተሰቦች መካከል ጥብቅ ወዳጅነትንና ዝምድናን ለመፍጠር፣ በመካከል ያለን ጥል ለማጥበብ በሚል በተጋቢዎች የህፃንነት እድሜ ወቅት የሚፈፀም ነው። ጋብቻው ከመተጫጨት ጀምሮ እስከ ትዳር መመስረት (ጎጆ መውጣት) ድረስ ራሱን የቻለ ልማዳዊ ስምምነቶችና ስርዓቶች አሉት።[11]

ሌላው የማኅበረሰቡ ባህላዊ የጋብቻ አይነት የገላጥቦሽ ጋብቻ ነው። ይህ ጋብቻ ተጋቢዎች ከአሁን በፊት አግብተው የፈቱና ለረጅም ጊዜ ባለማግባታቸው እድሜያቸው የገፋ ሰዎች የሚፈፅሙት ነው። የገላጥቦሽ ጋብቻ የተጋቢዎች የቅርብ ዘመዶችና ጓደኞች እንዲሁም ጥቂት ሽማግሌዎች በተገኙበት ይፈጸማል። በዚህ የጋብቻ ስርዓት ጠላና ሌሎች መጠጦች ብቻ የሚቀርቡ በመሆኑ በአካባቢው ማኅበረሰብ ገላን እንደማጠብ ይቆጠራል። በዚህ የተነሳ የማኅበረሰቡ አባላት ጋብቻውን "ገላጥቦሽ" በማለት ይጠሩታል።

በማደጎም ሆነ በገላጥቦሽ የጋብቻ አይነቶች ማኅበረሰቡ የዘር ሀረግን በመቁጠርና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃን መሰረት በማድረግ ይፈፅማል። ይህም ሲባል የሁለቱ ተጋቢዎች ቤተሰብ ኢኮኖሚያዊ መሰረት የተመጣጠነ፣ ዝምድና የሌላቸው፣ ዘራቸው የጠራ፣ አጥንተ ሰባራነትና[12] ቡዳነት የሌለባቸው መሆን ይኖርበታል። ከተጋቡ በኋላ የአጥንት ሰባራነትና ቡዳነት በአንዳቸው ዘር ላይ ቢገኝ ጋብቻው እንዲፈርስ ይደረጋል። ተጋቢዎች አንፋታም ካሉ ከአካባቢው እንዲሰደዱ (እንዲርቁ) ይደረጋል።

---

[11] ይህ በቤተሰብ ፈቃድ ህጻናት እንዲፈጸሙ የሚደረገው የጋብቻ አይነት በጎጂ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ያለእድሜ ጋብቻ (Early Marriage) በሚል ይጠራል። ያለእድሜ ጋብቻ እድሜያቸው ለትዳር ባልደረሱ ህጻናት የሚፈጸም በመሆኑ በጎጂ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ እንደ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ይቆጠራል። ይህንን ጋብቻ ሲፈጸም የተገኘ በህግ የሚቀጣ መሆኑን የሰሜን ጎንደር ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የባህል ጥናትና ልማት አጠቃላይ የስራ ሂደት ባለሙያ የሆኑት አቶ ያለው አዲስ ይገልጻሉ። ነገር ግን የማህበረሰብ አባላት በተገቢ በገጠርና በማህበር እያስመሰሉ የማደጎ ጋብቻ የሚፈጸሙ መሆናቸውን ከመረጃ አቀባዮቹ ለመረዳት ችያለሁ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በጎጂ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ህጋዊ ተቀባይነት ያላቸው የጋብቻ አይነቶች መኖራቸውን ሃላፊው ይጠቅሳሉ። እነሱም በማዘጋጃ ቤት ወይም በህጋዊ የመንግስት ተቋም የሚፈጸም መደበኛ ጋብቻ (Civil Marrige) እና ልማዳዊ (ባህላዊ) ጋብቻ (Customary Marriage) ናቸው። ልማዳዊ ወይም ባህላዊ ጋብቻ በሐይማኖት ወይም በሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት እድሜያቸው ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ በሆኑ ተጋቢዎች ፈቃድና ስምምነት የሚፈጸም ነው።

[12] በማህበረሰቡ የማህበረሰብ ስርዓት(social system) ውስጥ "አጥንተ ሰባራነት" የዘር፣ የብሄር፣ የጎሳ፣ የቡድን፣ የሐይማኖትና ሌሎች ማህበረሰባዊ ክፍፍልና ልዩነቶችን (social stratification) ይመስለታል። በዚህም በማህበረሰቡ አጥንተ ሰባራት ጭሰኛ፣ ባሪያ፣ ሴማኝ(ሙሜና)፣ አገልጋይ፣ ቡዳ ወዘተ የሆኑ ቡድኖችን ያጠቃልላል።

## 3. የንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ የቡዳ እምነትን እና ተረክን የተመለከቱ ዕንስ ሐሳቦች እንዲሁም ከጥናቱ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው ጥናታዊ ፅሁፎች ተዳሰዋል፡፡

### 3.1. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ክፍል ከጥናቱ ጋር በቀጥታ የሚያያዙ የቡዳንና የተረክን ምንነት የሚገልጹ ብያኔዎች (Definitions)፣ የተረክን አይነት እንዲሁም የቡዳ ጥቃት መከላከያ፣ መለያና መፈወሻ ስልቶችን የሚያመለክቱ እሳቤዎች (concepts and assumptions) እና የቡዳና የተረክ ጥናት መረጃ አሰባሰብና አተናተን የሚጠቀሙ የትኩረት አቅጣጫዎች (approaches and perspectives) በተመለከተ ከመስኩ ምሁራን አንጻር ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ቀርቧል፡፡

#### 3.1.1. የቡዳ ምንነት

ቡዳ በአማርኛ መዝገበ ቃላት ውስጥ በእይታ ሳቢያ የሚከሰት ህመምን ወይም ጉዳትን የሚመለከት ልምዳዊ እምነት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ደስታ (1962፡ 985) "በአይኑ ወግቶ የሚያሳምም" የሚል ፍቺ ሰጥተውታል፡፡ ከሳቴ (1968፡ 515) ቡዳ "ዐይነ ወርቅ ያለበት በአይኑ ሰው የሚወጋ" በማለት ይገልጹታል፡፡ ዐይነ ወርቅ የቡዳ ጥቃት የሚያደርስ ሰው መጠሪያ ወይም "ዐይኑ ትኩር፣ ትክ ብሎ የሰውን ደም ግባት የሚወጋ ማለት ነው" ከሳቴ (1968፡ 100)፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፡ 234) ቡዳ "እንደ ህብረተሰቡ ልምዳዊ እምነት ያየውን፣ ቀልቡ ያረፈበትን ሰው ወይም እንስሳ ለህመም ወይም ለሞት የሚዳርግ መጥፎ አይን ያለው ሰው" የሚል ፍቺ ተሰጥቶታል፡፡

ይህ እምነት በሀገራችን በሚገኙ ማኅበረሰቦች ቋንቋና ልማዳዊ እምነት ውስጥም የተለያዩ ስያሜዎች አሉት፡፡ እንደ Vecchiato (1960፡160) ጥናት ቡዳ በከፋ "ashafo"፣ በመገርንገር "orioin"፣ በሱማሌ "awir" ፣ በከምባታ "uddanchu"፣ በወላይታና በኮንሶ "koma" እና በሲማዊ እና በተወሰኑ ኩሻዊ የቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪዎች "ቡዳ" የሚል ስያሜ አለው፡፡ እንዲሁም

በቡዳንት የሚጠረጠሩ ሰዎችና እምነቱ በአፋር "buta"፣ በሶማሊያ "bida" (Honea, 1963: 20)፣ በሰሜን ሸዋ ደግሞ "ጠይብ" (Remininck, 1974: 280) በሚል ስያሜ ይጠራል።

Leslau (1991: 86, 1972: 48) "evil eye" የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል "ቡዳ" በሚል የአማርኛ ቃል ተርጉመውታል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ይህ እምነት ምዕራባውያን እና ምዕራባውያን ባልሆኑ ሀገሮች ባህልና ቋንቋ እንደሚገኝ ጥናቶች ያመላክታሉ። በነዚህ ሀገራት በሚገኙ ቋንቋዎችም የተለያዩ ስያሜዎች አሉት። ከነዚህ መካከል በስፓኝኛ "mal de ojo"፣ በጣሊያንኛ "mal'occhio"፣ በእብራይስጥኛ "ayin horeh" በአረብኛ "ayin harsha"፣ በስኮትላንድኛ "droch shuil"፣ በፈረንሳይኛ "mauvais oeil"፣ በጀርመንኛ "bosen blick"፣ እና በጥንት የሮማ ቋንቋዎች ደግሞ "oculus mains" የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው (Stven, 2003; Poots,1998 እና MacComic, 2011)።

### 3.1.2. የቡዳ ጥቃት

የቡዳ ጥቃት አንድ ሰው አስቦትም ሆነ ሳያስበው እይታው ወይም አድናቆቱ የሚያስከትለውን ህመም፣ ችግር፣ ውድመትና ሞት የሚያመለክት ሀገረሰባዊ እምነት ነው። ይህንን ሃሳብ Dundes (1992: 258) እንደሚከተለው ያብራረሉ፦

> The evil eye is fairly consistent and uniform folk belief based upon the idea that an individual, male or female, has the power, voluntarily or involuntarily, to cause harm to another individual or his property merely by looking at or praising that person or property. The harm may consisit of illness, or even death or destruction.

እንደ Dundes ገለጻ በቡዳንት የሚጠረጠረው ሰው (possessor of evil eye) እይታ ህይወት ባላቸውና በሌላቸው ነገሮች ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን ብዙ ሀገረሰባዊ እምነቶች የሚጋሩት ጉዳይ ነው። ይህ በእይታ ሳቢያ የሚከሰተውን የቡዳ ጥቃት (የጥቃቱ) ምንነት፣ ሂደትና መንገድ አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ሃሳቦችን ያቀርባሉ።
የመጀመሪያው ሃሳብ የቡዳ ጥቃት ምንነትና የጥቃት መንገድ ከሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህርይ ጋር የሚያያዝ ነው። ይህም የማንኛውም ሰው የምቀኝነት፣ የቅናት፣ የንዴትና ሌሎች ሀያልና ጥልቅ ስሜታዊ ጉዳዮች በሰው ልጅ አይን ይገለጻሉ የሚል ነው (Lykiardopoulos, 1981: 225)። ከእነዚህ ስሜቶች መሀከል ቁጣንና ንዴትን ያዘለ ወይም አተኩሮ የሚመለከት አይን የሚታየውን አካል (እንስሳት ወይም ሰው) ሊያስደነግጥና ፍርሃትን ሊፈጥር ይችላል።

ከዚህ ሃሳብ ጋር ተያይዞ Steven (2003: 15-19) አንድን ሰው ወይም ነገርን አትኩሮ መመልከት ወይም ሙሉ በሙሉ አይንን በአንድ ግለሰብ ላይ ማድረግ በግለሠቡ ስሜት ጣልቃ እንደመግባትና

ነፃነቱን እንደመንጠቅ የሚቆጠር መሆኑን ይገልጻሉ:: በቀደሙት ልማዳዊ እምነቶችም በሰው ላይ አይን በመጣል ወይም በመትከል (casting a glance) የሰውየውን የውስጥ መንፈስ ገልጦ ማየት ይቻላል ተብሎ ይታመን እንደነበር Steven ያብራራሉ:: አንድ ነገር ላይ አይንን ጥሎና ሰክቶ መመልከት (glance or gaze at things) ደግሞ ነገሩን ለመቆጣጠር የመፈለግ አላማን ያሳያል:: ይህ ፍላጎት ተሟልቶ የአይን ማረፊያ የሆነውን ነገር በእይታ መቆጣጠር ነገሩን በተጨባጭ የመዳሰስ፣ የመቅመስ፣ የማሽተት ስሜት ወይም አዕምሯዊ ግንዛቤ ይሰጣል (Cavallaro, 2007: 131):: ከዚህ በመነሳት አንድ ሰው ሌላን ሰው  በተለያዩ ስሜቶች ውስጥ በመሆን አተኩሮ በሚመለከት ጊዜ የእይታው ማረፊያ የሆነው ሰው ስሜት ይረበሻል ተብሎ ይታሰባል:: የቡዳ ጥቃት እሳቤም ከዚህ የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ይመነጫል::

ሁለተኛው በስነ ልቦና ባለሙያዎች የሚስነረዘረው ሃሳብ የቡዳ ጥቃት ወይም እምነት በሰው ልጅ አዕምሮ የሚፈጠር የስሜት መቃወስን የሚያመለክት አተያይ ነው:: ይህንንም Dundes (1991: 265) Freud ን እና ሌሎች የስነ ልቦና ባለሙያዎችን በመጥቀስ የቡዳ እምነት አንድ ሰው ማንኛ ውም ሰው ይቀናብኛል በሚል ስጋት፣ ፍርሃትና ጭንቀት የሚፈጠር የስሜት መቃወስ እንደሆነ ይገልፃሉ:: አብዛኛው ሰው አንድ አይነ ገብ የሆነ ነገር ሲኖረው የሌሎችን ቅናትና ምቀኝነት ይፈራል:: ይህ አይነ ገብ የሆነው ነገር ድንገት ችግር ቢደርስበት ለችግሩ ምክንያት ይቀኑብኛል በሚላቸው ሰዎች ያሳብባል:: ከዚህ በመነሳት Freud (1959; 393) የቡዳ እምነት ሰዎች በእኔ ሀብት፣ ንብረትና ውበት ይቀኑብኛል ወይም ይመቀኙኛል የሚል ፍርሃት የወለደው ነው ይላሉ:: በመሆኑም የቡዳ ጥቃት (እምነት) በራስ ሊኖር የሚገባን ጥፋት በሌላ ሰው የማላከኪያ ወይም የማስተላለፊያ መንገድ (divice of projection) እንደሆነ የስነ ልቦና ባለሙያዎች ይገልጻሉ::

በስነ ሰብና በፎክሎር ምሁራን ዘንድ የቡዳ እምነት የሀገረሰባዊ ልማድ አካል እንደሆነ ይታመናል:: በዚህም ቡዳ በብዙ ሀገረሰባዊ እምነቶች ውስጥ የሚገኝ አንድ ሰው በሰው፣ በእንስሳትና በሌሎች ነገሮች ላይ እይታው ጥቃት ያደርሳል የሚል እምነት ነው:: ጥቃት የሚያደርስበት ምክንያትም በውል የታወቀ ወይም ያልታወቀ ስሜትና ፍላጎት ሊሆን ይችላል:: ይህ በውል የታወቀ ወይም ያልታወቀ ጥቃት የማድረስ ስሜትና ፍላጎት በአብዛኛው ማኅበረሰብ በዘር የሚመጣ ወይም የሰይጣን ባህሪ ተደርጎ ይታመናል::

በፎክሎር ጥናቶች እና በብዙ ሀገረሰብ እምነቶች ውስጥ የቡዳ እምነትና ጥቃት በቀጥታ ከአይን ወይም ከእይታ ጋር ይያያዛል:: ይህም ዕይታ በተለያየ የእይታ አኳሀንና ስሜት ሲገለጽ፣ በመንካት፣ አጠንቦ በመሆን፣ በድምጽ (በንግግር) ሊታጀብ ይችላል (Elworthy, 1895: 35):: ከዚህ

በመነሳት የጥቃቱ አይነትና መንገድም እንደ አይታው አኳሆንና ስሜት እንዲሁም ከአይታው ጋር እንደሚከናወኑ ድርጊቶች ይለያያል። ለምሳሌ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች በግሪክ ወዳጃዊ ባልሆነ (በማፍጠጥ፣ በማጉረጥ፣ በንዴትና በቅናት) እይታ ከተመለከቱ፤ በእንግሊዝ አንድን ሰው፣ እንስሳ፣ እቃና ተክል አተኩረው ካዩ፣ በጥንት ግብፃውያን አይተው ካደነቁ ወይም ካሞገሱ፤ እንዲሁም በኬንያ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች የያዙትን እቃ ለሰውየው ከሰጡ የቡዳ ጥቃትን ያደርሳሉ ተብሉ ይታመናል (Gubbins, 1946; Griffiths, 1938; Matsuzona, 1993)። ጥቃት የሚያደርሱትም በውል በታወቀ ወይም ባልታወቀ የቅናትና የምቀኝነት ስሜት ውስጥ በሚከሰት እይታ ነው።

በተለያዩ ማኅበረሰቦች የቡዳን እምነት አስመልክቶ የተደረጉ የባህል፣ የታሪክና የፎክሎር ጥናት ውጤቶች የቡዳ ጥቃት ምክንያት ቅናት እንደሆነ ይገልጻሉ። የእምነቱ መሠረታዊ አሳቤም ቅናትና ምቀኝነት መሆኑን ያስረዳሉ። ቅናት ከቡዳ ጋር በዋናነት የመዛመዱ ምክንያት "envy" የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል "invidia" ከሚለው የላቲን ቋንቋ የመጣ ሲሆን ማየት የሚል ቀጥተኛ ትርጉም የሚሰጥ በመሆኑ ነው (Dundes, 1991: 262)።

Dundes ቡዳን አንድን ነገር ከማየትና ከማድነቅ ወይም ከመፈለግና ከመቅናት ጋር ያያዙታል።

> To see some thing is to want it, perhaps. A common reaction to desirable object is to praise it, to admire it. An expression of admiration or praise is understood to imply at least a tinge of envy. Envy can accordingly be expressed either by eye or by mouth (or by both) (Dundes, 1992: 263).

እንደ Dundes በተፈጥሮ አንድን ነገር ስናይ እናደንቀዋለን ወይም እናሞግሰዋለን። አድናቆትን ወይም ሙገሳን መግለጽ ደግሞ ቢያንስ በውስጡ መጠነኛ ቅናት አለው ተብሎ ይታሰባል። ቅናት በአይን ወይም በአፍ (በሁለቱም) ሊገለጽ ይችላል። ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው በእይታ ወይም ከእይታ ጋር በሚቀርብ አድናቆትና ሙገሳ ሳቢያ በሚፈጠር የቅናትና የምቀኝነት ስሜት አማካኝነት የቡዳ ጥቃት ይከሰታል።

በአጠቃላይ የቡዳ ጥቃት በቡዳነት የተፈረጀ ሰው አስቦትም ይሁን ሳያስበው እይታው ህይወት ባላቸውና በሌላቸው ነገሮች ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን በተለያዩ ሀገራት ያሉ ሀገረሰባዊ እምነቶች የሚጋሩት ጉዳይ ነው። ነገር ግን ጉዳት (ጥቃት) ያደርሳል የሚባለው ሰው ማንነት፣ የእይታ አኳኋንና ስሜት፣ ጥቃት የሚያደርስበት ምክንያት፣ ለጥቃቱ የሚጋለጡ ነገሮችና ጥቃቱን የመከላከያ፣ የመለያና የመፈወሻ ዘዴና ስርዓት ከዋኙ እንደየማኅበረሰቡ ባህል፣ ልማድና እምነት ይለያያል። የቡዳ እምነት አሳቤም ሆነ ጥናትና ምርምር እነዚህን ሁሉ ያጠቃልላል።

### 3.1.3. የቡዳ ጥቃት የመከላከያ፣ የመለያና የመፈወሻ ዘዴዎች

#### 3.1.3.1. የቡዳ ጥቃት የመከላከያ ዘዴ

በብዙ ማኅበረሰቦች ልማዳዊ እምነት አንድ ሰው ሀብቱን፣ ውበቱንና ጤንነቱን በእይታና ከእይታ ጋር በሚመጣ አድናቆት ሳቢያ ከሚከሰት የቡዳ ጥቃት ለመጠበቅ የተለያዩ የመከላከያ ስልቶችን ያከናውናል። Lykiordopoulos (1981: 225) የቡዳ ጥቃትን ለመቀልበስና ለመከላከል የሚወሰዱ ፎክሎራዊ ዘዴዎችን "first those that involve material objects that are worn or carried on a person, or used on the house or garden, and second those that involve behaviour of some kind, such as spitting, praying, gesturing, walking in a certain manner, etc." በሚል በሁለት ምድብ ይከፍሏቸዋል። የመጀመሪያው ምድብ በእንስሳት፣ በሰው፣ በመኖሪያ ቤት እና በሰብል ላይ የሚንጠለጠሉ፣ የሚታሰሩና የሚደረጉ ጌጦችና ቁሶችን ሲያጠቃልል የሁለተኛው ምድብ ደግሞ ምራቅ መትፋት፣ ጸሎት፣ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የአረማመድ አኳኃን እና ሌሎች ድርጊቶችንና ስርዓቶችን ያካትታል። Dundes (1992: 258) በበኩላቸው የቡዳ ጥቃት የመከላከያ ስልቶች "Preventive measures include wearing apotropaic amulets, making specific gestures or spiting, and uttering proctective verbal formulas before or after praising or complimenting aperson." መሆናቸውን ይጠቁማሉ። በመሆኑም በቡዳ ልማዳዊ እምነት ላይ የቀረቡ ጽሁፎችንና ጥናቶችን መሠረት በማድረግ የቡዳ ጥቃት የመከላከያ ዘዴዎችን ክታቦች፣ ጌጣጌጦችና ቁሶች፣ ጸሎቶች፣ የተለመዱ አካላዊና ቃላዊ ገለጻዎች እና ሌሎች በማለት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

ክታብ በአብዛኛው የቡዳ ልማዳዊ እምነት ባላቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ የሚጠቀስ የመከላከያ መሳሪያ ነው። ይህ ክታብ የሚዘጋጅበት መንገድ፣ የሚታሰርበት ቦታ እንዲሁም መጠን የሚለያይ ሲሆን በውስጡም ሀይማኖታዊና አስማታዊ ጽሁፎች ወይም ድግምቶችን ይይዛል። እነዚህ ክታቦች በውስጣቸው በሚይዙት ሃይማኖታዊ ወይም አስማታዊ ጽሁፎች አማካኝነት የቡዳን ጥቃት ይከላከላሉ ተብሎ ይታመናል።

በአንዳንድ ማኅበረሰቦች በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ የሚደረጉ ቁሳቁሶችና ጌጣጌጦች ከጊዜንታቸው ባለፈ የቡዳን ጥቃት ይከላከላሉ ተብሎ ይታመናል። ለምሳሌ ያህል በደቡባዊ የህንድ ክፍል ባሉ ማኅበረሰቦች ዘንድ ውብ ሴቶች የእይናቸውን ቅንድብ በመቀንደብ፣ ህፃናት ደግሞ ሰማያዊ ዶቃ አንገት ላይ በማሰር፣ በጣሊያን ከወርቅ፣ ከመዳብ፣ ከከበሩ ድንጋዮች የተሰሩ "man tica or mano cornuta" የተሰኙ ጌጦችን በሰውነት ክፍሎቻቸው ላይ በማድረግ የቡዳን ጥቃት ይከላከላሉ (Woodburne, 1991: 78; Steven, 2003: 21)።

ከጌጦች ባለፈ ቁሶችን በቤት፣ በእንስሳት፣ በሰብል ላይ ማንጠልጠል የቡዳ ጥቃትን ይከላከላል በሚል ይታመናል፡፡ በግብፅ የበግና የሌሎች እንስሳትን ቀንድ በቤት ላይ ማንጠልጠል (Griffiths, 1938፡ 24)፣ በሞሮኮ በሰብል ላይ ማሰሮ ማስቀመጥ (Woodburne, 1991: 78) የቡዳ ጥቃትን ይከላከላል የሚል እምነት አላቸው፡፡ የእነዚህ ጌጣጌጦችና ቁሶች ዋና አላማ የቡዳውን እይታ መቀልበስ ነው፡፡ ይህም ቡዳ የሚባለው ሰው በቶሎ በእነዚህ ጌጦችና ቁሶች ላይ አይኑን ያሳርፋል፡፡ በዚህ ወቅትም እይታውን ይቀለብሳል፤ ጥቃት አይደርስም ተብሎ ይታመናል፡፡

የተለመዱ ቃላትንና ሀረጋትን (Formulaic phrases or oral formulas) መጥራትና መናገር ሌላው በቃላዊ ገለጻ መንገድ የቡዳ ጥቃት የመከላከያ ዘዴ ነው፡፡ እነዚህም የቅዱሳንን ወይም የፈጣሪን ስም[13] ቡዳ ከሚባለው ሰው ፊት መጥራትን፣ ጸያፍ ስድብ አዘል ቃላትና ሀረጋትን መናገር ያጠቃልላል፡፡ ከዚህ ተያይዞ የተለያዩ የእጅ ምልክቶችን ማሳየት፣ ራስን ከቡዳው መደበቅ፣ አረማመድ መቀየር፣ በአካላዊ ገለጻ የቡዳ ጥቃት የመከላከያ ብልሀት ነው፡፡ እነዚህ አካላዊና ቃላዊ ገለጻዎች በዋናነት ቡዳውን በመሳደብና በማሸማቀቅ እንዲሁም ራስን ከቡዳው እይታ በማራቅ ጥቃቱን የመከላከያ ስልቶች ናቸው (Dundes,1992 እና Lykiordopoulos, 1981)፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰው አንድን ነገር ሲያደንቅ ያደነቀውን ነገር መልሶ እንዲያንኳስስ ወይም እንዲባርክ በማድረግና በማቃረን ጥቃቱን መከላከል እንደሚቻል ይታመናል፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው ማኅበረሰብ አስማታዊ ድግምቶች፣ ሐይማኖታዊ ፀሎቶች፣ ሐይማኖታዊ መጽሐፍትን ማነብነብ (ማንበብ) የቡዳ ጥቃትን ይከላከላል፡፡ እነዚህ ጸሎቶችና ንባቦችም የቡዳውን የማጥቃት መንፈስ ያርቃሉ ተብሎም ይታመናል (Mullen, 2011: 215)፡፡

### 3.1.3.2. የቡዳ ጥቃት የመለያ ዘዴዎች

በዋናነት በቡዳ እንደተጠቃ በሚጠረጠር ግለሰብ ላይ የሚታዩ የህመም ምልክቶች የቡዳ ጥቃት የመለያ ዘዴዎች ናቸው። ከነዚህም ውስጥ የሰገራ ድርቀት፣ ሆድ ቁርጠት፣ ራስ ምታት፣ ስንፈተ ወሲብ፣ በተደጋጋሚ ማዛጋት፣ ጥርስን ማፋጨት፣ አቅልን መሳትና የልብ ድካም፣ የህጻናት ሰውነት መላላጥና በተለየ ድምጽ ማልቀስ፣ የእናቶችና የእንስሳት (የላሞች) የጡት ወተት

[13] ክርስቶስ ስም፣ ላ ኢላ ኢለላሀ ፣ በስመ አብ ወ ወልድ ወ መንፈስ ቅዱስ፣ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

መድረቅ የተለመዱ የቡዳ ጥቃት የህመም ምልክቶች ናቸው (Abu-Rabia, 2005: 241፣ Matsuzono, 1993: 13፣ Stevens, 2003: 17 እና Lykiardpous, 1981)::

ከህመም ምልክቶች በተጨማሪ የተለያዩ ስርዓተ ክዋኔዎች መፈጸም ሌላው የቡዳ ጥቃት የመለያ ዘዴ ነው። ለምሳሌ በዩክሬን አንድ ሰው በቡዳ መጠቃቱን ለመለየት ሰም ይነበባል:: ይህም የቀለጠ ሰም ከሻማ ላይ ይወሰድና በባልዲ ባለ ውሃ ውስጥ በማንጠባጠብ ጸሎት ይደረግበታል:: በውሃው ላይ የተንጠባጠበው ሰም ከውሃ ላይ ከተንሳፈፈና ከባልዲው ጠርዝ ከተጣበቀ በሰውየው ላይ የቡዳ ጥቃት እንደደረሰ ይታመናል። ሰሙ ውሃ ውስጥ ከሰመጠ ግን የቡዳ ጥቃት እንዳልሆነ ይረጋገጣል (Steven, 2003: 18)::

### 3.1.3.3. የቡዳ ጥቃት የመፈወሻ ዘዴዎች

አብዛኛው ማኅበረሰብ የቡዳ ጥቃትን የሚከላከልበትና የሚፈውስበት ከልማዳዊ እምነቱ እና ከሀይማኖቱ የመነጨ ፎክሎራዊ መንገዶች አሉት። ዘዴዎችም የማኅበረሰቡን የእምነት ስርዓት (ritual) መሠረት ያደረጉ ናቸው። በዚህም የአብዛኛው ማኅበረሰብ የፈውስ ስርዓተ ክዋኔ (healing ritual) ሲታሰብ የሐይማኖታዊ እና የባህላዊ (የልማዳዊ) እምነት የፈውስ ዘዴዎች ይጠቀሳሉ (Mullen, 2011: 213)። እነዚህን የፈውስ ዘዴዎች የሚጠቁሙ፣ የሚሰጡ፣ የሚመሩና የሚያከናውኑ ሰዎችም በማኅበረሰቡ ተለይተው ይታወቃሉ። የእነዚህ ሰዎች እውቀት፣ ልምድና የሀይል ምንጭ ደግሞ መለኮታዊና ተፈጥሯዊ ሊሆን ይችላል (Hufford, 1986: 306):: ከዚህ በመነሳት የቡዳ ጥቃት የፈውስ ዘዴን ተፈጥሯዊና መለኮታዊ በሚል መመደብ ይቻላል::

በመለኮታዊ መንገድ የሚፈውሱ ተቋማት ወይም ግለሰቦች የፈውስ መንገድ በሐይማኖታዊ እና በልማዳዊ እምነት በሚገኝ እውቀትና ክህሎት የሚሰጥ ሊሆን ይችላል:: በሃይማኖት ተቋም ስር የሚካተቱ የፈውስ መንገዶች በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመታገዝ ፀሎት በማድረግ፣ ፀበል በመርጨት፣ መስቀል በማሳለም፣ ቅዱስ ቁርባን በመስጠት፣ በቂሶች፣ በሼኮችና በመሳሰሉት የሐይማኖት መሪዎች የሚደረግ ነው። እነዚህ የሐይማኖት መሪዎች የፈጣሪን ስም በመጥራት፣ ፀበል በመርጨት፣ ቁርዓንን በመቅራት እና የመሳሰሉትን ተግባራትን በመፈጸም የፈውስ አገልግሎት ይሰጣሉ። በሁለተኛው ምድብ የሚጠቀሱ ፈዋሾች ደግሞ ከልማዳዊ እምነት በሚያገኙት እውቀትና ክህሎት በመታገዝ ፈውስ ይሰጣሉ:: እነዚህ አካላት ከዛር መንፈስ፣ ከአጋንንት፣ ከሰይጣን እና ከመሳሰሉት መንፈስ በሚያገኙት እውቀት እና ጥበብ በመታገዝ ህሙማተኛን ይፈውሳሉ።

ተፈጥሯዊ የፈውስ መንገድ ደግሞ ፈዋሹ በአካባቢ ከሚያገኛቸው እንደ ቅጠላ ቅጠል፣ እፅዋት፣ ማዕድናት፣ እንስሳት እና የመሳሰሉትን በመጠቀምና መድኃኒቶችን በመቀመም የሚፈውስበት ዘዴ ነው።

ከላይ የተጠቀሱት የፈውስ መንገዶች እያንዳንዱ ማኅበረሰብ ሐይማኖታዊ ወይም ልማዳዊ እምነቱ ባስቀመጠው ደንብና ስርዓት እንዲሁም የክዋኔ አውድ፣ አጋጣሚ፣ ቦታ፣ ጊዜ እና የከዋኝ (ፈዋሽ) ማንነት የሚገዙ ናቸው። ማኅበረሰቡ ለነዚህ የፈውስ ስርዓቶች የተለያየ እምነትና አስተሳሰብ ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ አንዳንድ ማኅበረሰቦች በሀይማኖቱ አማካይነት የቡዳን ጥቃት መከላከልና ፈውስ ማግኘት የሀይኖማቱ የእምነት መሠረት ወይም አካል አድርገው ሲቀበሉት በልማዳዊ እምነቱ አማካይነት ከቡዳ ጥቃት መከላከልና መፈወስ መቻል ደግሞ እንደ ህክምና ይቆጠሩታል (Mullen, 2011: 214)።

በአጠቃላይ የቡዳ ጥቃት አሳቤ ጥቃቱ የሚደርስበት መንገድና ምክንያት፣ የጥቃቱ አድራሽና ተጋላጭ ማንነት፣ የጥቃቱ የመከላከያ፣ የመለያ እና የመፈወሻ ዘዴ እንደየማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት ይለያያል። የራሳቸው የሆነ የእምነት ስርዓትና ፍቺም ይኖራቸዋል። ለምሳሌ ያህል Dundes ቡዳ የሚባለው ሰው ጥቃት የሚያደርስበትን ምክንያት፣ የጥቃቱን የመፈወሻ ዘዴ፣ የዘዴውን ተምሳሌታዊ ፍችና ፋይዳ ከእርጥበት፣ በጥቃቱ ሳቢያ የሚከሰተውን ጉዳት ከድርቀት ጋር ያያይዙታል። የእርጥብና የደረቅ ተምሳሌታዊ ፍቺንም እንደሚከተለው ይገልጹታል፦

> Life depends up on liquid. From the concept of the "water of life" to semen, milk, blood, bile, saliva, and the like, the consistent principle is that liquid means life while loss of liquid means death. "Wet and dry" as an oppositional pair means life and death. Liquids are living; drying is dying! (Dundes, 1992; 266)

እንደ Dundes ገለፃ ህይወት በፈሳሽ ነገሮች የተመሰረተች ናት። ለህይወት መሠረት ከሆነው ውሃ ጀምሮ እንደ የወንድ የዘር ፈሳሽ፣ ወተት፣ ደም፣ ሀሞት፣ ምራቅና የመሳሰሉት ፈሳሾች መኖር የህይወትን፣ የፈሳሾች መጥፋት ደግሞ የሞትን ትዕምርት ይወክላሉ። በዚህም ርጥብና ደረቅ (wet and dry) የተሰኙ ጥንድ ተቃርኖዎች በህይወት የመኖርና ያለመኖርን ፍቺ ይይዛሉ። ከዚህ በመነሳት በአብዛኛው ማኅበረሰብ የቡዳ ጥቃት የሚደርስባቸው ሰዎች ወይም ነገሮች በእርጥበትና በልምላሜ ጊዜ እንደሆነ ይታመናል። ለምሳሌ የሚያጠቡ እናቶችና ላሞች፣ ቡቃያቸው ያማረ ዛፎችና ፍራፍሬዎች፣ ያሸቱ ሰብሉች እና የመሳሰሉት ለቡዳ ጥቃት ተጋላጭ ናቸው። የቡዳ ጥቃት ሰለባ በሚሆኑበት ጊዜም የሚያጠቡ እናቶችና ላሞች ጡት፣ ቡቃያቸው ያማረ ዛፎችና

ፍራፍሬዎች ይደርቃሉ። እንዲሁም ያሸቱ ሰብሎች ፍሬ አልባ ይሆናሉ። በዚህ የተነሳ የቡዳ ጥቃት ድርቀትን ያስከትላል። ይህንን ድርቀት ለመፈወስም ተጠቂው ፀሎት የተደረገበት ውሃ እንዲጠጣ፣ እንቁላል ሰውነቱ (ጭንቅላቱ) ላይ እንዲፈስ እንዲሁም ምራቅ እንዲተፋበት ይደረጋል። የእነዚህ የፈውስ ዘዴዎች ፋይዳም የደረቀውን ነገር ማርጠብና ወደ ቀደመው ማንነቱ መመለስ እንደሆነ Dundes (1991: 268-274) ያብራራሉ። በቡዳ ላይ የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮችም ከቡዳ ጥቃት ጋር የተያያዙ የመከላከያ፣ የመፈወሻና ሌሎች እምነታዊ ድርጊቶችና ክንዋኔዎች የሚኖራቸውን ፋይዳ እና ተምሳሌታዊ ፍቺዎችን መግለጽ ያካትታል።

### 3.1.4. የቡዳ እምነት አጠናን ስልት

በዚህ ጥናት የጥናቱ ዳራ (ገጽ 1) ላይ የቡዳን ልማዳዊ እምነት አስመልክቶ የተካሄዱ የስነ ሰብዕና የፎክሎር ጥናቶች በአብዛኛው በእምነቱ ስርዓት (belief system)፣ ባህላዊና ማህበራዊ ተግባር፣ ጥንተ አመጣጥና የስርጭት መንገድ፣ ከሌሎች እምነቶችና ትረካዎች ጋር ባላቸው ትስስር ላይ እንደሚያተኩሩ Ross ን (2010: 47) በመጥቀስ ተገልጿል።

የቡዳ እምነት ከሌሎች ልማዳዊ እምነቶች ማለትም ከጥንቆላ፣ አስማትና የመናፍስት እምነት ጋር መዛመዱ፣ የብያኔው (ስያሜው) አሻሚ መሆን፣ የመከላከያ እና የመፈወሻ ዘዴዎችና ስርዓቶቹ መለያየትና መብዛት ጥናቱን ውስብስብ ያደርገዋል። በዚህ ውስብስብ ባህሪው የተነሳ የቡዳ እምነት ጥናት "evil eye complex " በሚል ስያሜ ይታወቃል (Dundes, 1990; Galt, 1987; MacComic, 2011)። ነገር ግን Lykiardpoules (1986) እና Galt (1987) የአብዛኛውን ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ያማከሉ የቡዳ እምነት ገጽታዎች እንዳሉና እነዚህን ገጽታዎችንም በመያዝ ማጥናት የሚቻል መሆኑን እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

Galt (1987፡ 669-671) በአብዛኛው ማኅበረሰብ የቡዳ ልማዳዊ እምነት ስርዓት ውስጥ አራት ተመሳሳይ ፅንሰ ሀሳቦች (ጉዳዮች) ጎልተው እንደሚታዩና እነዚህን ጉዳዮች በመያዝም ማጥናት የሚቻል መሆኑን ይገልፃሉ። እነዚህም (1) ለእይታ መጋለጥ፣ (2) በአስማታዊ ሀይል ወይም በስውር ጥበብ ጉዳት ማድረስ፣ (3) ቅናት፣ (4) የመከላከያና የመፈወሻ ዘዴዎች ናቸው። በዚህም ለእይታው የሚጋለጠው ነገር አይነት፣ ጥቃት ያደርሳል የተባለው ሰው የእይታ አኳሀንና ስሜት፣ ጥቃት የሚያደርስበትን (የቡዳነት) ሀይል ምንጭ፣ ምክንያትና ስሜት (በርሱ ፈቃድ ወይስ በሌላ፣ በቅናት ወይስ በምቀኝነት ወዘተ) እንዲሁም ጥቃቱን የመቀልበሻ፣ የመመለሻ፣ የመከላከያ፣ የመለያና የመፈወሻ እርምጃዎችና የፈውስ ስርዓተ ክዋኔዎችን መመርመርና መግለጽ እንደሚቻል ይገልፃሉ።

በተመሳሳይ መልኩ Lykiardpoules (1986: 223) በቡዳ እምነት ላይ በሚካሄዱ ወይም በተካሄዱ ጥናቶች ላይ የሚገኙ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለመተንተን የሚያስችሉ ሁለት ሰፋፊ ምድቦች መኖራቸውን እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤ "The study of the material on the evil eye can be divided into two major categories: the first dealing with the action of casting the evil eye, and protective measures against it, and the second with the process of cure of the affected party." እነዚህ ምድቦች በስራቸው ሌሎች ንዑሳን ክፍሎች ሲኖራቸው በአብዛኛው ማኅበረሰብ የቡዳ እምነት እንደሚገኙ ይገልፃሉ፡፡ የቡዳ ጥቃት እና የጥቃቱ መከላከያ መንገዶች በሚለው የመጀመሪያው ምድብ የጥቃቱን አድራሽ (የቡዳው) ማንነትና ሐይል፣ የጥቃቱ መንገድና ምክንያት፣ የተጠቂዎች ማንነት፣ በጥቃቱ ሳቢያ የሚደርሰው የጉዳት አይነት እንዲሁም ለነዚህ ጥቃቶች የሚወሰደውን የመከላከያ ዘዴዎችን ያጠቃልላል፡፡ የቡዳ ጥቃት የመፈወሻ ዘዴዎች በሚለው ሌላኛው ምድብ ደግሞ ጥቃቱን የሚለዩና የሚፈውሱ ሰዎችና በስርአቱ ላይ የሚከናወኑ ሂደቶችንና ስርዓተ ክዋኔዎች ይመለከታል፡፡

እነዚህንና ሌሎች ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ጥናት በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ውስጥ የቡዳ ጥቃት ምንነትና አይነት፣ የቡዳ ጥቃት ተጋላጭነት፣ ለጥቃቱ የሚወሰዱ የመከላከያ፣ የመለያና፣ የመፈወሻ ስርዓተ ክዋኔዎች አይነትና ዘዴ፣ እንዲሁም ተጠኚ ማኅበረሰቡ ለቡዳ ያለው አመለካከት ተጠንቷል፡፡

### 3.1.5. የተረክ ምንነት

ተረክ በሰፊው ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለው፣ በማንኛውም ማኅበረሰብ ወይም ቡድን ውስጥ የሚገኝ፣ ዘመንና ባህል ተሻጋሪ የሆነ፣ በሁሉም የኪነ ጥበብ ቅርጾች የትኛውንም ጭብጥ ማቅረብ የሚያስችል ህልቆ መሳፍርት ቅርጾች ያለው በቃል፣ በጽሁፍ፣ በስዕል፣ በአካላዊ ገጽታና እንቅስቃሴ በአንዱ ወይም ከሌላው በማዛመድ የሚገለጽ የመግባቢያ መንገድ መሆኑን Barthes እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> narrative is present in myth, legend, fables, tales, short stories, epics, history, tragedy, drame [suspense drama], comedy, pantomime, paint-ings (in Santa Ursula by Carpaccio, for instance), stained-glass windows, movies, local news, conversation. Moreover, in this infinite variety of forms, it is present at all times, in all places, in all societies; indeed narrative starts with the very history of mankind; there is not, there has never been anywhere, any people without narrative; all classes, all human groups, have their stories, and very often those stories are enjoyed by men of different and even opposite cultural backgrounds: narrative remains largely unconcerned with good or bad literature. Like life itself, it is there, international, transhistorical, transcultural (1975: 237).

ተረክ ልምድና ገጠመኝን ተለማጣቂ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንድ የተከሰተ ሁነትን የማሳያ፣ አደራጅቶ የማቅረቢያ መንገድ ነው (Oring, 1986: 121)። በመሆኑም ተረክ ተከታታይነት ያሏቸው ድርጊቶችና ሁነቶች ሲፈፀሙ የሚያሳይ ትረካ ነው። እነዚህ ሁነቶች፣ ክስተቶችና ድርጊቶችም በተለያዩ ቅርፆች ይቀርባሉ።

የዚህ ጥናት ትኩረት ከፎክሎር ቃላዊ የተረክ ቅርጾች ውስጥ በዝርዉ ቃል የሚቀርቡ የትረካ ቅርጾች (oral prose narratives) ላይ ነው። ዝርው ቃል ተረክ ግጥማዊ ባልሆነ ቋንቋ የሚተረክ ነው። በትረካው ውስጥም ተለማጣቂነትና ተያያዥነት ያላቸው ልዩ ልዩ ድርጊቶች፣ ድርጊቶቹን የሚፈፅሙ ገፀባህሪያት፣ ድርጊቱን የሚፈፅሙበት ቦታና ጊዜ ይይዛል።

ተረክን የመተረክና የማድመጥ ጽኑ ፍላጎት ከሰው ልጅ የስልጣኔ ታሪክ ጋር አብሮ የኖረ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው። በዚህም ተረክ በማንኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ ያለ በዕለታዊ ሕይወት በተለያየ መልኩ የሚከወን የማኅበረሰቡን ማንነት፣ እምነት፣ ልማድና ባህል የሚይዝ ነው፣

በአጠቃላይ ዝርዉ ቃል ትረካ ተከታታይነት ያሏቸው ክስተቶች፣ ድርጊቶች ወይም ሁነቶች የሚፈጸሙበት፣ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቦታና ጊዜ የሚያሳይ፣ የአንድን ማኅበረሰብ ወይም ቡድን ልማድ፣ ባህልና እምነት የሚያንጸባርቅ ነው። ፈጠራውና ተስተላልፎቱ ቃላዊ የሆነ ከአንድ ትውልድ በላይ የሚዘልቅ፣ ከሰው ልጅ የታሪክ ስልጣኔ ጋር አብሮ የሚጓዝ፣ ራሱን እንደዘመኑ ማህበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታ በመቀያየር የሚኖርና የሚተረክ ነው (Dégh, 1972: 54; Oring, 1986: 122 እና Vansina, 1983: 101)።

### 3.1.6. የተረክ አጠናን ስልት

በርካታ የፎክሎር አጥኚዎች ሀገረሰባዊ ተረኮችን የተለያዩ ፈርጆችን (የማዋገኛ ስልቶችን Genre classification and categorization) መሰረት በማድረግ ጥናትና ምርምር ያካሂዳሉ። ከተለመዱ የማዋገኛ መስፈርቶች መካከል የተረኩ ስልታዊና ቅርፃዊ ገፅታ፣ ርዕሰ ጉዳይ፣ የመከሰቻ አጋጣሚ፣ ሚና ወይም አውድ፣ ቀዬአዊ ስያሜዎችና ክፍፍሎሽ ይጠቀሳሉ።

በአንድ ማኅበረሰብ የተረክ ስልታዊና ቅርፃዊ ገፅታ ጥናት ውስጥ ተረኩ የሚገለፅበት ቅርፅ (ዝርዋዊነት፣ ግጥማዊነት)፣ የቅርፁ ርዝመትና እጥረት፣ የቋንቋ አጠቃቀም ወዘተ ይዳስስበታል። በርዕሰ ጉዳይ ተከፋፍለው የሚቀርቡ የተረክ ጥናቶች በዋናነት ጭብጡን

(ፅንሰ ሐሳቡን) ይመረምራሉ፡፡ ተረኩ ለምን እና እንዴት በማንና በምን ሁኔታ ተከወነ የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት የተረኩን የመከሰቻ አጋጣሚ፣ ሚና፣ አውድ መሰረት በማድረግ ማጥናት ይቻላል፡፡ ሌላው ሀገረሰባዊ ተረክን የማጥኛ መንገድ ቀዬአዊ ስያሜዎችንና ክፍፍሎችን ነው፡፡ ይህ ስልትም የሀገረሰባዊ ተረኩ ባለቤቶች ተረኩን ለይተው የሚጠሩበትን ሀገር በቀል ስያሜ በመከተል ክፋፍሎ የማጥኛ መንገድ ነው፡፡ በዚህ ስልት የትረካው ባለቤቶች ስለትረካዎቻቸው ያላቸውን አተያዮች መሰረት በማድረግ ከፋፍሎ ማጥናት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሀገረሰብ ተረክን አንዳንድ ምሁራን ሚት፣ አፈ ታሪክና ተረት በሚል ካስቀመጧቸው የዝርዉ ቃል ትረካ ቅርፆች በተጨማሪ የአንድን ማኅበረሰብ፣ ቡድን ወይም ግለሰብ ልምድና ገጠመኝ መሰረት ተደርገው የሚቀርቡ ዝርው ቃል ተረኮች ያሉ መሆናቸውን Dégh (1972)፣ Stahl (1972) እና Oring (1986) ይገልፃሉ፡፡ እነዚህ ተረኮች በማኅበረሰቡ ዘንድ በተረኩ ባለቤት ልምድና ገጠመኝ የመነጩ እውነተኛ ታሪኮች ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡

የፎክሎርና ስነሰብዕ አጥኚዎች እነዚህን የእውነተኛ ገጠመኝ ትረካዎችን "True experience stories" (Dégh, 1972); "Personal experience stories" ወይም "memorate" (Stahl, 1972; 269) እና "Life history" (Oring, 1986 እና Goldstain, 1964) የሚል ስያሜና ዘውግ በማበጀት ይጠሯቸዋል፡፡ ምሁራኑ ባስቀመጡት ምድብ ውስጥም የተለያዩ እውነተኛ የተረክ አይነቶች መኖራቸውን ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል Bascom (1973: 256) "myth" ፣ "legend" እና "folktale" በሚል ከከፋፈሏቸው የፎክሎር የዝርዉ ቃል ተረክ ቅርጾች ውስጥ "personal experience story" ተጨማሪ የዝርዉ ቃል ቅርጽ ሊሆን እንደሚችልና በዚህ ውስጥም የአንድ ቡድን ወይም ግለሰብ የህይወት ታሪክ፣ ገጠመኝና ትዝታዎች እንደሚያካትት ለ Dorson በፃፉት ማስታወሻ (Note) ገልጸዋል፡፡

እነዚህ የእውነተኛ ገጠመኝ ትረካዎች (true experience stories) በዕለት ተዕለት ማህበራዊ ተራክቦ ውስጥ የምንተርካቸውን ሰርካዊ ታሪኮችን (every day stories) ትዝታዎች (reminiscence) እና ክስተቶችን፣ ገጠመኞችን፣ ሲባል የሚሰሙትን (hearsays)፣ ጭምጭምታዎችን ወይም ሀሜቶችን (rumors) እና አጠቃላይ ግለሰባዊ ልምዶችን ያጠቃልላሉ Dégh (1972: 78)፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝ መሰረት ተደርገው የሚተረኩ ዝርዉ ቃል ትረካዎች በርዕሰ ጉዳያቸው ወይም በተራኪው ማንነት ተመርኩዘው የተለያዩ ክፍልፋዮች በማቅረብ ማጥናት የሚቻል መሆኑን Dégh ይገልፃሉ:: በዚህም የእውነተኛ ገጠመኝ ትረካዎችን የስራ ገጠመኝና ትዝታዎች (labor reminiscence)[1] ግለ ታሪክና የህይወት ታሪክ እና የስደትና ፍልሰት ወይም ስፈራ (emigrant and immigrant stories) ታሪኮች በማለት ይከፍሏቸዋል:: የዚህ ጥናት ትኩረትም ግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝ መሰረት ተደርገው በሚቀርቡ ትረካዎች ላይ ነው::

### 3.1.7. ግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝ ተረኮች (Personal Experience Narrative)

በአንድ ግለሰብ ልምድና ገጠመኝ ላይ ተመስረተው የሚቀርቡ ትረካዎች በአብዛኛው በአንደኛ መደብ የትረካ ስልት የሚቀርቡ፣ በቃል የሚደረሱና የሚተላለፉ ናቸው፡፡ እነዚህ ትረካዎች የተራኪውን የተለየ የአተራረክ ብልሃት (ውበትና ድራማዊ አቀራረብ) እና ልምድና ገጠመኝ የያዙ፣ አለማዊና እምነታዊ ታሪኮችን የሚያጠቃልሉ እንደሆኑ (Stahl, 1977, 1983; Elis, 2011 እና Allison, 2011) ይገልጻሉ::

እነዚህ በግለሰብ ልምድና ገጠመኝ የሚቀርቡ ትረካዎች ተስተላልፎታቸው፣ አደራረሳቸውና አቀራረባቸው ቃላዊ ሲሆን ለማኅበረሰቡ የትረካ ልማድና ስምምነት ማለትም የትረካ ቅርፅ፣ አውድና ፋይዳ ተገዥ ናቸው፡፡ በዚህ ባህሪያቸው ከፎክሎር ዘርፍ ውስጥ በቃላዊ ትውፊት (ስነቃል) ስር ይመደባሉ፣ ይዛመዳሉ፡፡

አንዳንድ የፎክሎር አጥኚዎች (Stahl, 1983: 270; Ellis, 2011: 460 እና Dégh, 2011: 781) የአንድን ግለሰብ ልምድና ገጠመኝ ተመርኩዘው የሚቀርቡ ትረካዎችን እምነታዊ እና አለማዊ በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል፡፡ ልምድና ገጠመኝን መሰረት አድርገው የሚቀርቡ እምነታዊ ትረካዎችን "memorate" በሚል ስያሜ ይጠሯቸዋል፡፡

እነዚህ እምነታዊ ትረካዎች (memorates) በአብዛኛው በአንደኛ ወይም በሁለተኛ መደብ የሚተረኩ ናቸው፡፡ ጉዳያቸውም ከልዕለ ሰብዕ በላይ የሆኑ እምነታዊ ስርዓቶችና ድርጊቶች አማካይነት የተገኙ ልምድና ገጠመኞችን መተረክ ነው፡፡ ከልምድና ገጠመኞች መካከል በመንፈስ መገለጥ፣ ከመናፍስት ጋር መገናኘት፣ በመለኮታዊ ሀይል መፈወስ እና መፈወስ[14] እንዲሁም ሞቶ መነሳት (near death experience) ይገኙበታል፡፡

---

[14] ከሁለቱ ቃል ውስጥ አንዱ 'ፈ' ይጠብቃል::

በእምነታዊ ትረካዎች አማካይነት አንድ አጥኚ ማኅበረሰቡ ለልማዳዊ ሆነ ለሐይማኖታዊ እምነቱ የሚኖረውን የፍቺ አውድ፣ ግለሰባዊ አመለካከትና የተስተላልፎት ሂደት መረዳት የሚችል መሆኑን Pentikainen (2011: 853) ይገልጻሉ፡፡ Stahl (1983: 270) በበኩላቸው *"Memorate usually reflect either the teller's acceptance or question of the traditional belief at the base of the story."* በማለት የ Pentikainen ሀሳብ ያጠናክራሉ፡፡

ግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝን መሰረት ተደርገው ከሚቀርቡ የትረካ አይነቶች ሌላው አለማዊ ትረካ ነው፡፡ ይህ ትረካ ታሪካዊ ክስተቶችን፣ የጉዞ ማስታዎሻዎችን፣ ትዝታዎችን፣ የስደት ወይም የፍልሰት ታሪኮችን እና ሌሎችን ያጠቃልላል፡፡

እንደ Stahl (1972, 270-275) ገለፃ እነዚህ ግለሰባዊ ትረካዎች የተራኪውን (የታሪኩ ባለቤትን) ልምድና ገጠመኝ፣ የተረኩን የመረጃ ምንጭነትና ተራኪው ለተረኩ የሚኖረውን አመለካከት መሰረት በማድረግ "other oriented" እና "self oriented" በማለት በሁለት መንገድ የሚተረኩ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ በ "other oriented" በሚቀርቡ ትረካዎች ተራኪው በሌሎች ሰዎች የተከናወኑ እምነታዊም ሆነ አለማዊ ገጠመኞች የሚተርኩበት ሲሆን በ "self, oriented" ደግሞ ተራኪው የታሪኩ፣ የድርጊቱ ወይም የስርዓቱ ተሳታፊና ባለቤት ነው፡፡ በዚህም ተራኪው በሕይወቱ ያጋጠመውን ወይም የፈጸመውን እምነታዊና አለማዊ ተረክ ራሱን እንደምስክር በመቁጠር ይተርካል፡፡ በትረካው ወቅትም ማኅበረሰባዊ፣ ግለሰባዊ እምነቶችንና እሴቶችን ይጨምራል፡፡

ከላይ የቀረቡት የግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝ ትረካዎች አይነትና የትረካ መንገድ ለዚህ ጥናት መረጃዎች የመተንተኛ መንገድ በመሆን አገልግለዋል፡፡ በዚህም ተጠኚ ማኅበረሰቡ ከቡዳ እምነት ጋር በተያያዘ ያለውን ልምድና ገጠመኝ መሰረት በማድረግ "በኔ የደረሰ" ፣ "በአይኔ በብረቱ ያየሁት"፣ "ሲባል የሰማሁት" እና "በተረት የማውቀው" በማለት የሚተርኳቸው እምነታዊ ተረኮች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 3.1.8. አውዳዊ የጥናት ፈለግ

አውድ አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ (text) የሚከወንበትን ሁኔታ፣ ስርአት፣ ምክንያት፣ ቦታ፣ ጊዜ እና አጠቃላይ ድባብ የሚመለከት ሲሆን አውዳዊ ፈለግ የአጠናን ስልት ደግሞ ይህንን ፎክሎራዊ ጉዳዩ በበቀለበት ባህላዊና ማህበራዊ ቀየ ውስጥ የማጥናትና የመግለጽ ተግባር ነው፡፡

Ben-Amos (1993፡ 215) በርካታ ሙሁራን የተለያዩ የአውድ ገጽታዎችን በተለያየ መንገድ በመከፋፈል መረጃ የመሰብሰቢያ፣ የመተንተኛና የመግለጫ ዘዴዎችን እንዳስቀመጡ ይገልጻሉ። በግላቸውም በዋናነት ሁለት ቁልፍና መሠረታዊ የፎክሎር የአውዳዊ ትንታኔ ዘዴዎች መኖራቸውን ይጠቁማሉ። እነዚህም የባህልና የሁነት አውድ ናቸው። የባህል አውድ ሰፊው የፎክሎር የአውድ ትንታኔና ፈር ማስያዥያ ሲሆን የማኅበረሰቡን የወል እውቀት፣ግንዛቤና ልማዳዊ ስምምነት እንዲሁም ማኅበረሰቦቹ ለልማዳዊ እምነቶቻቸው፣ ባህሪዎቻቸው እና በቋንቋቸው ውስጥ ላሉ ዘይቤያዊ ገለጻዎች ያላቸው ፍቺና ስሜት ያጠቃልላል። የሁነት አውድ ደግሞ ፎክሎራዊ ጉዳዩ የሚከወንበትን አጠቃላይ ድባብ ይመለከታል(Ben-Amos,1993፡ 215-216)።

Bauman (1986፣360-368) እንዲሁ ፎክሎረኛው በመስክ ያገኛቸውን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ሊያቀናጅባቸውና ሊያደራጅባቸው የሚችሉ የአውዳዊ ጥናትና ትንታኔ መንገዶችን ባህላዊ እና ማህበራዊ አውድ በሚል ሁለት ምድብ ከፍለው ያስቀምጣሉ። በነዚህ ምድቦች ውስጥም ስድስት ንዑሳን ክፍሎች መኖራቸውን ይገልፃሉ።

### 3.1.8.1. ባህላዊ አውድ

ባህላዊ አውድ የሚጠናው ፎክሎራዊ ጉዳይ በማኅበረሰቡ ባህል ውስጥ የሚኖረውን የፍቺ ስርዓት ማለትም ተምሳሌታዊና ዘይቤያዊ ውክልናን እንዲሁም ከልዩ ልዩ የፎክሎር ቅርጾች ጋር የሚኖረውን ትስስር የሚመለከት እሳቤን፣ ቀዬአዊ እውቀትን፣ ዝንባሌንና አተያይን ያካትታል። ይህ አውድ ፍቻዊ፣ ተቋማዊና የተግባቦት ስርዓት የተሰኙ ሦስት ገጽታዎች አሉት።

የመጀመሪያው ገጽታ የሆነው ፍቻዊ አውድ ባለቤቶቹ ለሚጠናው ፎክሎራዊ ቅርጽ ወይም ጉዳይ ያሏቸው እውቀት፣ ግንዛቤና ልምድ ላይ ያተኩራል። ከዚህ በተጨማሪ ይህ አውድ ተጠኚው ጉዳይ በባህሉ ውስጥ ያለውን ፍቺና ትርጓሜ ይመለከታል።

ሁለተኛው የባህላዊ አውድ ገጽታ ተቋማዊ አውድ ነው። ተቋም በሰፊው ፖለቲካን፣ ሐይማኖትን፣ ዝምድናን (ዘርን)፣ ምጣኔያዊ ሀብትን በጠባቡ ደግሞ ጉርብትናን፣ የህብረት ስራዎችን ወዘተ የሚያጠቃልል ነው። በመሆኑም ይህ አውድ ልዩ ልዩ የባህል ገጽታዎች እንዴት እርስ በእርስ እንደሚያያዙና እንደሚዛመዱ ለመተንተን የሚያግዝ ነው። በዚህም ፎክሎረኛው የሚጠናው ጉዳይ ከየትኛው ተቋም ወይም የባህል ገጽታ እንደሚዛመድ ማጥናት ይኖርበታል። ይህን አውድ መሰረት በማድረግ የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት የሆነው የቡዳ እምነት ጋር የሚያያዙ እንደ

ባህላዊና ሐይማኖታዊ የፈውስ ተቋማት፣ በቡዳነት የሚጠረጠሩ ቡድኖችና የጥቃቱ ሰለባዎችን ማንነት ወዘተ ለመገንዘብና ለመተንተን ተሞክሯል።

ሦስተኛው የባህላዊ አውድ ገጽታ የተግባቦት አውድ ሲሆን አውዱ የፎክሎሩ ባለቤቶች ልዩ ልዩ ቅርጾች አንዱን ከሌላው የሚለዩበትን የሚመሳሰሉበትን ቅርጽ፣ ስያሜ እና የግንኙነት ስርዓት ይመለከታል

### 3.1.8.2. ማህበራዊ አውድ

ማህበራዊ አውድ ለፎክሎረኛው ፎክሎራዊው ጉዳይ የሚቀርብበት (የሚከወንበት)ን ጊዜ፣ ቦታና ፋይዳ፣ የተሳታፊዎችን (የታዳሚዎችን) ማንነትና የሚኖራቸውን ሚና፣ የአቀራረቡን (አከዋወን) ልማዳዊ ስምምነቶችና መርሆች እንዲሁም በየደረጃው የሚከናወኑ ሁነቶችን፣ ክስተቶችንና ድርጊቶችን ቅደም ተከተል ለማጤን የሚያግዝ ነው። ይህ አውድም ሶስት ገፅታዎች አሉት።

የመጀመሪያው የማህበራዊ አውድ ገጽታ ማህበራዊ መሠረት አውድ ሲሆን የሚጠናው ጉዳይ የየትኞቹ ቡድኖች ነው የሚለውን ማህበራዊ አደረጃጀትና ማንነት ይመለከታል። ፎክሎራዊው ጉዳይ በግለሰብ ደረጃ ከግለሰቡ ህይወትና ልምድ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ እንዲሁም ለግለሰቡ የሚያስገኝለትን ፋይዳ እና የሚሰጠውን ትርጉም ለመመርመር የሚያግዝ የማህበራዊ አውድ ሁለተኛ ገጽታ ደግሞ ግለሰባዊ አውድ ነው። ሶስተኛው የማህበራዊ አውድ ገጽታ ሁኔታዊ አውድ ነው። ሁኔታዊ አውድ የፎክሎራዊውን ጉዳይ ተጨባጭ መቼት፣ የተሳታፊዎች ማንነትና ሚና፣ የክዋኔ መርህና ልማዳዊ ስምምነት፣ አተረጓጎም፣ እንዲሁም የሁነቶችን፣ የክስተቶችንና የድርጊቶችን አወቃቀርና አደረጃጀት ያካትታል።

በ Bauman (1986) ከተጠቀሱት የፎክሎር ባህላዊና ማህበራዊ አውዶች በተጨማሪ Oring (1986; 135-141) ሀገረሰባዊ ተረኮችን ለመረዳትና ለመተንተን የሚያግዙ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ግለሰባዊ እና ንጽጽራዊ የተሰኙ አውዶችን አቅርበዋል። ባህላዊ አውድ የተረኩን እሳቤ፣ ብያኔ፣ ተምሳሌታዊ ፍቺ ሲይዝ ማህበራዊ አውድ ደግሞ ተረኩ የሚተረክበትን መቼት፣ መርህ፣ ልማዳዊ ስምምነትና ቴክኒክ እንዲሁም የተረኩን አደረጃጀት ያጠቃልላል። ግለሰባዊ አውድ ተረኩ ከእያንዳንዱ የማኅበረሰቡ አባል ህይወት ጋር የሚዛመድበትን መንገድ ለመረዳት ያግዛል። ከዚህ በተጨማሪ ንጽጽራዊ አውድ ተረኩ ከቀረበበት አውድ እንዲሁም ከበቀለበት ማኅበረሰብ ባህልና ልማድ ባሻገር ከሌሎች ተረኮች ጋር ያለውን ግንኙነት ለመመርመር የሚረዳ መሆኑን Oring ይገልጻሉ።

## 3.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል የሚዳሰሱት ጥናታዊ ስራዎች በተለያዩ የጥናትና ምርምር ጉባኤዎችና መጽሔቶች ላይ የቀረቡ ጥናታዊ መጣጥፎች (articles) ናቸው፡፡ በዚህም ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው አምስት ጥናታዊ መጣጥፎች ተቃኝተዋል፡፡

በ Reminick (1974) "The Evil Eye Belief among the Amhara of Ethiopia" በሚል ርዕስ በ Ethology የጥናትና ምርምር መጽሄት ላይ የቀረበ ጥናታዊ መጣጥፍ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ የአማራን ማኅበረሰብ የቡዳ እምነት ስርዓት መመርመር እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ በዚህም የማኅበረሰቡ ጠቅላላ የእምነት ስርዓት (መዋቅር) በአራት እንደሚከፈልና የቡዳ እምነትም አንዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ አጥኚው የቡዳ እምነት፣ ምንነት፣ ምንጭ፣ የጥቃቱ አድራሽ ማንነት፣ ለጥቃቱ የሚወሰዱ የመከላከያ፣ የመለያና የመፈወሻ፣ ተቋማት፣ ዘዴዎችና ስርዓተ ክዋኔዎችን አብራርተው አቅርበዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አጥኚው ከእምነቱ ጋር የተያያዙ እንደ ጥንቆላ፣ ቅናት፣ ማኅበረሰባዊ ክፍፍሉሽ ወዘተ ያሉ አሳቤዎች ያሏቸውን ባህላዊና ማህበራዊ አውድ እንዲሁም ተምሳሌታዊ ፍቺን ተንትነው አሳይተዋል፡፡ ይህም የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው፡፡

ነገር ግን ለመተንተኛነት ይዘውት ከተነሱት ንድፈ ሃሳብ (symobolic analysis) አንጻር የቡዳ ጥቃትን የፈውስ ስርዓተ ክዋኔ (ritual) እና ተፈጥሯዊ አውድ አለማየታቸው እንዲሁም ትረካዎችን በስፋት አለመመልከታቸው የጥናቱ ደካማ ጎን ነው፡፡ በተጨማሪም የጥናቱ ትኩረትና በጥናቱ የተንተኑት መረጃዎች የተገኙት ሰሜን ሸዋ መንዝ ሆኖ ሳለ የጥናት ውጤታቸውን የሁሉም የአማራ ማኅበረሰብ (ገበሬዎች) እምነት አድርገው ማቅረባቸው ሌላው የጥናቱ ደካማ ጎን ነው፡፡ የ Reminick ጥናት በቡዳ እምነት ስርዓት ላይ ማተኮሩ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት የቡዳ እምነት ላይ ብቻ ሳይሆን በተረኮቹና በተፈጥሯዊ አውድ ላይ መመስረቱ ከ Reminick ጥናት ይለያል፡፡

Finneran Nail "Ethiopian Evil Eye Belief and the Magical Symbolism of Iron Working" (2003) በሚል ርዕስ በ Folklore ጥናታዊ መጽሄት ላይ የቀረበ ሲሆን የጥናቱ አላማ በኢትዮጵያ (አክሱም አካባቢ) የቡዳ እምነት ከእደ ጥበብ ሰራተኞች ጋር ያለው ግንኙነትና ተምሳሌታዊ ፍቺ ማሳየት ነው፡፡ አጥኚው የቡዳ እምነት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ እንደ ሰይጣን ወይም የመጥፎ ነገሮች ሁሉ ምክንያት ተደርጎ የሚቆጠር መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በቡዳነት የሚጠረጠሩ ሰዎች ከማኅበረሰቡ የተገለሉ፣ የተነጠሉና በመጠኔነት የሚታሰቡ፣ ማህበራዊ ቦታቸው ዝቅተኛ የሆነ፣ ብረት የሚያቀልጡ የእደ-ጥበብ ሙያተኞች መሆናቸውን ይጠቅሳሉ። Finneran በኢትዮጵያ፣ በአፍሪካና በሌሎች አገራት ልማዳዊ እምነቶች ውስጥ የቡዳ እምነት የተጠናበትንና የተገለጸበትን ሁኔታ የተለያዩ ጥናቶችን በመቃኘት ያስረዳሉ፡፡ የተገለሉና የተነጠሉ እንዲሁም መጤ ተደርገው የሚታሰቡ በእደ ጥበብ የሚተዳደሩ ቡድኖች ከኢትዮጵያ ባለፈ በአፍሪካም በቡዳነት እንደሚጠረጠሩ ምሳሌዎችን በማቅረብ ያብራራሉ፡፡ አጥኚው የቡዳ እምነት በኢትዮጵያ ልማዳዊ እምነት ውስጥና ከሌሎች አገራት ጋር ያለው ግንኙነት በስፋት መቃኘታቸው ለአጥኚዎች ጠቃሚ፣ ለንጽጽራዊና ቅኝታዊ ጥናት ተገቢ ቢሆንም ከአጥኚው ርዕስና አላማ ጋር አብሮ አይሄድም። በዋናነት ተገለሉ፣ ተነጠሉ ወይም ቡዳ ተባሉ የሚባሉት የእደ ጥበብ ሰራተኞች ከቡዳነታቸውና ከጥበበኛነታቸው ጋር የሚያያዙ እሳቤዎችና ተምሳሌታዊ ፍቺዎች በጥልቀትና በስፋት ቢተነተኑ ከጥናቱ ርዕስና አላማ ጋር ይስምሩ ነበር፡፡ ይህንን ባለማድረጋቸውም የዚህ ጥናቱ ደካማ ጎን ነው።

ይህ ጥናት በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ውስጥ የቡዳ ጥቃት ምንነት፣ አይነት እንዲሁም የመከላከያ፣ የመለያና የመፈወሻ ዘዴዎችና ስርዓተ ክዋኔዎችን ከእምነቱ የተያያዙ ተረኮችን የሚመረምር በመሆኑ ከ Finneran ጥናታዊ መጣጥፍ የተለየ ነው፡፡

Honea "Buda in Ethiopia" (1956) በሚል ርእስ ባቀረቡት አጭር ማስታወሻ (Note) ቡዳ በኢትዮጵያ በተለያዩ የቋንቋ ቤተሰቦች ውስጥ የተለያዩ ስያሜዎች ያሉት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ Honea በዚህ ጽሁፍ ቡዳ በዘር የሚወረስ ምናልባትም እስከ ህይወት ፍጻሜ የሚዘልቅ ሲሆን ጥቃቱን የሚያደርሰው ሰው የማያውቅ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የተለመዱ የቡዳ ጥቃት የመከላከያ መንገዶች፣ የጥቃቱ ምልክቶችና ለፈውስ የሚያገለግሉ መድኒቶችንም ዘርዝረዋል፡፡ Honea የቡዳ ጥቃት ተጋላጭነት፣ አይነት፣ መከላከያና መፈወሻ መንገዶችን እና ስርዓተ ክዋኔዎችን አልጠቀሱም። ይህ ጥናት ግን እነዚህን ጉዳዮች በዝርዝር የተመለከተ በመሆኑ ከ Honea ጽሁፍ ይለያል።

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያለው ጥናታዊ መጣጥፍ "Evil Eye Health Beliefs and Social Tensions among the Sidama" የሚለው የ Vecchiato (1991) ጥናት ነው፡፡ የዚህ ጥናት አላማ የሲዳማ ብሄረሰብን የእምነት ስርዓት በብሄረሰቡ ጤንነት ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊና አዎንታዊ ተጽእኖ ማሳየት ነው።

በብሄረሰቡ ቡዳ የሚባሉት የእደ ጥበብ ሰራተኞች ሲሆኑ እነዚህ ቡድኖችም ቡዳነት ከልጅ ወደ ልጅ በዘር ያስተላልፋሉ ተብሎ የሚታመን መሆኑን አጥኚው ይገልጻሉ። በብሄረሰቡ ምግብና መድሃኒት በሚወስድበት፣ በእርግዝና እና በወሊድ ወቅት እንዲሁም በክብት ጥበቃና በሰብሎች የቡቃያ ጊዜ የቡዳ ጥቃት እንደሚከሰት አጥኚው ያስረዳሉ። እነዚህ ቡድኖች በማኅበረሰቡ ዝቅተኛ ተቀባይነት የሚሰጣቸው፣ መሬት የሌላቸው፣ የተናቀ ስራን (ብረት መቀጥቀጥ፣ ቆዳ መፋቅና ሸማና ሸክላ ስራ) በመስራታቸው ይናደዳሉ። በዚህ የተነሳም መሬት ባላቸውና ባላባቶች በሆኑ ሰዎች ላይ ቅናት ያድርባቸዋል፣ የቡዳ ጥቃትም ያደርሳሉ ተብሎ ይታመናል።

የ Vecchiato ጥናት ከተለያዩ የልማዳዊ እና የቡዳ እምነትን አስመልክቶ ከቀረቡ ጽንሰ ሃሳቦች ጋር ተዛምዶና ተተንትኖ ቀርቧል። በጥናቱም የሲዳማ ብሄረሰብ የቡዳ ጥቃትን (እምነትን) በብሄረሰቡ የሚፈጠሩ ማህበራዊ ውጥረቶችን ማስፈን (ማርገብ)፣ ማህበራዊ ደረጃን (ማንነት) ለማጽናት እንዳገዛቸው ተገልጿል። የዚህ ምክንያት ደግሞ በብሄረሰቡ ለሚከሰቱ ህመሞችና ሌሎች ችግሮች ቡዳ የሚባሉት ሰዎች ምክንያት በመሆናቸውና ተገለው በመኖራቸው የተነሳ ነው።

የ Vecchiato ጥናት የቡዳ እምነትና ጥቃት ምንነት እንዲሁም የጥቃቱን አድራሽ ማንነትና አይነት፣ ጥቃቱ የሚደርስበት መንገድና አጋጣሚ በማየቱ ከኔ ጥናት ጋር ይያያዛል። ነገር ግን አጥኚው ለቡዳ ጥቃት የሚወሰዱ የመከላከያና የመፈወሻ ስርዓተ ክዋኔዎችን በጥልቀት አለመመርመሩና ስለ ቡዳ የሚነገሩ ተረኮችን አለማጥናቱ ከዚህ ጥናት ይለያል።

# 4. በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ቡዳ፣ ቡዳነትና ቡዳዊ ተረኮችን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ በቡዳ፣ በቡዳነትና በቡዳዊ ተረኮች ላይ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 4.1. ቡዳና ቡዳነት በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ

በዚህ ክፍል በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ውስጥ የቡዳ ምንነትና ፍቺ፣ የቡዳ ጥቃት አይነትና ምንጭ፣ የጥቃቱ ተጋላጭነት፣ መከላከያ፣መለያና መፈወሻ ዘዴ እና ስርዓተ ክዋኔ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 4.1.1. የቡዳ አገባባዊ ፍቺ

በተጠኚ ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ቡዳ የሚለው ቃል የልማዳዊ እምነቱ፣ በቡዳነት የሚጠረጠሩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እንዲሁም የቡዳ ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎች መጠሪያ ነው፡፡ በሰሜኑ የሀገራችን[15] አካባቢ ላይ ከልማዳዊ እምነት ጋር ተያይዘው የተሰሩ ጥናቶችም (Quren, 1979: 249; Honea, 1960: 60 እና Salamon, 1999) ቡዳ የሚለው ስያሜ የቡዳ እምነትን፣ ተጠርጣሪዎችንና የቡዳ ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎችን በአንድ የያዘ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

የመጀመሪያው ስያሜ እምነቱን የሚያመለክት ነው፡፡ በሰሜን ጎንደር ባሉ ማኅበረሰብ የቡዳ እምነት ሲባል አንድ ሰው አንድን ህይወት ያለውንም ሆነ ህይወት የሌለውን ነገር በማየቱ ብቻ ወይም አይቶ በማድነቁ ሳቢያ ጉዳት (ጥቃት) ያደርሳል የሚለውን ልማዳዊ እምነት ይመለከታል፡፡ እምነቱ ጥቃቱን ለመከላከል ወይም ለመለየትና ለመፈወስ የሚፈፀሙ ፎክሎራዊ ጉዳዮች እና ስርዓቶች ወይም ተግባሮችን ያጠቃልላል፡፡ በመሆኑም በማኅበረሰቡ የዚህ ልማዳዊ እምነት መጠሪያ "ቡዳ" ይባላል፡፡

ሁለተኛው ስያሜ ደግሞ ጉዳት (ጥቃት) ያደርሳሉ ወይም ለጉዳት የሚዳርግ መንፈስ አለባቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የሚጠሩበት ነው፡፡ ተጠርጣሪው ግለሰብ ከሆነ "ቡዳ" ቡድኖች ከሆኑ ደግሞ "ቡዶች" የሚል ስም ይሰጣቸዋል፡፡

---

[15] እንደ ጥናቶቹ ገለጻ የሰሜን ሀገራችን ክፍል ሲባል ጎንደር፣ ትግራይና ሰሜን ሸዋ አካባቢዎችን ይመለከታል፡፡

ስስተኛው ማኅበረሰቡ ቡዳ የሚለውን ስያሜ በቡዳ የተበሉ ሰዎች በቡዳው አምሳል ወይም መንፈስ ሆኖ ሲለፈልፍ የሚጠራበት ነው። አንድ ሰው በቡዳ ተበልቶ የፈውስ ስርዓት በሚከናወንበት (በሚለፈልፍበት) ወቅት በበላው ሰው አንደበት ይናገራል ተብሎ ስለሚታመን በበላው ሰው ስም ወይም "ቡዳ" ወይም "ቡዳው" እየተባለ ይጠራል።

### 4.1.2. የቡዳ ማህበረ-ባህላዊ ፍቺ በስሜን ጎንደር ማኅበረሰብ

አንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ከማህበራዊና ባህላዊ አውድ አንጻር ለመተንተን ለሚጠናው ፎክሎራዊ ጉዳይ ማኅበረሰቡ የሚሰጠውን ፎክሎራዊ አተረጓጎም፣ ዘልማድ ወይም የፍቺ አተያይ (semantic dimensions) እንደ ተምሳሌታዊ (ዘይቤያዊ) ውክልና እንዲሁም የሚከወንበትን ምክንያት፣ ስርዓት፣ ሂደትና መቼት ማጤን እንደሚያስፈልግ Bauman (1986: 363) ይገልፃሉ።

የተጠኚ ማኅበረሰብ አባላት ቡዳ የሚለውን ቃል በእለት ተእለት ማህበራዊ እና ባህላዊ ገጽታዎች ውስጥ የተለያዩ ተምሳሌታዊና ዘይቤያዊ ውክልና በመስጠት ማህበራዊ ችግሮችን፣ ቅናትን፣ ምቀኝነት፣ መጥፎ እድሎችን እና አጋጣሚዎችን ይገልጹበታል። ለምሳሌ በማኅበረሰቡ አንድ ሰው በእግሩ እየተጓዘ ድንገት ድንጋይ ቢያደናቅፈው ያደናቀፈው ድንጋይ ቡዳ እንደሆነ[16] ይታመናል። በተመታበት ወቅትም ጥቂት መቀመጥና ያደናቀፈውን ድንጋይ "ቡዳ... ቡዳ" በማለት መሳደብና በድንጋይ መምታት ይኖርበታል። ድንጋዩን ባይመታውና ቡዳ ብሎ ባይሰድበው የሚሄድበት ጉዳይ አይሳካም፣ መንገድ ላይም እክል ይገጥመዋል ተብሎ ይታመናል። ይህ በድንጋይ የተወከለው የቡዳ ፍቺ መጥፎ እድልንና አጋጣሚን ያመለክታል።

ሌላው በማኅበረሰቡ የእለት ተእለት ማህበራዊ ተራክቦዎች ውስጥ ቡዳ የሚለው ቃል የምቀኝነትን ፍቺ ይይዛል። ለምሳሌ በማኅበረሰቡ አንድ ሰው ያሰበው ሳይሳካ፣ ያለመው ግብ ሳይመታ ሲቀር "ምን አይነት ቡዳ የሆነ ሰው" ወይም "ምን አይነት ቡዳ የሆነ ቀን አጋጠመኝ" ይላል። በቡዳነት የተመሰሉት ሰው ወይም ቀን ለሰውየው ስኬት አልባነት እንደምክንያትና ምቀኛ ተደርገው ይታሰባሉ።

በማኅበረሰቡ አንድ ሰው አንድን ስራ ለመስራት አስቦ ወይም አቅዶ በልቡ ያሰበውንና ያቀደውን ሌላው ሰው ቢያውቅ ወይም ቢገምት ያን ሰው "ቡዳ" ይሉታል። ተምሳሌታዊ ፍቺውም አዋቂ

[16] "ቡዳ" ሲባል በቡዳነት የሚጠረጠረው ሰው ሳይሆን የምቀኝነትና የመጥፎ እድልን ተምሳሌታዊ ፍቺን የሚያመላክት ነው።

ወይም ብልህ እንደማለት ነው።[17] ይህንንም ጉዳይ "ከባለቤት ያወቀ ቡዳ ነው" በሚለው አባባላቸው ይገልጹታል። ከዚህ በተጨማሪ በማኅበረሰቡ አንድን ሰው በሀሜት ወይም ፊት ለፊት "ቡዳ እኮ ነው!" ወይም "ቡዳ እኮ ነህ!" ማለት የሰውየውን ባህርይ እና ችሎታን የሚገልጹ ሁለት ፍቺዎችን ይይዛል። የመጀመሪያው ፍቺ ሰውየው አንድን ተግባር ለብቻው (በድብቅ) ሰርቶ ሲጠቀም ወይም ሚስጥሩን፣ ምኞቱን፣ ፍላጎቱንና ማንነቱን የማይናገር፣ ድብቅና "ልቡ የማይገኝ" መሆኑን ለማመልከት የሚነገር ነው። ሁለተኛው ፍቺ ደግሞ ሌሎች ሰዎች ሊያደርጉት ወይም ሊያከናውኑት የማይችሉትን ነገር እሱ ሲፈፅም ብልህነቱን ወይም አዋቂነቱን ለመግለጽ የሚቀርብ ነው። ከብልህነትና ከአዋቂነት ጋር በተያያዘ በሰሜን ሸዋ ቡዳ "ጠይብ" እየተባለ ይጠራል (Reminick, 1974፡ 280)። "ጠይብ" የሚለው ቃል ደግሞ ጠቢብ ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም "ብልህ፣ ዐዋቂ፣ ተራቃቂ.." እንደማለት ነው (ኪዳነ ወልድ፣1948፡ 489)።

ከዚህ በተጨማሪ በማኅበረሰቡ ዘንድ ጢንዚዛ በቡዳ ይወከላል። ለምሳሌ ያህል ጥቁር ጢንዚዛ ከቤት ውስጥ ከገባ "ቡዳ ገባ ይባላል" በዚህም ከቤቱ ውስጥ ባሉ ቤተሰብ ውስጥ አንዱ በቡዳ ሊጠቃ እንደሚችል ጥቆማ ይሠጣል። በዚህ ጊዜ የቡዳ ጥቃት መከላከያ እርምጃዎች ይወስዳሉ። በመሆኑም ጥቁር ጢንዚዛ እንደ ቡዳ እና የቡዳ ጥቃት አመልካች ተደርጎ ይታመናል። ጢንዚዛው ከቤት ከመውጣቱ በፊትም እንዲገደል ይደረጋል። በሚገደልበት ወቅትም "አንተ ቡዳ አውቄብሃለሁ" ይሉታል። የዚህ ፍቺም ጥቃት ለማድረስ ያሰበውን ቡዳ መንፈስ እንደመግደልና እንደማሸማቀቅ ይቆጠራል።[18]

### 4.1.3. የቡዳ ጥቃት በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ

በሰሜን ጎንደርም ሆነ በሌሎች ማኅበረሰቦች በቡዳነት የሚጠረጠር ሰው አንድን ሰው፣ እንስሳ፣ ተክልና ግዑዝ ነገር ላይ አይኑን በመጣሉ (በመመልከቱ) ሳቢያ ጉዳት ማድረስ የቡዳ ጥቃት እንደሆነ በዚህ ጥናት በምዕራፍ ሶስት የንድፈ ሃሳብ ዳራ ላይ ተገልጿል። ይህ ጥቃት "በቡዳ መበላት" ይባላል። በመሆኑም በዚህ ክፍል በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት መሰረት በቡዳ የመበላት አሳቤ ምንነት፣ ቡዳ የሚባለው ሰው ማንነት፣ ማንን፣ ለምን፣ መቼና እንዴት ጥቃት እንደሚያደርስ፣ የቡዳ አይነቶችና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ተተንትነው ቀርበዋል።

---

[17] አዋቂነቱ ወይም ብልህነቱ እንደ አዎንታዊ ወይም መልካም ጥበብ አይታይም። የዚህ ፍች ምንጭ ምናልባት በቡዳነት የሚጠረጠሩ ሰዎች እንዳች አሉታዊ ሀይል ወይም ስውር ጥበብ አላቸው ከሚለው እምነት ጋር የሚያያዝ ይመስላል።
[18] ከዚህ በተቃራኒ በማኅበረሰቡ ልማድ አፈንጋጭ ቀለም ያለው ጢንዚዛ የመልካምና የሲሳይ ተምሳሌት ተደርጎ ይታመናል። ወደ ቤት በገባ ጊዜም "እንኳን" ገባ ይባላል።

#### 4.1.3.1. በቡዳ የመጠቃት (የመበላት) ፅንሰ ሀሳብ በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ

በ "ቡዳ መበላት" የሚለው እሳቤ በማኅበረሰቡ ዘንድ በቡዳነት የሚጠረጠረው ሰው አንድን ነገር በተመለከተ ጊዜ ህመም ወይም እንከን መፍጠርን ይመለከታል። በማኅበረሰቡ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች በሠው ወይም በእንስሳ ላይ አይናቸውን በጣሉ ጊዜ በአንዳች "ስውር ጥበብ" ህመምን ይፈጥራሉ፤ ሰውነትን ያከሳሉ፤ የሠውየውን ልቦና ይሰልባሉ፤ ከፍ ሲልም ጥቃት ያደረሱበትን (የበሉትን) ሰው ገድለው የራሳቸው ያደርጋሉ ተብሎ ይታመናል። ይህን በእይታና በስውር ጥበብ አማካይነት የሰውን ልቦና መስረቅ፣ ሰውነት ማክሳትና እና ሀብትን፣ ንብረትንና ህይወትን ማሳጣት ማኅበረሰቡ በ "ቡዳ መበላት" የሚል ፍቺ ይሰጠዋል። በዚህም በቡዳነት የተፈረጁ ሰዎች ወይም ቡድኖች በእይታና በስውር ጥበብ በሰው፣ በእንስሳና ሌሎች ነገሮች ላይ ጥቃት(ጉዳት) ሲያደርሱ "በሉ" ይባላል። የሚበሉበት (ጥቃት የሚያደርሱበት) መንገድም በአንዳች "ሰይጣናዊ" ወይም "ስውር ጥበብና ሀይል" እንደሆነ ይታመናል። በዚህም ቡዳ በሚባለው ሰው (ጥቃት አድራሹ) እና በቡዳ ተበላ በሚባለው ሰው (በሰለባው) መካከል ምንም አይነት አካላዊ ንክኪ አለመኖሩን መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ።

ሁሉም መረጃ አቀባዮቹ ቡዳ የሚባለው ሰው "ሲበላ" ወይም ጥቃት ሲያደርስ አይተው ወይም ሌላ ሰው አየሁ ሲል ሰምተው የማያውቁ መሆኑን ይገልጻሉ። ይህንንም ሀሳባቸውን "ቡዳ በቀኝ እጁ ካራ [ቢላዋ] በግራ እጁ [የሰው] ስጋ ይዞ ሲበላ ያየ የለም።" በሚለው አባባላቸው ያጠነክሩታል። ወይዘሮ ላውሸ ጓዴ[19] ይህንን ጉዳይ "ቡዳ እንደ ጋኔል ወይም መንፈስ ነው እንጅ የሠውን ሰው በካራ ገዝግዞ፣ ስጋው ቆርጦ፣ ደሙን መጥምጦ አይበላውም፣ አይጠጣውም በአይኑ ብሌን ነው የሚወጋ" (22/08/03 ዓ.ም. ደልጊ ከተማ፣ የቡድን ውይይት።) በማለት የቡዳን የመበላት እሳቤን ይገልፃሉ።

ይህ ቡዳ የሚባለው ሰው እይታ ወይም የአይን ብሌን በሰው ብቻ የተገደበ ሳይሆን እንስሳትንም በእይታው ጉዳት ያደርሳል ተብሎ ይታመናል። ጥቃት ሲደርስባቸውም በቡዳ ተበሉ ይባላል። ቄስ መላከ ገነት ካሴ አለሙ[20] እንስሳት በቡዳ ተበሉ የሚባሉበትን መንገድ "የዛ ሰውየ አይን ቅድም እንዳልነው በቡዳው አይን ላይ የተቀረፀ ነገር አለ ይህ ሰው ያያት ላም ላሚቷን ጋቷ ትልቅ ሆኖ ያያት እንደሆን ደም ትታለባለች። ይህ ምንድን ነው የሰውየው አይን እዛ ሄዶ ስለወደቀባት ነው" (22/08/03 ዓ.ም. ደልጊ ከተማ፣ የቡድን ውይይት።) በማለት ይገልጻሉ።

---

[19] ወይዘሮ ላውሸ ጓዴ፣ የ38 ዓመት የቤት እመቤት እና በጣፅላ ወረዳ የደልጊ ከተማ የቀበሌ 01 ነዋሪ ናቸው።
[20] እድሜያቸው 70 ሊሆን የሚጠጋ ወረዳ የሀገር ሽማግሌና የደብረ ገነት ደልጊ ቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ናቸው፡

### 4.1.3.2. የቡዳ ጥቃት ምንጭ በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ

በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ውስጥ የቡዳ ጥቃት ምንጭ መንፈስና ሰው እንደሆነ ይታመናል።

የቡዳ ጥቃት ምንጭ መንፈስ እንደሆነ ለሚያምኑ የማኅበረሰቡ አባላት ቡዳ እርኩስ መንፈስ ሲሆን አመጣጡንም ከሰው ልጅ አፈጣጠር፣ ከሰይጣን ወደ ምድር መውረድና ከሰው ልጅ የሆጥያት ብዛት ጋር በማያያዝ የተለያዩ አስረጅ ትረካዎችን ያቀርባሉ።

በማኅበረሰቡ ቃላዊ ትውፊት መሠረት አዳም ብዙ ልጆች ነበሩት። ከእነዚህ ልጆች መሀከል የተወሰኑት በጣም ቆንጆ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ቆንጆ ያልሆኑ ነበሩ። አንድ ቀን እግዚአብሄር የሰው አምሳልን በመያዝ የአዳም ልጆችን ለመጎብኘትና ለመባረክ ወደ አዳም ቤት ይገኛል። እግዚአብሄርም የአዳምን ልጆች ለመመረቅ አዳምን ልጆችህን አምጣቸው ይለዋል። አዳምም በሰው አምሳል ከቤቱ በእንግድነት በመገኘቱ የሚያምሩ ልጆቼን አይቶ ጉዳት ያደርስብኛል በሚል ፍርሀት ቆንጆ የሆኑትን ልጆች በመደበቅ የማያምሩትን አምጥቶ ሰውየው (እግዚአብሔር) እንዲመርቅለት ያደርጋል። እግዚአብሔርም ውብ ያልሆኑትን ከመረቀ በኋላ የተደበቁትን ሁሉም የተደበቁ መንፈሶች ይሁኑ አላቸው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በእግዚአብሔር የተረገሙት የአዳም ልጆች ርኩስ መንፈስ ሆኑ። ከእነዚህ ርኩስ መናፍስት ውስጥም አንዱ ቡዳ እንደሆነ ይታመናል (ቄስ መላከ ገነት ካሴ አለሙና አቶ መንገሻ ስዩም)። በዚህም ማኅበረሰቡ ቡዳ ርኩስ መንፈስ ሲሆን ይህ ርኩስ መንፈስ ደግሞ በፈጣሪ ርግማን የመጣ እንደሆነና የዚህ መንፈስ ያረፈበት ሰውም ቡዳ ይሆናል በሚል ያምናል።

ከዚህ በተጨማሪ በማኅበረሰቡ ዝርዉ ቃል ተረክ ውስጥ የቡዳ አመጣጥ ከሰይጣን ወደ ምድር መላክ ጋር በማያያዝ የቡዳ ምንጭ መንፈስ መሆኑን ቄስ መልአከ ሰላም ተውህቦ ማሩ[21] የሚከተለውን ትረካ ያስረዳሉ።

> ቡዳ የሚለውን የኛ መፅሐፋችን ርኩስ መንፈስ ነው የሚለው። ርኩስ መንፈስ ማለት አዳምና ሄዋንን አሳስቶ እፀ በለስ አስበልቶ እኔ አምላክ ነኝ እንደ አምላክ አመስግኑኝ አሉ ዳያቢሎስ። ከሱ ጋራ አምላክ ነው ያሉት እግዚአብሔር ተቃውሟቸው እናንተ እንግዲህ የኔ ጓደኛ ከሆናችሁ ከዚህ መኖር የለባችሁም ብሎ ወደ ምድር ጣላቸው ይላል ወደዚህ ምድር። እነሱ የአየር ኃይል ነው የሚባሉት ተፈጥሮአቸው ግን መላይክት ናቸው። እንደ ሚካኤል እንደ ገብርኤል ከነፍስና ከአየር ነው ተፈጥሮአቸው። እነዚህ ከዚህ ምድር የመጡት ለኛ ለአዳም ልጆች ተቃራኒ ሆነው። ቡዳ ይሆናሉ። ወባም ይሆናሉ። በብዙ የአዳም ልጅ የሚበክሉ። አጋንንት መንፈስ ርኩስ ይባላል። ርኩስ መናፍስት ይላቸዋል መጽሃፋችን። እነሱ ቡዳም

[21] በደንቢያ ወረዳ የጭሎ ቀበሌ ነዋሪ ማህበር ነዋሪ እና የደብረ ሰላም ጭሎ ማሪያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ናቸው። እድሜያቸውም 72 ነው።

> እየሆኑ በአይናቸው ሰውን ይበላሉ። (ቄስ መልአከ ሰላም ተውህቦ ማሩ፣ 28/08/03 ዓ.ም፣ የቡድን ውይይት)

ከትረካው መረዳት እንደሚቻለው በማኅበረሰቡ ዘንድ ቡዳ የመጥፎ እድል፣ የህመም፣ የበሽታ እና የቅናት ምንጭ አጋንንት (ሰይጣን) እንደሆነ ይታመናል። ይህ አጋንንት በሰው ላይ እያረፈ ጠባይንና ቅርጹን እየቀያየረ በሰዎች ላይ ጉዳት ያደርሳል፣ ይገድላል፣ የነገ ተስፋውን ያጨልማል፣ ሀብትና ንብረቱን ያሳጣል ተብሎ ይታመናል።

የቡዳ ምንጭ መንፈስ ነው ከሚለው ጋር ተያይዞ መሪጌታ አዳነ አስፋ[22] ቡዳ በቡዳነት በሚጠረጠረው ሰው ላይ ተጠርጣሪው ባላወቀበት መንገድ በሰውየው ላይ የሚያድር የሰይጣን መንፈስ እንደሆነ ይገልጻሉ። ይህ እርኩስ መንፈስ በቡዳነት በሚጠረጠረው ሰው ላይ አርፎ የሰውየውን ተግባርና ስም በመውሰድ መንፈሱ በአንድ ሰው ላይ ጥቃት ሲያደርስ የተጠርጣሪውን ሰው ስም እየጠራ፣ ተግባርና ባህሪውን እየጠቀሰ በማኅበረሰቡ ዘንድ ቡዳ ተብሎ እንዲጠራና እንዲገለል ያደርገዋል ይላሉ። የዚህ እርኩስ መንፈስ ምንጭ ደግሞ የሰው ልጅ ሀጥያት መብዛትና የስምንተኛው ሺ ፍጻሜ (ትንቢት) መድረስ መሆኑን ይገልጻሉ።

> አምስቱ ስንደረት ስናስሉት ፓርሰሉት ተብለው እስከ ስምንተኛው ሺህ ታስረው የነበሩ አጋንቶች ነበሩ። በስምንተኛው ሺህ ትፈታላችሁ ተብለው ቃል ተገብቶላቸው ስለነበር ዛሬ ተፈተው በየቤታችን፣ በየምድጃችን፣ በልጆቻችን ተሰራጭተው እነዚህ አጋንቶች ባልና ሚስቶችን በማጣላትና በማጋደል ቦታውን ይዘውታል። እነዚህ ሲፈቱ ግን ስራ ስላጡ እኔ አንተን በላሁህ አንተ እኔን በላሁህ እየተባባሉ የሚያስለፈልፉ እርስ በእርስ ለማጋደል የተሰራጩና የተለቀቁ አጋንቶች በመሆናቸው ስምንተኛው ሺ ለመድረሱ ስለሚያረጋግጥ እነዚህ ናቸው አዳኝ ማነው ስምህን ያልከኝ [ሙሉቀን] ሙሉቀንን በላው ሙሉቀን አዳነን በላው እያልን እንድንለፈልፍና እንድንጋደል የሚያደርጉ አጋንት ናቸው። እንጂ ሰውን ሰው አይበላውም። (መርጌታ አዳነ አስፋ፣10/09/03 ዓ.ም፣ ቃለመጠይቅ)

ከላይ በቀረበው የመርጌታ አዳነ እስፋ ሀሳብ መሠረት ቡዳ የሚባሉ ተለይተው የሚታወቁ ሰዎች ቡዳነትን ፈልገው ያመጡት ሳይሆን ሳያስቡት በላያቸው ላይ ያረፈ እርኩስ መንፈስ ነው። ይህ እርኩስ መንፈስ ደግሞ የስምንተኛው ሺ ትንቢት በመፈጸሙ የመጣ የሰው ልጅ የሀጥያት ብዛት ውጤት ነው በሚል ይታመናል።

የቡዳ ጥቃት ምንጭ ሰው እንደሆነ ለሚያምኑ የማኅበረሰቡ አባላት ደግሞ ቡዳ ሰው ሲሆን አመጣጡንም በመድሃኒት እና በዘር አማካይነት እንደሆነ ይታመናል። በማኅበረሰቡ በቡዳነት

[22] በጎንደር ቅሬያ ወረዳ የሰር ሳር ውሻ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ ሲሆኑ የባህል መድሀኒት ባለሙያ እና የወረዳው የባህል መድሃኒት ባለሙያዎች ማህበር አባል ናቸው። እድሜያቸውም 53 ነው። ለቡዳ ጥቃት በባህላዊ መድሃኒት አማካኝነት የፈውስ አገልግሎት ይሰጣሉ።

የሚጠረጠሩና ተለይተው የሚታወቁ (በስም የሚጠቀሱ) ግለሰቦችና ቡድኖች እንዳሉ ይታመናል፡፡ የእነዚህ ተጠርጣሪዎች የቡዳነት ምንጭ በመድሐኒት (በእፅ) እና በዘር እንደተገኘም ይነገራል፡፡ ማኅበረሰቡ እነዚህ ተጠርጣሪዎች ቡዳነትን በአጋጣሚና በዘር ያገኙት መሆኑን ያውቃሉ በሚል ያምናል፡፡ በዚህም ቡዳ በተጠርጣሪዎቹ ላይ ያደረ እርኩስ መንፈስ ሳይሆን ራሳቸው ተጠርጣሪ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እንደሆኑ ይታመናል፡፡

በቡዳነት የሚጠረጠረው ሰው ቡዳ መሆኑን ያውቃል የሚባልበት የመጀመሪያው ምክንያት ቡዳ በዕፅ ይመጣል በሚለው አስተሳሰብ ነው፡፡ ይህም በማኅበረሰቡ ልማድ አንድ ሰው ሀብታም፣ ጀግና፣ ጎበዝ፣ ጥሩ ተሚጋች ለመሆን መድሃኒት ይጠጣል፡፡ በዚህም ይሳካለታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ነገር ግን ሀብታም፣ ጀግና ጎበዝ ለመሆን የሚጠጣው መድሃኒት በአጋጣሚ ቡዳ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ይህ ሊከሰት እንደሚችልም ከመጠጣቱ በፊትም ሆነ ከጠጣ በኋላ ያውቀዋል ይባላል፡፡[23] በመሆኑም ቡዳ የሚባላው ሰው ቡዳነትን ሳያስበው በአጋጣሚ ያመጣው ቢሆንም እንኳ ቡዳነቱን ግን ያውቀዋል ብለው ያምናሉ፡፡

ሌላው ማኅበረሰቡ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ወይም ቡድኖች ቡዳነታቸውን የሚያውቁ መሆኑን የቡዳ ዘር ያለባቸውን ቡድኖች እንደ አብነት ይጠቅሳል፡፡ በዋናነት በተለምዶ አጠራር "ፈላሻ" ወይም ራሳቸውን "ቤተ እስራኤል" እያሉ የሚጠሩ ቡድኖች የቡዳነት የዘር ሀረግ እንዳለባቸውና ቡዳ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ እነዚህ የቡዳ ዘር አለባቸው የሚባሉ ቡድኖች ቡዳ መሆናቸውን አምነው ባይቀበሉም ከእነሱ ውጭ ባሉ ማኅበረሰቦች ወይም ቡድኖች በቡዳነት የሚጠረጠሩ መሆኑን ያውቃሉ፡፡

በአጠቃላይ በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ውስጥ በመድሃኒት ወይም በዘር አማካይነት ቡዳ የሆኑ ሰዎች መኖራቸውንና ቡድንታቸውንም እንደሚያውቁ ይታመናል፡፡ ከዚህ በመነሳትም ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ቡዳ ከሆኑበት አንጻርና ከሚያደርሱት ጉዳት አኳያ የተለያዩ የቡዳ አይነቶች እንዳሉ ይጠቀሳል፡፡

---

[23] በዚህ ጥናት ውስጥ ገጽ 40 (4.1.4.1.1) ላይ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

### 4.1.4. የቡዳ አይነቶች በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ

በማኅበረሰቡ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ከሚያደርሱት ጥቃትና ቡዳ ከመሆኛ መንገድ አንጻር የተለያየ ስያሜ አላቸው፡፡ በዚህ ክፍል የቡዳ አይነቶች ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ከሚያደርሱት ጉዳትና ቡዳ ከመሆኛ አንጻር ቀርቧል፡፡

#### 4.1.4.1. የቡዳ አይነቶች ከቡዳነት አንጻር

በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ስርዓት መሰረት ቡዳነት ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ቡዳ የሆኑበትን (የሚሆኑበትን) መንገድ ይመለከታል፡፡ በዚህም የቡዳ ጥቃት አድራሾች በዘር፣ በትምህርት ወይም በእፅ እና በተፈጥሮ ቡዳ እንደሚሆኑ ይታመናል፡፡ ማኅበረሰቡ ይህንን መሠረት አድርጎም የዘር ቡዳ፣ የእፅ ወይም የትምህርት ቡዳ እና የተፈጥሮ ቡዳ በሚል ስያሜ ይጠራቸዋል፡፡

##### 4.1.4.1.1. የዕፅ ወይም የትምህርት ቡዳ

በማኅበረሰቡ ዘንድ ከሠውና ከተፈጥሮ የላቀ ሀይል ያላቸው፣ የሰው ልጅ ሊፈጽማቸው የማይችሉ ተግባራትንና ተአምራትን የሚያከናውኑ ተቋማትና ግለሰቦች እንዳሉ ይታመናል፡፡ ተቋማቱ ያሉባቸው ቦታዎችና ግለሰቦች ተለይተው የሚታወቁ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ከግለሠቦቹ ይልቅ ቦታቸው ብቻ ይጠቀሳል፡፡ እነዚህ የልዕለ ሀይል ባለቤት እንደሆኑ የሚታመኑ ተቋማትና ግለሰቦች ለሰዎች አንዳች ጥቅምን የሚያስገኝ ወይም ጉዳትን የሚያስከትል ስውር ሀይልና ጥበብን በእጽ ወይም በመድሃኒት ይሰጣሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ግለሰቦቹና ተቋማቱ በእፁ ወይም በመድሐኒቱ አማካይነት ሰዎችን ሀብታም፣ ጀግና፣ ዝነኛ፣ ተሚጋች ወዘተ የማድረግ ሀይል አላቸው ይባላል፡፡ ከዚህ ተያይዞ ጀግንነትን፣ ሀብትን፣ ዝናን ሌሎች ጥቅሞችን ለማግኘት የሚወሰደው መድሃኒት በአጋጣሚ ቡዳ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህ በመነሳት ቡዳነት በእፅ ወይም በመድሃኒት እንደሚመጣ ማኅበረሰቡ ያምናል፡፡ በዚህ መንገድ የሚመጣ ቡዳነትን የተጠኚ ማኅበረሰብ አባላት *"የመድሃኒት ቡዳ"* ወይም *"የእፅ ቡዳ"* በማለት ይጠሩታል፡፡

ማኅበረሰቡ በመድሃኒት ቡዳ እንደሆኑ የሚታመኑ ሰዎች ቡዳ የሆኑበትን መንገድ ማለትም የመድሃኒቱን (የእፁን) አወሳሰድ፣ የሚወስዱበትን ቦታና ምክንያት እንዲሁም መድሃኒቱን የሰጧቸውን ሰዎች ማንነት "ሲባል የሰማሁት" በሚል ይተርካል፡፡ ከትረካው መረዳት እንደሚቻለው በማኅበረሰቡ እምነት ሰዎች ሀብታም፣ ጀግና፣ ዝነኛ፣ ለመሆን፣ ተሚገቶ

ለመርታት፣ ትምህርትን ቶሎ ለመረዳት፣ ወዘተ ቋራ፣ መንዝ፣ ጎጃምና ሱዳን ጠረፍ አካባቢ ካሉ መድሃኒት ሰጪዎች ወይም እፅ አጠጭዎች ዘንድ ይሄዳሉ ይባላል፡፡ ከነዚህ ሰዎች ዘንድ በመቅረብ የሚጠበቅባቸውን ክፍያ ወይም ስጦታ ከሰጡ በኋላ መሆን የሚፈልጉትን ነገር ይናገራሉ፡፡

ተጥሉም የሚፈልጉትን ሀይል ወይም ጥበብ ለማግኘት መድሐኒት ሰጭው የሚያዛቸውን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ከሠው የተለየ ሀይልና ጥበብ ይሰጣል የተባለውን መድሐኒት ወይም እፅ መጠጣትን ያካትታል፡፡ እነዚህ በመጠጥ መልክ የሚሰጡ መድሐኒቶች (እፆች) ተመሳሳይ መጠን፣ ቀለምና ቅርፅ ባላቸው ዋንጫዎች ወይም ስኒዎች ተቀምመው በፈሳሽ መልክ ይቀመጣሉ፡፡ እፆችም ሀብታም፣ ጀግና፣ ጎበዝ፣ አራሽ ወዘተ የማድረግ ሀይል ያላቸው ሲሆን ከስኒዎች አንዱ እንደ ኢጋጣሚ ቡዳ የማድረጊያ ጥበብን ይይዛል፡፡ መድሐኒት ሰጭውም እንዳች ሀይልና ጥበብና ፈልገው ለመጡት ሰዎች ቡዳ የመሆን እድል ሊገጥማቸው እንደሚችል ይነግራቸዋል ይባላል፡፡ ከዚያ በኋላ የተደረደሩትን ስኒዎች በማንሳት ይጠጣሉ፡፡ ከዚያም የእድላቸውን ውጤት (የወረሱትን ጥበብ ወይም ሀይል) መድሐኒት አጠጭው (እፅ ሰጭው) ይነግራቸዋል፡፡ በዚህ መንገድ ከሰዎቹ መካከል ሀብታም፣ ጀግና፣ጎበዝ፣ ዝነኛ፣ ወዘተ. እሆናለሁ ብሎ የጠጣው እፅ የቡዳ ሆኖ ሲገኝ ሠውየው ቡዳነትን በእፅ አገኘው ይባላል፡፡ ከዚህ በመነሳት በማኅበረሰቡ "የእፅ ቡዳ" በሚል ይጠራል፡፡ አቶ ታረቀኝ እምሩ[24] ከላይ የቀረበውን ጉዳይ የሚያጠናክር ሀሳብ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> "አንድ ታዋቂ የሆነ ሰው በፍንጃል[25] ይቀምምላቸዋል ነው የሚባለው፡፡ የሀብትም የድህነትም፣ የጉብዝናም፣ የሙግትም በደንብ ይዘልለዋል[26]፡፡ በኋላ የሚደርስ ይደርሰዋል፡፡ እያነሳ ይጠጣዋል፡፡ ሀብት የደረሰው የሀብት፡፡ ድህነት የደረሰው የድህነት፡፡ እንደ እፅ ነው፡፡ ከዛ ደህና የሚሆኑት ደህና፣ ቡዳ የሚሆኑት ቡዳ ይሆናሉ፡፡" (ታረቀኝ እምሩ፣ 04/08/03 ዓ.ም.፣ ቃለመጠይቅ)

በማኅበረሰቡ ዘንድ የቡዳነታቸው ምንጭ እፅ እንደሆነ የሚታመን ሰዎች እላይ እንደተገለፀው በቅድሚያ ሙሉ በሙሉ ቡዳ ለመሆን ፈልገውና ፈቅደው የሚጠጡት እንዳልሆነ *"መጀመሪያ እሚሄዱት ሀብት እናገኛለን ብለው እንጂ ቡዳነትን መማር ፈልገው አይደለም፡፡ ምክንያቱም በሰው ስማቸው እንዲጠሩ አይፈልጉም፡፡ ሠው ሊበሉ ሳይሆን ለሀብት ነው የሚሄዱት"* በማለት ቄስ መላክ ገነት ተውህቦ ማሩ (28/08/03 ዓ.ም፣ የቡድን ውይይት) ይገልፃሉ፡፡ በማኅበረሰቡ

---

[24] በደንቢያ ወረዳ የቆላድባ ከተማ የቀበሌ 01 ነዋሪ ናቸው፡፡ እድሜያቸው 52 ሲሆን በንግድ ስራ ይተዳደራሉ፡፡ በመኖሪያ ቤታቸውም በቡዳ ለተበሉ (ለዐበ ለዐይኑ) ሰዎች ወንዘኛዊ መድሃኒትና የቡዳውን መንፈስ በማናገር በአነስተኛ ክፍያ የቡዳ ጥቃት ፈውስ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በዚህ አገልግሎትም ለ25 ዓመታት ቆይተዋል፡፡
[25] ስኒ
[26] ማዘጋጀት ወይም መቀመም፡፡

ልማዳዊ እምነት መሰረት በዚህ መንገድ ቡዳ የሆነ ሰው ቡዳ የማድረጊያ መድሐኒት ከጠጡ ሰዎች ጋር ይቀላቀላል፡ ወዳጅነትን ይመሰርታል ተብሎ ይታመናል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በአሁኑ ወቅት በእፅ አማካይነት ቡዳ እንደሆኑ የሚታመኑ ግለሰቦች ቡዳነትን ያስተምራሉ የሚለው እምነት እየተስፋፋ ይገኛል። በዋናነት ቡዳ ያደርጋቸዋል የሚባሉትም የቅርብ ልጆቻቸውን፣ ዘመዶቻቸውንና ወዳጆቻቸውን ነው። ከዚህ የተነሳ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች መብዛታቸውን ማኅበረሰቡ ይገልጻል። አልፎ አልፎ የእፅ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች የሚያገኟቸውንና የሚለድፏቸውን ሰዎች ባላወቁበት መንገድ እነሱ ቡዳ የሆኑበትን እፅ ከሚበሉበትና ከሚጠጡት ላይ በመጨመር ቡዳ ያደርጓቸዋል ተብሎም ይታመናል። በዚህ መንገድ ቡዳ እንደሆኑ የሚታመኑ ሰዎች ቡዳ የሆኑበትን መንገድ አስረጅ በማቅረብ ይገልጻሉ፡፡

በመስከ ቆይታዬ ፀበል ላይ የሚደረገውን የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓተ ክዋኔ በቆላድባ ከተማ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ተገኝቼ ተከታትያለሁ። በምልከታዬ ወቅት አንድ በቡዳነት የሚጠረጠር ግለሰብ "እንዳላድግ ወይም አገር እንዲጠላኝ፣ አገር ጥየ እንድመንን ከጠላው ወይም ከእንጀራው ከእርጎው ጠብ አርገው ይሰጡኛል። ያን ምን ይሆናል አጋንንት፡፡ ከዛ ሠው ቡዳ ይለኛል። ቡዳ ነው ይባላል።" በማለት በቡዳነት የሚጠረጠሩ ሰዎች በቅናት ተነሳስተው ቡዳ እንዳረጉትና ይህንን መንፈስ ለማስለቀቅ ፀበል ቦታ መገኘቱን ገልፆልኛል። ከዚህ ጋር ተያይዞ አቶ መንገሻ ስዩም[27] ሲባል የሰማሁት ያሉትን አስረጅ ተረክ "በመድሐኒት ቡዳነት ለመዳ ተብሎ ከብዙ ነገር ተከለከለ፣ ተገለለ፣ ችግር ገጠመው፤ ሰዎች ሄደህ ተጠመቅ አሉት፤ ለፈለፈ፡፡ ከጠላው አግብተውበት ያንን እየጠጣ ሳያውቀው ጨምረውበት ነው፡፡ እነዚህ የተማሩት ናቸው፡፡ ዘረ ቡዳዎች አይደሉም" (28/08/03 ዓ.ም.፣የቡድን ውይይት) በማለት ይገልጻሉ፡፡ በዚህ መንገድ ቡዳ የሆኑ ግለሰቦችን (ቡድኖችን) የትምህርት ወይም "የተማሩ ቡዶች" በማለት ይጠሯቸዋል፡፡

#### 4.1.4.1.2. የዘር ቡዳ

በአንዳንድ ማኅበረሰቦች ቡዳ በዘር የሚመጣ የዕጣ ፈንታ ጉዳይ እንደሆነ ይታመናል (Dundes, 1992: 265)። በዚህም ቡዳ የሆኑ ቤተሰቦች ቡዳ የሆኑ ልጆችን ይወልዳሉ በሚል ይታመናል Vicchiato (1994, 1036-1037) በሲዳማ ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት ቡዳ ከቤተሰብ ወደ ቤተሰብ በዘር የሚወረስ ወይም የሚተላለፍ ተደርጎ የሚታመን መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

[27] አቶ መንገሻ ስዩም በደንቢያ ወረዳ የቆላድባ ከተማ ቀበሌ 01 ነዋሪ ናቸው። እድሜያቸው 86 ሲሆን የወረዳው የሀገር ሽማግሌ ተጠሪና የወረዳውን ታሪክ ያውቃሉ የሚባሉ ናቸው።

በተመሳሳይ መልኩ በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ቡዳንት በዘር የሚመጣ መሆኑን ያምናሉ። ይህንንም አባ ሲኖር ተገኝ "የሌባ ዘር ሌባ፣ የቆማጣ ዘር ቆማጣ፣ የቡዳ ዘር ቡዳ ይሆናል" በማለት ይገልጻሉ።

በማኅበረሰቡ የቡዳንት ዘር እንዳለባቸው የሚታመኑት በዋናነት በእደ ጥበብ ይተዳደሩ የነበሩት፣ በተለምዶ "ፈላሻ" ወይም "ካይላ" የሚባሉት፣ ራሳቸውን ግን "ቤተ እስራኤል"[28] በሚል የሚጠሩ ቡድኖች ናቸው። እነዚህ ቡድኖች በማህበረሰባዊ ልማዳዊ እምነት ውስጥ ለቡዳንት መነሻም እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ። በቀደሙት ጊዜያትም ቡዳ እንደ ግለሰብ ሆነ እንደ ቡድን ሲጠቀስ የነዚህ ቡድኖች ስም በትይዩነት እንደሚቀመጥ ማኅበረሰቡ ይገልፃል። አቶ መንገሻ ስዩም "ቤተእስራኤል ፈልሰው የመጡት ያልተጠመቁት ፈላሻዎች ቅድም እንደተነገረው በወገራም በደንቢያም አክሱም ዙሪያ ያሉት እነሱ ናቸው የዘር ቡዶች የሚባሉት" በማለት ቤተ እስራኤላውያን ቡዳ እንደሆኑ ይታመን እንደነበር ይገልፃሉ። እነዚህ ቡድኖች ኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ በእደ ጥበብ ይተዳደሩ ነበር። በዚህ ሙያቸውም ካይላ[29] የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸው ነበር። አቶ መንገሻ ስዩም "ዘር የሚባለው ካይላ ነው። ካይላ እንኳቸው ነበር ይሄ ብረታ ብረት የሚሰሩ፣ ጋን የሚሰሩ፣ አሁን ጠቅልለው አገራቸውን ኮብልለው የገቡት" በማለት የቤተ እስራኤላውያን ማንነት ይገልፃሉ። እነዚህ ቡድኖች የቡዳንት ዘር እንዳለባቸው ስለሚቆጠር ከሌላው ማኅበረሰብ ተገለውና ተነጥለው ይኖሩ ነበር።

ማኅበረሰቡ በቀደምት ጊዜያት ወደ ቤተ እስራኤላውን ቤት በሄዱ ጊዜ "አይናችን እንዳይወጋችሁ ከቤታችን አትምጡ ይሉን" ነበር በማለት ቤተ እስራኤላውያን ራሳቸው ቡድንታቸው አምነው ይቀበሉ እንደነበር ያስረዳል። በተጨማሪም "እኛ ካልበላን ምንም ካላልን ሸክላው አይሰራ" በማለት

---

[28] ቤተ እስራኤላውያን የእስራኤል የዘር ግንድ ያላቸው (እላቸው ተብሉ የሚታመኑ) በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩና እየኖሩ [እስራኤል የገቡና ለመግባት በመጠባበቅ ላይ] የሚገኙ በተለምዶ "ፈላሻ" የሚባሉ ራሳቸውን "ቤተ እስራኤል" ብለው የሚጠሩ ናቸው። እምነታቸውም አይሁድ (Jewish) ሲሆን አሪታዊና የሙሴ ትዕዛዛትን ከመጠበቅ የመነጨ ነው። እነዚህ የአይሁድ እምነት ተከታዮች በኢትዮጵያ በተለይም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ጎንደርና በከፊል ትግራይ እንዲሁም በተወሰኑ ጎጃም አካባቢዎች ሊሮም በመኖት የራሳቸውን ባህል፣ እምነትና ሀይማኖት እንዲሁም ልማዳዊ ስርአት ጠብቀው የኖሩ ናቸው። ቤተ እስራኤላዊን በቀደሙት ጊዜያት "ሙሴ ኦፕሬሽን" እና "ሰለሞን ኦፕሬሽን" (Operation Mosses before 1984, Operation Solomon and beyond 1991-1997) በሚል የእስራኤል መንግስት ባዘጋጃቸው ጉዞዎች (The low of return to home) አማካኝነት ወደ ቀደመ የዘር ግንድ ሀገራቸው እስራኤል የገቡ ሲሆን አሁንም በመሄድ ላይ ይገኛሉ (BenEzer, (2005); Flad, (1869); Kaplan, (1992); Leslau, (1951)፣ Salamon, (1999); Seeman, (2009); Shelemay, (1993))።

[29] ካይላ የሚለው መጠሪያ እንዳንዴ ቡዳ የሚለውን ቃል የሚተካበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ በማህበረሰቡ "አንተ ካይላ" ማለት "ቡዳ ነህ" እንደ ማለት ነው። ደስታ ተክለ ወልድ (1962፣ 643) ደግሞ ካይላ "የፈላሻ ወገን" እንደሆነ እንዲሁም "በጎንደርና በቀበ[ወገን]] መሰሰል ያለ የካይላ ሜዳ የሚባል ስፍራ መጠሪያ ሲሆን ፈላሾች ካይላ የተባሉት በፋሲል ግዜ በካይላ [ሜዳ] ስለተቀመጡ ይሆናል" በማለት ይገልጻሉ።

የቡዳ ጥቃት የሚያደርሱበትን ምክንያት ይናገሩ እንደነበር የተጠኚ ማኅበረሰብ አባላት ይገልፃሉ፡፡ በማኅበረሰቡ እነዚህ ቡድኖች በቡዳነት ሃይል አማካኝነት ሌሊት ወደ ጅብ ይቀየራሉ፤ ጅብ ይጋልባሉ ተብሎም ይታመናል፡፡ የማኅበረሰቡ አባላት ይህንን ወደ ጅብነት የመለወጥና ጅብን የመጋለብ ሀይልን "ቀን ከህዝብ ሌት ከጅብ" በሚለው አባባላቸው ይገልጹታል፡፡ በዚህ የተነሳ ቤተ እስራኤላውያን ቡዳ እየተባሉ ከሌላው ማኅበረሰብ ተገለው ይኖሩ ነበር፡፡ ማኅበረሰቡ እነዚህን ቡድኖች ከየትኛው የዘር ሀረግ ቡዳነትን እንዳመጡት የሚገልጸው ነገር የለም፡፡ በደፈናው ሲወርድ ሲዋረድ ከቀደመ አባቶቻቸው በዘር ያመጡት በማለት ይናገራል፡፡

Quirin(1979: 249); BenEzer (2005፡ 28) እና Salaman (1999፡ 35-39) በአማራ ማኅበረሰብ ትውፊታዊ ልማድ ውስጥ ብረት የሚያቀልጡና አፈር በመጠቀም የተለያዩ መሳሪያዎችን የሚሰሩ እንደ "የአንጓች ሀይል" ባለቤት ተደርገው የሚቆጠሩ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ ይህንን ሐይል በመጠቀምም የሰውን ነፍስ ይነጥቃሉ፣ ደም ይመጣሉ፣ ወደ ጅብም ይለወጣሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ዘንድ ቤተ እስራኤላውያን የእደ ጥበብ ባለሞያ እና "የአንጓች ሀይል" ባለቤት እንደሆኑ ይታመናል፡፡ በዚህም ቤተ እስራኤላውያን "እንደ ቡዳ" ወይም "ነፍስ በላ" (soul eaters) ተደርገው ይታሰባሉ፡፡ በቤተ እስራኤራላውያን ባህል፣ እምነት፣ ልማድና ታሪክ ላይ የተካሄዱ ጥናቶችም ቤተ እስራኤላውያን ከቡዳ ጥቃት ጋር የሚያያዙባቸው የተለያዩ ምክንያቶችን ያሳያሉ፡፡

የቤተ እስራኤላውያን ክርስቲያን ጎረቤቶች ቤተ እስራኤላውን ቡዳ እንደሆኑና እነዚህ ቡዳዎችም ትክክለኛ ማንነታቸው ሰው ሳይሆን ጆብ ናቸው ብለው የሚያምኑ መሆኑን "the *buda* disguises itself as human during the day but reverts to its original form at night." በማለት Salaman (1999: 35-39) ይገልጻሉ፡፡ Salaman ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ በአሁኑ ሰአት ግን እስራኤል እየኖሩ የሚገኙ ቤተ እስራኤላውያንን ትረካዎች በመጥቀስ ክርስቲያን ጎረቤቶቻቸው ጅብ፣ ቡዳ ፣ ነፍሰ በላ፣ እያሉ ይሰድቧቸው እንደነበር ይገልጻሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጎረቤቶቻቸው ቤተ እስራኤላውያንን ቡዳ በሚል የሚፈርጁበትና ጆብ በሚል የሚሰድቡበት ምክንያት ራሱን የቻለ ተምሳሌታዊ ፍች ያለው መሆኑን Salaman ይገልጻሉ፡፡ ይህም የአይሁድ እምነት ተከታይ መሆናቸውን (ክርስትናን አለመቀበላቸውን)፣ የተናቀ ስራ መስራታቸውን፣ ወዘተ. ምክንያት

በማድረግ ክብራቸውን ለማዋረድ፣ ሰብአዊነታቸው ለመግፈፍ እንዲሁም ከክርስቲያን ጎረቤቶቻቸው ጋር እንዳይቀላቀሉ ለማሳቀቅና ለማሸማቀቅ የሚጠቀሙበት መሆኑን ያብራራሉ፡፡[30]

ከዚህ በተቃራኒ Quirin (1979: 251) ቤተ እስራኤላውያን በአማራ ማኅበረሰብ ቡዳ የመባላቸው ምክንያት ከእደ ጥበብ ባለሙያነታቸው የመነጨ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ ትንሽ ቡድኖች አፈርን ወደ ሸክላነት (ሸቃንት) እሳትን ወደ ብረትነት እንዴት ይቀይራሉ ከሚለው የስልጣኔ እውድ አንፃር እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ይህን ስራ የሚያከናውኑት አንዳች ልዕለ ተፈጥሯዊ ሀይል ቢለገሱ ወይም ቢኖራቸው ነው ተብሎ የሚታመን መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ይህን ሀይል በመጠቀምም በሰው ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ Quirin እንደ ቤተ እስራኤላውያን ቃላዊ ትውፊት በዘመነ መሳፍንት (በ16ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ) የየጁ ስርወ መንግስት ቡዳ የሚለው የነሱን ስድብ ወደ ቤተ እስራኤላዊያን እንዳላከኩትና በኋላም ይህ ስድብ እየጎላ ሄዶ ቡዳ ተብለው ሊጠሩ መቻላቸውን ይገልጻሉ፡፡

#### 4.1.4.1.3. የተፈጥሮ ቡዳ

በማኅበረሰቡ ከዘር እና ከእፅ በተጨማሪ ማንኛውም ሰው በእይታ ብቻ ህመም ወይም ጉዳት የማድረስ ሀይል በተፈጥሮ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ማንኛውም ሰው አንድ ነገር ተመልክቶ ህመም ወይም ችግር የማድረስ ተፈጥሯዊ ባህሪ አለው ተብሎ ይታመናል፡፡ የዚህ አይነት ባህሪ ያለበት ሠው "አይነ ባርጤዛ ያለበት" ይባላል፡፡

ይህ በተፈጥሯዊ ባህርይ የሚከሰተው የቡዳ አይነት በዘር እና በእፅ ይገኛል ከሚባለው ቡዳነት ይለያል፡፡ በዘር ወይም በእፅ መንገድ ቡዳ እንደሆኑ የሚቆጠሩ ሰዎች በእይታቸው ለሚያስከትሏቸው ጉዳቶች የተለያዩ የመከላከያ፣ የመለያና የመፈወሻ ስርዓተ ክዋኔዎች አሏቸው፡፡ እንዲሁም የጥቃቱ አድራሽ ማንነትም ይታወቃል፡፡ በተፈጥሮ ቡዳ የሚከሰት ጉዳት ግን የጉዳቱ አድራሽ ማንነት የማይታወቅ ሲሆን ለተከሰተው ጉዳት የሚወሰደው የመከላከያና የመፈወሻ ዘዴም ውሱን ነው፡፡ ከዚህ ባህሪው በመነሳት የአይነ ባርጤዛ ምንነት፣ ጉዳትና የመከላከያ መንገድ በዚህ ንዑስ ርዕስ ቀርቧል፡፡

[30] እኒህ ጸሐፊ "The Hyena People: Ethiopian Jews in Christian Ethiopian." በሚለው መጽሃፋቸው የቤተ እስራኤላውን "ክርስቲያን ጎረቤቶች" ቤተ እስራኤላውያንን ቡዳና ወደ ጅብ ናቸው የሚሉበትን ምክንያቶች፣ ቤተ እስራኤውን ደግሞ ቡዳ አለመሆናቸውን የሚገልጹባቸውን መንገዶች፣ ከቤተ እስራኤላውና ከቡዳ ጥቃት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ከተለያዩ ጥናቶችና ጽሁፎች እንዲሁም ከቤተ እስራኤላውያን ትረካዎች አንፃር በዝርዝር አቅርበዋል፡፡

በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት እንደ ዶሮ፣ እርጎ፣ ወተት ቁርጥ (ጥሬ ስጋ) የመሳሰሉ ምግቦች በሚበሉት ወይም በሚዘጋጁት ጊዜ የምግቡ ተሳታፊ ያልሆነን ማንኛውንም ሠው የመብላት ፍላጎትና ስሜት ይቀሰቅሳሉ፣ ያጓጓሉ ወይም ያስጎመዥሉ ተብሎ ይታሰባል። እንደ አጋጣሚ ይህ ሰው የመብላት ጉጉትና የመጎምዥት ስሜት ከተፈጠረበትና ምግቡን አተኩሮ ከተመለከተ በአይኑ እንደበላው ይቆጠራል። በዚህም ምግቡ የተመረዘ ይሆናል። ይህን ምግብ የተመገቡ ወይም እየተመገቡ ያሉ ሰዎች ለተለያዩ ህመሞች ይጋለጣሉ፣ ወደፊትም ለእይታ የተጋለጠውን ምግብ የመብላት ፍላጎታቸው ይቀንሳል ከፍ ሲልም ሲበሉ ይታመማሉ ተብሎ ይታመናል። ይህ እምነት በማኅበረሰቡ "አይነ ባርጤዛ" ይባላል።

ይህንን እምነት አቶ መንገሻ ስዩም "ለምሳሌ እኔ የሥጋ ጉምጀ[31] አለብኝ። በጣም ለስጋ ጉምጀ ነኝ። ለእኔ ሳይሰጠኝ አንተ ግን ስትበላ አይሃለሁ። ስትጎርስ አይሃለሁ። ስትቆርጥ አይሃለሁ። ባርጤዛ ይሉሃል ይህ ነው። የእኔ አይን ነው ምግብህን የወጋህ። ከዛ ሆድህን ያምሃል። እያማረኝ ነዋ ሽቅብ ቁልቁል[32] የምል"[33] በማለት የአይነ ባርጤዛ ምንነትና የሚከሰተውን ችግር ያስረዳሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ቄስ መላከገነት ተውህቦ ማሩ በእሳቸው የደረሰውን ምሳሌ በመጥቀስ "የኔ ባለቤት ዶሮ ትሠራለች ዶሮ እስከ እንቁላል ስትሠራ አንዲት ሴት ትክ ብላ [አተኩራ] አይታ ሄደች። እንዲታቀምሳት ግና ወጡ አልወጣም። አሁን ያችን የዶሮ ወጥ በላሁ። [በኋላ] አስጠላኝ! አስጠላኝ! የዶሮ መረቅ ሲሸተኝ ያመኛል። ያመኛል። ያች ሴትዮ አይኗ ባርጤዛ ነው።"[34] በማለት በአይነ ባርጤዛ ሳቢያ የሚከሰትን ችግር ይገልጻሉ።

ከሁለቱም መረጃ አቀባዮች ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው በአይነ ባርጤዛ ሳቢያ ችግር የሚከሰተው በአንድ ሰው ፊት ምግብ ቀርቦ ሰውየው ሳይጋበዝ ሲቀር ወይም ሲዘጋጅ ተመልክቶ ለመብላት ሲፈልግ፣ ሲጓጓ ወይም ሲጎመዥ ነው። በማኅበረሰቡ ልማድ ይህ ስሜት በአይን ይገለፃል፤ አይኑን ምግቡ ላይ ይጥላል ተብሎ ይታመናል። በዚህ ጊዜ ምግቡን በአይኑ ወጋው ወይም በላው ይባላል።

በዘር ወይም በእፅ መንገድ ቡዳ ሆኑ የሚባሉ ሰዎች አንድን ሰው ካዩ ለህመም ወይም ለሞት ይዳርጋሉ። ህመም ወይም ሞት እስከተለ የተባለው ቡዳም በተለያዩ መንገዶች ይታወቃል። ነገር ግን በአይነ ባርጤዛ ህመም ወይም ችግር ሲከሰት አጋጣሚው፣ ቦታውና ጊዜው እንጅ የጥቃት

[31] መኮምዥት።
[32] አይንን ማቅበዝበዝ።
[33] ሚያዝያ 28/ 2003 ዓ.ም፤ ደንቢያ ወረዳ ቆላድባ ከተማ። የቡድን ውይይት።
[34] ሚያዝያ 30/ 2003 ዓ.ም ፤ ደንቢያ ወረዳ በጭሉ ቀበሌ ገበሬ ማህበር። የቡድን ውይይት

አድራሹ ሰው ማንነት በውል አይታወቅም፡፡ ከዚህ የተነሳ ማኅበረሰቡ "ሁሉም ሰው ቡዳ ነው" የሚል አመለካከት አለው፡፡ አይን ባርጤዛ አንዳንዴ "የሰው አይን" በሚል ይገለፃል፡፡ ይህ "የሰው" የተባለው "አይን" በማኅበረሰቡ ማንኛውንም ሰው ያጠቃልላል፡፡ ከዚህ በመነሳት ማንኛውም ሰው ሲርበው ወይም የሚወደውን ምግብ ሰው ሲበላ ካየ የመብላት ፍላጎቱ ይቀሰቀሳል፣ ይጎመዠል ወይም ይጓጓል የሚል ተጠየቅን ማቅረብ ይቻላል፡፡

በመስክ ቆይታዬ እንዳስተዋልኩት በአይን ባርጤዛ ሳቢያ የተፈጠረን ህመም ወይም ችግር ሲተርኩ የጉዳት አድራሹን ማንነት እንደ ሌሎች የቡዳ ጥቃት አይነቶች በስም እየጠቀሱ ሳይሆን "አንድ ሠው"፣ "የሆነ ሰው"፣ "አንዲት ሴት" ወይም "የሰው አይን አይቶኝ" በማለት ነው፡፡

ይህ በተፈጥሯዊ ባህርይ የሚከሰት የቡዳ ጥቃት አይነት በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት መሰረት የራሱ የመከላከያ ስልቶች አሉት፡፡ እነሱም አንድ ሠው ምግብ በሚመገብበት ጊዜ በአቅራቢያው ያሉ የምግቡ ተሳታፊ ያልሆኑ ሰዎችን እንዲሳተፉ መጋበዝ፣ "እንብላ ማለት"፣ ማጉረስ፣ ወይም የሚበላውን ነገር ለሠው የማያበላ ከሆነ ደበቅ አድርጎ መብላት[35] ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ማንም ሠው አንድ እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ባሉበት ቦታ ምግብ የሚመገብ ወይም የሚያዘጋጅ እና ምግቡ ለነዚህ ሰዎች ለእይታ የሚጋለጥ ከሆነ ሰዎቹን ቢያውቃቸውም ባያውቃቸውም እንዲበሉ በመጋበዝ፣ ከቻለ በማጉረስ ወይም እንዲቀምሱለት በማድረግ በአይን ባርጤዛ ሳቢያ የሚመጣን ህመም መከላከል ይቻላል፡፡ እንዲበላ የተጋበዘው ሠው ከጎረሰ፣ ከቀመሰ፣ ከበላ ወይም የጠገበ መሆኑን ከተናገረና ግብዣውን ካመሰገነ ምግቡን ቢመለከት እንኳ ጉዳት አያስከትልም ተብሎ ይታመናል፡፡

በመስክ ቆይታየም በተለይ በቆላድባ፣ በማክሠኝትና በጎንደር ከተማ ባሉ ምግብ ቤቶች ውስጥ ሰዎች ያዘዙት ምግብ ከፊታቸው ሲቀርብ ከመመገባቸው በፊት አጠገባቸው ያሉ ሰዎችን "እንብላ" በማለት ሲጋብዙ ተመልክቻለሁ፡፡ እንዲሁም በማኅበረሰቡ ዘንድ እንግዳ ወይም ጎረቤት ድንገት በምግብ ሰዓት ቢመጣና እንዲሳተፍ ተጋብዞ ግብዣውን ባይቀበል "ባይሆን ለአይን ባርጤዛው አንድ ጊዜ ጉረስ" ይባላል፡፡ ተጋባዡ በምግቡ ላይ እንዲሳተፍ ሲጠየቅ የማይበላ ከሆነ እንዴ እንኳ እንዲጎርስ መደረጉ በሰውየው እይታ ሳቢያ የሚከሠተውን የአይን ባርጤዛ ጥቃት መከላከልን ያመለክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በማኅበረሰቡ የማዕድ ስርዓት ታላላቆች ወይም እንግዶች በሚመገቡበት ሰዓት አንድ ሠው መብራት (ፋኖስ ወይም ኩራዝ) ከተመጋቢዎች ፊት

35 አቶ ደሳለኝ ሳህሌ፣ ሚያዚያ 28/ 2004 ዓ.ም፣ ደንቢያ ወረዳ ቆላድባ ከተማ የቡድን ውይይት፡፡
አቶ ደሳለኝ ሳህሌ ዕድሜያቸው 51 ሲሆን ስራቸው በፍርድ ቤት አካባቢ የማመልከቻ ጸሀፊ ናቸው፡፡ ነዋሪነታቸው ቆላድባ ከተማ ቀበሌ 01 ነው፡፡

ለፊት ይዞ እንዲቆም ይደረጋል። ለዚህ መብራት ያዥም ዳረጎት (ጉርሻ) ይሰጠዋል። ምናልባት ይህ ዳረጎት ለመብራት ያዥው የሚሰጥበት ምክንያት በምግቡ ላይ ያሳርፋል ተብሎ የሚገመተውን የአይነ ባርጤዛ ችግርና ህመም ለመከላከል ሳይሆን አይቀርም።

በሌላ በኩል አይነ ባርጤዛ ያለበት ሠው በጉጉትና በጉምዥት ያየውን ምግብ ከመመረዝ እና የተመረዘውን ምግብ በበላ ሰው ላይ ችግር ከመፍጠር በተጨማሪ የእይታው ማረፊያ የሆነውን ምግብን ወደ ትልንት የመቀየር ሀይል እንዳለው ይታመናል። በተለይ አቶ መንገሻ ስዩም ‹‹በግልጥ›› የታየ ያሉትን ሁነት እንደሚከተለው ይገልፃሉ፦

> አንድ ቢትወደድ ናቸው ሲበሉ፣ እንደዚህ አድርገው ሊቆርጡ ሲሉ እዚያ የቆመው አሽከራቸው አይቷል። ያቺን ሊቆርጧትና ሊጎርሷት የነበረችውን ስጋ ቁጭ አደረጉና መብላቱን አቁመው ሠው ይጠሩና ‹‹እቺን ከድናችሁ አኑሩ›› አሏቸው። ያቺ ስጋ እንዲያው አንድ ሰዓት ተኩልም አልቆየች ስትተላ። ተላች በቃ የዚያ አይን ያረፈባት። ይሄ በግልጥ ታይቷል። አሁን ያ አሽከራቸው ሳይበላ እሱ አንድ ነገር ሳያደርግ ማንም ቤተሠብ አይበላም። ቀድሞ ከበላ ጥሩ - ከበላ ምን ብሉ ያይሀል (ሚያዚያ 28/ 2004 ዓ.ም፣ ደንቢያ ወረዳ ቆላድባ ከተማ የቡድን ውይይት)።

አንድ ሰው ምግብ በሚበላት ወቅት በቡዳነት የሚጠረጠረው ሰው ምግቡን ቢመለከትና ተጋባዥ ሳይሆን ቢቀር ምግቡን በመመረዝ በተመጋቢው ላይ ህመምን ይፈጥራል የሚለው እምነት ከሰሜን ጎንደር ማኀበረሰብ ባለፈ በሌሎች ማኀበረሰቦች ልማዳዊ እምነት የሚገኝ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ። ለምሳሌ ያህል በስፔንና በሰሜን አሜሪካ ትንንሽ የገጠር ምግብ ቤቶች ውስጥ በህዝብ ፊት ሌሎችን ሳይጋብዙ መብላት መርዝን እንደ መብላትና ራስን ለህመም አሳልፎ እንደመስጠት ይታመናል። ይህንን ለመከላከልም ተመልካቹን "ምግብ ከእኔ ጋር መብላት ትፈልጋለህ" በማለት የግብዣ ጥያቄ ማቅረብና ከተመልካቹም "መልካም ምግብ ይሁንልህ" የሚል ምላሽ ማግኘት ያስፈልጋል። ይህ ስነልሳናዊ ቀመር በተመልካቹ የሚከሰትን ቅናትና ምቀኝነት ያፈርሳል ተብሎ ይታመናል (Dundes, 1992፡ 168-169)። ከዚህ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ሀገሮች ልማዳዊ እምነት ውስጥ ደግሞ አንድ ሰው ለጎረቤቱ ደንታ ሳይኖረው ወይም ሳያቀምስ ምግብ የሚበላና የሚጠጣ ከሆነ እንዲቀናበትና ራሱንም ለቡዳ ጥቃት እንዲጋለጠ የሚቆጠር መሆኑን Dundes ይገልጻሉ። በሰሜን ጎንደር ደንቢያ አካባቢ ማኀበረሰብም እንደ ወተት፣ እርጎና ጠጅ የመሳሰሉ መጠጦችን ለጎረቤት ሳያቀምሱ መጠጣት ለሰው አይን ጥቃት ያጋልጣል፤ በዚህም ለህመም ይዳርጋል ተብሎ ይታመናል።

### 4.1.4.2. የቡዳ አይነቶች ከሚያስከትሉት ጉዳት አንጻር

የሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ አባላት የቡዳ ጥቃት ከሚያስከትለው ጉዳት አንፃር "ቁመኛ" እና "ቁመተ" ቡዳ በማለት ይከፍሉታል፡፡

በማኅበረሰቡ ዘንድ አንድ ሰው በልማዳዊ ወይም በሐይማኖታዊ መንገድ የቡዳ ጥቃት ፈውስን ያገኛል፡፡ በዚህም የቡዳው መንፈስ ከተጠቂው ላይ ይወገድለታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ በእፅ ቡዳ እንደሆኑ የሚታመኑ ሰዎች የሚያደርሱት ጥቃት መፈወስ (መንፈሱን ከተጠቂው ማላቀቅ) የማይቻልበት አጋጣሚ መኖሩንና የፈውስ ስርዓት ቢደረግለትም እንኳ ህመሙ የማይቀር መሆኑን መረጃ አቀባዮቹ ይገልፃሉ፡፡

በማኅበረሰቡ የቡዳ እምነት መሰረት የዚህ አይነት የቡዳ ጥቃት "ቁመኛ ቡዳ" ተብሎ ይጠራል፡፡ በቁመኛ ቡዳ የተበላ ሰው እስከ ህይወት ፍጻሜው ድረስ የቡዳው መንፈስ ይዋረሰዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ የተነሳም መንፈሱ በቁሙ ያሰቃየዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተለያዩ በሽታዎችም እየተመሰለ "ወይ አይገለው፣ ወይ አያድነው በቁሙ እየገዘገዘ እያለባለበ ያሰቃየዋል" በማለት አቶ ታረቀኝ እምሩ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቁመኛ ቡዳ ሰለባ የሆነ ሰው ጥቃት ካደረሰበት ሰው ጋር አይን ለአይን በተያየ ጊዜ ለህመም ይዳረጋል ተብሎ ይታመናል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ቁመኛ ቡዳ ከሰው በተጨማሪም በከብቶች ላይ ጥቃት ያደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተለይ ለገበሬው የኢኮኖሚው መሠረት የሆኑት እንደ በሬ፣ ላም እና ሌሎች የቤት እንስሳት ድንገት ቢታመሙና ከህመማቸው እንዲድኑ የመፍትሄ ርምጃ ተወስዶ የማይሻላቸውና እያደር ሰውነታቸው የሚቀንስ ከሆነ በቁመኛ ቡዳ እንደተበሉ ይታሰባል፡[36]

የቤት እንስሳትና ህፃናት ለቁመኛ ቡዳ ጥቃት ተጋላጭና በቡዳው ዘንድ ተመራጭ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ምክንያቱም ህፃናትም ሆኑ እንስሳት ከቡዳ ጥቃት ለመፈወስ ጥቃት ያደረሰባቸውን ሰው ማንነት በማስለፍለፍ ማወቅ የማይቻል በመሆኑ ነው፡፡

ቁመተ ቡዳ ለፈውስ ስርዓት ፋታ ሳይሰጥ ቡዳ በሚባለው ሰው እይታ በተጋለጠ ጥቂት ቀናትና ሰዓታት ውስጥ ለሞት የሚዳርግ የቡዳ ጥቃት አይነት ነው፡፡ በአብዛኛው የዚህ

---

[36] በሰሜን ጎንደር አንዳንድ አካባቢዎች ቁመኛ ቡዳ ከብቶችንና ሌሎችን እንስሳት ብቻ ጥቃት የሚያደርስ (የሚበላ) የቡዳ አይነት ተደርጎ ይቆጠራል። በአካባቢው በሬና ላም "ጥቁም ከብት" በማለት ይጠራሉ። ምናልበት ቁመኛ ቡዳ ሲባል በእነዚህ የቁም ከብቶች ላይ ጥቃት የሚያደርስ (የሚበላ) እንደማለት ሊሆን ይችላል።

ጥቃት ሰለባ የሚሆኑት ታመው የማያውቁ ሰዎች፣ እርጉዝ ሴቶች፣ ህፃናት እና በውበትና በውፍረት አይነገብ የሆኑ እንስሳት ናቸው፡፡ በማኅበረሰቡ በድንገት የሚከሰትና ለሞት የሚዳርግ ህመም የቁመጥ ቡዳ ውጤት እንደሆነ ይታመናል፡፡ በዚህም በማኅበረሰቡ በቁመጥ ቡዳ ተለይተው የሚታወቁ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ይጠቀሳሉ፡፡ " እገሌ ካየ አይምርም፡፡ ባንዴ ነው ቆርጦ የሚጥል" በማለት ቁመጥ ቡዳ የሚባሉ ሰዎችን የጥቃት ሃይል ማኅበረሰቡ ይገልፃል፡፡

በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት መሰረት ቁመጥ ቡዳ በአንድ ሰው ላይ የቡዳ ጥቃት በማድረስ ለሞት ከዳረገ በኋላ በጨለማ ከተቀበረበት ቦታ በመሄድ አስከሬኑን በማውጣት ወደ ቤቱ ይወስደዋል፡፡ ከቤቱ ከወሰደ በኋላ በእንዳች ስውር ጥበብ ልቦናውን በመመለስ የቤት ውስጥ አገልጋይ ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

በልማዳዊ (በባህላዊው) የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ላይ የቡዳ ጥቃት የደረሰበት ሰው ባጠቃው ሰው አንደበት ሆኖ በሚናገርበት ጊዜ ጥቃት አድራሹ ማንን በልቶ እንደገደለ ይናገራል፡፡ በዚህ ጊዜ በአካባቢው በቁመጥ ቡዳ ተበልተው የሞቱ ሰዎች ይታወቃሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

### 4.1.5. የቡዳ ጥቃት ተጋላጭነት

በዚህ ርዕስ ስር በማኅበረሰቡ ዘንድ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ተለይተው የሚታወቁበትን መንገድ፣ ለቡዳ ጥቃት ተጋላጭ (ሰለባ) የሚሆኑ ነገሮች፣ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ጥቃት የሚያደርሱበት ጊዜ፣ ምክንያት እና የሚያስከትሉት ጉዳት ቀርቧል።

በአንዳንድ ማኅበረሰቦች በቡዳነት የሚፈረጁ ሰዎች በአካላዊ ገፅታ፣ በእይታ አኳሀንና ስሜት፣ በጾታ፣ በቀለም እና በሌሎች ባህሪያት ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል በጣሊያን ቡዳ (Jettatore) በአብዛኛው ወንድ ሲሆን አይነ ሸውራራ እንደሆነ ይታመናል፡፡ እንዲሁም በእንግሊዝ አንድ ሠው አሳትን ለረዥም ጊዜ አተኩሮ የሚመለከት ከሆነ በቡዳነት ይጠረጠራል፡፡ በሜዲትራኒያን አካባቢ ባሉ ማኅበረሰቦች ደግሞ የአይናቸው ብሌን ሰማያዊ የሆኑ ሰዎች ቡዳ ናቸው ተብሉ ይታመናል (Lykriardopoulos, 1981: 223 - 224)፡፡

በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ግን ቡዳ የሚባሉ ሰዎችን ከሌላው ማኅበረሰብ በእይታ አኳሃንና ስሜት፣ በቀለም፣ በአካላዊ ገፅታም ሆነ በሌሎች ባህሪዎቻቸው ለይቶ ማመልከት አይቻልም፡፡

በእፅ፣ በዘርና በተፈጥሮ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ከማኅበረሰቡ አባላት በአኗኗር፣ በሀይማኖት፣ በቀለም፣ በአለባበስ እና በእይታ ተመሳሳይ ናቸው። ማኅበረሰቡ "ቡዳ ከኛ የሚለይበት አንድም የተለየ ምልክት የለውም" ብሎ ያምናል።

በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት በእፅና በዘር ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ቡዳ መሆናቸው የሚረጋገጠው በልተው ሲገኙ እና የተበላው ሥው ስለ ቡዳዎቹ በሚለፈልፍበት[37] ጊዜ ነው። ይህንንም አቶ መንገሻ ስዩም ቡዳ የሚታወቀው በመልኩ ሳይሆን፣ በተግባሩ እንደሆነ "አንተ ለምሳሌ ጥሩ ሰራተኛ ሊያሰኝህ የቻለው ምንድን ነው? [ስራዬ] እሱም ስራው ነው። ለፈለፈና - ይሄ ቡዳ ነው" እንደሚባል ያስረዳሉ (28/08/03 ዓ.ም.፣ የቡድን ውይይት)። በመሆኑም በማኅበረሰቡ አንድ ሥው ሌላውን ሰው መብላቱ የሚታወቀው በቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ላይ የበላው ሥው መንፈስ በተበላው ሥው ሲጋና ደም ላይ አድሮ የበላሁት እኔ ነኝ ብሎ ሲናገር ነው።

ይህ የቡዳው መንፈስ በበላው ሰው ውስጥ መስረጽና እኔ ነኝ በማለት መናገር "በመድሐኒት በተያዘው ሥው ላይ ይለፈልፋል እንጅ እሱ [ቡዳው] ቁጭ ብሎ በአካል በአምሳል [አይለፈልፍም] አቶ እንጆ መልኩ አይመጣም። ድምጡን ይልካል እንጅ ህይወቱን አናየውም" በማለት መንገሻ ስዩም (28/08/03 ዓ.ም፣ የቡድን ውይይት) ይገልጻሉ። ከዚህ በመነሳት የተባለው ሥው ከተናገረ ወይም ከለፈለፈ በኋላ በማኅበረሰቡ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ወይም ቡድኖች ተለይተው ይታወቃሉ።

ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ጥቃት የሚያደርሱበት መንገድ፣ የእይታ አኳሃንና ስሜት እንዲሁም ለጥቃቱ ተጋላጭ የሚሆኑ ነገሮች እንደየማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት የሚለያዩ መሆናቸውን ምሳሌዎችን በማቅረብ በዚህ ጥናት በምዕራፍ ሶስት ተገልጿል። በተጠኚ ማኅበረሰቦችም ሰው፣ እንስሳት፣ ሰብል፣ እና ሌሎች ግኡዛን ነገሮች በማኅበረሰቡ ተለይተው በሚታወቁና ቡዳ በሚባሉ ሰዎች ወይም ቡድኖች የእይታ ማረፊያ ከሆኑ ለህመም፣ ለአደጋና ለሞት ይዳረጋሉ ተብሎ ይታመናል። ነገር ግን እነዚህ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ጥቃት በሚያደርሱበት ወቅት የሚኖራቸው የእይታ አኳሃንና ስሜት በውል የማይታወቅ ሲሆን ከሌላው ማኅበረሰብ የተለየ አይደለም። እይታቸው ሆነ የጥቃት መንገዱ ተጨባጭ ሳይሆን እንዳች አስማታዊ ወይም ስውር ጥበብ እንደሆነ ይታመናል። ቀደም ሲል እንደተገለጸው የቡዳ ጥቃት ሲከሰት በቡዳው (ጥቃት አድራሽ) እና በቡዳ ተበላ በሚባለው (በተጠቂው) መካከል ምንም አይነት

[37] በማኅበረሰቡ መለፍለፍ ማለት እንደ ሥው የቡዳ ጥቃት ሲደርስበት (ሲበላ) ጥቃት ያደረሰበትን (የበላውን) ሥው መንፈስ ስመውረስ የበላው በተበላው ላይ አድሮ የበላሁት እኔ ነኝ ሲል ነው። በቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ክዋኔ ላይ ስለበላው ሰው የሚለፍፈውን ሁሉ ይናገራል ይባላል።

አካላዊ ጉዳት እንደሌለ ይታመናል፡፡ ይህንንም ወይዘሮ ዘርትሁን እሸቱ[38] "ሰዎቹ [ቡዳዎቹ] ግን አይታዩም፡፡ ሲበሉም አይከስቱም፡፡ የታመሙት መጥተው ነው የሚያስቸግሩን- የምናስቸግራቸው" (ሚያዚያ 30/2003 ዓ.ም. ቃለ መጠይቅ) በማለት ይገልፃሉ፡፡

በማኅበረሰቡ ዘንድ በአብዛኛው ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ጥቃት የማያደርሱበት (የማይበሉት) ነገር የለም ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህንንም የቡዳ ጥቃት ሲደርስ በሚከናወነው የፈውስ ስርዓት ላይ በሰለባው ላይ መንፈሳቸውን በማሳደር የሚናገሩ መሆኑን "መሬቱንም በልተነዋል ነው የሚሉት፣ ዋልካውን[39] በልተነዋል ነው የሚሉት፣ በለሳውን[40] በልተነዋል ነው የሚሉት፣ የእገሌን ላም የእገሌን ልጅ እኔ ነኝ የበላሁት የገደልሁት እያሉ በተያዙ ጊዜ ይለፈልፋሉ"፡፡ በማለት አሙሃይ ፈለጉ በለጠ[41] (ሚያዚያ 30/2003 ዓ.ም. ቃለ መጠይቅ) ይገልፃሉ፡፡ በዋናነት በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት መሰረት ህጻናት፣ የሚያጠቡ እናቶችና ላሞች፣ የደለቡ በሬዎች፣ ቡዳ ከሚባሉ ሰዎች ኮከብ ጋር "ኮከቡ የገጠመ" ማንኛውም ሰው እና ከቡዳው ጋር የቀረበ ዝምድና እና ወዳጅነት ያለው ለቡዳ የበለጠ ተጋላጭ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

በተለይ ህፃናትና እንስሳት በተበሉ ጊዜ እገሌ በላኝ ብለው የማይለፈልፉ በመሆናቸው ለጥቃት ይመርጧቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ የተነሳ ህፃናትና እንስሳት በአብዛኛው የቡዳ ጥቃት ሰለባ ይሆናሉ፡፡ ለሞትም ይዳረጋሉ፡፡ ህጻናትንና እንስሳትን መብላቱ ወይም በልቶ መግደሉ በቡዳ የተበላ ሰው በሚፈወስበት ወቅት ሲለፈልፍ ይጋለጥበታል ይባላል፡፡ "ይህን ያህል እንቀልባ ሰቅያለሁ"[42] በማለትም ጥቃት ያደረሰባቸውን ህጻናት ቁጥር እንደሚናገር አቶ ደሳለኝ ሳህሌ ይገልጻሉ፡፡

በማኅበረሰቡ የቡዳ እምነት ለእርሻ የሚሆኑ የደለቡ በሬዎች፣ የሚያጠቡ ላሞችና እንቦሳዎች ቡዳ ካየቸው ለጥቃት የሚዳረጉ ሲሆን በተለይ በሬው በተበላ ጊዜ "ሲጠምዱት አያርስም። መሬቱ ገደል መስሎ ይታየዋል። አባያ ሆኖ አልታረስም እንቢ ይላል። በእሳት ስናቃጥለው ብድግ አይልም" በማለት አቶ መስፍን ከበደ[43] (30/08/03 ዓ.ም ፣የቡድን ውይይት) ይገልጻሉ።

[38] በደንቢያ ወረዳ የጭቅ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪና የቤት እመቤት ናቸው። እድሜያቸውም 38 ነው።
[39] ለተለያዩ አገልግሎት በተለይ ለጨዋና ለሸንበቆ ተስማሚ የሆነ ጥቁር አፈር ያለበትና ውሃ የሚቋጥር መሬት።
[40] ማሳ ወይም ሰብል።
[41] እድሜያቸው 63 ሲሆን በደንቢያ ወረዳ የጭቅ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ ናቸው። እንዲሁም የደብረ ሰላም ጭሉ ማሪያም ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ናቸው።
[42] እንቀልባ ተጭቶ ከተለፋ ቆዳ የሚሰራና ለህጻን ልጅ ማዘያ የሚያገለግል ስስና ለስላሳ ቆዳ
[43] በደንቢያ ወረዳ የጭቅ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪ፣ በግብርና ሙያ የሚተዳደሩ የ61 ዓመት አዛውንት ናቸው።

የምታጠባ ላም ቡዳ ባያት ጊዜም ወተቷ ይደርቃል፤ ደም የተቀላቀለ ወተት ትታለባለች ተብሎ ይታመናል።

እንደ ማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ሠው ላይ ጥቃት የሚያደርሱት በውበት፣ በሀብት፣ በኃሳ፣ በዘር፣ በቀለም ሳይሆን "ኮከቡ ከገጠመ" ብቻ ነው ብለው ያምናሉ። ኮከብ በማኅበረሰቡ የአንድ ሰው መልካም ወይም መጥፎ እድል ማለት ነው። በዚህም አንድ ሰው ከቡዳው ኮከብ ጋር ገጠመ ሲባል ለቡዳው ለጥቃት የሚፈልገውን ሰው እንዳገኘ ሲቆጠር፤ ለተጠቂው እንደ መጥፎ እድል ይቆጠራል።

"ኮከብ መግጠም" ከቡዳ እምነት ውጭ በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት መሠረት በጠንቋዮች ከሚከናወነው የኮከብ ቆጠራ ጋር ይያያዛል። በስሜን ጎንደር ማኅበረሰብ አባላት ልማድ ሁለት ሰዎች ከመጋባታቸው በፊት ወደ ጠንቋይ በመሄድ ኮከባቸውን ይጠይቃሉ። ጠንቋዩም የሴቷንና የወንዱን የእናትና የአባት ስም በመደመርና በማስላት የኮከባቸው አይነት በመንገር ኮከባችሁ ገጥሟል ወይም አልገጠመም ይላል። ኮከባቸው ገጥሟል ከተባለም ሁለት ተጋቢዎች አልሚና ለሚ ወይም ተስማሚ እንደሆኑ ይቆጠራል፤ በዚህም ይጋባሉ። ኮከባቸው ተቃራኒ ከሆነ ግን ቢጋቡም የማይፋቀሩ ትዳራቸውም የማይሰምር ሁለቱ በሀሳብና በስሜት የማይስማሙ ተደርጎ ይታመናል።[44]

መሪጌታ አዳነ አስፋ[45] ኮከብ መግጠም የሚለውን አሳቤ ከአጋጣሚ ወይም ከእድል ጋር ያገናኙታታል። በዚህም ቡዳ በአጋጣሚ ይበላል ብለው ያምናሉ። ለዚህም ራሳቸውን እንደ ምሳሌ በመውሰድ "አንተ መልከ መልካም ነህ እኔ መልከ ጉፋያ ነኝ። እንደ አጋጣሚ እኔን ሊበላኝ ይችላል። መልከ መልካሙን ትቶ ጉፍያውን ይበላዋል፡ አይመርጥም" ይላሉ። በዚህም ቡዳ "ያው ኮከቡ የገጠመውን መንገድ ላይ ወይም ቤተክርስቲያን…ቆንጆ፣ ጥቁር፣ ቀይ ሳይል ይበላል" በማለት አቶ አስናቀው ዘሪሁን የመርጌታ አዳነን ሀሳብ ያጠናክራሉ። ከዚህ በመነሳት በማኅበረሰቡ ዘንድ ማንኛውም ሠው በቡዳ ለሰመበላቱም ሆነ ለላለመበላቱ እርግጠኛ ሆኖ መናገር የማይቻል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

---

[44] ከዚህ ጋር ተያይዞ በማኅበረሰቡ ቃል ግጥም ውስጥ
አትማን አትማን ትሰለጫለሽ ደም፤
አስምኔኘ እንደ ከብቶቹን የሞ።
የሚል ይገኛል። በዚህ ቃል ግጥም እየተቃለው በፍቅር የወደቀው (የተቸገረው) ተፈቃሪዋ በውበት ሆነ በሌላ ነገር ከሌሎች ሴቶች በመብለጧ ሳይሆን ኮከባቸው በመጣጣሙ የተነሳ ነው። በዚህም ኮከብ መግጠም ማለት የተፋቃሪዎችን እንዳች መፈታቀድ፤ መፈላለግ ወይም ሊመነዳቀዳዊ መሳሳብን ያመለክታል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በማኅበረሰቡ ዘንድ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ቤተሰቦች፣ ቤተ ዘመዶች እና ወዳጆቹ ለቡዳ ጥቃት ተጋላጭነታቸው ሰፊ ነው ተብሎ ይታመናል። ማኅበረሰቡ ይህንን እምነቱን "ቡዳ በወዳጁ ይብሳል" በሚለው አባባሉ ይገልጻል። በተጨማሪም አቶ አጥቢያ አስረስ "ቡዳ ቤተሠቡን ሁሉ እያቀያየመ እስካሁን ድረስ ያለ ነው። ቡዳ ማለት ልጁን ያልማረ ነው። ልጁን በልቷል። መናገር አያስፈልግም፡ ብዙ ቡዳዎች ልጆቻቸውን በልተዋል" በማለት ይገልፃሉ። በመስክ ቆይታየም ቃለ መጠይቅ ባዳረግሁበት ወቅት ቡዳ የሚባሉ ሰዎችን ስም እየጠቀሱ በልተው የገደሏቸው ያሏቸውን ልጆቻቸውን፣ ሚስቶቻቸውንና የቅርብ ዘመዶቻቸውን የበሉባቸውን አጋጣሚና ምክንያት ሲባል ከሰሙት በመነሳት ተርከውልኛል። በተለይ በእዕ አማካይነት ቡዳ የሆኑ ሰዎች መጀመሪያ ቡዳ የማድረጊያ እፅን በሚጠጡበት ወቅት ዕፁ ውጤታማ እንዲሆን በመጀመሪያ ከቤተሰባቸው ወይም ከቅርብ ዘመዳቸው አንዱን በመብላት እላያቸው ላይ ላደረው መንፈስ አለቃ በመስዋዕት መልክ ያቀርባሉ ተብሎ ይታመናል። ይህንን መስዋዕት በየአመቱ ያቀርባሉ ተብሎ ይታመናል። ማኅበረሰቡ ይህንን መስዋዕት "የቡዳ ግብር" በማለት ይጠሩታል። ይህንን ግብር ለመስጠትም ቡዳዎች በየዓመቱ በማህበር በመሆን ይሰበሰባሉ። እያንዳንዱ ቡዳም የዚህ የቡዳ ማህበር[46] አባል ይሆናል ይባላል። በዚህ ወቅት (ግብሩ ሲደርስ) ቡዳ ግብር የሚያቀርበው (የሚበላው) ሰው ሲያጣ ልጁን፣ ሚስቱን ወይም የቅርብ ዘመዱን በመብላት በግብር መልክ ያቀርባል በሚል ያምናሉ። በሌላ ጎኑ በማኅበረሰቡ ቡዳ ቡዳን አይበላም ተብሎ ይታመናል።[47]

በማኅበረሰቡ ቡዳ የሚባለው ሠው የቡዳ ጥቃት የሚያደርስበት የራሱ ምክንያት አለው። የመጀመሪያው ከላይ እንደተገለፀው ለግብር ነው። ሁለተኛው ደግሞ ቡዳ የሚባለው ሰው አንድን ሠው በልቶ ከገደለ እና ከተቀበረ በኋላ አስከሬኑን አውጥቶ ይወስደዋል፤አገልጋይም ያደርገዋል። ተብሎ ይታመናል። ይህንንም የማኅበረሰቡ አባላት "ለኛ አይከሰቱም ግን ቡዳ ለሆኑት ይከሰትላቸዋል። ማገኛቸውንም ስራ ወስደው ያሰሩታል" በማለት ይገልጻሉ።

---

[46] የቡዳ ማህበር በማኅበረሰቡ ሊሚዮ እምነት ቡዳ የሚባሉ ሰዎች የሚሰባሰቡት ህቡዕ ተቋም ነው። የሚሰበሰቡበትን ቦታና ቀን ቡዳ ከሚባሉ ሰዎች በስተቀር ማንም እያውቅም ተብሎ ይታመናል።
[47] (1) ቡዳ ቡዳን አይበላውም፣ (2) ቡዳ በወዳጁ ይብሳል እና (3) ቡዳ ወዳጁንና ሌሎች ሰዎችን ቡዳነትን ያስተምራል የሚሉት ሶስት ነጥቦች የሚያጋጩቸው ነገር ያለ ይመስላል። በማኅበረሰቡ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች በቤተሰቦቻቸው፣ በቅርብ ዘመዶቻቸውና ወዳጆቻቸው እሌሎች በተለየ ጥቃት ያደርሳሉ ተብሎ ይታመናል። ጥቃቱም እስከ ሞት ሊደርስ ይችላል። በሌላ ጎኑ ቡድነትን ለዘመዶቻቸውና ለልጆቻቸው ያስተምራሉ ተብሎ ይታመናል። በዚህ መሰረትም ማህበረሰቡ በአሁኑ ሰዓት እየበዛ የመጣው የትምህርት ቡዳ ነው ይላል። ከዚህ ተጠይቅም ምናልባት ቡዳው ለልጁ ወይም ለወዳጁ ቡዳነትን የሚያስተምረው ጥቃት በማድረስ (በመብላት) ለዘመዶ፣ ለሞትና ለሌሎች ችግሮች እንዳይዳረግ በማሰብ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ቡዳን ቡዳ አይበላውም በሚል ማኅበረሰቡ ያምናልና።

ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ በእፅና በዘር ቡዳ የሆነ ሰው ሰውን መብላቱ ግዴታ ስለሚሆንበት ነው ይላሉ። በተለይ በዘራቸው ቡዳ የሚባሉት ቤተ እስራኤላውያን "እኛ ካልበላን ምና ምን ካልሆን ሸክላውም አይሰራ፣ ሁሉም ይበተናል የሚሉ በእርግጠኛ ካይሎች ነበሩ- የዘር ትውልዶች" በማለት የሚበሉበትን ምክንያት አቶ መንገሻ ሽባባው ይገልፃሉ።

በማኅበረሰቡ ዘንድ ቡዳ ለሚባሉ ሰዎች እይታ የተጋለጠ ማንኛውም ሰው በየትኛውም ጊዜና ቦታ የመበላት እድል ሊኖረው ይችላል።

## 4.1.6. የቡዳ ጥቃት የመከላከያ ዘዴዎች

የቡዳ እምነት አለማቀፋዊ አሳቤ ያለው መሆኑን የሚያመለክተው በአንዳንድ ማኅበረሰቦች የቡዳ ጥቃት ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎችና አንዳንድ ስርዓቶች ከሞላ ጎደል ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑን ምሁራን (Dundes, 1992; Steven, 2003 እና Lykiordopoulos, 1981) ይገልጻሉ። ከእነዚህም ውስጥ ኪታብ ማሰር (Wearing aptropaic amulelets)፣ የተለመዱ አካላዊ እና ቃላዊ ገለፃዎች (Hand and other gestures and verbal or oral formulas)፣ ፀሎቶችና ጌጣጌጦች ይጠቀሳሉ።

በሰሜን ጎንደር ማህበረሰብ ክላይ የቀረቡት የመከላከያ ዘዴዎች ይተገበራሉ። በማኅበረሰቡ በዋናነት የቡዳ ጥቃት የመከላከያ መንገድ ራስንና ንብረትን በቡዳነት ከሚጠረጠረው ግለሰብ እይታ አለማጋለጥ ነው። ይህንንም ጉዳይ "አይኑ ካላየ ቡዳ አይበላም" በሚለው አባባላቸው ያጠናክሩታል። ነገር ግን በቡዳነት የሚጠረጠሩ ግለሰቦች እንደሌሎች ህብረተሰብ ክፍሎች እንደ ሰርግ፣ ለቅሶ፣ ገበያ፣ ስብሰባ በመሳሰሉ ማህበራዊ ግንኙነቶች ተሳታፊ በሚሆኑበት ጊዜ እና ራስን ሆነ ንብረትን ከተጠርጣሪዎች እይታ ማራቅ የማይቻልበት አጋጣሚ ሲፈጠር ማኅበረሰቡ የተለያዩ የቡዳ ጥቃት መከላከያ ርምጃዎችን እና ስርዓቶችን ቀድሞ ያከናውናል። ከተለመዱ የመከላከያ ዘዴዎች መካከል ክታብ ወይም ጥፈት እና መድሃኒት ማሰር፣ ፀሎት ማድረግ፣ ቡዳውን መሳም ወይም ሰላም ማለት፣ የተለመዱ ቃላትን መናገር፣ ትረካዎችን መተረክና ጌጣጌጦችን መጠቀም ይገኙበታል።

### 4.1.6.1. የቡዳ መድሃኒት

የቡዳ መድሃኒት በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት ውስጥ ከቡዳ ጥቃት መከላከያ እስከ መፈወሻ ስርዓቶች ድረስ የሚጠቀስ ፎክሎራዊ ጉዳይ ነው። ይህ መድሃኒት የቡዳ ጥቃት መከላከያ፣ መለያ፣ መፈወሻ እና መመለሻ እንዲሁም የሚታሰር፣ የሚሸተት፣ የሚጨስ፣ የሚታጠንና

የሚጠጣ በሚል አይነቱ እና ተግባሩ ይለያያል። ይህ ንዑስ ርዕስ ለቡዳ መከላከያነት የሚውለውንና በማኅበረሰቡ ዘንድ የቡዳ መድሃኒት እየተባለ የሚጠራውን ይመለከታል።

ይህንን መድሃኒት ከተለያዩ እፅዋት ቅጠልና ስር እንዲሁም የእንስሳት ቆዳና ስጋ የሚያዘጋጁት በማኅበረሰቡ የባህላዊ መድሃኒት አዋቂ የሚባሉት ናቸው። ከእነዚህም አካላት በተጨማሪ በልምድ አንዳንድ ሰዎች የቡዳ መድሃኒቶች ያዘጋጃሉ። በመስክ ቆይታም አቶ አስራት ሙጨ የተባሉ ግለሰብ የቡዳ መድሃኒት ብቻ ከሚያውቁ ሰዎች እንደተማሩና እንዳወቁ ነግረውኛል። ሲያዘጋጁም ተመልክቻለሁ። ባህላዊ የቡዳ መድሃኒት አዘገጃጀት ሚስጥራዊ እንደሆነ በቃለ መጠየቅና በቡድን ውይይት ወቅት ተገንዝቢያለሁ። በተለይ አቶ ታረቀኝ እምሩ የመድሃኒቶች የቅመማ ሂደት እና ለቅመማ የሚያስፈልጉ ነገሮች የማይነገሩ መሆናቸውን ይገልፃሉ። ነገር ግን በማኅበረሰቡ የቡዳ መድሃኒት ሲያዘጋጁ የማይቀየሩ ነገሮች ነጭ ሽንኩርት ጤና አዳም የብሳና ቅጠል እና የጅብ ቆዳ ናቸው። እንደ አቶ አስራት ሙጨ አገላለጽ እነዚህ ቅመማ ቅመሞችና ስሮች በአንድ ከተዘጋጀ በኋላ ውሃ ባልነካ ጨርቅ ተጠቅልሎ ይታሰራል ይላሉ። ከባህል መድሃኒትነት አዋቂዎች ወይም በልምድ ከሚያዘጋጁ ግለሰቦች የተገኘው የቡዳ መድሃኒት ውሃ ባልነካና ከንጹህ ጥጥ በተሰራ ጨርቅ ተጠቅልሎ እና ተሰፍቶ አንገት ወይም እጅ ላይ ይታሰራል። በዚህም ቡዳን ይከላከላል ብለው ያምናሉ። በማኅበረሰቡ ዘንድ በተለይ በገጠሩ አካባቢ በሁሉም ዕድሜ የሚገኙ ሰዎች በቡዳ ጥቃት ለመከላከል የቡዳ መድሃኒት ያስራሉ። ይህንን ጉዳይ ወይዘሮ ሻሼ ታየ "...እኔን ይገፍ ነው የምገባው ቡዳ እንዳይበላይ ለልጆቹ በሙላ ይህችን አስሬ [አንገቷ ላይ ያሰረችው የቡዳ መድሃኒት እያሳየችኝ] እገባለሁ። ቢቃ አሁን እንዳይበላኝ" በማለት ይገልጻሉ። በዚህም ማንኛውም ሰው የቡዳ መድሃኒት ካሰረ ቡዳ አይበላውም በማለት ያምናሉ። ይህንን እምነት አቶ መንገሻ ስዩም "የቡዳ መድሃኒት እስር የሚሄድ ሰው ፆ ቡዳ አይደርስበትም፡ ወዲያ ርቆ ነው የሚሄድ። ቢትሄድበትም እሱ መሮጥ እንጂ አይጠጋህም" በማለት መድሃኒቱ የቡዳውን እይታ ማራቅና የመቀልበስ ሀይል ያለው መሆኑን ይገልፃሉ። በመሆኑም የቡዳ መድሃኒት ያሰረን ሰው ቡዳው ተደብቆ ወይም እንደ አጋጣሚ ባላወቀበት ጊዜ ቢመለከተው እንኳ ጥቃት አይደርስበትም ተብሎ ይታመናል። ነገር ግን አንድ የቡዳ መድሃኒት ያሰረ ሰው በቡዳ ከሚጠረጠር ሰው ጋር አይን ለአይን ከተያዩ ከአንገቱ ወይም ከእጁ ላይ ያሰረውን የቡዳ መድሃኒት ማሽተትና ማሸት ይኖርበታል። በዚህም ጊዜ የቡዳውን ጥቃት ይቀለብስለታል። እይታውንም በቶሎ ይመልሳል። ቡዳውንም ያሳፍራል ወይም ያሸማቅቃል ተብሎ ይታመናል።

#### 4.1.6.2. ክታብ (ጥፈት)

በማገበረሰቡ ዘንድ ክታብ ወይም "ጥፈት" ክእይን ጥላ፣ ከሰው አይን ወይም ከቡዳና ከሌሎች እርኩሳን መናፍስት የመጠበቅ ሀይል አለው ተብሎ የሚታመን፤ ከብራና ወይም ከወረቀት ላይ የሰፈሩ ድግምቶችን፣ ውዳሴዎችን እና ሌሎች አስማታዊ ፅሁፎችን የያዘ፤ በቆዳ ተጠቅልሎ አንገት፣ ክንድ እና እጅ ላይ የሚታሰር ነው። ይህን የመከላከያ መድሃኒት የአብነት ተማሪዎች፣ ደብተራዎች እና ጠንቋዮች ያዘጋጁታል። በአብዛኛው በተማሪዎች የሚዘጋጀው ጥፈት ወይም ክታብ መልክአ ገብርኤል፣መልክአ ሚካኤል፣ መልክአ ሩፋኤል፣ ወዘተ የሚሉ አጫጭር የውዳሴ ጽሁፎች የያዘ ነው። ማገበረሰቡ የእግዚአብሔር ቃል ያለበት በመሆኑ ከቡዳ እና ከእርኩስ መንፈስ ይጠብቃል የሚል እምነት አለው። ከጠንቋዮች ወይም ከደብተራዎች የሚዘጋጀውን ክታብ ወይም ጥፈት ግን በውስጡም አስማታዊ ድግምቶችን የያዘ፣ በዕድሜ፣ በፆታ፣ ለመከላከል እንደተፈለገው ነገር የተለያየ፣ በትዕዛዝ ወይም እንደ በሽታው/ ህመሙ ባህሪ በምርመራ የሚዘጋጅ ነው። ለምሳሌ ቡዳን ለመከላከል የሚታሰረው ክታብ በውስጡ የቡዳ ጥቃትን የሚያርቁ ድግምቶችና አስማታዊ ሀተታዎች ይፃፉበታል።

#### 4.1.6.3. ንቅሳቶችና ሌሎች ቁሶች

በተጠኚ ማገበረሰቦች ዘንድ ንቅሳት፣ የፀጉር አቆራረጥ፣ በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ የሚደረጉ ጌጦች ከጌጥነት ባለፈ ቡዳን ጨምሮ ሌሎች እርኩስ መንፈሶችን ይከላከላሉ ተብሎ ይታመናል። እነዚህ ጌጦች በላዕላይ ተግባራቸው ለውበትና ለጌጥ የሚደረጉ ቢመስሉም ታህታይ ተግባራቸው ግን የቡዳ ወይም ክሰው አይን እና እርኩስ መንፈስ ጥቃትን ከአጊያጨ ማራቅ ነው።

የመጀመሪያው እንደ ጌጥ የሚቆጠረው የቡዳ ጥቃት መከላከያ መንገድ የፀጉር አቆራረጥና አያያዝ ነው። በማገበረሰቡ ልማዳዊ እምነት መሰረት የህፃናት ሆነ የወጣቶች ጭንቅላት መቁሰል፣ ፀጉር መበጣጠስ፣ መነሳትና ማጠር ምክንያት ለሰው አይን መጋለጥ እና በቡዳ መበላት እንደሆነ ይታመናል። ይህንንም ለመከላከል ወጣት ሴቶችና ልጃገረዶች ደግሞ ፀጉራቸውን እንዲያሳጥሩ ወይም በሻሽ አለበለዚያ በኩታ እንዲሸፍኑ ይደረጋል። በተለይ ፀጉራቸው የሚያምር ወይም ሉጫና ረጅም የሆነ ህፃናት፣ ወጣት ሴቶችና ልጃገረዶች ቡዳ ለሚባለው ሰው አይን ገብ ይሆናሉ ተብሎ ይታመናል።

በዚህም ወጣት ሴቶችና ልጃገረዶች ከቅርብ ቤተሰብ ውጭ ፀጉራቸውን ማሳየትም ሆነ ተገልጦ መሄድ ራስን ለቡዳ ወይም ለሰው አይን ጥቃት አሳልፎ እንደመስጠት ይቆጠራል። የሩቅ ሃገር

ሰው በእንግድነት ከቤት ሲመጣ፣ ሲያስተናግዱ፣ ሲሰሩ፣ ሲቀመጡ፣ ሲተኙ ፀጉራቸው እንዳይታይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ። አንዲት ሴት ፀጉሯን በሻሽ ወይም በነጠላ መሸፈን የማትችል ከሆን ደግሞ በቡዳ ላለመበላት ወይም በሰው አይን ላለመጠቃት እንደ ወንዶች ፀጉሯን ማስጠር ይኖርባታል።

ከዚህ በተጨማሪ ህፃናትን ከቡዳ ጥቃት ለመከላከል ፀጉራቸውን በግማሽ በምላጭ እንዲላጩ፣ በሙቀስ እንዲቆረጡ ወይም ቁንጮ እንዲደረግላቸው ይሆናል። እንዲሁም ፀጉራቸውን ሙሉ በሙሉ በምላጭ ከተላጩ በኋላ ጭንቅላታቸው "አስተናግር" በሚባል ተክል ቅጠል በመጭመቅ መቀባት ከሰው አይን ጥቃት ይከላከላል ተብሎ ይታመናል። ህፃናትን በዚህ መልክ ፀጉራቸውን የመላጨቱ፣ የማስጠር ወይም የቅጠል ጭማቂ የመቀባቱ ምክንያት ምናልባት በቡዳነት የሚጠረጠረው ሰው ፀጉራቸውን ተመልክቶ የማድነቅ ወይም የመቅናት ፍላጎትን ለማደናቀፍ ወይም አይታውን ለማገደል ይመስላል።

ሁለተኛው በተጠኚ ማኅበረሰቦች ዘንድ በስፋት እንደ ጌጥ የሚቆጠረው የቡዳ ጥቃት መከላከያ መንገድ ንቅሳት ወይም በማኅበረሰቡ አጠራር "ጥቁራት" ነው። ንቅሳት አንድ የቡዳ መከላከያ ዘዴ መሆኑን Young (1970, 5) ይገልፃሉ። ንቅሳት በማኅበረሰቡ አባላት ዘንድ በተለይ በገጠር አካባቢ በሀፃንነት እድሜ የሚከናወን በአሁኑ ወቅት እየቀረ የመጣ ባህል ነው። በአብዛኛው የምትነቀሰው ወይም በማኅበረሰቡ አባባል "የምትጠቆረው" ሴት ናት። ይህች ሴትም ጠቋሪ ትባላለች። ለንቅሳት የምትጠቀምባቸው ነገሮች የተለያዩ ቅጠሎች፣ ስራስሮች ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥም ቡዳ መከላከል የሚያስችል መድሃኒት ወይም ስር የሚጨመርበት መሆኑን Young (1970, 7) ይገልፃሉ። ንቅሳቱ እስከ የዕድሜ ዘመናቸው የማይለቅ ሲሆን የሚነቀሱት አይነትና የሚነቀሱበት የሰውነት ክፍልም የተለያየ ነው።

በዋናነት የሚነቀሱት ቅርጽ የመስቀል፣ የኮብ፣ የ"ቶ" ፊደል ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ የስማቸውን ፊደላት ይነቀሳሉ። እነዚህን ቅርጾች የሚነቀሱበት የሰውነት ክፍልም በአብዛኛው ሴቶች በግንባራቸው፣ አንገታቸው በአገጫቸው በጉንጮቻቸው፣ በእግሮቻቸውና በእጆቻቸው ላይ ነው። ንቅሳቱ ከውበትነት ወይም ከጌጥነቱ ባሻገር በቡዳነት የሚጠረጠር ሰው ልጅቱን በሚመለከትበት ወቅት በውበቷ ወይም ከቁንጅናዋ ይልቅ ንቅሳቷ ላይ አይኑን እንዲያሳርፍ በሚል ነው። በዚህ ወቅትም አይታው ወይም የማጥቃት ሐይሉ በጌጣጌጡ ላይ ሲያርፍ ይደከማል ተብሎ ይታመናል። በተለይ አንገታቸው ረጅምና መልካቸው ቀይ የሆኑ ሴቶች ከሰው አይን ጥቃት ለመከላከል አንገታቸውን፣ እግራቸውና እጃቸውን ይነቀሳሉ። በዚህም አንዲት ቆንጆ ሴት

በሰውነት ከፍሏ ላይ ለእይታ ግልጽ ያልሆነ ንቅሳት የሌላት እንደሆነ *"ባይሆን ለሰው አይን ማረፊያ አንድ ነገር (ንቅሳት) አርጉላት እንጂ"* ይባላል።

ሦስተኛ የቡዳ ጥቃት መከላከያ መንገድ በጆሮ በአንገት በእጅና በእግር ላይ የሚንጠለጠሉ፣ የሚታሰሩ ወይም የሚደረጉ ጌጣጌጦች መጠቀም ነው። እነዚህን ጌጣጌጦች በማኅበረሰቡ አጠራር ጉትቻ፣ አምባርና ድሪ የሚል መጠሪያ ሲኖራቸው ከብረት፣ ከነሃስ፣ ከመዳብ፣ ከብርና ከወርቅ ይሰራሉ። በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት መሰረት ከብረት፣ ከነሃስ፣ ከመዳብ፣ ከብር እና ከወርቅ የተሰሩ ጌጣጌጦች አንዳንዶቹም የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ቡዳንና ሌሎች እርኩስ መንፈሶችን ያርቃሉ ተብሎ ይታመናል።[60]

በመስክ ቆይታዬም አንዳንድ ሴቶች (ልጃገረዶች፣ ወጣቶችና እናቶች) በአንገታቸው ላይ የማርትሬዛን ወይም ጠገራ ብር፣ የሀገራችን የድሮ እና የአሁን ዘመን መንግስታትና ሌሎች ሀገራት ሳንቲሞችን እና የጆሮ ውስጥ ቆሻሻ መጥረጊያን፣ አንገታቸው ላይ በክር (እንደ ማተብ) አስረው ተመልክቻለሁ። በተለይ ከመዳብ ከብርና ከብረት ወይም በማኅበረሰቡ አጠራር ከቆርቆር የሚሰራው 'ድሪ' የሚባለው ጌጥ ይዘወተራል። በማኅበረሰቡ ዘንድ እነዚህ ጌጣጌጦች ከጌጥነታቸው ባሻገር ከሰው አይን ከቡዳና ከእርኩስ መናፍስት ይጠብቁናል የሚል እምነት አለ። በተለይ ከቡዳ ጋር ተያይዘው የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የክፉ አይን ባለቤት የሆነ ሰው ከሰዎቹ ይልቅ ከጌጣጌጦቹ ላይ ስለሚያተኩር የመጉዳት ሀይሉ ይቀንሳል ይላሉ። ጌጣጌጦቹ ላይ አተኩሮ መመልከቱ የቡዳ ጥቃት መንፈሱ ከሴትዮዋ ይልቅ ጌጣጌጡ ላይ ያርፋል በዚህም እይታው ይቀለበሳል ብለው ያምናሉ።

የመጨረሻው የቡዳ ጥቃት የመከላከያ ስልት በእንስሳትና በማሳዎች በቤትና በግቢ በር ላይ ቁሳቁሶችን መጠቀም ነው። በአንዳንድ አውሮፓውያን ልማዳዊ እምነት ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በተክሎች፣ በእንስሳት፣ በማሳዎች በቤትና በግቢ በር ላይ በሚንጠለጠሉ ወይም በሚቀመጡ ቁሶች የቡዳውን ጥቃት ለመቀልበስ ይሞክራሉ። በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ዘንድ በቤትና በግቢ በር እና በማሳ ላይ የከብት ጭንቅላት እስከነ ቀንዱ ይደረጋል። በተለይ የበሬ ወይም የላም ጭንቅላት አጽም በመተላለፊያ መንገድ ዳርና በደረሰ የሰብል ማሳ መካከል ከፍ

[60] በተለይ ብረትና ብረት ነክ ነገሮች በሚከበረበት ልማዳዊ እምነት ውስጥ ከማንኛውም ክፉ ነገር ይጠብቃሉ ተብሎ ይታመናል። በምሳሌ ያህል አንዲት ሴት ወልዳ በምትተኛበት ወቅት አልጋዋ ብረት (እንካሴ፣ የብረት ዘነዘና፣ ቢላ) ይቀመጣል። ይህም እሷንና የተወለደውን ህፃን ከእርኩስ መንፈስ ለመጠበቅ የሚደረግ ተግባር ነው። እንዲሁም ማንኛውም ሰው ጫካ (ማሳ ላይ) ሲያድር ራሱን ከክፉ ነገር ለመጠበቅ ከትራሱ ወይም ከአጠገቡ ብረት ያስቀምጣል።

ተደርጎ ይቆመጣል። የዚህ ልማድ ምክንያትም የከብት ጭንቅላቱ "የሰው አይን ማረፊያ እንዲሆን" የሚል ነው። ከከብት ጭንቅላት ውጭም የላስቲክና የልብስ ቅዳጅ በማሳዎች መካከል ወይም ዳር ይደረጋል። ከሌሎች ጥናቶችም ሆነ በተጠኚ ማኅበረሰብ ልማዳዊ እምነት መሰረት በሁሉት የሚጠረጠረው ሰው በመጀመሪያ ከሰብሉ ላይ በተሰቀለው ነገር ላይ አይታውን ስለሚያደርገው የመጉዳት ሀሳቡን በተሰቀለው ቁስ ላይ ያሳርፋል። በዚህም ጥቃት የማድረስ ሀይሉ ይደክማል ወይም ይጠፋል የሚል እመለከትን ያሳያል።[49] ይህ ባይሆን ግን በማህብረሰቡ ዘንድ ቡዳው ሰብሉን አይቶ እንዳንደም አይቶ ካደነቀ ፍሬ አልባ የማድረግ፣ የማድረቅና የማውደም ሀይል አለው ተብሎ ይታመናል።

4.1.6.4. ፀሎት

ተጠኚ ማኅበረሰቦች በአብዛኛው (በተለይም በገጠር አካባቢ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ (ክርስትና) እምነት ተከታዮች ናቸው። የአካባቢው የእምነት መሪዎችና አባቶች እንዲሁም አንዳንድ የማኅበረሰቡ አባላት ቡዳ እርኩስ መንፈስ፣ ኢጋንንት ወይም ሰይጣን ነው የሚል እምነት አላቸው። በመሆኑም ፀሎት ማድረግ እርኩስ መንፈስን ይከላከላል ወይም ይጠብቃል ተብሎ ይታመናል። መርጌታ አዳነ አለፋ የቡዳ መከላከያ መድሃኒት "እኔ በእውቀቴ የማስበው ማለዳ ፀሎት ማረፍም ደግሞ መነሳት ንእምን በአሃዱ አምላክ ብሎ በክርስቶስ አምኖ መነሳት። እኔ በዚህ አምናለሁ" በማለት ይገልጻሉ። አቶ ሞላ አያሌው እንዲሁ አንድ ሰው በቡዳ ላለመበላት "የተማረ ይደግማል። ያልተማረ ደግሞ በቅን ልቦናው አዘውትሮ ደብር መሳምና አማልጅኝ አማልጅኝ እያለ መስገድ ነው ያለበት" ብለው ያምናሉ።

---

[49] መረጃ ሰጭዎቹ በቃለመጠይቁ ጊዜ ምርት የተሰበሰበበት ወቅት በመሆኑ እነዚህን ክንውኖች መመልከት አልቻልኩም። ነገር ግን የእነዚህ እና የሌሎች ፈረጃ ተሚዶ በተደረጉበት ጊዜና አሁንም አልፎ አልፎ በመድ ለመጠየቅ ወደ ደምቢያ ወረዳ እና ጭህራ (ጎንደር ዙሪያ ወረዳ) አካባቢ ስመጣ በምንገባበት ወቅት በመንገድ ላይ ባሉ ሰብሎች ላይ እንደ ሰንደቅ አላማ ከፍ ብለው የሚታዩ የሳር/የእንጨት ቀርቀሮ ወይም ጣሳዎችና የከብት ጭንቅላት አጽም እመለከት ነበር። በአሁኑ ጊዜ ለምን እነዚህ ነገሮች እንደሚሰቀሉ በምጠይቅበት ወቅትም ከማህበረሰቡ ሁለት አይነት መልስ አግኝቻለሁ። አንደኛው ከአዕዋፍት ጥቃት ለመከላከል ይህም አዕዋፍት ሰብሉ ላይ የሚጠብቅ ሰው ያለ መሆኑን ለማስመሰልና አይተው እንዳይበሉ ለማድረግ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከሰው አይን ለመከላከል የሚል ነው። ነገር ግን ለአዕዋፍ ጥቃት (መበላት) ተጋላጭ በሆኑ ሰብሎች (ገብስ፣ ማሽላ፣ ስንዴ ወዘተ ...) ቁሶቹ መሰቀላቸው ለአዕዋፍ ጥቃት ለመከላከል ነው ቢባልም ከአዕዋፍ ጥቃት ይልቅ ለተባይና ለትላትሎች ተጋላጭ በሆኑ ሰብሎች (እንደ ጤፍ፣ ዳጉሳ፣ ሰሊጥ ወዘተ...) ላይ የእነዚህ ቁሶች መቀመጥ ለምን አስፈለገ ሲባል ምን አልባት "የሰው አይን ለመከላከል" የሚለውን እመለከት የሚያሳይ ይመስለኛል።

#### 4.1.6.5. አካላዊና ቃላዊ ገለጻ

ከላይ የቀረቡት እንደ ክታብና የቡዳ መድሃኒት ማሰር፣ ፀሎትና ጉጣጉጥ ማድረግ እና አንድ ሰው ቡዳ ከሚባለው ሰው ጋር አይን ለአይን ባይተያይ ወይም ቡዳው በድብቅ ቢመለከተው እንኳን ጥቃቱን የመከላከል ሐይል አላቸው ተብለው የሚታመኑ ናቸው። ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ቡዳ የሚባለው ሰው ከመሃከል ሲኖር ወይም አይን ለአይን (ፊት ለፊት) ሲያጋጥም በአካል እንቅስቃሴና በንግግር የሚገለጹ የተለያዩ የቡዳ ጥቃት መከላከያ መንገዶች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ቡዳውን መሳም፣ ሰላም ማለትና መሳደብ፣ ስለ ቡዳ ታሪኮችን መተረክ፣ ኮቴውን መርገጥ እና ሌሎች ይጠቀሳሉ።

በማኅበረሰቡ ልማድ መሰረት በቡዳነት የሚጠረጠር ሰው በመሃከል ሲገኝ ወይም አይን ለአይን ሲያጋጥም አለመፍራት፣ አለመጨነቅና፣ አለመደናገጥ፣ ራስን በቶሎ ከእይታው ማራቅ፣ ፊትን ቢጋቢ መሸፈን፣ አንገት መድፋትና ጀርባን መስጠት ተመራጭ የመከላከያ መንገድ ነው። ነገር ግን የቡዳው እይታ የሚያስፈራ ወይም በቡዳው እይታ ልቡ የሚሸበር፣ የሚፈራ፣ የሚጨነቅና ሊያጠቃኝ ይችላል የሚል ስጋት የሚያድርበት ከሆነ የመጀመሪያው አካላዊና ቃላዊ ምላሽ የመከላከያ ዘዴ ሰላምታ መስጠት ነው። የሰላምታ አሰጣጡ መንገድም አንድ ሰው ቡዳ የሚባለውን ሰው ከርቀት ሲመጣ ካየው ቡዳ የሚባለው ሰው ሳያየው በፍጥነት ጉልበቱን፣ ትንፋሹን ወይም እጁን በመሳም ሰላምታ ማቅረብ ነው።[50] ቡዳ ለሚባለው ሰው ሳያይ ድንገት ሰላምታ መስጠት የማጥቃት ፍላጎቱ እንደሚሸሽ ይቆጠራል። በዚህም ቡዳ የሚባለው ሰው የማጥቃት ሀይሉ በሰላምታው ይፈረሳል ተብሎ ይታመናል።

ሁለተኛው በአካላዊና በቃላዊ ምላሽ ቡዳን መከላከያ መንገድ ቡዳ ከሚባለው ሰው ፊት ስለ ቡዳ የተለያዩ ታሪኮችን ወይም አፀንቶችን መተረክ (ማውራት) ነው። በማኅበረሰቡ በተለይ ቡዳው በአቅራቢያ ወይም በመሃከል በሚገኝ ወቅት ከአሁን በፊት በሰውየው ላይ ስለለፈለፉ ሰዎች ወይም ሌሎች ከቡዳ ጥቃት ጋር የተያያዙ ታሪኮችንና አፀንቶችን ከአጠገብ ላለ ሰው በሚመስል መልኩ መተረክ የቡዳ ጥቃት ይከላከላል ተብሎ ይታመናል። በዚህ ጊዜ ቡዳው የመብላት ስሜቱ ይቀዘቅዛል። በቀጥታ አይሁን እንጂ ስለቡዳው የሚነገረው /የሚተረከው ታሪክ ለሱ እንደሆነ

[50] የሰላምታ አሰጣጥ መንገዱ እንደ እድሜያቸው፣ ማኅበራዊ ደረጃቸውና ዝምድናቸው ይለያያል። ለምሳሌ ያህል በቡዳ ላለመበላት ቅድመ ጥንቃቄ የሚያደርገው ሰው ቡዳ ከሚባለው ሰው በእድሜ ወይም በማኅበራዊ ደረጃ ዝቅ ያለ ከሆነ እንደ ቅርበታቸው ቡዳ የሚባለው ሰው ጉልበቱን፣ እጁን ወይም ጭንቅላቱን እንዲስመው በማድረግ ሰላምታ ማቅረብ ይኖርበታል።

ያውቃል፣ በዚህ የተንሳም ቀና ብሎ ለማየት ያፍራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህንን ሃሳብ አቶ ሙሌ ፍስሃ[51] እንደሚከተለው ይገልፁታል፡-

> እንዲያውም ቡዳን አታግልሉት፣አትፍሩት ነው የሚባል፡፡ መፈራት የለበትም እንዲያውም ቡዳ ሲመጣብህ 'አንተ ይኼ ቡዳ እሱ እንደዚህ ሆኖ…እ…የእገሌን ልጅ በላው' ወይም ደግሞ 'እገሌን እሱ ትናንት ቡዳ በላት' ማለት፡፡ በዚህም ቡዳ ሲመጣ ስለ ቡዳ አውሩት ነው የሚባል በባህል ደረጃ፡፡ እንዲያውም፣ ሰዎችን እንዳይጎዳ እሱን ከማግለል ይልቅ ሲመጣ ስለ ቡዳ ወሬ አውሩ ነው የሚባለው፡፡ በዚያን ሰዓት ቡዳው ይሸማቀቅና አንገቱን ይደፋል፡፡ (ሙሌ ፍስሃ፣ግንቦት 12/2003 ዓ.ም፣ ቃለ መጠይቅ)

በመሆኑም በተጠኚ ማኅበረሰቦች ልማዳዊ እምነት መሰረት ቡዳ በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች ምክንያት ከሰዎች መሀከል ሲገኝና አይኑን ከሰው በጣለ ጊዜ ተደናግጦ ራስን ከእይታ ከማራቅ ወይም ቡዳውን ከማግለል ይልቅ ለሌላ ሰው በማስመሰል ቡዳው ባለበትና በሚሰማበት መልኩ ስለቡዳ በማውራት ቡዳውን በማሸማቀቅና አንገት በማስደፋት ቡዳን መከላከልና እይታውን ማስቀየስ ይቻላል፡፡

ሁለተኛው በቃላዊ ምላሽ ቡዳን የመከላከያ ዘዴ የተለመዱ ስድቦችን ከቡዳው ፊት መሳደብ ነው፡፡ እነዚህ የተለመዱ የስድብ ቃላት "ቡዳ"፣ "ጅራታም"፣ "አንካሳ"፣ እና "ባለጭራ" የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህን ቃላት ሰዎች በቡዳነት የሚጠረጠረው ሰው አጠገባቸው በሚሆንበትና አይን ለአይን በሚተያዩበት ወቅት አንተ ቡዳ፣ ጅራታም፣ ባለጭራ፣ ጅብ፣ አንካሳ በማለት ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንጓጠጥ ያስፈልጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ቡዳው ስድቦቹን የሚሰማበት አጋጣሚ ከተፈጠረ ወይም ለመሳደብ የማይቻል ከሆነ[52] አጠገባቸው ያለን ሰው ወይም ነገር የሚሳደቡ በመምሰል ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ይሳደባሉ፡፡

እነዚህ የስድብ ቃላት በቡዳነት የሚጠረጠረውን ሰው ስሜት የሚጎዱና አንገት የሚያስደፉ ስድቦች ሊሆኑ ለተናጋሪው ግን የቡዳውን ጥቃት ማባረሪያና እይታውን መቀልበሻ መንገድ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ በሌላ መልኩ እነዚህ የስድብ ቃላት ከስድብነት ባለፈ ከቡዳ እምነት ጋር የተያያዘ ተምሳሌታዊ ፍቺ ያላቸው ይመስላል፡፡ ይህም በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት መሰረት በቡዳነት የሚጠረጠር ሰው በሌሊት ወደ ጅብነት ይቀየራል ወይም ጅብ ይጋልባል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም "አንተ ጅራታም" እና "ባለ ጭራ" ሲሉ ጅብ የተባለ እንስሳን እንዲሁም

---

[51] በጉንደር ቁራታ ወረዳ የማህበረሰብ አቀማ ነዋሪና የማህበረሰብ ሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ናቸው፡፡
[52] ከመጣሱ ሊያበሳጭ ይችላል የሚል ስጋት ሲፈጠር፣ ቡዳ ከሚባለው ሰው ጋር የማኅበራዊ ደረጃና እድሜ ሰፊ ልዩነት እና የጠበቀ ዝምድና ወዳጅነት ሲኖር

እንሶ ሴሉ ደግሞ የጅብን አረማመድ ለማመልከት ይመስላል። ይህን በዘይቤ ተራ ከተመለከትነው ቡዳውን ጅብ ነህ የሚል ትርጉም ይሰጣል።

ሌላው የቡዳ መከላከያ መንገድ ምራቅን መትፋት ነው። ምራቅ የሚተፋውም በተለያየ መንገድና አጋጣሚ ነው። የመጀመሪያው አጋጣሚ ቡዳ የሚባለው ሰው በሚያጋጥምበት ወቅት የረገጠውን መሬት በመርገጥ በዳናው ላይ ምራቅን መትፋት ነው። ይህ የሚሆነውም ቡዳ የሚባለው ሰው ድንገት አይቶኛል ወይም ሳይሰማኝ አይቀርም የሚል ፍርሃትና ጥርጣሬ ሲያድር የሚፈፀም ነው። በዚህም በማኅበረሰቡ ቡዳ የሚባለው ሰው የረገጠው ቦታ ላይ "አንተ ቡዳ አውቄብሃለሁ" በማለት መርገጥና መትፋት አይታውን ያረክሳል፤ ጥቃቱንም ይከላከላል ተብሎ ይታመናል።

በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት ገና ከተወለዱ እስከ አስር ዓመት ገደማ ያሉ ህፃናትን ያደነቀ፤ የአንድን ሰው አዲስ ወይም አይነ ግብ (ውብ) ነገር እንዲሁም የደለቡ ወይም የእርሻ በሬዎች፣ ጡቱ ወተት የሚሰጡ ላሞችን ተመልክቶ በጥልቅ ስሜት ያደነቀ፤ አድናቆቱን በገለጸበትና አይታውን ባሳረፈበት ነገር ላይ ምራቁን እንዲተፋ (እንትፍ እንትፍ እንዲል) ይደረጋል። ምራቁን ባይተፋ አይታውን ያሳረፈበትና ያደነቀው ነገር ለህመምና ለችግር ይዳረጋል ተብሎ ይታመናል። በተለይ የሚታዩና የሚታቀፉ ህጻናት ለአይታ ከተጋለጡና ከተደነቁ የቡዳ ጥቃትን ለመከላከል ተጠርጣሪው ህፃኑን እንዲያቅፍ፣ እንዲስምና ምራቁን እንትፍ እንዲል ይደረጋል። አንዳንድ ጊዜ ምራቅን እንትፍ የማድረግ ስርዓት ህፃኑን የያዘ ማንኛውም ሰው እንዲፈጽም ይደረጋል። ይህንን የማይፈጽም ሰው ቢኖር ግን ራሱን ለቡዳነት ጥርጣሬ አሳልፎ እንደሰጠ ይቆጠራል።

የቡዳ ጥቃትን ለመከላከል የሚደረገው ምራቅ የመትፋት ስርዓት ራሱን የቻለ ፋይዳ አለው። በማኅበረሰቡ በሰው ፊት (በሰው ላይ) ምራቅን መትፋት በጣም ነውርና አፀያፊ ድርጊት ነው። አንድ ሰው በአጠገቡ ወይም በአካባቢው ሰው መኖሩን ሳያውቅ በአጋጣሚ ምራቁን ቢተፋ አጠገቡ ያለ ሰውም ድንገት ቢመለከተው ይቅርታ ይጠይቃል። ነገር ግን አንድ ሰው ሌላውን ሰው ቢጠላው ወይም ቢጣላው ለሰውየው ያለውን ጥላቻና ንቀት ለመግለጽ በጠላው ወይም በተጣላው ሰው ፊት ለፊት ምራቁን ይተፋል። ከፊት ለፊቱ ወይም ከሰውነቱ ክፍል ላይ የተተፋበት ሰውም በራሱም ሆነ በማኅበረሰቡ ዘንድ እጅግ በጣም እንደተናቀና እንደተዋረደ ይቆጠራል። የቡዳ ጥቃትን ለመከላከል ከቡዳ ፊት ሆነ ቡዳው በረገጠው መሬት (ዳና) ላይ ምራቅን መትፋት ከዚህ ጋር ይያያዛል። በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት ቡዳንና የቡዳን መንፈስ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅና መሳደብ የማጥቃት አይታውን፣ ስሜትና ፍላጎቱን ይቀሰብሳል ተብሎ ይታመናል። በዚህም ማኅበረሰቡ ምራቅን በመትፋት የቡዳ መንፈስን (ቡዳን የሚበላው ሰው) ያዋርዳል፤ ንቀታቸውን

ይገልፃሉ። በዚህም መሰረት ምራቅ የቡዳውን እይታ፣ የማጥቃት ስሜትና ፍላጎት የመቀልበስ፣ የማርከስና ማጥፋት ፋይዳ አለው።

### 4.1.7. የቡዳ ጥቃት የመለያ ዘዴ

ህመምን የመለያ ዘዴ እንደ የባህል ህክምና አዋቂዎች እውቀት፣ማህበራዊ ልማድ፣ ባህልና ስርዓት ከቦታ ቦታ፣ ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ ይለያያል። በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብም በእይታ፣ በምርመራና በሙከራ የቡዳ ጥቃት የመለየት ተግባር ይከናወናል። እነዚህን ዘዴዎች በመጠቀም የቡዳ ጥቃት ፈዋሾችና ሌሎች ሰዎችም ማኅበረሰባዊ ልማድና እምነት በመከተል ይለያሉ። በዚህ የመለያ ዘዴዎች የሚገኘው የህመም ምልክትም የቡዳ ጥቃት የሚያስከትለውን ጉዳት ያሳያሉ።

የመጀመሪያው የቡዳ ጥቃት የመለያ ዘዴ እይታ ነው። በማኅበረሰቡ ዘንድ የቡዳ ጥቃት መከሰቱን የሚያመለክቱ በእይታ የሚረጋገጡ ምልክቶች አሉ። እነሱም ሰው ላይ በተደጋጋሚ ከንፈር መንከስ፣ ጥርስና ጥርስን ማፋጨት፣ አይን ማፍጠጥና ማጉረጥረጥ ሲሆን፣ እንስሳት ደግሞ የአይናቸው ብሌን እና የሽንታቸው ቀለም ቢጫ መሆን፣ ተረጋግቶ አንድ ቦታ አለመቀመጥ ወይም ለረጅም ሰዓት አንድ ቦታ ላይ መቀመጥና በሬዎች እርሻ ቦታ ለመጠመድና ለማረስ አስቸጋሪ መሆን፣ የሚታለቡ ላሞች ጡት ማበጥ፣ መንጠፍ ወይም ደም የተቀላቀለበት ወተት መውጣት፣ ወዘተ ናቸው።

ሁለተኛው የመለያ መንገድ ቃላዊ ምርመራ ነው። በማኅበረሰቡ ልማድ መሰረት አንድ ሰው በድንገት ሆዴን ቆረጠኝ፣ ልቤን ወጋኝ የሚል ከሆነ ቡዳ እንደበላው ይታመናል። እንዲሁም በቡዳ የተበላ ሰው 'ይቅበዘበዛል፣ እሬ ይላል፣ ጉሮሮውን ዝጉት ያደርገዋል እንዱ ምልክት ነው" በማለት አቶ ደሳለኝ ሳህሌ (28/08/03 ዓ.ም፣የቡድን ውይይት) ይገልፃሉ። ማስፋሸግ፣ ማስለቀስና መጮር ልብ ድካምና ሆድ ቁርጠት ዋነኛ የቡዳ ጥቃት ምልክቶች ሲሆኑ እነዚህ ምልክቶች በአፀዋቸው በቡዳ መድሐኒት ወይም አስለፍላፊው ሰው ምርምራ አማካይነት የሚለዩ ናቸው። እንዲሁም አንድ ሰው የቀረቡት የህመሞች ምልክቶች የሚሰማው ከሆነ ከዘመናዊ ህክምና በፊት የቡዳ ጥቃትን ከሚለዩና ከሚፈውሱ ሰዎች ዘንድ እንዲወሰድ ይደረጋል።[53]

[53] የማህበረሰቡ ልምድ መሰረት በቡዳ የተጠቃ (የተበላ) ሰው ህመም ቢጸናበት እንኳ ወደ ዘመናዊ ህክምና ተቋማት እንዲሄድ፣ መድሃኒት እንዲወስድና መርፌ እንዲወጋ አይመከርም። ማህበረሰቡ በቡዳ የተበላ ሰው እነዚህ ህክምናዎች ከተደረገለት ይሞታል ተብሎ ይታመናል።

የአስረኛ ክፍል ተማሪ የሆኑት ሰላምና ዘቢያንሽ በቡዳ በተበሉ ጊዜ የፈውስ ስርዓቱ ከመከናወኑ በፊት የነበረውን ሁኔታ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፤

> መጀመሪያ ልቤን ኳድ ኳድ አረገኝ ወደታይ ይዞ ጭልጥ ጭልጥ ነው የሚለው። ልብህ ያመልጥሃል። ጭራሽ ድካም ይላል። ከዛ ሰው ማየት አልፈልግም። ጫማ እናጢስ ምናምን ሲሉ ልቤ ፍርት ፍርት ይላል። እፈራለሁ። እና ጫማ ሲያጨሱ ሲሉ ወጥተሽ ሩጭ ወጥተሽ ሩጭ አትያቸው ይለኛል። (ሰላም ጌጡ[54] 10/09/03 ዓ.ም፣ ቃለ መጠይቅ)

> በልጅነቱ በሌተኛል ያው በላኝ። በጀመሪያ ሲጀምረኝ ልቤን ነው ያመመኝ ከዚያ በኋላ እየሸፈነኝ ሄደ። ከዚያ በኋላ ራስነቴን አላውቅ ማለቴ ተሰወርኩኝ። መጨረሻ ያደረጉኝን ነገር አላውቅም። ሰደን ግን ራሴን አወቅሁ። (ዘቢያንሽ ማንደፍሮ[55] 10/09/03 ዓ.ም፣ ቃለ መጠይቅ)

በዚህ መሰረት የልብ ድካም፣ ፍርሃትና ሰው ላለማየት መፈለግ የቡዳ ጥቃት ምልክቶች በመሆናቸው ተበይው የፈውስ ስርዓት ተደርጎላቸው ከህመሙ እንደዳኑ ከመረጃ አቀባዮች አረጋግጫለሁ፡ ለመረዳት ችያለሁ።

ሦስተኛው የቡዳ ጥቃት የመለያ ዘዴሞ ሙከራዊ ዘዴ ነው። ይህም በቡዳ እንደተበላ የሚጠረጠርን ሰው የተለያዩ ነገሮችን በመጠቀም የቡዳ ጥቃት መሆንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ ሙከራ ይደረጋል። ከእነዚህ ውስጥ ቡዳ እንጓል መጠየቅ ነው። ልብ ድካም፣ ፍርሀት፣ ሽብር አይን ማፍጠጥ የቡዳ ምልክቶች እንደሆኑ ከላይ ተገልጿል። ነገር ግን እነዚህ የህመም ምልክቶች የሌላ በሽታ ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ይህን ለማረጋገጥም ምልክቶቹ የታዩበትን ሰው "ቡዳ" "ጅራታም" እንጓል ይጠየቃል። በዚህ ጊዜ ጅራታም ወይም ቡዳ የማይል ከሆነ ቡዳ እንደበላው ይጠረጠራል፡ በማኅበረሰቡ ልማድ በቡዳ የተበላ ሰው "ቡዳ" አይልም ተብሎ ይታመናል።

ሌላው በሙከራ የቡዳ ጥቃት የመለያ መንገድ ለቡዳ ጥቃት መከላከያነት የተዘጋጀን መድሃኒት በግራ እፍንጫው እንዲያሽት በማድረግ ነው። በዚህም በቡዳ እንደተበላ የሚጠረጠረው ሰው በግራ እጁ መድሃኒቱን የማይቀበልና በግራ አፍንጫው የማያሸት ከሆነ በቡዳ እንደተበላ ይታመናል። የቡዳ መድሃኒትን በግራ እጅ በመስጠት የቡዳ ጥቃት መለየት የሚቻል መሆኑን እቶ ቃረቀኝ አምሩ እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

---

[54] የፎገራ ቁሬያ ወረዳ በአንፍራዝ ከተማ የጉባኤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪ።
[55] የፎገራ ቁሬያ ወረዳ በአንፍራዝ ከተማ የጉባኤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪ።

> የቡዳ መድሀኒቱን በጨርቅ ቋጥረህ ወይም በፍንጃል ይዘህ በዚህ እጅህ [የግራ እጃቸውን እያሳዩ] እንካ ትለዋለህ። እጁን ይቀበልሃል። ሰውነቱ ይንቀጠቀጣል። ኃይል ከሆነ አምጣው ይልሃል፤ ቀረብ ስታደርግለት ዐይኑን አደርጎ ይደፋዋል። ቡዳ ግራ እጁ እርሙ ነው /ቡዳ ከሆነ/ መድሀኒቱን እንካ ስትለው ቶሎ ብሎ ቀኙን ይሰዳል። አይደለም ትልና በግራ እንካ ስትለው እረ እረ እያለ እንዲህ አድርጎ [የግራ እጃቸው ወደ ብብታቸው እያስገቡ] እስር ያደርጋል። (ታረቀኝ እምሩ፤ 04/09/03 ዓ.ም፣ ቃለመጠይቅ)

ስለሆነም በቡዳ የተበላው ሰው የቡዳ መድሀኒቱን በግራ እጁ እንዲቀበልና እንዲያሸት በመሞከር መለየትና ተገቢውን ፈውስ መስጠት እንደሚቻል ይገልፃሉ።

በፎክሎር ጥናት ውስጥ የግራና ቀኝ ጥንድ ተቃርኖ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠውና በአብዛኛው ማኅበረሰብ ልማድ ውስጥ የተለያዩ ተምሳሌታዊ ፍችን ያዘለ ነው። በዚህም ግራ የስህተት፣ የደካማነት፣ የመጥፎ አጋጣሚና የርኩስ መንፈስ (ሰይጣን) ተምሳሌት ተደርጎ ይቆጠራል። ለምሳሌ ያህል በአውሮፓ አንድ ሰው ጠዋት ከእንቅልፍ ሲነቃ በግራ ከተነሳ ቀኑን ሙሉ ቁጡና ተናዳጅ ይሆናል ተብሎ ይታመናል (Barber, 2011፡ 1093-1094)። በተጠኚው ማኅበረሰብ ልማድም አንድ ሰው ጧት ከእንቅልፉ ሲነቃ "በቀኝ አውለኝ" በማለት ፈጣሪውን ይለምናል። እንዲሁም "በቀኝ ያውልህ" በማለት ለሌላውን ይመርቃል። የማኅበረሰቡ አባላት በቀኝ እጃቸው የተለያዩ ስራዎችን ያከናውናሉ። በዚህም ቀኝ እጅ ጠንካራ ይሆናል። ነገር ግን ግራ እጅ የቀኝ እጅን ያህል ጠንካራ ቢሆንም አንዳንድ ስራዎችን በግራ እጅ ማከናወን በማኅበረሰቡ ልማድ ነውር ተደርጎ ይታመናል። ለምሳሌ በግራ እጅ እቃን ማቀበልና መቀበል፣ መብላት፣ ሰላም ማለት ወዘተ በባህሉ ነውር ናቸው።

በመጽሀፍ ቅዱስም እንዲሁ ቀኝ የእግዚአብሔር ወይም የቅዱስ መንፈስና የጽድቅ ግራ ደግሞ የሀጢያትን ፍች ይዞ ይገኛል። በዘፀ 15፥ 6 የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ የተከበረና ሀያል እንደሆነ፣ "እግዚአብሔር ሁልጊዜ በፊቴ አደርገዋለሁ እርሱ በቀኜ ስላለ አልናወጥም" መዝ 15፥ 4 እና ህዝ ቁ 8 ደግሞ በቀኝ በኩል መቆየት የምህረት በግራ ጎን መቆየት ደግሞ የሀጢያት ብዛት መሆኑን የሚያመለክት ነገር ቀርቧል። ከዚህ በትይዩ በማኅበረሰቡ እምነትም ቀኝ እጅ የእግዚአብሔር ግራ ደግሞ የሰይጣን ተደርጎ ይታሰባል። የአንድ ሰው ቀኝና ግራ ጎን በእግዚአብሄር መላዕክትና በሰይጣን ይታጀባሉ (ይጠበቃሉ) ተብሎ ይታመናል። በዚህም አንድ ሰው መልካም ነገሮችን በሰራ ጊዜ በቀኝ በኩል ያሉት መላዕክት ይቀርቡታል፣ ያሰበውም ይሞላል፣ ወደ እግዚአብሔር ቤት ይሄዳል ይላሉ። በግራ ጎን በኩል ያሉት የሰይጣን ጭፍሮች እርባ ክንድ ያህል ይርቁታል። ነገር ግን ክፉ ነገሮች በሰራና ባሰበ ጊዜ በግራ በኩል የሚያጀቡት የሰይጣን ጭፍሮች ይጠጉታል ተብሎ ይታመናል።

ከመጽሐፍ ቅዱስና ከማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት በመነሳት ከቡዳና ከግራ ጋር ተያያዘው የሚነሱ ጉዳዮች የእርኩስ መንፈስና የሰይጣን ስራ እንደሆነና በፈውስ ስርዓቱ ላይም ደካማና ተሸናፊ መሆኑን የሚያመለክት ፍቺ ይሰጣል።

### 4.1.8. የቡዳ ጥቃት የመፈወሻ ዘዴዎች

በስሜን ጎንደር በሚገኙ ማኅበረሰቦች ልማዳዊ እምነት ውስጥ አንድ ሰው የቡዳ ጥቃት ሲደርስበት (ሲበላ) ለጥቃቱ የተለያዩ ሀገረሰባዊ ልማዶችንና ሐይማኖታዊ ስርዓቶችን በመከተል የተለያዩ የመፈወሻ ዘዴዎችና ስርዓቶች ይከናወናሉ። እነርሱም ልማዳዊ፣ ሐይማኖታዊ እና ማኅበረሰባዊ እውቀት የፈውስ ዘዴና ስርዓት ናቸው። እነዚህ የመፈወሻ ዘዴዎች በውል የታወቀ የፈውስ ስርዓት፣ ስርዓቱ የሚፈጸምባቸው ቦታዎችና ተቋማት፣ የከዋኔ ሂደት እንዲሁም ስርዓቱን የሚመሩ ግለሰቦችና በስርዓቱ ላይ የሚሳተፉ ሰዎችን ያካትታል።

#### 4.1.8.1. ልማዳዊ የቡዳ ጥቃት ፈዋሾችና የፈውስ ስርዓተ ከዋኔ

በዚህ ክፍል በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ በልማዳዊ መንገድ የቡዳ ጥቃትን የሚፈውሱ ሰዎች ማንነት፣ የእውቀት ምንጭ እና የሚያከናውኑት የፈውስ ስርአተ ከዋኔ ተዳሷል።

##### 4.1.8.1.1. ልማዳዊ የቡዳ ጥቃት ፈዋሾች

እንደ Aspen (1994: 172-174) ጥናት በልማዳዊ መንገድ ቡዳን ጨምሮ ሌሎች "እርኩሳን መናፍስትን" የሚፈውሱ ሰዎች የእውቀት ደረጃ እና ማኅበረሰባዊ ተቀባይነት የሚለካባቸው መስፈርቶች ያሉ መሆኑን ይገልጻሉ። ከነዚህም ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን ያላቸው ቅርበትና ለመፈወስ የሚጠቀሙበት ፅሑፍ፣ ለፈውስ የሚያስከፍሉት የክፍያ መጠን፣ የሚፈወሱበት ሀይል ምንጭ (በእርኩስ መንፈስ፣ በፈጣሪ እገዛ፣ በመፅሀፍ ወይም በመድሐኒት)፣ ለፈውስ በሚሰጡት የመድሐኒት አይነት፣ የፈውስ ስርዓተ ከዋኔ (ritual practice) እና ሌሎች ናቸው። በዚህ መስፈርት መሰረት እነዚህ ባለሙያዎች (curing, healing and spiritual mediation experts) በተለያዩ ስሞች ይጠራሉ።

በተጠኚ ማኅበረሰቦችም Aspen ባስቀመጧቸው "የእርኩሳን መናፍስት" ፈዋሾች የመለያ መስፈርቶች መሰረት በአካባቢው የሚጠቀሱ የተለያዩ ሰዎች አሉ። በማኅበረሰቡ ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን እውቀት ያላቸው ሰዎች ደብተራ ወይም መርጌታ ሲባሉ ማኅበረሰባዊ ደረጃቸው ከፍ ያለ ነው። ቡዳንና ብዙ እርኩሳን መናፍስትን የመፈወስ እውቀትን ከቤተክርስቲያን እውቀት

እንዳገኙ ይታመናል። ለምሳሌ ያህል መርጌታ አዳነ አሰፋ ቡዳ፣ እርኩስ መንፈስንና ሌሎች ደዌዎችን የመፈወስ ችሎታን ከቤተክርስቲያን እምነት ጋር ተያይዞ በተቋም ደረጃ ገብተው በመማር ያገኙት እንደሆነ ይናገራሉ። ይህንን እውቀት በመጠቀምም በራሳቸው ቡዳን ጨምሮ ለሌሎች ህመሞች የሚሆኑ መድሐኒቶችን በመቀመም በአነስተኛ ክፍያ በቤታቸው የፈውስ አገልግሎት እንደሚሰጡ ይገልፃሉ።

የቡዳ ጥቃት የፈውስ መንገድን ከሌላ ወገን በሚገኝ እውቀት ትምህርትና ልምድ ያገኙት እንደሆነ የሚታመኑ ሰዎች ደግሞ የቡዳ መድሐኒት አዋቂ ወይም ቡዳ አስለፍላፊ በመባል ይጠራሉ። እነዚህ ሰዎች የፈውስ ሀይል ምንጭ በአብዛኛው በተግባራዊ ልምምድ የሚገኝ እውቀት ነው። በዚህም የቡዳ ጥቃት መከላከያ መድሐኒቶችን ከሌላ ወገን በመግዛት የፈውስ ስርዓቱን ከሌላ ወገን በመማርና በመለማመድ የሚያገኙት ነው። ለምሳሌ ያህል አቶ ኡመር ኢብራሂም[56] በቡዳ የተበሉ ሰዎችን ከመድሐኒት አዋቂ ሰዎች በመግዛት በማጠጣትና በማሽተት የሚፈወስ መሆኑን ይህንን እውቀትም ያገኙት በልምምድ እንደሆነ ይገልፃሉ (24/08/03 ዓ.ም፣ ቃለ መጠይቅ)። አቶ ወርቁ ታደሰ[57] እንዲሁ የቡዳ መድሐኒት ከሌላ ሰው በመግዛት የፈውስ ስርዓት ያከናውናሉ። የዘውትን መድሐኒቱ በመጠቀም የመፈወስ እውቀትንም "ከአንድ አባት የተማርኩት" ነው ይላሉ (26/08/03 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)።

እነዚህ ግለሰቦች በማገበረሰብ ዘንድ ከቡዳ በተጨማሪ ሌሎች ደዌዎችና በሽታዎችን ይፈውሳሉ ተብሎ ይታመናል። ራሳቸውንም ባህላዊ መድሐኒት አዋቂ በማለት ይጠራሉ። በመንግስትም የባህላዊ መድሐኒት አዋቂነት ፈቃድ ተሰጥቷቸው እንደሚሰሩ አቶ ወርቁ ታደሰ ካሳዩኝ የንግድ ፈቃድ ወረቀት ለመረዳት ችያለሁ። በአካባቢው ያሉ የባህል መድሐኒት አዋቂዎች ሁሉም የቡዳ ጥቃትን አይፈውሱም።

ከላይ ከቀረቡት የቡዳ ጥቃት ፈዋሾች በተለየ መልኩ ሰይጣናዊ ሀይል በመጠቀም የቡዳ ጥቃትን የሚለዩና የሚፈውሱ አሉ። የእነዚህ ግለሰቦች የሀይል ምንጭም ከሰይጣን ጋር በሚኖር ወዳጅነት የተገኘ ሚስጥራዊ ስጦታ ተደርጎ ይታመናል። አንዳንዶም የአስማታዊ ሀይል ባለቤት እንደሆኑ ይጠረጠራሉ። ለምሳሌ ያህል አቶ ታረቀኝ አንድ ሰው በእርኩስ መንፈስ ተይዞ ወደ እርሳቸው በመጣ ጊዜ መንፈሱ ዛር፣ ጋኔል ወይም ቡዳ መሆኑን የመለየትና የመፈወስ እንዲሁም ጋኔልን

[56] አቶ ኡመር ኢብራሂም የጣቁሳ ወረዳ የደልጊ ከተማ ነዋሪና በንግድ ሙያ የሚተዳደሩ ሲሆኑ በልምድና ከሌሎች ሰዎች መድሃኒት በመግዛት በቡዳ የተበሉ ሰዎችን ይፈውሳሉ። እድሜያቸውም 58 ነው።
[57] አቶ ወርቁ ታደሰ የጣቁሳ ወረዳ የደልጊ ከተማ ተወልደው ያደጉ፣ የቄስ ትምህርት የተማሩና ለ25 አመታት በባህል ህክምና ሲያገለግሉ የኖሩ ናቸው። እስካሁም የባህል ህክምና ፈቃድ በማውጣት ለተለያዩ በሽታዎች፣ ደዌዎችን እንዲሁም የቡዳ ጥቃትን በመለየት ባህላዊ መድሃኒቶችን የሚሰጡና የሚፈውሱ ናቸው።

የማናገር ሀይል ያላቸው መሆኑን አብነቶችን በመጥቀስ ያስረዳሉ። በተጠኚ ማኅበረሰቦችም አቶ ታረቀኝንና የዚህ ሀይል ባለቤት የሆኑ ሌሎች ሰዎችን "ቡዳ አስለፍላፊ" በማለት ይጠሯቸዋል።[58] እነዚህ ሀይል በመጠቀም የቡዳውን መንፈስ በማናገርና በማስለፍለፍ ይፈውሳሉ ተብሎም ይታመናል።

### 4.1.8.1.2. ልማዳዊ የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓተ ክዋኔ

በማኅበረሰቡ በልማዳዊ መንገድ የቡዳ ጥቃትን የሚፈውሱ ሰዎች ተለይተው የሚታወቁና እንደ ባለሙያ የሚቆጠሩ ቡዳ አስለፍላፊና የቡዳ መድሃኒት አዋቂ እየተባሉ የሚጠሩ ግለሰቦች ናቸው። እነዚህ ግለሰቦች የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓትን በአብዛኛው በቤታቸው አልፎ አልፎ ደግሞ በተጠቂው ቤት በመገኘት የሚፈጽሙ ሲሆን የፈውስ ዘዴውም የተለያዩ ስርዓተ ክዋኔዎች አሉት። እነዚህ ስርዓቶችም መለየት፣ማስለፍለፍ፣ መመለስ ናቸው። በመስክ ቆይታዬ አቶ ወርቁ ታደሰ በልማዳዊ መንገድ የቡዳ ጥቃት ሲፈውሱ በተመለከትኩትና ከመረጃ አቀባዮች ባገኘሁት መረጃ መሰረት ልማዳዊው የፈውስ ስርዓተ ክዋኔ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በባህላዊ (ልማዳዊ) የፈውስ ዘዴ አንድ ሰው የቡዳ ጥቃት እንደደረሰበት ከተለየ በኋላ የመጀመሪያው የፈውስ ስርዓት ጥቃት ያደረሰበትን (የበላውን) ሰው መለየት ነው። በማኅበረሰቡ የእምነት ስርዓት ውስጥ በቡዳ የተጠቃ ሰውን ለማስለፍለፍ፣ ልቡናውን ለመመለስና ከህመሙ ለመፈወስ የጥቃት አድራሹ (የቡዳው) ማንነት ተለይቶ መታወቅ የግድ ነው።

በቡዳ የተበላን ሰው በመኪና ጎማ ጭስ ማጠን፣ቢጋስ ብረት መተኮስና ማስፈራራት፣መግረፍና መስደብ የቡዳውን (ጥቃት አድራሹን) ማንነት ለመለየት የሚያግዙ የፈውስ ስርዓቱ ተግባራት ናቸው።

የመጀመሪያው የመለያ ዘዴ የመኪና ጎማ በማጨስ ማንነትን እስኪናገር ድረስ ማጠንና ማጨናነቅ ነው። በቡዳ የተበላን ሰው በመኪና ጎማ ጭስ በማጠን እስጨንቆ የበላውን ሰው ማንነት ለማወቅ ከተበላው ሰው ጋር የሥጋ ዝምድና የሌላቸው ቢያንስ ሶስት ሰዎች እንዲይዙት ይደረጋል። ይህም የሚሆነው ቡዳ ከዘመዱ ፊት ራሱን አያጋልጥም፣ አይለፈልፍም ተብሎ ስለሚታመን ነው። በዚህ መሰረት በቡዳ የተበላውን ሰው ቢጋቢ ወይም በቆዳ በመሸፈን በጎማው ጭስ እንዲታፈን ይደረጋል። በዚህ ጊዜም የያዙትን ሰዎች ለመምታትና ነጥቆ ለመሮጥ

---

[58] በዚህ መንገድ የቡዳ ጥቃትን የሚፈውሱ ሰዎች በቀዳሚነት ሂደት 'ቡዳ አስገኝ' ይባሉ እንደነበር Young (1970) በበጌምድር (በጎንደር) ማኅበረሰብ የሀገረሰባዊ መድሃኒት እምነት አስመልክቶ ባካሄዱት ጥናት ይገልጻሉ።

ይሞክራል፡፡ በጭሱ ብዛት መጮህ፣ የያዙትን ሰዎች መምታት ሲጀምርና ለማምለጥ ሲሞክር በቡዳ አስለፍላፊው "አንተ ቡዳ ማን ነህ? ተናገር!" እያለ ይጠይቀዋል፡፡ ማንነቱን ከተናገረም በጭስ መታጠኑም ሆነ መጨናነቁ እንደሚቀርለት ይነገረዋል፡፡

ሌላው የመለያ ዘዴ በቡዳ የተበላው ሰው በጋለ ብረት (በአብዛኛው ማረሻ) ለመተኮስ በመሞከር ማስፈራራት ነው፡፡ በቡዳ የተበላው ሰው በጉማ ጭስ ታጥኖ የበላውን ሰው ለመናገር ፈቃደኛ ሳልሆን ጊዜ በእጣት የጋለ ብረት ወደ ተበላው ሰው ግንባር በማስጠጋት የበላውን ሰው እንዲናገር ፈቃዱ ያስፈራራዋል፡፡ በዚህ ጊዜ በቡዳ የተበላው ሰው በጋለ ብረት ሳለመተኮስ የበላውን ሰው ማንነት ይናገራል ተብሎ ይታመናል፡፡[59]

በማኅበረሰብ ዘንድ በመድሀኒትና በማስለፍለፍ የቡዳ ጥቃት የሚፈውሱ እና ከፍተኛ ከበሬታና ታዋቂነት ያላቸው አንዳንድ ግለሰቦች ደግሞ በቡዳ የተበላውን ሰው ያለ ሰው እርዳታ የበላውን ሰው ማንነት በማፍጠጥ፣በመሳደብና በመግረፍ እንዲናገር ያደርጋሉ፡፡ በተለይ ከሰይጣን ጋር ወዳጅነት ወይም አንዳች አስማታዊ ሀይል አላቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ቡዳ አስለፍላፊዎች አንዳንድ ጊዜ ያለ ስድብና ግርፋት በቀላሉ የበላውን ሰው እንዲናገር የማድረግ ብቃት አላቸው ይባላል፡፡ ለምሳሌ አቶ ታረቀኝ (04/09/03 ዓ.ም፣ ቃለመጠይቅ) የቡዳ ጥቃት በሚፈውሱበት ጊዜ አንዳንዴ በቡዳ የተበላ ሰው " ገና ሲመጣ ወው ነው የሚል፡፡ አይኔን ሲያይ ፊቱን እንደ ሙሽራ ይሸፍናል፡፡ ያፍራል፡፡ "አትውሰደኝ! እረ የነፍስ ያለህ! አታጋልጠኝ! አታጋልጠኝ! እረ ልንገርህ ቆይ ልንገርህ ይላል፡፡ ሳልነካህ ምንም ሳልልህ ንገረኝ ስለው ጭርስርስ አድርጎ እስከነ ምናምኑ ይነግረኛል፡፡" በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች የቡዳው ማንነት (ሙሉ ስምና አድራሻ) ከታወቀ በኋላ ቀጣዩ የፈውስ ስርዓት ማስለፍለፍ ወይም መለፍለፍ ነው፡፡

በማኅበረሰብ የሌማዳዊ (የባህላዊ) የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ውስጥ መለፍለፍ ወይም ማስለፍለፍ ሲባል በቡዳ የተበላው ሰው በበላው ሰው አንደበት የበላውን ሰው በተመለከተ በቡዳ አስለፍላፊው ወይም በቡዳ መድሃኒት አዋቂው አማካይነት ለሚጠየቀው ማንኛውም ነገር ምላሽ መስጠትን ይመለከታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የበላውን ሰው በመሆን የተለያዩ ተግባራትን ይከናወናል ተብሎ ይታመናል፡፡

---

[59] በተለይ ማህበረሰቡ ዘንድ በቡዳ የተበላን ሰው በማስፈራራት ሲመሰኪ ከማ ጭስ በማጨስ፣ ግንባሩን በጋለ ብረት በመተኮስ የበላውን ሰው ማወቅ ይቻላል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህም የሚሆነው የተበላው ሰው ግንባር በጋለ ብረት በሚተኮስበት ጊዜ የበላው በላው ሰው ላይ ይታያል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህም ልማድ በአሁኑ ሰዓት በመጥፋት ላይ ይገኛል፡፡

በሰሜን ጐንደር ማኅበረሰብ የቡዳ እምነት ስርዓት ውስጥ አንድ ሰው የቡዳ ጥቃት ሲደርስበት (በቡዳ ሲበላ) ጥቃት ያደረሰበትን (የበላውን) ሰው ባህሪ፣ አንደበትና ተግባር ይወርሳል ተብሎ ይታመናል። በዚህም በቡዳ የተበላው ሰው ስጋና ደም የቡዳው መንፈስ ማዳሪያ ይሆናል። ከመጠቃቱ በፊት የነበረው የሰውየው ሰብዕና ወይም ማንነት በቡዳው ይነጠቃል በሚል ይታመናል። በቡዳ የተበላ ሰው በበላው ሰው አንደበትን፣ አስተሳሰብን መላ ራስን መነጠቅ በማኅበረሰቡ ልማድ "መሰወር" ይባላል። የበላው ማንነት ተለይቶ ከታወቀበት እስከ የፈውስ ስርዓቱ ተጠናቆ ለበሽታው እስከሚመለስበት ድረስ ቡዳ የተበላው ሰው የቀደመ ማንነት (ድምፅ፣ ስምና ተግባር) ተሰውሮ ቡዳ በሚባለው ሰው ድምፅ፣ስምና ተግባር ይተካል። የጥቃቱ ሰለባም ከአሁን በፊት ያልነበረውን ሀይልና ጉልበት ያገኛል። ሀይሉም ሆነ ጉልበቱ የተበላው ሰው ሳይሆን ከቡዳው ያገኘው ነው። ከዚህ በተጨማሪ በፈውስ ስርዓቱ ላይ የሚከናወኑ እንደ መነሳትና መውደቅ፣ግርፋትና ለሎች አካላዊ ጉዳቶች በበላው ሰው ላይ እንደሚፈፀሙ ይታመናል።

በዚህ መሰረት ተለይቶ የታወቀውንና በተባለው ሰው ላይ የሰረፀውን መንፈስ ማስለፍለፍ አንዱ የፈውስ ስርዓት አካል ነው። የማስለፍለፍ ስርዓቱም የራሱ የሆነ ስርዓትና ፋይዳ አለው።

በቡዳ የተበላው ሰው በቡዳው አንደበት ሆኖ ማስለፍለፍ እንደማዋረድ ይቆጠራል። በዚህም የቡዳው መንፈስ በአዋቂው ፈቃደኛ ሆኖ ላይለፈልፍ ይችላል። በዚህም እንደ ቡዳ መድሃኒት አዋቂው ወይም አስለፍላፊው የፈውስ ችሎታ የተለያዩ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። ለምሣሌ ያህል አቶ ታረቀኝ አስቸጋሪ የሆነ ቡዳ በነጠማቸው ጊዜ መድሀኒት በማጠጣት ሲያስለፈልፍ አቶ ወርቁ ታደሰ ደግሞ መድሃኒት በማሽተት እና በማስፈራራት ሲያስለፈልፉ ተመልክቻለሁ።

ማንኛውም በቡዳ የተበላው ሰው የሚለፈልፈውና የሚጠየቀው ጥያቄ በአብዛኛው ቀድሞ የሚታወቅና የተቀመረ እንደሆነ አቶ ታረቀኝ ይገልፃሉ። ይህም "አንተ ማን ነህ እለዋለሁ ጋኔል እንደሆነ 'ጋኔል ነኝ' ይላል ቡዳ እንደሆነ 'ቡዳ ነኝ' ይላል። ማንህ ስለው 'እገሌ ነኝ' ይላል። ምን ሰዓት የት በላ አገኘኻትን ስለው 'ውሃ ስትሄድ'፣ 'ገበያ ስትሄድ' ወይ ደግሞ 'ከመንገድ አገኘኋት' እና 'በላኋት' ይላል" (04/09/03 ዓ.ም፣ ቃለ መጠይቅ)። እንዲሁም እንዲለፈልፍ መድሃኒት ሲሉበት በቡዳው ወይም በሰውየው አንደበት ማንኛውም ወሬ ያወራሉ "ልክ አንተ እንደማወራህ የፈለኩትን ያወራል እኔ ሳልጠይቀው አስቀድሞ ራሱ ያወራኛል። መድሃኒት ቀምሷል። አስበርታል። እቅሉን አጥፍታል" (04/09/03 ዓ.ም፣ ቃለመጠይቅ)። ይላሉ።

በቡዳ የተበላ ሰው የሚለፈልፍባቸው የተለመዱ ምክንያቶች አሉ። እነሱም ጥቃት አድራሹ (ቡዳው) ማንነት በጥልቀት ለማወቅ፣ ስለ ጥቃቱ ጠቅላላ መረጃ ለማግኘት ልቦናው የመመለስ መንፈሱን ማርከሻ ምንነት ለመለየት የሚሉት ናቸው።

የቡዳውን ማንነት ለማወቅ ለሚጠየቁት ጥያቄዎች በቡዳ የተበላው ሰው የሚሰጠው ምላሽ በአብዛኛው የበላው ሰው በመሆን ሙሉ ስም፣ ስራ (ሙያ)፣ የዘር ሐረግ፣ ያደገበትንና የተወለደበትን አድራሻ ነው። እንዲሁም ጥቃት የደረሰበትን ሰው እንዴት እንዳገኘው፣ ለምን እንደበላው፣ የትና መቼ እንደበላው፣ ቡዳነትን እንዴት እንዳገኘው፣ በትምህርት ከሆነ ከነማን ጋር እንደተማረ፣ እስካሁን ጉዳት ያደረሰባቸው ሰዎች፣ እንስሳትና ሌሎች ነገሮችን በዝርዝር እንዲናገርና እንዲተርክ ይደረጋል። በተለይ በቡዳ የተበላው ሰው በበላው ሰው አንደበት ሲለፈልፍ እስካሁን ቡዳው ማንን በልቶ እንደገደለ እንዲሁም ወደፊት ለመብላት ያሰባቸውን ወይም ያጠመዳቸውን ሰዎች በተመለከተ መረጃ ይሰጣል። በማኅበረሰቡ የቡዳ እምነት መሰረት 'ማጥመድ' ማለት ቡዳው ቀጣይ ሊበላው ያሰበው ሰው ማለት ሲሆን ሲለፈልፍም እገሌን አጥምጀዋለሁ[30] ይላል።

በመጨረሻም የቡዳው መንፈስ በቡዳ ከተበላው ሰው ለመልቀቅ ምልክቱ ወይም ማርከሻው ምን እንደሆነ ከተናገረና ምንነቱ ከታወቀ በኋላ የሚከተለው የፈውስ ስርዓት "መመለስ" ይባላል። 'መመለስ' በቡዳ የተበላውን ሰው ከቡዳው መንፈስ ለማላቀቅ የሚደረግ ስርዓት ነው። ልቦናን የመመለሻ ዘዴዎችም 'ምስ' እና ቃል ማስገባት ናቸው።

በማኅበረሰቡ ምስ የሚባሉት የአህያ ፋንድያ፣ የዶሮ ኩስ፣ አመድ፣ የጠላና የቡና አተላ የመሳሰሉ ነገሮችን መመገብና መጠጣት እንዲሁም አመድ ላይ መንከባለል፣ ዘሎ መውደቅ፣ ድምጽን ከፍ አድርጎ መጮህና ሌሎች የተለያዩ ድርጊቶችን ማከናወን ናቸው። ይህ የሚሆነው ቡዳ ተበላ የሚባለው ሰው በቡዳው መንፈስ ውስጥ በመሆን በበላው አንደበት ሆኖ ምሱ ምን እንደሆነና ምን ቢያደርግ ሊለቅ እንደሚችል በሚጠየቅ ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ከላይ ከተጠቀሱት ያልተለመዱ ነገሮችና ድርጊቶች መካከል አንዱን ይናገራል። የቡዳ አስለፍላፊውም በቡዳ ተበላ የተባለው ሰው የተናገረውን ምስ ሳያይ በቅርብ ርቀት በመደበቅ ካለበት ፈልጎ እንዲበላው ያደርጋል። በቡዳ የተበላው ሰውም ፈልጎ ይበላል፣ ድርጊት ከሆነም ያከናውናል። ከጥቂት ደቂቃ በኋላም ልቦናው ይመለስላል ተብሎ ይታመናል።

[30] ይህም ባበላው ሰው ላይ ጥቃት ሲያደርስ በተደጋጋሚ እየመጣ ወደሌላ እንደሚሄድ ነው።

በማኅበረሰቡ "ምስ" በቡዳ የተጠቃን ሰው ልቦናን የመመለሻ ዘዴ ሲሆን ከዚህ በትይዩ ደግሞ በቡዳ በተበላው ሰው ላይ ያለውን መንፈስ ማርከሻ መንገድ ነው። ይህ የሚሆነውም የቡዳ ጥቃት ፈዋሹ (ቡዳ አስለፍላፊው) የቡዳ መንፈስን ለማርከስ የሰው ልጅ በንቁ ልቦናው ሊመገባቸው የማይችሉ ምግቦችን እንዲመገቡ እና ያልተለመዱ ድርጊቶችና ተግባራት እንዲያከናውኑ በማድረግ ነው። በሌማዳዊ የፈውስ ስርዓት ምልከታዬ ወቅትም በደልጊ ከተማ (ጣቁሳ ወረዳ) እንዲት በቡዳ ተበላች የተባለች ሴት የአህያ ፋንድያ ስተባላ ተመልክቻለሁ። በማኅበረሰቡ እምነት ይህን ምስ የሚበላው ወይም የሚያከናውነው ተጠቂው ሳይሆን በተጠቂው ላይ ያደረው መንፈስ ነው።

በአጠቃላይ ቡዳ ተበላ የተባለውን ሰው ልቦና የመመለሻና ጥቃቱን የማርከሻ መንገድ "ምስ" ሲሆን ምሱን ከበላና ካከናወነ በኋላ ልቦናው ይመለሳል ተብሎ ይታመናል። ልቦናው ከተመለሰ በኋላ ደግሞ የቡዳ መድሃኒት አዋቂው (አስለፍላፊው) ለዘለቄታዊ ፈውስ የሚያግዝ የቡዳ መድሃኒት ይሰጠዋል።[61]

## 4.1.8.2. ሐይማኖታዊ የቡዳ ጥቃት ፈዋሾችና የፈውስ ስርዓተ ክዋኔ

### 4.1.8.2.1. ሐይማኖታዊ የቡዳ ጥቃት ፈዋሾች

በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ ቡዳ የሰይጣን ተግባር ተደርጎ ይታመናል። ይህንን የሰይጣን ተግባር መከላከልና ከጥቃቱም መዳን የሚቻለው ከሃይማኖታዊ ፀሎቶች በተጨማሪ በፀበል ነው። በማኅበረሰቡ ዘንድ ፀበል ሌላው የቡዳ ጥቃት የመፈወሻ ሃይማኖታዊ ተቋም ነው። በዚህ ተቋምም የቡዳ ጥቃት ሰለባዎች እና ጥቃት አድራሾች (ቡዳ የሚባሉ ሰዎች) ከቡዳ መንፈስ ይፈወሳሉ ተብሎ ይታመናል። ይህ ሃይማኖታዊ ስርዓት መፀበል[62] ሲባል ስርዓቱን የሚመሩት ደግሞ ፀበል አጥማቂዎች በሚል ይጠራሉ።

በማኅበረሰቡ እሳቤት ዘንድ ፀበል አጥማቂዎች የፈውስ ሀይላቸው ምንጭ መለኮታዊ እንደሆነ ይታመናል። የዚህ መለኮታዊ ሀይል ባለቤት ለመሆን የተለየ ሃይማኖታዊ እውቀት የሚጠይቅ ሳይሆን በእግዚአብሔር በመመረጥ የሚገኝ ፀጋ መሆኑን አባ ፍስሃ ይገልፃሉ። በሰሜን ጎንደር አካባቢ ይህ ሀይል አላቸው ተብለው በሚታመኑ ሰዎች የሚመሩ በርካታ የፀበል ቦታዎች አሉ።

---

[61] ምናልባትም ሕሙና ጠንቋ የሆኑ "ምስ"ን በቡዳ የተጠቃው ሰውን ጤና እንዳያውሉ ፈዋሹ ምሱን እንዳይውጠው ከዋጠውም መልሶ እንዲተፋው ያደርጋሉ።

[62] ከመስክ ቆይታዬ እንዳስተዋልኩት "መፀበል" ማለት በፀበል ቦታ የሚከናወኑ መንፈሳዊ ድርጊቶችን ማለትም ፀሎት፣ ስግደት፣ ፆም፣ ፀበል መጠመቅ፣ መቁጠሪያና መስቀል የመሳለሙትን የሚያጠቃልል ነው።

ማኅበረሰቡ በነዚህ ፀበል ቦታዎች በመገኘት ከቡዳ ጥቃት የሚፈወሱ መሆኑን ያምናሉ። ይህን ፈውስ ደግሞ የሃይማኖታቸው የትውፊት መሰረት ወይም ትሩፋት አድርገው ይቆጥሩታል። ፀበል አጥማቂዎች የፈውስ ስርዓቱን የሚያከናውኑት አንድም በአምላክ አንድም በመላዕክትና ፃድቃን አማላጅ ስለመና መሆኑን ይገልፃሉ። በፀበል አማካይነት አጥማቂዎች የሚያከናዉኑትን የፈውስ ስርዓት በፀበል ቦታ ተገኝቼ ለመመልከት ችያለሁ።

የፀበል ቦታ የፈውስ ስርዓት ሂደትና ክዋኔ ምልከታ ያደረኩት በደንቢያ ወረዳ በቆላድባ ከተማ በቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ነው። በዚህ ቤተክርስቲያን ቡዳን ጨምሮ ሌሎች አጋንታዊ መንፈሶች (ጋኔል፣ ዛር፣ ቆሌ፣ መተት፣ ድግምት ወዘተ) እና ጥቃቶች እንዲሁም በሽታዎችና ደዌዎች በአባ ፍሰሓ አጥማቂነት ከሀያ ዓመት በላይ የፈውስ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ እንደሆነ የማኅበረሰቡ አባላት ይገልፃሉ። በአሁኑ ሰዓትም በቤተክርስቲያኑ በአባ ፍስሃ አማካይነት በፀበል በቡዳ ጥቃት የደረሰባቸውን፣ አጋንታዊ መንፈስ ያረፈባቸውንና ቡዳ የሚባሉ ሰዎችን ከቡዳ ጥቃት የመፈወስና አርኩስ መንፈስን የማስወጣት ስርዓት ይፈፀማል። የዚህ የፈውስ ስርዓት ሂደትና ክዋኔም የሚከተለው ነው።

### 4.1.8.2.2. ሐይማኖታዊ የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ክዋኔ

የፀበል የፈውስ ስርዓት ክዋኔ የሚፈፀመው በቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ሲሆን ከጠዋቱ አንድ ሰአት እስከ ረፋዱ አምስት ሰዓት ይከናወናል። በፆም (አርብና ረቡዕ እና ሌሎች አፅዋማት) እና በበአላት ቀን እስከ ሰባት ሰዓት ሊዘልቅ ይችላል። ቆላድባ ከተማ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚሰጠው የፀበል ፈውስ ላይ በልማዳዊ (ባህላዊ) የፈውስ ዘዴ ለውጥ ያላገኙ የቡዳ እና የሌሎች አጋንታዊ ጥቃት ሰለባዎች፣ የቡዳ ጥቃት ምልክት የታየባቸው፣ በቡዳነት የሚጠረጠሩ እና በሌሎች በሽታዎች የታመሙ ሰዎች ይሳተፋሉ።

ስርዓቱን በዋናነት የፀበል አጥማቂው በተጨማሪም ዲያቆናት ይመሩታል። በሁሉም የእድሜ ክልል ያሉ እና የየትኛውም ሃይማኖት (እምነት) ተከታይ የሆነ እንዲሁም ፀበል ማንኛውንም ችግርና ህመም የመፍታትና የመፈወስ ሃይል አለው ብሎ የሚያምን ማንኛውም ሰው በፀበሉ ፈውስ ማግኘት የሚችል መሆኑን አጥማቂው ይገልጻሉ።

ይህ የፀበል የፈውስ ስርዓት ተለማማጅነትና ተከታታይነት ያላቸው እንደ ፀሎት፣ መርጨት እና አጋንታዊ መንፈስን ማስወጣት ወይም ልክፍን መመለስ የተሰኙ የሚከተሉት ሂደቶች አሉት።

የመጀመሪያው የሃይማኖታዊ የቡዳ ጥቃት የፈውስ ዘዴ ስርአትና ሂደት ፀሎት ነው። ይህንን ለማከናወን ንጋት አስራ ሁለት ሰአት ጀምሮ ሁሉም ተጠማቂዎች የተለያየ መጠን ያለው ውሃ በጀሪካ በመያዝ በፀበል ቦታው ይገኛሉ። በውሃ የተሞላውን ጀሪካን ፀሎት በሚደረገበት አዳራሽ ያስቀምጡታል። ተጠማቂዎችም በአዳራሹ ውስጥ በመቀመጥ በዲያቆናት በሚደረገው ፀሎት ተሳታፊ ለመሆን ዝግጁ ይሆናሉ። በአዳራሹ ውስጥ የተለያዩ የቅዱሳን፣ የቅዱሳትና የኢየሱስ ክርስቶስ ምስሎች የያዙ ስዕላት ተሰቅለው ይታያሉ። አንድ ሰአት አካባቢ ዲያቆናት ከተጠማቂዎች እና በጀሪካን ውስጥ ባለው ውሃ ላይ ፀሎት ማድረግ ይጀምራሉ። ፀሎቱ ከሁለት እስከ ሦስት ሰአት የሚፈጅ ሲሆን የተለያዩ የፀሎት አይነቶች ይፀለያሉ። እንዲሁም የተለያዩ የቅዱሳን፣ የቅዱሳት፣ የሰማዕታት፣ የጻድቃን ገድላት እንዲሁም ኢየሱስና ሐዋሪያቱ የፈፀሟቸው ተአምራት ይነበባሉ፡፡ ፀበል አጥማቂውና ተጠማቂዎቹም በፀሎቱ ይካፈላሉ፣ ተአምራትንና ገድላትን ያዳምጣሉ፡፡

በዲያቆናቱ የሚፀለዩ ፀሎቶችና የሚነበቡት ተዓምራትና ገድላት የቡዳ ጥቃትን ይፈውሳሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ መንፈሳዊ ክንውን ወቅት መንፈሱ ይሰቃያል ይባላል፡፡ እንደ ሀይማኖቱ የእምነት ትውፊት የቅዱሳን፣ የማርያም፣ የስላሴ እና የሌሎች መላዕክት ስም በተጠራ እና ያከናወኗቸው ተአምራትና ገድላት በተነገሩ ጊዜ በሰው ላይ ያሉ የቡዳም ሆኑ ሌሎች ኢጋንታዊ መንፈሶች ይጨነቃሉ፣ ይሰቃያሉ፣ ይቃጠላሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ ጊዜም መንፈሶቹ ካደሩበት ሰው ላይ ለመልቀቅ ይዘጋጃሉ ይባላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዲያቆናት አማካይነት በሚቀርበው ፀሎትና በሚነበበው ተአምርና ገድል አማካይነት በአዳራሹ ውስጥ ካሉ ተጠማቂዎችና ካመጡት ውሃ ላይ የቅዱሳን፣ የቅዱሳት፣ የመላእክት፣ የፈጣሪ በረከት፣ ሃይልና መንፈስ ያርፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተለይ እየተፀለየበትና እየተነበበት ያለው ውሃ የተባረከና የተቀደሰ እንዲሁም የቅዱሳን፣ የመላእክትና የፈጣሪ ሃይል ያለበት ይሆናል፡፡ በዚህም ውሃነቱ ይቀርና የተቀደሰ ውሃ ወይም ፀበል ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ በፀሎት አማካይነት ወደ ተቀደሰ ውሃነት የተቀየረው ፀበልም በሰው ላይ ያደረን ማንኛውንም እርኩስ መንፈስ ያባርራል፣ ያቃጥላል፣ የቡዳና ሌሎች ህመሞችንና ችግሮችን ይፈውሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

ፀሎቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሁሉም ተጠማቂዎች በጀሪካን የሞላውን ፀበል በመያዝ ፀበል ወደ ሚረጭበት ቦታ ይወስዱታል፡፡ ሁሉም ተጠማቂዎች የያዙትን ፀበል በፀበል ቦታው ካለው በርሜል ውስጥ በመጨመር እርቃናቸውን ይቀመጣሉ፡፡ ከፀሎት ስርዓቱ ቀጥሎ ያለው

ሐይማኖታዊ የፀበል ላይ የፈውስ ስርዓት ሂደት ፀበል አጥማቂው የሚያከናውኑት ተጠማቂዎችን ፀበል የመርጭት ስርዓት ነው፡፡

ፀበል አጥማቂው በበትረ መስቀላቸው መስቀለኛ በማድረግ ለመፀበል የተቀመጡትን ሰዎች ይባርካሉ፡፡ ቀጥሎ በፀበል ከሞላው በርሜል ውስጥ በመጨለፍ ፀበል መርጨት ይጀምራሉ፡፡ ፀበሉ በተጠማቂዎች ሰውነት ባረፈ ጊዜ መጮህ፣ መወራጨት፣ መውደቅና መነሳት ይጀምራሉ፡፡ በፀበል የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ጊዜ ቡዳ የተበላው ሆነ ቡዳ የሚበላው ሰው ፀበሉ ሰውነት ባረፈ ጊዜ ተጠቂዎቹ ራሳቸውን በመሳት ወይም ማንነታቸው ተሰውሮ ሲጋኙ ደግሞ የቡዳው መንፈስ ማደሪያ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

በፀበል ቦታው የሚከናወነው ማንኛውም ድርጊትና ንግግር የተጠቂው ሳይሆን በተጠቂው ላይ ያደረው መንፈስ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ በዚህም ይህንን መንፈስ ፀበል አጥማቂው ማናገር (ማስለፍለፍ) ይጀምራሉ፡፡ ፀበል አጥማቂውም ፀበሉን በተጠቂው የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቹ ላይ እየረጩ የቅዱሳንና የመላዕክትን ስም እየጠሩ በተጠቂው ላይ ያደረውን የቡዳ መንፈስ ጥያቄዎች እየሰጡ ያስለፈልፉታል፡፡ ይህ የማስለፍለፍ ስርዓትም ከልማዳዊው የፈውስ ስርዓት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ልማዳዊ (ባህላዊው) የቡዳ ጥቃት ፈዋሽ በማስፈራራት፣ በመገረፍ፣ በመስደብና፣ መድሐኒት በማጠጣት ያስለፈልፋል፡፡

በፀበል የፈውስ ስርዓትም ፀበል አጥማቂው ፀበል በመርጨት፣ መንፈሱን በማዋረድ፣ የመላዕክትንና የቅዱሳን ስም በመጥራት በግዳታ እንዲለፈልፍ ያደርጉታል፡፡ በፀበል ላይ በሚደረገው የማስለፍለፍ ስርዓትም እንደልማዳዊ የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ሁሉ የቡዳ ጥቃት አድራሹን ማንነት ጥቃት ያደረሰበትን ቦታና ጊዜ፣ የቡዳነቱን ምንጭ የተመለከቱ ጥያቄዎች ቡዳ በበላው ሰው ላይ ላለው ወይም ላደረው የቡዳው መንፈስ ይቀርባሉ፡፡ መንፈስም በተጠየቀው መሰረት አንድ በአንድ እንደሚከተለው ይመልሳል፡፡

አጥማቂ፡- ማን ነህ?
መንፈስ፡- አዴ፡፡
አጥማቂ፡- ለምንድነው ነው የተመረከው?
መንፈስ፡- ለሀብት ብዬ፡፡
አጥማቂ፡- ሀብት አለህ የለህም?
መንፈስ፡- አለኝ፡፡
አጥማቂ፡- የት ሀገር ነህ?
መንፈስ፡- ጀንዳ፡፡[33]

[33] ከአገሊያ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበር ስም ነው፡፡

አጥማቂ፡፡ ከምን አገኘቱህት ነው ከምን አገኘሁት?
መንፈስ፡፡ ገረዲት ነበርን፡፡ አውን ከዚህ [ቆላድባ] ሆና እኔ ገበያ ስሄድ አገኘኋት፡፡ እሪ ወደኔ ተቃጠለኩ፡፡
አጥማቂ፡ ለምንድን ፈለጋሃት [የበላሃት] የነበር ለምንህ ነው፡፡
መንፈስ፡፡ ለውሴ ነገር፡፡ ለእረምም፣ ለቤት ስራም፡፡
አጥማቂ፡ አውንስ?
መንፈስ፡፡ አውንማ ተዋርደኩ! ተዋረድኩ!
አጥማቂ፡ የት ሆነር ነው [ቡዳነትን] ያመጣኸው?
መንፈስ፡፡ ቋራ፡፡
አጥማቂ፡፡፡ ስማ እንጀ ከፀት ትበላለህ?
መንፈስ፡ እም፡፡

በማለት የተለያዩ ጥያቄዎች እያቀረቡ እንዲመለስ ያደርጋሉ፡፡ እንዳንዴ የቡዳው መንፈስ ከአሁን በፊት ጥቃት ስላደረሰባቸው ሰዎች እንዲሁም ቡዳ የሆነበትን መንገድ ከምልልስ ባለፈ ዘለግ ያለ ትረካ ያቀርባል፡፡ የዚህ ትረካ (ቡዳውን የማስለፍለፍ) አላማ ከፈውሱ በተጨማሪ በማኅበረሰቡ ዘንድ በተለይ በፀበል ቦታ ለተገኙ የእምነቱ ተከታዮች የቡዳ ጥቃት የሚያደርሰው ሰይጣን መሆኑን ለማመልከትና ሰይጣንን ለማዋረድ ነው፡፡ በመጨረሻም ፀበል አጥማቂው 'ትለቃለህ አትለቅም' የሚል ጥያቄ ያቀርቡለታል፡፡ መንፈሱም መቼ እንደሚለቅ ይናገራል፡፡ በፀበል የቡዳ ጥቃት ፈውስ ስርዓት ፈውሱ በአንድ ቀን ብቻ የሚጠናቀቅ አይደለም፡፡ የቡዳ ጥቃት ያደረሰው ሰው ማንነትና መንፈስ ከታወቀ በኋላ ለተወሰነ ጊዜ እየተፀበለ መንፈስ እንዲለቃይ ይደረጋል፡፡

ፀበል ከተረጨ እና የቡዳ መንፈስ ከለፈለፈ በኋላ ያለው ሃይማኖታዊ የቡዳ ጥቃት ስርዓትና ሂደት ከተጠቂው ላይ ያደረውን መንፈስ ማስወጣትና ልቦናን መመለስ ነው፡፡ ይህ ስርዓት የሚከናወነውም ፀበል የመርጨት ስርዓቱ እንደተጠናቀቀ የቡዳ መንፈስ ያደረባቸውን ሰዎች በመለየት ነው፡፡ ከተለዩ በኋላ መንፈስን ቃል በማስገባትና መሃላ በማስፈፀም፣ በመስቀል የተጠቂውን ጭንቅላት በመምታትና ፀበል በማጠጣት ይከናወናል፡፡ በመስቀል ጭንቅላቱን ሲመታና ፀበል ሲጠጣ መንፈስ ይቃጠላል፣ ይሰቃያል ተብሎ ይታመናል፡፡

በፀበል አጥማቂው አማካይነት የቡዳው መንፈስ ቃል መሃላ ከገባና፣ ፀበሉን ከጠጣ በኋላ የተጠቂው ልቦና ይመለሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚያም በቀደመ ስሙና ማንነቱ ይጠራል፣ የተለመደ ስራውን ያከናውናል፡፡

በፀበል የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ላይ ከቡዳ ጥቃት ሰለባዎች በተጨማሪ በማኅበረሰቡ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ቡድንታቸውን ለማስለቀቅ እንደተገኙ በቡዳ የሚጠረጠሩ ሰዎች

ገልፀውልኛል፡፡ በሙስከ ቆይታዬ ያገኘሁት በቡዳንት የተጠረጠር ግለሰብ ባላወቀበት መንገድ ከሚበላው ወይም ከሚጠጣው ላይ በድብቅ ቡዳ የማድርጊያ እፅ አድርገውበት ቡዳነት እንደሙጣበት ይገልፃል፡፡ ይህ እፅም አጋንንት እንደሆነ እንደሚያመንና በፀበል ለመፈወስ ፀበል ቦታ መገኘቱን ገልፆልኛል፡፡ እነዚህ በቡዳንት የሚጠረጠሩ ግለሠቦች ወደ ፀበል የሚመጡት በሽማግሌዎች አማካይነት በቡዳንት እየተጠረጠሩ መሆናቸው ከተነገራቸውና በፀበል እንዲያስለቅቁ ከተጠየቁ በኋላ ነው፡፡ ፀበል ቦታ ተገኝተው እጥማቂው እስከ ወሰኑት ቀን ድረስ ሲጠመቁ ከቆዩ በኋላ ከቡዳንት ነፃ መሆናቸውን የሚያመለክት ወረቀት በመያዝ ወደ ሀገራቸው ይሄዳሉ፡፡

### 4.1.8.3. የማኅበረሰባዊ እውቀት የቡዳ ጥቃት የፈውስ ዘዴ

በማኅበረሰቡ ልማዳዊ ዕምነት መሠረት ከባህላዊ (ልማዳዊ) የቡዳ ጥቃት ፈዋሾች በተጨማሪ ማንኛውም የማኅበረሰቡ አባል የሚፈጽማቸው የተለያዩ የቡዳ ጥቃት የመፈወሻ ዘዴዎች አሉ፡፡ እነዚህ ዘዴዎች ያለ ቡዳ ጥቃት ፈዋሽ እርዳታ በማንኛውም ሰው አማካይነት ሊፈጸሙ የሚችሉ ናቸው። የፈውስ ስርዓቱም በሁሉም ማኅበረሰብ የታወቀ ነው። እነዚህን የቡዳ ጥቃት መፈወሻ ዘዴዎች የማኅበረሰብ እውቀት በሚል እንደሚከተለው ቀርበዋል።

የመጀመሪያው ማኅበረሰባዊ እውቀትን በመጠቀም የቡዳ ጥቃት የመፈወስ ዘዴ ቡዳ በሚባለውና በቡዳ ተበላ በተባለው ሰው የሚኖር አካላዊ ንክኪና ቃላዊ ምላሽ ነው። በልማዳዊና በሐይማኖታዊ የፈውስ ስርዓት ላይ ቡዳ በሚባለውና ጥቃት እንዳደረሰበት (እንደበላው) በሚታመነው ሰው መካከል ምንም አይነት አካላዊ ግንኙነት አይኖርም። በዚህም ቡዳ የሚባለው ሰው በአካል በፈውስ ስርዓቱ ላይ አይገኝም። በማኅበረሰባዊ እውቀት የፈውስ ዘዴ ግን አንድ ሰው የቡዳ ጥቃት ሲደርስበት በቡዳ መድሃኒት ግን እንዳጠቃው (እንደበላው) ከተለየ በኋላ በላው የሚባለው ሰው ቡዳ በተበላው ሰው ፊት በአካል ተገኝቶ ሰውነቱን እንዲዳብሰውና "እግዚአብሄር ይማርህ" ወይም "ይቅር ብያለሁ" እንዲለው ማድረግ ፈውስ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል። በዚህም ቡዳ የሚባለውን ሰው በራሱ ፍቃድ ወይም አስገድዶ በማምጣት ቡዳ በተበላው ሰው በአካል ተገኝቶ እግዚአብሄር ይማርህ እንዲለውና ሰውነቱን እንዲዳብሰው ይደረጋል።[64]

---

[64] ይህ የፈውስ ዘዴ በአሁኑ ጊዜ እምብዛም ሲፈጸም አይስተዋልም። የዚህ ምክንያት ደግሞ በአሁኑ ሰዓት አንድን ሰው በቡዳንት መጠርጠር፣ 'ቡዳ ነው' ወይም 'ሰው ይበላል' ማለት በሕግ የሚያስቀጣ በመሆኑ ነው። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ቡዳ የሚባለዉ ሰዉ ለቡዳ ፈዉስ መሆኑን ሳያውቀዉ መንገድ በመዳጀት በማስመሰል ቡዳ የተበላዉ ሰዉ መጥቶ እእግዜር ይማርህ እእንዲለዉ ይደረጋል።

አቶ ደሳለኝ ሳህሌ (28/08/03 ዓ.ም፣ የቡድን ውይይት) "በቡዳ የተበላው ሰው ደህና ዘመድ ካለው የበላው ሰውዬ ተገዶ እንዲመጣ ተደርጎ ወዲያው በትኩሱ ጀርባውን ላይ ተዳበሰና ይቅር ብያለሁ ካለ ቢቃ ይሻለዋል" በማለት ቡዳ የሚባለው ሰው የፈውሱ አካል እንደሆነ ይገልፃሉ። አቶ መንገሻ ስየም "ሌትዮይቱ በቡዳ ተበላች አሁን በኛ ጊዜ ነው። ተበላች። ጀግና ጀግና ወንድሞች አሏት። 'እንሌ ነው የበላኝ' አለች ፒዱና ያዙት ተባለ። ና እግዜር ይማርሽ በላት አሉት። ተይዞ መጣ ታስሮ [illegible] መጣ። እግዜር ይማርሽ አላት ዳነች። ራሱ አድኗት ሄደ"። በማለት በአይኔ በብርቱ ያየሁት ያሉትን የፈውስ ስርዓት ይገልጻሉ።

ቡዳ የሚባለውን ሰው በማምጣት ሰለባውን እግዚአብሄር ይማርህ እንዲልና ሰውነቱን እንዲዳብስ ማድረግ መንፈሱን ቡዳ ወደ ሚባለው ሰው እንደመመለስ ይቆጠራል። በዚህም ቡዳ የሚባለው ሰው ቡዳ የተበላውን ሰው እግዜር ይማርህ ካለውና ሰውነቱን ከዳበሰው ሰዓት ጀምሮ ሙሉ ጤነኛ ይሆናል፤ ለበሽታውም ይመለሳል ተብሎ ይታመናል።

ሌላው በማኅበረሰባዊ እውቀት አማካኝነት የቡዳ ጥቃት የመፈወሻ ዘዴ ቡዳ የሚባለው ሰው ባላወቀበት መንገድ ከልብሱ ላይ ቀዶ በመውሰድ አቃጥሎ ማጠን ወይም አመዱን በቅቤ በማድረግ ቡዳ የተበላውን ሰው መቀባት ነው። ይህ ልማድ በሰሜን ጎንደር ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ማኅበረሰቦችም ይፈጸማል። ለምሳሌ በበደዊ ማኅበረሰብ ጥቃት ያደረሰው ሰው ተለይቶ ከታወቀ በኋላ ቡዳው ባላወቀበት መንገድ ከሚለብሰው ልብስ ላይ ቆርጦ በመውሰድ እንዲቃጠል ተደርጎ በቡዳ የተጠቃው ሰው ይታጠነዋል። ከጥቃቱም ይፈወሳል ተብሎ ይታመናል። ከዚህ በተጨማሪ ቡዳ የሚባለው ሰው የተረገጠውን አፈር አንድ ጭብጥ በመውሰድ ስኒ ውስጥ ባለ የፈላ ውሃ ውስጥ በማድረግ ቡዳ የተበላው ሰው እንዲታጠን በማድረግ የቡዳ ጥቃትን ይፈውሳሉ (Abu-Rabia, 2005)። በተመሳሳይ መልኩ በሰሜን ጎንደር ማህበረሰቦች ልማዳዊ እምነት ውስጥም ይህ በቡዳው ጨርቅ እና ቡዳው በረገጠው አፈር የመፈወስ ስርዓት ይከናወናል።

ይህንን ስርዓት አቶ መንገሻ ስየም "የዚያ ሰውዬ ጨርቅም የፈውስ መድሃኒት ነው። የዚያ የቡዳውን ጨርቅ ቀደህ አምጥተህ በእሳት አቃጥለህ አመዱ በቅቤ ተለውሶ ያ የተባለውን ሰው ሰውነቱን ንብራው" ይቀባል። ወዲያው ይሻለዋል" (28/08/03 ዓ.ም፣ የቡድን ውይይት) በማለት ይገልፃሉ። "የቡዳው ጨርቅ ቆርጣችሁ አምጡ ይባላል ያው በአገራችን ብዙ ባህሎች አሉ። ጨርቁ ይታጠናል። የቡዳውን ኮቴ [ዳና] ቆንጥሩ ተብሎ አፈር ይቆነጠራል። አፈሩን ከሰውነቱ ያሹታል እንደ እምነት..." በማለት ወ/ሮ ሻሸ ታየ (28/08/03 ዓ.ም፣ የቡድን ውይይት) የአቶ

---

"እንዝርት

መንገሻ ሁነብ ያጠናክራሉ። ከዚህ በተጨማሪ በማኅበረሰቡ ዘንድ ቡዳ የሚባለውን ሰው ልብስ ማቃጠል በተበላው ላይ ያደረውን የቡዳ መንፈስ እንደማቃጠል ይቆጠራል:: በዚህም መንፈሱ ከተጠቂው ላይ ይለቃል ተብሎ ይታመናል።

## 4.2. ቡዳዊ ተረኮች በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ

ተረክ ልምድ፣ ነጠመኝ እና እውቀት የማስተላለፊያ እና የመግባቢያ ቅጥ ነው:: ይህ እውቀት፣ ነጠመኝና ልምድ ከማኅበረሰቡ ጋር በሚኖር ማህበራዊ ተራክቦ የሚገኝ ሲሆን የማኅበረሰቡን የትረካ ደንብና ልማዳዊ ስምምነት መሠረት ተደርጐ ይቀርባል። ተረክን ከበቀለበትና ካለበት ማህበረ-ባህላዊ አውድ መመርመር የተረኩን ፋይዳ ለማወቅ እንደሚያግዝ Bascom (1954) ይገልጻሉ።

አንድ አጥኚ ተረክን በሚያጠናበት ወቅት በትረካው አማኒይነት መተላለፍ የተፈለገው ጉዳይ፣ ትረካው የተፈጠረበትንና የሚተረክበትን ምክንያትና ፋይዳ፣ ትረካው የሚቀርብበትን የተወሰነ ቦታ፣ ጊዜና ቅርፅ፣ የተራኪውን ግለሰባዊ ማንነት፣ የታዳሚው ግንዛቤና ተሳትፎ፣ የተረክ ባለቤቶች ለተረኮቻቸው የሚሰጧቸው ቀዬአዊ ስያሜ እና ያሏቸውን ዝንባሌና አተያይ ማጤን እንደሚገባ Degs (1974: 54) እና Bascom 1954፡ 334) ይገልጻሉ።

የሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ አባላት የቡዳ እምነትን አስመልክቶ የአንድን ግለሰብ ገጠመኝና ልምድ መሰረት ተደርገው የሚቀርቡ ትረካዎችን "*የቡዳ ታሪክ*" በሚል ስያሜ ይጠሯቸዋል:: የቡዳ ታሪክ በሚል በሚጠሯቸው ትረካዎችም ከእምነቱ ጋር ተያይዞ የሰሟቸው፣ በህይወት ዘመናቸው በእነሱ ላይ የደረሰን ወይም በሌላ ሰው ላይ ሲከሰቱ የተመለከቷቸውን እምነታዊ ድርጊቶች፣ ሁነቶችና ክስተቶችን ይተርካሉ። ትረካዎቹም በቡዳ ከተበሉ፣ የቡዳ ጥቃትን ከፈወሱ ወይም መንፈስን ካናገሩ፣ የፈውስ ስርዓቱን ከተመለከቱ ሰዎች የተገኙ ልምዶችንና ገጠመኞችን ያካትታሉ። እነዚህ ትረካዎች በተራኪው እምነታዊና እውነተኛ ተደርገው የሚታመኑ ናቸው::

ከቡዳ ታሪኮች በተጨማሪ ከቡዳ እምነት ጋር ተያይዞ በአፈ ታሪክ እና በተረት መልክ የሚቀርቡ ትረካዎች አሉ። አፈ ታሪክ በማኅበረሰቡ ከአባቶች በቃል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የአፍ ታሪክ እንደሆነ ይገለፃል። በአፍ ታሪክ አማኒይነትም ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ያላቸውን ሀይልና ቡዳ የመሆኛ መንገዶችን ይተርካሉ። ከአፈ ታሪክ በተጨማሪ ማኅበረሰቡ ቡዳ ነክ የሆኑ ታሪኮችንም በተረት መልክ ይተርካሉ። እነዚህ ትረካዎች ግን ፍጹም ፈጠራ እንደሆኑ ይታመናል:: በተረቶቹ

እማኝነትም ቡዳ የሆኑ ሰዎች ነገሮችን እና ራሳቸውን ወደ ጅብነት የመለወጥ አስማታዊ ወይም ጥበባዊ ኃይል የተመለከቱ ታሪኮች ይተርካሉ።

በአጠቃላይ በማኅበረሰቡ በተለያዩ አውዶች የቡዳ እምነትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ተረኮች የማኅበረሰቡን አባላት ግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝን መሠረት ያደረጉ ናቸው። እነዚህ ተረኮችም እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል።

### 4.2.1. ግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝ ተረኮች በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ

ልምድንና ገጠመኝን መሠረት ተደርገው የሚቀርቡ ትረካዎች በአንደኛና በሁለተኛ መደብ የትረካ ስልት የሚተረኩ፣ በቃል የሚቀርቡና የሚተላለፉ፣ የተራኪውን ድራማዊ አቀራረብና በንግግሩ ውስጥ ያሉትን ተምሳሌታዊ ፍቾችን እንዲሁም የግለሰቡን ልምድና ገጠመኝ የያዙ፣ አለማዊና እምነታዊ ትረካዎችን የሚያጠቃልሉ እንደሆነ በቀደመው ምዕራፍ ተገልጿል። እነዚህ ተረኮችም የተረኩ ባለቤት ወይም የተራኪውን ልምድና ገጠመኝ፣ የተረኩን ምንነት እና የመረጃ ምንጭ መሠረት በማድረግ ይተረካሉ። በዚህ መሰረትም በሰሜን ጎንደር አካባቢ ያሉ ማኅበረሰቦችም የቡዳ እምነትን የተመለከቱ ዝርው ቃል ትረካዎቻቸውን *"በኔ የደረሰ"፣ "በአይኔ በብረቱ ያየሁት"፣ "ሲባል የሰማሁት"* እና *"ከተረት የማውቀው"* በሚል ዘውግ ይተርካሉ።

#### 4.2.1.1. "በኔ የደረሰ" ተረኮች

በማኅበረሰብ ዘንድ የቡዳ እምነትን አስመልክቶ የማኅበረሰቡ አባላት ከቡዳ ጥቃት፣ ከቡዳ የፈውስ ስርዓት ጋር የተያያዙ ገጠመኞችና ልምዶች በትረካ መልክ ያቀርባሉ። በዚህም የቡዳ ጥቃት ሠለባ የሆኑና የቡዳ ጥቃት የሚፈውሱ ግለሰቦች በተረኩ ውስጥ በተገለጸው ታሪክ ወይም ድርጊት ፈጻሚ ወይም ተሳታፊ በመሆን "በእኔ የደረሰ" ወይም "እኔን የገጠመኝ" የቡዳ ታሪክ በማለት ይተርካሉ። በዚህ የተረክ አይነትም ተራኪዎቹ ለቡዳ እምነት ያላቸው አመለካከት፣ ለፈውስ ስርዓት ያላቸውን እምነት እንዲሁም ግላዊ ማንነታቸውን ይገልጹበታል። *በእኔ የደረሰ* የቡዳ እምነት ትረካ ተራኪዎቹ በአብዛኛው *"እኔን የገጠመኝ"፣ "እኔን የደረሰኝ"*፣ *"አንድ ጊዜ ቡዳ በልቶኝ"*፣ ወዘተ በማለት እንደ መግቢያ በመጀመር የቡዳ ጥቃትና የፈውስ ስርዓት ይዘቶችን ከተረኩ በኋላ በመጨረሻም *"ይሄ እንግዲህ በኔ የደረሰ"*፣ *"እኔን የገጠመኝ"* ወይም *"እኔ ያደረኩት ነው"* በማለት ትረካቸውን ይደመድማሉ። ትረካውን በሚተርኩበት ጊዜ እየተረኩት ያለው ነገር (ታሪክ) በእውን የተፈጸመ መሆኑን ለማሳየት የተለያዩ የእውነት ማድረጊያ ብልሃቶችን ይጠቀማሉ። እንዲሁም በሁነቱ ውስጥ የነበረን ሰው በመጥራት፣ ሁነቱ የተከሰተበትን ወር፣

ቀን፣ ሰአት፣ የአየር ሁኔታ፣ የሁነቱን ድባብ እና ድርጊት በድራማዊና በአካላዊ ገለጻ በማጀብ ይተርካሉ።

ስእኔ የደረሰ ተረኮች አማካይነት ተራኪው የቡዳ እምነትን በተመለከተ ያለውን ግለሰባዊ አተያይ፣ እውቀትና እምነት እንዲሁም የሚገበረለትን ልማድ መገንዘብ ይቻላል። ለምሳሌ ያህል የሚከተለው ስእኔ የደረሰ ተረኮች የሚገበረለትን የቡዳ እምነት ስርዓት፣ ለእምነቱ ያላቸውን አመለካከትና ተረኩን የእውነት ማድረጊያ ቴክኒኮችን አጉልተው ያሳያሉ።

> እኔንም በልቶኝ ነበር። **ዲያቆን ሳለሁ በተለይ! በተለይ! በተለይ! ዲያቆን** ሳለሁ። የአባቴ ቤት ሰባት ወጋግራ የሳር ቤት ነው። አሁን *ታመምኩ*። *ታምሜ* በሰባቱ ወጋግራ የሚጠረጠሩት ቡዳ የሚባሉት ሰዎች በሰባቱ ወጋግራ **ቆመዋል**። **ቆመው** ይታዩኛል። ኋላ መጨረሻ አንዱ ሰውየው[ቡዳው] በአየሁት ቁጥር ስፈራው እኖር ነበር አሁን ሙቷል። እንደገና ደግሞ አንዲት ካይላ የምትባል፡ **ካይላ እንስው ነበር ይህን ቤተእስራኤል** እነሱ ይባላሉ ነው የሚባል። እሷ ደግሞ ከአንዱ ወጋግራ ቁጭ ብላ ጥርሷን ፃም ፃም ትለኛለች። እመመኝ። አንዱ ደግሞ ጥቁር ሰውየ በአንዱ ወጋግራ ቆሞ ያየኛል። ጥርሱን ግጥጥ ግጥጥ ሲያደርግብኝ ያመኛል። ፃም ፃም ፃም እያለ **በጦር ወግቶኝ ሄደ**። በጦር የወጋኝም ደጌ እነዚህ ወንድሞች ሁሉ እሱ እስከ መንፈቅ ከዚህ ሚንቶየ ላይ ቆስሉ ላነ። (ቄስ መላከ ገነት ተውህቦ ማሩ፣ 30/08/03 ዓ.ም፣ የቡድን ውይይት)

በተረኩ ውስጥ ጎልተው የሚታዩት ቃላት፣ ሀረጋትና ዓረፍተነገሮች በተረኩ ውስጥ ያለን የተረክ አይነት፣የሚገበረለትን የቡዳ እምነት ስርዓት፣ የተራኪውን ግላዊ አመለካከት፣ የማንነት ግንባታና ተረኩን እውነት የማድረጊያ ቴክኒኮች የሚያመለክቱ ናቸው።

እላይ የቀረበው ተረክ በዋናነት ከ'ሚሞሬት' ግለሰባዊ ተረክ የሚመደብ ነው። ይህ ተረክ ከልዕለ ሰብዕ በላይ በሆነ መንገድ የቀየት እምነታዊ ድርጊቶች የሚተረኩበት ነው። ለምሳሌ በዚህ ተረክ ውስጥ ተራኪው በቤቱ ወጋግራ ያሉ ቡዳዎች ቆመው እንደታዩዋቸውና በተደጋጋሚ በጦር ሚንቶቸው (ደርባቸው) ላይ እንደተወጉና የተወጉትም እንደቆሰለ ገልጸዋል። ቡዳዎችን ማየታቸውና በጦር መወጋታቸውን የተረዱበት መንገድ ከተለመደው የስሜት ህዋሳት በተለየ ወይም በቦታው የነበሩ ሰዎች ባልተገነዘቡበት መንገድ ነው። ይህን ሐይል ያገኙበት መንገድም ቡዳ በሚባሉ ሰዎች መንፈስ በመዋረሳቸው (Possesd) የተነሳ መሆኑን መረዳት ይቻላል። የዚህ ምክንያት ደግሞ ቡዳ የሚባሉትን ሰዎች "ፃም ፃም" ሲሉና ጥራሳቸውን ሲያገጡባቸው ከቤት ውስጥ ካሉት ሰዎች መሀከል ለእይታ የተከሰቱላቸው ለእሳቸው (ለተራኪው) ብቻ ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ "እኔን በተለይ" ፣ "ዲያቆን ሳለሁ" እና "የአባቴ ቤት ሰባት ወጋግራ የሳር ቤት ነው" የሚሉት ገለጻዎች ተራኪው ማንነቱን የገነባበት ግላጼዎች ናቸው። እኔ "በተለይ እኔን" እና "ዲያቆን ሳለሁ" የሚሉት ገለጻዎች መደጋገማቸው ተራኪው በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን ማኅበረሰባዊ ደረጃ ወይም ክብር ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል። ምክንያቱም ዲያቆናት እርኩስ መንፈስ አይቀርባቸውም ተብሎ ይታሰባል። ነገር ግን ተራኪው የቡዳ ሰለባ ሆኗል። በዚህም፣ እንደም ሁሉም ሰው የቡዳ ተጋላጭ የመሆን እድል ያለው መሆኑን፤ እንድም እንዴት እኔን ቡዳ ሊያጠቃኝ ቻለ የሚል ቁጭትን ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪ በማኅበረሰቡ ቡዳ የሚባሉ ቡድኖች ተለይተው የሚታወቁ መሆኑን "...ካይላ እንለው ነበር ይህን ቤተእስራኤል እነሱ ይባላሉ ነው የሚባል።" ከሚለው ገለጻ መረዳት ይቻላል።

አስረጅ ተረክ ሁለት

> ለምሳሌ ያህል እነ ዶክተር ደረጀ እነ ወርቁ እየሁ ሊያዋልዱ ብለው ለነ የሴላትን እርጉዝ ናትና ልትወልድ ነው ብለው የሞቱች ነገር ናት። አሁን ተጠራሁ። እኔን ይዘውኝ ሄዱ። ሄድኩና ዶክተር ደረጀ ፈቀዱልኝ ገባሁ ከማዋለጃ ቤት። ወርቁም እዚያ አለ። ገባሁና ቀስ ብላ ሙታ ያበቃች ናት። መድሃኒቱን ጠጋ አደረኩባት። እነሱ ቢነሱ ቢወድቁ ቢመራመሩ እንቢ አላቸው - እነ ዶክተርን። ተጠቅታለች። ወስዷታል። ቀስ አድርጌ [መድሃኒቱን] በአፍንጫዋ ጠጋ አደረኩላት። ጠጋ ሳደርግላት ያን ጊዜ ብድግ አለችና ው. . ው...ው አለች። ጤና ጣቢያ ከዶክተሩ ወሰደ። አሁን ያንን አስለቀቅኩና ሳበቃ ወደ ቤቷ ሰደድናት። አሁን ዶክተር ደረጀ "ጥቁር አንበሳ ነው" የሚለኝ። አሁን ዛሬ ወርቃየ ሲጠራኝ "ጥቁር አንበሳ" ብሉ ነው ስሜን የሚጠራው (አቶ ታረቀኝ እምሩ፣ 04/09/03 ዓ.ም፣ ቃለ መጠየቅ)።

አስረጅ ተረክ ሶስት

> ነገሬህለሁ እሱ መድሐኒቱን ጠጋ ሳደርግበት ብድግ ብድግ ነው የሚለው። በአልጋ መጥተው በእግራቸው ነው የሚሄዱት። እንኳን በህይወት ያሉ የሞቱ ሰዎች ሞተዋል ተብለው ሰሌን ተገዝቶላቸው ጃንገ.. ጃንገ በፈረስ መጥቶ ሰውየው መድሐኒት ሊወስድ መጥቶ ሲነግረኝ ለሰውየው ሰሌን ተገዝቶል። ተመንደር ሁላ መርዶ ተልኳል። በየሀገሩ ተልኳል። ኋላ እስቲ እንሂድ ብለው ተጠራጥረው መጡ። ቢቃ ሞቷል ተብሎ እየተለቀሰ ነው። መርዶ ለለቅሶ እየተላከ ነው። ከዛ በኋላ መጡ። በበመድ ተልከው እየበረሩ ከእኔ መጡ። እንዲያው ትረፍ ብሎት ነው መሠለኝ ያን መድሃኒት ወስደው ጠጋ ቢያደርጉለት ያ የሞተ ሰውዬ ብድግ አለ። እኔ የለሁም እዚያው ነው በሰጠኋቸው መድሃኒት የጨረሱት። ያ እንዲያ ሆነ ዳነ። አልቃሽ በየሀገሩ ተልኳል። ግን እንዲያ ሆኖ ዳነ። (አቶ ታረቀኝ እምሩ፣ 04/09/03 ዓ.ም፣ ቃለ መጠየቅ)።

እላይ የቀረቡት ሁለት የግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝ ተረኮች የባህላዊ የቡዳ ጥቃት ፈዋሹ የፈውስ ስርአቱ ተአማኒነት፣ ግለሰባዊ የማንነት ግንባታ እና ማኅበረሰባዊ ክብርና ተቀባይነት ጎልቶ የታየባቸው ናቸው።

ተራኪው የፈውስ ስርዓቱን እውነትነትና ተጨባጭነት እንዲሁም ግለሰባዊ ማንነቱን የገነባበት መንገድ በትረካው ውስጥ ያሉ ድርጊቶችንና ሁነቶችን ድራማዊና ቅደም ተከተላቸውን በጠበቀ መልኩ በመተረኩና አንዳንድ አካላዊ ተምሳሌታዊ ፍቾችን በመስጠት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተራኪው አውቆትም ይሁን ሳያውቀው የፈውስ ትረካው በመጽሃፍ ቅዱስ የፈውስ ትረካ ጋር ይቀራረባል፡፡

በትረኩ ውስጥ ጎላ ብለው የሚታዩት ገላጺዎች ተምሳሌታዊ ፍቺ አላቸው፡፡ ይህም "የሞተች ነገር ናት" እና "የሚደል ተብሎ የተሰቀለ ነው" የሚሉት ህመምተኞች (የቡዳ ጥቃት ሰለባዎች) ከፈውስ በፊት የነበሩበትን አካሄን (የጥቃቱን መጠን)፤ "ቀስ አድርጌ [መድሃኒቱን] ጠጋ አደረኩላት" እና "ያን መድሃኒት ጠጋ ቢያደርጉለት" የሚሉት ገለፃዎች የፈውሱን ሂደትና መንገድ፤ "ብድግ አለች" እና "የሞተው ሰው ብድግ አለ" የሚሉት ድርጊታዊ ገለፃዎች የመድሃኒቱን (የፈዋሹን) የፈውስ ሀይል እንዲሁም "በእሊያ መጥተው በእግራቸው ነው የሚሄዱት" የሚለው ገለፃ እና "ጥቁር አንበሳ" የሚለው ቅጽል ስም የፈዋሹን የፈውስ ብቃት ወይም ደረጃ ያሳያሉ፡፡ እንዳኞ ሀይልን በመጠቀም ከሞት አፋፍ ላይ ያሉ (ሞቱ የተባሉ) ሰዎችን የሚፈውስ መሆኑን ተራኪው ይገልፃል፡፡ በዚህም ማንነቱንና በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ቦታና ስፍራ ከፍ ያደርገዋል፡፡

በመስክ ቆይታዬም ከአነጋቢው ከሚጠቀሱ የቡዳ ጥቃት ፈዋሾች መካከል ተራኪው በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ ተራኪው በትረካው በማህበረሰቡ ዘንድ ፈውሱ ተአማኒነት ያለው መሆኑን የገለጹበት መንገድ "ጥቁር አንበሳ" በሚለው ቅጽል ስም ነው፡፡ ይህም የጤና ባለሙያዎቹ (እነ ዶክተር የሚላቸው) ከአገሪቱ የመጨረሻው (ከፍተኛው) የህክምና መስጫ ተቋም ጋር በማወዳደር የፈውስ ብቃታቸው ወይም ደረጃቸው ከፍተኛ መሆኑን ለመመልከት ነው፡፡ እነዚህ የጤና ባለሙያዎች ይህንን ስም በመስጠት ብቃታቸውን ከመሰከሩና ካከበሯቸው የተቀሩት የማኅበረሰቡ አባላት የሚሰጧቸውን ቦታ መገመት አያዳግትም፡፡

በትረኩ ውስጥ የተገለፀው ሞቱ የተባሉና በጠና የታመሙ ሰዎችን ከሞት ማስነሳትና ከበሽታ መፈወስ በማኅበረሰቡ ሃይማኖታዊ መጽሐፍ (መጽሐፍ ቅዱስ) ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ ውስጥም ኢየሱስና ሐዋርያቱ የሞቱ ሰዎችን አስነስተዋል፡፡ በሽተኞችን ፈውሰዋል፡፡ በዚህም በወቅቱ ተቀባይነትን በማግኘታቸው ብዙ ተከታይን አፍርተዋል፡፡ የፈውስ መንገዱ ይለያይ እንጂ የአቶ ታረቀኝና የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ ተቀራራቢነት አላቸው፡፡ ከሁለቱም ትረካዎች የተወሰዱ ተቀራራቢነት የሚታይባቸው ገለጻዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. "...ጴጥሮስ ሁሉንም ከዘፍሉ አስወጥቶ ተንበርክኮ ፀለየ። ወደ ሬሳውም ዘወር ብሎ ጣቢታ ተነሽ አለ። እርሷም ዐይኗን፣ ጴጥሮስን ባየች ጊዜ ቀና ብላ ተቀመጠች" (ሐዋ፥ ፱፡ ፵)
2. ... ያበት ስማቸውን ቤት። ...ቀስ እያርኩ [መድሃኒቱን] በአፍንጫዋ ጠጋ አደረኩለት ... ያን ጊዜ ብድግ አለች (ከእቶ ታረቀኝ ትረካ ውስጥ)
3. [እየሱስ] "... ሽባውን 'ተነስ ቃሬዛህን ይዘህ ወደ ቤትህ ሂድ' አለው። ሽባውም ተነስቶ ወደ ቤቱ ሄደ (ማቴ፥ ፱፡ ፮-፯) ")
4. በእሌን መጥተው በእግራቸው ነው የሚሄዱት (ከእቶ ታረቀኝ ትረካ ውስጥ)

በነዚህ አራት ትረካዎች (ገለፃዎች) ውስጥ ጴጥሮስ፣ እየሱስ እና አቶ ታረቀኝ የፈወሱበት መንገድና ሀይል ይለያይ እንጅ አካላቸው ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል። ተራኪው (ፈዋሹ) አውቆት ይሁን ሳያውቀው ማንነቱን ለመገንባትና ማኅበረሰባዊ ተቀባይነቱን ለማጉላት የመጽሐፍ ቅዱስ ተግባራትና ትረካዎች ተጠቅሟል።

4.2.1.2. 'በአይኔ በብረቱ ያየሁት' ተረኮች

በዚህ ተረክ አማካይነት የማኅበረሰቡ አባላት ልማዳዊ የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓትን፣ የቡዳ ጥቃት ሰለባዎች ያጋጠሟቸውን ህመሞች እንዲሁም ከቡዳ ጥቃት ጋር ተያይዘው የተመለከቷቸውንና ያከናወኗቸውን ድርጊቶች የሚገልፁበት ነው። በዚህ ተረክ እያንዳንዱ የማኅበረሰብ አባል ለቡዳ እምነት ያለውን እምነት፣ ዝንባሌና አተያይ ይገልጽበታል። ማኅበረሰቡ በአይኔ በብረቱ ያየሁት ትረካዎችን "ቡዳን በምን ለየኸው ብትለኝ"፣ "እንዴት አጋጠመህ ብትለኝ"፣ "ባይኔ በብረቱ ያየሁት ነገር አለ"፣ "ቡዳ መብላቱን ምልክት ያሳየኝ" በሚል በመጀመር በቅርብ ቤተሰቦቻቸው፣ በመዶቻቸውና ወዳጆቻቸው ላይ የተከሰተን ወይም በአጋጣሚ ያዩትንና የተሳተፉበትን የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት እንዲሁም ከቡዳ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ይተርካሉ። በመጨረሻም "በዚህ አረጋገጥኩ"፣ "ይህንን በአይኔ አይቻለሁ"፣ "ይህ በህይወቴ ያየሁት ጉዳይ ነው"፣ "ይህ በእኔ ሲሆን የታየ ነው"[88] በማለት ትረካዎቻቸውን ይደመድማሉ። እነዚህ የመግቢያና የመደምደሚያ ንዑሳኖች የተረኩትን ትረካ ተአማኒ የማድረጊያ ቴክኒኮች ናቸው። ከነዚህ ቴክኒኮች በተጨማሪ የተረኩ የተፈጸመበትን ሁነትና ድባብ፣ በተረኩ ውስጥ ያሉ ድርጊት ፈጻሚ ሰዎችን ንግግር፣ ስሜትና ድርጊት ድራማዊ በሆነ ስልት በማቅረብ ትረካውን የበለጠ ተጨባጭ ያደርጉታል።

[88] በአካል መልክ የተረኩትን ተረቶች ሕቁ ይሏል።

አስረጅ ተረክ አራት

> እኔ ቡዳ ሲበላ አላየሁም። ግን መበላቱን ምልክት ያሳየኝ እኔ ወደ ገበያ እሄዳለሁ ምሽቱም አብራኝ ትሄዳለች። አሁያ ጭኝ ወደ ገበያ እየሄድን አንድ ሰው በሆያ በመኪናው መንገድ ሽቅብ ይሄዳል። ታድያ እንዲህ እንዲህ [ጭንቅላታቸው ግራና ቀኝ እያዞሩ] እያለ ያያል። ደሞ ወደኛ ያያል። እሷ [ሚስቱ] ጠጉሯን እየፈታች ትሄዳለች። ዘወር ብየ አይቶ አንቺ ለምንድነው መንገድ ላይ ፀጉርሽን የምትፈቺ አልታለሁ። ስቆጣት እንደገና ትተዋለች። በኋላ እውነቱን አሁ ነው ብለው እናቴቱ ይቆጣል። አሁን ያ ሰውየ አለፎ ሄዶ። ጎልቻ አዲስ ጎልቻ አዚች [ጭንቅላታቸውን እየነኩ] ላይ አድርጓል። በልብሱ የሆነ ነገር እንዲህ አድርጎ[የቀኝ እጃቸውን ወደ ብብታቸው እያስገቡ] ሸፋፍኗል። ሰሬው ጭዳ[37] ናት። አስተውየዋለሁ። ራሱን በሻሽ ጠምጥሟል። በኋላ ሄደን ውሰን ገበያ ተመልሰን እንመጣለን። መጥተን [ሚስቴ] ከቤት ስትደርስ እንዲህ ደርሳ ተበሳጨች። ምን ሆነሽ ስላት አንዱን ጭብጥ! አንዱን ለቀቅ አንዱን ጭብጥ አንዱን ለቀቅ ታደርጋለች። እንዲህ ስታደርግ አየኋት ይሄ ነገር ምንድን ነገር ነው አልኩና አንስቼ ባህል አለ ይሄማ ቡዳ ነው አልኩ። ያን ሰውየ ጠረጠርኩት። ቡዳ ነው አልኩና ጣሪያ ላይ ያለውን [መድሐኒት] አምጥቸ አሸተትኳት። ሳሽታት እኔ ነኝ አለ -ያ ሰው። 'ምንድን ይዞህ ነበር እስቲ ምልክቱን ተናገር?' አልኩት። 'ሞዳ ነው ሰሬየ! ጎልቻየን እዚህ አድርጌ ነበር' 'እ…እ. ከምን ኖረህ ነው?' 'ጎርጎራ ዘመድ ተየቶ ሄጀ አሁን ወደ ሀገሬ እሄዳለሁ ነው'። 'ወዴት ነው ሀገርህ?' 'ወገራ… አይ የዛን ጊዜ ፀጉሯን እየፈታች አየኋት የዛን ጊዜ ቀሰምኳት'። ይሀን ሲል እንግዲህ ይህን ሰውየ አይቸዋለሁ። በኋላ ምስህ ምንድን ነው ተባለ እንዲህ ያለ ነው ምኑ አለ። ካለ በኋላ ጤናዋን መለሰላት (ለስናቀው ዘሪሁን[38]፣ 30/08/03 ዓ.ም ቃለመጠይቅ)።

በዚህም በማህበረሱ ውስጥ የቡዳ ጥቃት እንዴት እንደሚከሰት፣ ለጥቃቱ የሚከናወኑ የፈውስ ስርአቶች (የጥቃቱን መለያና መፈወሻ ዘዴዎችን) ከተረኩ መገንዘብ ይቻላል። ተራኪውም የቡዳ እምነት መኖሩን ወይም ቡዳ በእይታ ሰው ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን በሚስታቸው ላይ የደረሰውንና ያዩትን እንደ እዉነት ያቀርባሉ። ተረኪው በተረኩ ውስጥ የቡዳ ጥቃት አድራሹን ማንነትና አኳኋን በተደጋጋሚ ስእላዊ በሆነ መንገድ የገለጹበት ምክንያት አንድም የቡዳ ጥቃትን ተጨባጭነት ለማስረገጥ አንድም ደግሞ እየተረኩት ያለው ታሪክ ያዩትና በድርጊቱ የተሳተፉበት መሆኑና እውነትነቱን ለማጉላት ነው።

## 4.2.1.3. 'ሲባል የሰማሁት' ተረኮች

ቡዳ የደረሰ እና በእይኔ በብረቱ ያየሁት በሚል የሚቀርቡ ትረካዎች የግለሰቡን ልምድና ገጠመኝ መሠረት ተደርገው የሚቀርቡ በመሆናቸው በተራኪው በኩል ፍጹም እውነት ተደርገው ይታሰባሉ። የዚህ ምክንያት ደግሞ ተራኪው የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ወይም የጥቃቱ ስለሰዎቹ በሚያከናውኑት ድርጊት ፈጻሚ፣ ተሳታፊ ወይም ተመልካች በመሆኑና ራሱን

[?] ኣዲስ ወይም ውጥ ያልገባው ሰላብ
[?] ከፍተኛ ወረዳ የጭቃ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነዋሪና የ67 ዓመት አዛውንት።

እንደምስክር በመቆጠር የሚተረክ በመሆኑ ነው። ሲባል የሰማሁት ትረካዎች ግን በአብዛኛው በእድሜዋ ሆነ በተራኪ በኩል ፍጹም እውነት ተደርገው የሚተረኩ እና የሚታመኑ አይደሉም።

በሌላ ጉኑ የተረኩ ባለቤት ወይም የታሪኩ ፈጻሚ ማንነት ስለሚታወቅ ወይም ስለሚጠቀስ ፍጹም ሐሰት ተደርገው አይቆጠሩም። የተረኩቹ እውነትነትና ታማኒነት የሚታወቀው ተራኪው ወይም አድማጩ ስለቡዳ በሚኖራቸው አመለካከትና እምነት ነው። በሲባል የሰማሁት ትረካዎችም አማካይነት ማኅበረሰቡ የቡዳ ምንጭ ወይም አመጣጥ፣ የቡዳ ጥቃት መንገድ፣ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ቡዳ የሚሆኑበትን ዘዴ እና ምክንያት፣ በቡዳው መንፈስ የሚያከናውናቸው ተግባራት፣ የፈውስና የመከላከያ ዘዴዎች፣ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ያሏቸውን ነገሮችን የመለወጥ ወይም የመለወጥ[illegible] ስውር ጥበብና አስማታዊ ሐይል እንዲሁም አጠቃላይ ማኅበረሰቡ ለቡዳ እምነት ያለውን አመለካከት ይተርክበታል።

አብዛኛው የማኅበረሰቡ አባላትም በነዚህ ዙሪያ የተነገሩ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሲባል የሰማሁት ትረካዎችን ይተርካሉ። ተራኪዎቹም ሲሉ ወይም ሲባል የሰማሁት፣ *ከታላላቅ ሰዎች የሰማሁ*፣ እና *ይህ እንግዲህ አንዱ በአይኔ በብረቱ ያየሁት ብሉ/ላ የነገረ/ችኝ ነው።* በማለት ይተርካሉ። ለተረኩም ሆነ ለቡዳ እምነት ያላቸውን አተያይ "ይባላል እኔ ግን አላምንም" ወይም "ቢሆንም አምናለሁ" በማለት ይጠቀማሉ።

#### 4.2.1.4. "በተረት የማውቀው" ተረኮች

በስሚን ነገር አካባቢ ማኅበረሰቡ በተረት አማካይነት የቡዳ እምነትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ትረካዎች አሉት። በዘውን ጊዜ በዚህ ትረካ ውስጥ የሚጠቀሱ ሰዎች፣ ድርጊቶች የተፈጸሙባቸው ቦታዎችና ጊዜዎች በማኅበረሰቡ ፈጠራዊ ተደርገው ይቆጠራሉ። በተረቱ አማካይነት የቀረበው ጉዳይ ግን ማኅበረሰቡን ልማዳዊ እምነት መሰረት ያደረገ ነው። ከቡዳ እምነት ጋር ተያይዞ በተረት የሚቀርበው ጉዳይ በአብዛኛው ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ጥቃት በማድረስ (በመብላት) እንዲሞት ካደረጉትና አስከሬኑን መቃብር ፈንቅለው በማውጣትና ቤታቸው በመውሰድ በአንዳች አስማታዊ ወይም ጥበባዊ ነፍስ በመስጠት አገልጋይ ማድረግን ይመለከታል።

---

[illegible]

አስረጅ ተረክ አምስት

> በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሁለት ልጆች ነበሩ፡፡ የአንዷ ልጅ እናት ቡዳ በልቷት ሞታለችና ተቀበረች፡፡ ነገር ግን በተቀበረች በሦስት ቀኑ ቡዳው ወስዳት ከቤቱ ከዚያ የተደገመባት ለበቅ[70] አለች አሉ፡፡ ያችን ለበቂቱን በለበቂ ሄዶ ጋኑን ሾጥ ሲያደርጋት ሲትዮዋ ትቆማለች፡፡ አዙሮ ደግሞ ሲትዮቱን በለበቅ ሲላት ጋን ትሆናለች፡፡ ቡዳው ይሄን ሲያረግ ልጁ ታያለች፡፡ ደሞ እናቷ በቡዳ ተበልታ የሞተችባት ታያለች፡፡ ኋላ ሲኖሩ ሲኖሩ ከዛ እንደ አጋጣሚ ልጅቱ ጎረቤት ስለሆኑ እስቲ ጋንህን ስጠኝ ትለዋለች፡፡ እረ ምን ጋን አለኝ ሲላት ያችን እናቲቱ የምትሆነን ጋን ሰጣት፡፡ ከዛ ቀስ ታደርግና ትወስድና የተደገመበትን ለበቅ ወስዳ ከቤቷ ላጥ ብታደርጋት እናቷ ቀጥ አለች ነው (መኳንንት ሙላት፣ 10/09/03 ዓ.ም፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የዚህ ተረት ጭብጥ ቡዳ የሆኑ ሰዎች በአንዳች አስማታዊ ኃይል ወይም ጥበብን በመጠቀም የሞቱ ሰዎችን ነብስ በመስጠት ስራ ያሰራሉ የሚል ነው፡፡ ይህ ጭብጥ ከማኅበረሰቡ ዘንድ ፍጹም ሐሰት ወይም ተቀባይነት የሌለው እምነት አይደለም፡፡ ምክንያቱም በማኅበረሰቡ የቡዳ እምነት ስርዓት መሠረት ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ሰዎችን በልተው ከገደሉ በኋላ መቃብራቸውን በመፈንቀል የበሉትን ሰው ቤታቸው በመውሰድ አገልጋይ ያደርጉታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ እምነት መኖሩ የሚያመለክተው ደግሞ በማኅበረሰቡ አንድ ሰው በቡዳ ጥቃት ቢሞት ቡዳው አስከሬኑን አውጥቶ እንዳይወስደው ለመከላከል የሟች ወንድም ወይም የቅርብ ዘመድ አስከሬኑን በጥይት እንዲመታው መደረጉ ነው፡፡

4.2.2. ቡዳዊ ተረኮች የሚቀርቡበት አውድ

ግለሰባዊ ልምድና ክስመኝ መሠረት ተደርገው የሚቀርቡ የቡዳ እምነት ትረካዎች በማኅበረሰቡ ዘንድ በየትኛውም አጋጣሚ እና ቦታ አይተረኩም፡፡ የራሳቸው የመተረኪያ ምክንያት፣ ቦታ እና ጊዜ አላቸው፡፡ በዋናነት ትረካዎቹ የሚቀርቡት በቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት እና ቡዳ የሚባለው ሰው አይነ ለአይነ በሚያጋጥምበት ጊዜ ነው ፡፡

የእነዚህ ትረካዎች አውድ አንዳንድ ጊዜ አደባባይነትና ሚስጥራዊነት ይታዩበታል፡፡ ለምሳሌ ያህል በቡዳነት የሚጠረጠረው ሰው ወይም የቅርብ ዘመዶቹ ባሉበት ቡዳ የሚባለው ሰው ያደረሰው የቡዳ ጥቃት አይተረክም፡፡ ምክንያቱም በአካባቢው አንድን ሰው ቡዳ ማለት በስም ማጥፋት ወንጀል የሚያስከስስ በመሆኑ ነው፡፡ ቡዳ የሚባለውን ሰው ስም እየጠቀሱ ያደረሳቸውን ጥቃቶችና ሌሎች ልምድና ክስመኝ መሰረት መተረክ የሚቻለው ከቤት ወይም ከቤተሰብና እና ሚስጢር ይጠብቃል ከሚሉት ሰው ፊት ብቻ ነው፡፡

---

[70] ክፍኒያ

እንዲሁም ትረካዎቹ በልማዳዊና በሐይማኖታዊ የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ላይ በቡዳ ተበሉ የሚባሉ ሰዎች በተጠማቂዎችና አስጠማቂዎች ፊት በአደባባይ ቡዳ በላው የተባለው ሰው ቡዳ በላው በተባለው ሲጋና ደም በማረፍ የተጠየቀውን ሁሉ ይመልሳል፡፡ ይለፈልፋል፡፡ ይተርካል፡፡

### 4.2.3. ቡዳዊ ተረኮች የሚቀርቡበት ፋይዳ

ልምድና ንጠመኝ መሠረት ተደርገው የሚቀርቡ ቡዳዊ ተረኮች በዋናነት ልማዳዊ እምነትን በማገበረሰቡ አባላት ዘንድ የማስረጽ ፋይዳ አላቸው፡፡ እነዚህ ቡዳዊ ተረኮችን መተረክ እምነቱን ከማስረጽ በተጨማሪ የቡዳ ጥቃትን የመከላከልንና የፈውስ ፋይዳ አላቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ በማገበረሰቡ ዘንድ በቡዳነት ከሚጠረጠር ሰው ጋር ፊት ለፊት ሲያጋጥም አጠገብ ላለ ሰው በማስመሰል የቡዳ ጥቃትን የተመለከቱ ተረኮችን መተረክ ቡዳ የሚባለውን ሰው የማጥቃት ፍላጎቱን ይቀንሳል□ መንፈሱም ያፍራል ወይም ይሸማቀቃል ተብሎ ይታመናል፡፡

በልማዳዊው ሆነ በሀይማኖታዊ የፈውስ ስርዓት ላይ በቡዳ የተባለ ሰው በበላው ሰው አንደበት ይናገራል ተብሎ እንደሚታመንና ፈዋሾችም የጠየቁትን ማንኛውንም ጥያቄ ቡዳ የሚባለውን ሰው በመሆን ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን በቀደመው ምዕራፍ ተገልጿል፡፡ ይህ የፈውስ ስርዓትም ማስለፍለፍ ይባላል፡፡ ይህ በልማዳዊ ወይም በሀይማኖታዊ ፈውሶች የሚፈፀሙ የማስለፍለፍ ስርዓቶች ከምልልስ ባለፈ ዘለግ ያሉ ትረካዎች ይቀርቡበታል፡፡

በዚህ ስርዓት የቡዳው መንፈስ ቡዳነትን እንዴት እንደተማረው፣ ተጠቂውን እንዴት እንዳገኘው፣ ከአሁን በፊት ጥቃት ያደረሰባቸውን ሰዎች ማንነት፣ በአጠቃላይ በልምዱና በገጠመኙ መሠረት ያከናወናቸውን ተግባራትና የፈፀማቸው ድርጊቶች በላው በተባለው ሰው አንደበት ይተርካል፡፡ ይህ ትረካ ደግሞ አይቀሬ የቡዳ ጥቃት የፈውስ ስርዓት ነው፡፡ የቡዳው መንፈስ የሚጠየቀውን ጥያቄ፣ ማንነቱንና ከአሁን በፊት የፈፀማቸውን ነገሮች የማይለፈልፍና የማይተርክ ከሆነ የፈውስ ስርዓቱ እንደተጓደለ ይቆጠራል፡፡ ከዚህ በመነሳት ትረካ እንደ አንድ የመፈወሻ ዘዴ በመሆን ያገለግላል፡፡

### 4.3. የስሜን ጎንደር ማኅበረሰብ በቡዳ እምነት እና ቡዳዊ ተረኮች ላይ ያለው አመለካከት

በሰሜን ጎንደር ማኅበረሰብ በቡዳ ልምዳዊ እምነት ዙሪያ የተለያዩ አመለካከቶችና እምነቶች ይንፀባረቃሉ። ከነዚህም ውስጥ የቡዳ እምነት ወይም ጥቃት አለ ወይስ የለም? ካለ ጥቃት አድራሹ ሰው ወይስ መንፈስ? እንዲሁም ቡዳዊ ተረኮች የእውነት ወይስ የፈጠራ? የሚሉት ናቸው። በዚህም የባህል ቁሪዝም ጽህፈት ቤቶች፣ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች፣ የሐይማኖት አባቶችና ሌሎች የማኅበረሰቡ አባላት የተለያየ እምነትና አመለካከት እንዲሁም ተጠየቅና አስረጅ ተረክ በማቅረብ ይከራከራሉ፤ ይሟገታሉ።

በሰሜን ጎንደር ዞን ባህል ቱሪዝም ቢሮ (በመንግስት ደረጃ)፣ በጥቂት የማኅበረሰቡ አባላት፣ በአንዳንድ ቡዳ በሚባሉ ሰዎችና ቡድኖች ዘንድ የቡዳ እምነትም ሆነ ጥቃት ፍጹም ፈጠራዊና ሐሰት እንደሆነ ይታመናል። በእነዚህ አካላት "ሰውን ሰው አይበላም" በሚል አንድን ሠው በቡዳነት መፈረጅና በቡዳ ማመን ጎጅ ልማዳዊ ድርጊት ተደርጎ ይቆጠራል። በተለይ በመንግስት ደረጃ አንድን ሠው በቡዳነት መጠርጠር፣ ጥቃት አደረሰብኝ በሚል ክስ ማቅረብ፣ መሳደብ፤ ስሙን ከቡዳ ጋር ማገናኘት፣ አስገድዶ ቡዳ ተብላ የተባለውን ሠው ሰላምታ እንዲሰጥ ማድረግና በሠውየው ላይ የሐይል እርምጃ መውሰድ፣ ህገ ወጥነት፣ ሰብአዊ መብትን የመጋፋትና ስም የማጥፋት ወንጀል በመሆኑ በህግ ያስጠይቃል፡ ያስቀጣል።

በጥቂት የማኅበረሰቡ አባላትና በአንዳንድ በቡዳነት የተፈረጁ ግለሠቦችና ቡድኖች ዘንድ ደግሞ ማኅበረሰቡ አንድን ሠው ቡዳ የሚልበት ምክንያት ከቅናት፣ ከምቀኝነትና ከጥላቻ የመነጨ እንደሆነ ይገልጻሉ። በጣቁሳ ወረዳ በደልጊ ከተማ ያገኘሁት የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪ በትምህርት ቤቱ ቡዳ እንደሚባል፣ ጥቂት ሰዎችም ጥቃት አደረሰብን በማለት እንደሰፈሰፉበት ገልጾልኛል። ቡዳ የተባለበት ምክንያትም በትምህርቱ ጎበዝ በመሆኑ፣ ከአካባቢው የተለየ እምነት መከተሉ እና ይህ እምነትም በማኅበረሰቡ የሰይጣን ተደርጎ መታመኑ፤ እሱን የሚጠሉና የእሱን ስም የሚያጠፉ አንዳንድ ሰዎች ጥቃት አደረሰብን (በላን) በማለት በማስወራታቸው እንደሆነ ይገልጻል። በግሉም ሰው ሰውን ሊበላ የማይችል መሆኑና ቡዳም እንዳልሆነ ያምናል።

በማኅበረሰቡ ልምዳዊ እምነት ቡዳ የሚባሉ ሰዎች በሌሊት ራሳቸውን ወደ ጅብ የመለወጥ አንዳች ሀይል አላቸው ተብሎ ይታመናል። ወደ ጅብ ከተቀየሩ በኋላም ጅብን ይጋልባሉ። ከጅብ ጋር ይጫወታሉ ይባላል። በማኅበረሰቡ ይህንን የሚያሳዩ የተረት፣ የአፈታሪክና የልምድና ገጠመኝ ትረካዎች ይቀርባሉ። አንዳንድ በቡዳነት የሚጠረጠሩ ግለሠቦችና ቡድኖች እንዲሁም ጥቂት

የማኅበረሰቡ አባላት "ሰው ወደ ጅብ ይለወጣል" የሚለው እምነት ፍጹም ሐሰትና ተረት እንደሆነ ያምናሉ። በትረካዎቹ ላይም ሌላ የማፍረሻ ትረካዎችን ያቀርባሉ። ለምሳሌ፣ በማኅበረሰቡ በቡዳነት ከሚፈረጁት ቤተ እስራኤላውን ወገን የሆኑት አቶ ወርቁ መልኬ[71]፣ አቶ ናሁሰናይ አየለ[72]፣ አቶ ዲበኩሉ አየለ[73] በጎረቤቶቻቸው ቡዳ ይባሉ የነበረበት ምክንያት አንዳች የተለየ ሰይጣናዊ ሀይል ስላላቸው ሳይሆን በአኗኗራቸው የተነሳ እንደሆኑ ይገልፃሉ።

ቤተ እስራኤላውያን ኢትዮጵያ ውስጥ ሲኖሩ በየዘመኑ በተፈጠሩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሐይማኖታዊ ችግሮች እና ልዩነቶች ሳቢያ ቡዳ ከሚሏቸው ማኅበረሰቦች ተገለውና ተነጥለው በተራራማ አካባቢዎች ይኖሩ ነበር። መሬት አልባ በመሆናቸው የተነሳም በእደ ጥበብ ይተዳደሩ ነበር። ከሚሰሯቸው እደ ጥበባት መካከል የሸክላ ስራ ይጠቀሳል ((BenEzer, (2005); Flad, (1869); Quirin, (1979); Salamon, (1999); Seeman, (2009))። ይህን የሸክላ ስራ ለመስራትም ቀይ አፈር ፍለጋ በአካባቢው የተለያዩ ቦታዎች መዘዋወር ያስፈልጋል። ይህንን አፈር ለማግኘት ከቦታ የሚንቀሳቀሱት በሌሊት ነው። የዚህ ምክንያት ደግሞ በቀን ከእነርሱ ቡድን ውጭ ያሉ ማኅበረሰቦች አይናቸው ሰው ይበላሉ ቡዳም ናቸው ስለሚሏቸው ነው። በዚህም ቡዳ ከሚሏቸው ሰዎች አይታ እራሳቸውን ለማራቅና ለቡዳ ጥቃት ተጠያቂ ላለመሆን በሌሊት ስራቸውን ያከናውናሉ። በሌሊት በሚሰሩ ወቅትም እንደ ጅብ፣ ቀበሮ የመሳሰሉ የዱር እንስሳት ያስቸግራቸዋል። ነገር ግን ችግር ብልሀትን ይፈጥራል እንደሚባለው እነዚህ ቡድኖች ለስራቸው እንቅፋት የሆነውን ጅብ የሞተ እንስሳ ስጋ በመስጠት እየተላመዱት መጡ። አንዳንድ ሰዎች ከጅብ ጋር ከመላመዳቸው የተነሳ እንደ አህያ ቀይ አፈር ይጭኑት ነበር። ይህንን የተመለከቱ ቤተ እስራኤላውንን ቡዳ የሚሉ ሰዎች "ቤተ እስራኤሎች ጅብ ናቸው" ሲሏቸው እንደቻሉ እነ አቶ ወርቁ መልኬ፣ አቶ ናሁሰናይ አየለ፣ አቶ ዲበኩሉ አየለ ይገልጻሉ[74]። ከዚህ ጋር ተያይዞ አብ ሲኖር ተገኘ አንዳንድ ሰዎች ሌሎች ሰዎችን ቡዳ ወይም ጅብ የሚሏቸው ምክንያት የሰዎችን ስም ለማጥፋት እንደሆነ የሚከተለውን ትረካ በማቅረብ ያስረዳሉ።

---

[71] አቶ ወርቁ መልኬ እድሜያቸው 84 ሲሆን በሰሜን ጎንደር ወገራ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ በአሁኑ ሰዓት ወደ እስራኤል ለመሄድ ከመጠባበቅ ላይ ያሉ ቤተ እስራኤላዊ ናቸው።

[72] አቶ ናሁሰናይ አየለ የ 83 ዓመት አዛውንት እንዲሁም ቤተ እስራኤላዊ ሲሆኑ በአሁኑ ሰአት በእስራኤል ሀገር የቅርዓት መላሂ ከተማ ነዋሪ ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥም በነበሩበት ወቅት በሜን ጎንደር ጭልጋ አካባቢ ይኖሩ ነበር።

[73] አቶ ዲበኩሉ አየለ እድሜያቸው 80 ዓመት ሲሆኑ በአሁኑ ሰአት በእስራኤል ሀገር የቅርዓት መላሂ ከተማ ነዋሪ ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥም በነበሩበት ወቅት በሜን ጎንደር ጭልጋ አካባቢ ይኖሩ ነበር።

[74] ከአቶ ናሁሰናይ አየለ እና ከአቶ ዲበኩሉ አየለ ይህን መረጃ ያገኘሁት ለስራ ጉዳይ ወደ ኢትዮጵያ በ2004 ዓ.ም በመጡ ጊዜ ነበር።

> የአባታችን አበልጅ ነበር። እዚህ ደንገል በር ይኖር ነበር። ቡዳ ነው እያሉ ያሙታል። ሀብታም ነው። በጣም ሀብታም ነው። ከሰዎች ጋር ሙግት ይገጥማል። ተሟጋቱም ይረታል። አንድ ቀን ሻሁራ ከሚባል ሀገር ለሙግት ይሄዳል። የድሮ ሰው መንገድ ሲሄድ ያደርኩ እንደሆን ብሎ ብርድ ልብስ ጋቢውን አጣጥፎ ከበቅሎው ላይ ያረጋል። ከዚያ መሀል የዛ ሰውየ ጋቢ ሳያየው ያ ጋቢው ከበቅሎው ወልቆ ብሎ ይቀራል። የዛ ሰውየ ወደረኛችም ንጋት ላይ ያን ጋቢ ያገኙታል። ያንን ጋቢም በወሰጋታው ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደው የማን ነው ሲሉ ይጠይቃሉ። ያ ቡዳ የሚባለው የአባቴ አበልጆም በቅንነቱ እረ የኔ ነው ይላል። ይሄኔ ወደረኛች ለተሰበሰበው ሰው ትናትና ማታ ጅብ ሲጋልብ ጥሎት ሄዶ አገኘነው አሉ። ይሄ የሰውየውን ስም ለማጥፋት የተቀናበረ ነው (ሲኖር ተገኘ፣ 22/08/03 ዓ.ም፣ ቃለ መጠይቅ)።

በአጠቃላይ የቡዳ እምነትም ሆነ የቡዳ ጥቃት የለም የሚሉ አካላት ሠውን ሠው አይበላም። ሰዎች ሌላውን ሠው ወይም ቡድን ቡዳ የሚሉበት ምክንያት ከቅናት፣ ከጥላቻ እና ከስም መጥፋት ጋር የተያያዘ ነው ሲሉ ይከራከራሉ።

ሌላው በአብዛኛው በተጠኚ ማኅበረሰብ አባላት ዘንድ ተቀባይነት ያለው አመለካከት "የቡዳ እምነትም ሆነ ጥቃት አለ" የሚለው ነው። የቡዳ ጥቃት አለ በሚለው አመለካከት (እምነት) አብዛኛው የማኅበረሰቡ አባላት የሚደስማሙበት ቢሆንም የቡዳ ጥቃት አድራሹን ማንነት በተመለከተ ልዩነት ይታያል። ይህም የሐይማኖት አባቶች፣ በቡዳነት የተፈረጁ ግለሠቦችና አንዳንድ የማኅበረሰቡ አባላት የቡዳ ጥቃት በቡዳነት የሚጠረጠረው ሰው አስቦና አቅዶ በሌላ ሠው ላይ ጉዳት የሚያደርሠው እሱ ሳይሆን በሱ ላይ ያረፈ እርኩስ መንፈስ ነው ይላሉ። በዚህ አመለካከት አራማጆች ዘንድ የቡዳ ጥቃት እንደ እርኩስ መንፈስ በቡዳ የመፈወሻ ስርአት ላይ የሚከናወኑ ድርጊቶች ደግሞ የሠይጣን ተግባር ተደርገው ይቆጠራሉ። ለዚህም ሠይጣን በሰው ልጆች ላይ የተሰጠውን የማሳሳት ሀይል የሚፈፅማቸውን ተግባራት በልምድና በገጠመኝ የተገኙ እና ሌሎች ሐይማኖታዊ ትረካዎችን ያቀርባሉ።

መርጌታ አዳነ አለፋ የቡዳ ጥቃት የሚያደርሰው ሰው በውል ተለይቶ የሚታወቀው (ቡዳ የሚባለው) ሰው ሳይሆን በሱ ስምና ተግባር የተመሰለው እርኩስ መንፈስ ወይም ሰይጣን እንደሆነ በነቸው የደረሰ ያሉትን ተረክ መሰረት አድርገው ይከራከራሉ።

> ለእህቴን የኔ ትገኘ ወንድም ቡዳ ነው ተብሎ ተለፍልፎበት ነበር። ቡዳ እየተባለ ሲለፈለፍበት ታላቅ እህታችን ወንቅሽት ንፀርኤል የሚባል ፀበል ይዛው ሄደች። ሲጠመቅም በእሱ ላይ አድረን ብዙ ሰው እንደበላ አድርገነው ነበር ብሎ ለፈለፈ። ከዛም ለፍልፎና ተጠምቆ ንጹህ እንዲሆን አድርጋ ይዛው ተመለሰች። ዛሬ በእሱ ማንም በላኝ ብሎ የሚፈልፍ ሰው የለም። ዛሬ እሱ ራሱ ቡዳ እያለ ሲላደብ ይውላል። ይህንን የሚያደርጉት አጋንቶች በሰው ላይ እያደሩ እንጅ ሰው ሰውን አይበላው አይደለም (መርጌታ አዳነ አለፋ፣ 10/09/03 ዓ.ም፣ የቡድን ውይይት)።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በቡዳነት የሚጠረጠሩ ሰዎች የሚያደርሱትን ጥቃት በእቅድና በፍላጎት ይሁንኝ ብለው የሚፈጽሙት ሳይሆን እርኩስ መንፈስ በነሱ ላይ አድሮ ባላወቁበት መንገድ

ስይጣን የሚፈጥረው ህመምና ችግር ስመሆኑ አስረጅዎችን ይጠቅሳሉ፡፡ የመጀመሪያው እንደ ማስረጃ የሚያቀርቡት ጉዳይ ቡዳ የሚባሉ ሰዎች  አይታቸውን እንደ መሳሪያ በመጠቀም በጠላቶቻቸው ላይ ጉዳት ያደርሱ ነበር የሚለው ነው፡፡ በዚህም ቡዳ የሚባለው ሠው አስቦበት፣ አቅዶበትና ሆን ብሎ ጉዳት የሚያደርስ ቢሆን ቡዳ እያሉ የሚሰድቡ፣ የሚያገሉ ወይም ሀብት ንብረቱን የሚወስዱ ጠላቶቹ ላይ ጉዳት ያደርስ (ይበላ) ነበር ይላሉ፡፡

አንዳንድ በቡዳነት የሚጠረጠሩ ሰዎች የቡዳ ጥቃት በአንድ ሠው ላይ ያደረ እርኩስ መንፈስ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ በቡዳነት የሚጠረጠረው ሰውም የቡዳነት መንፈስ በላዩ ላይ ማረፉንና ጥቃት ማድረሱን የማያውቅ መሆኑን ራሳቸውን በምስክርነት ያቀርባሉ፡፡ በደንቢያ ወረዳ ቆላድባ ከተማ በቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ፀበል ቦታ ያገኘሁት በቡዳነት የሚጠረጠር ግለሠብ ቡዳ መሆኑን እንደማያውቅ ነገር ግን በአካባቢው ስሙ ከቡዳ ጥቃት ጋር ተዛምዶ የሚጠቀስ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ፀበል ከመጣ በኋላ ግን በላዩ ላይ ያረፈውን መንፈስ ቡዳ መሆኑን እንደተረዳና ከዚህ መንፈስ ለመላቀቅ ፀበል መፃኙን ገልጸልኛል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በስሜን ጎንደር ማኅበረሰብ የቡዳ እምነትና ስለ ቡዳ የሚተረኩ ተረኮችን መርምሮ ማሳየት ላይ ትኩረት አድርጓል። ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስም ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ባላቸው በጽሁፍ ሰነዶች፣ በቃለ መጠይቅ በምልከታና በቡድን ውይይት መረጃ ተሰብስቧል። መረጃዎቹ በጽሁፍ ማስታወሻ፣ በቪድዮ ካሜራ፣ በፎቶግራፍና በመቅረጸ ድምጽ አማካይነት ተጽፈውና ተቀርጸው ተይዘዋል። የተሰበሰቡ መረጃዎችም አውዳዊ ፊለግና የተረክ ትንተና ዘዴን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል።

በተገኘው መረጃ መሰረትም በቡዳነት የሚጠረጠር ሰው አንድን ሰው፣ እንስሳ፣ ተክልና ግዑዝ ነገር ላይ አይኑን በመጣሉ (በመመልከቱ) ሳቢያ በአንዳች ስውር ጥበብና ሀይል ጉዳት ማድረስ የቡዳ ጥቃት (እምነት) እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያሳያል። ይህን ጥቃት በማኅበረሰቡ "በቡዳ መበላት" የሚባል ሲሆን ቡዳ የሚባሉ ሰዎች ጥቃት የሚያደርሱበትን ስውር ጥበብና ሀይል በዘር፣ በተፈጥሮ ወይም በመድሃኒት ያገኙት እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል።

የቡዳ መድሃኒት ማሰር፣ ማሸትና ማጨስ፣ ከብራና ወይም ከወረቀት የተዘጋጀ በውስጡ የተለያዩ ድግምቶች፣ ውዳሴዎችና ሌሎች አስማታዊ ጽሁፎችን የያዘ ክታብን ማሰር፣ እንደ ንቅሳት፣ የጸጉር አቆራረጥና በተለያዩ የሰውነት ክፍል ላይ ጌጣጌጦችን ማድረግ፣ ሃይማኖታዊ ጸሎቶችን መጸለይ፣ ቡዳ የሚባለውን ሰው መሳም፣ ሰላምታ መስጠት፣ መሳደብ፣ ምራቅን መትፋትና የቡዳ ተረኮችን ቡዳ ከሚባለው ሰው ፊት መተረክና የመሳሰሉ አካላዊና ቃላዊ ክስቶች የማኅበረሰቡ የቡዳ ጥቃት የመከላከያ ዘዴዎች ሆነው ተገኝተዋል። እነዚህ የመከላከያ ዘዴዎችም ቡዳውን በማሸማቀቅና በማሳቀቅ እይታውን የመቀልበስ፣ የጥቃቱን መንፈስ የማብረርና የማርከስ ሀይልና ፋይዳ እንዳላቸው ታውቋል።

በማኅበረሰቡ ልማዳዊ እምነት ውስጥ የቡዳ ጥቃትን በመለየት የተለያዩ የፈውስ ዘዴዎችንና ስርዓተ ክዋኔዎችን የሚመሩና የሚፈጽሙ የቡዳ መድሃኒት አዋቂ፣ ቡዳ አስለፍላፊና ፀበል አጥማቂ የሚባሉ ግለሰቦች እንዳሉ ታውቋል። እነዚህ ግለሰቦችም የቡዳ ጥቃትን በእይታ፣ በቃላዊ ምርመራና በሙከራ በመለየት የተለያዩ የፈውስ ዘዴዎችን ያከናውናሉ። እነዚህ የፈውስ ዘዴዎች ሃይማኖታዊ፣ ልማዳዊና ማኅበረሰባዊ እውቀት በሚል ተለይተው የሚታወቁ የተለያዩ ስርዓተ ክዋኔዎች (rituals) ና ሂደቶች ያሏቸው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል። የሃይማኖታዊ

የቡዳ ጥቃት የፈውስ ዘዴ በፀበል አጥማቂው የሚከናወኑ ተያያዥነትና ተከታታይነት ያላቸው እንደ ፀሎት፣ ፀበል መርጨት፣ መንፈስን ማስወጣትና ልቦናን መመለስ የተሰኙ ሂደትና ክዋኔ ያሉት መሆኑ፣ የቡዳ መድሃኒት አዋቂዎችና የቡዳ አስለፍላፊዎች የሚመራው ልማዳዊው የፈውስ ዘዴ ደግሞ መለየት፣ ማስለፍላፍና ልቦናን መመለስ የተባሉ የአፈዋወስ ስርዓትና ሂደት እንዳሉት፣ ማኅበረሰባዊ እውቀት ዘዴ ደግሞ ማንኛውም ሰው የቡዳ መድሃኒት በመያዝ፣ በጋለ ማረሻ በማስፈራራትና ሌሎች ልማዳዊ ተግባራትን በመጠቀም የቡዳ ጥቃትን እንደሚፈውስ ታውቋል።

የቡዳ እምነት አስመልክተው የሚቀርቡ ትረካዎች የማኅበረሰቡን አባላት ግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝ መሰረት በማድረግ "በኔ የደረሰ"፣ "በአይኔ በብረቱ ያየሁት"፣ "ሲባል የሰማሁት"ና "በተረት የማውቀው" በሚል እንደሚተረኩ ታውቋል። ትረካዎቹም ቡዳ የሚባለው ሰው ፊት ለፊት በሚያጋጥም ጊዜ እና በፈውስ ስርዓተ ክዋኔ ወቅት የሚተረኩና የቡዳ ጥቃት የመከላከልና የመፈወስ ፋይዳ ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል።

## ዋቢ ፅሁፎች


ሰሜን ጎንደር ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ። ዓመታዊ ስታትስቲካል መጽሄት። ጎንደር፣ አዋሽ ማተሚያ ቤት፣ 2004።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። መጽሀፈ ሰዋሰው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948።

ከሳቴ ብርሃን።

ደስታ ተክለ ወልድ። ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል። አማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980።

ፈቃደ አዘዘ። የስነቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፤ ኢትዮ ጥቁር ዓባይ አታሚዎች፣ 1991።

Abu-Rabia, Aref. "Evil Eye and Cultural Beliefs among the Bedouin Tribes of the Negev, Middle East." *Folklore*. Vol. 116, no. 3 (2005): 241- 254.

Allison, Randal. "Personal Experience Story" in *An Encyclopedia of Beliefs customs, Tales, Music and art.* California; ABC-CLIO. LLC, 2011, 980- 982

Aspen, Harald. "Sprit, Medium, and Human Worlds: The Amhara pesants of the North Ethiopian Highland and their Tradition of Knowledge." Dissertation. University of Trondheim, 1994.

Barthes, R. and Lionel, D. "An Introduction to the Structural Analysis of Narrative." *New Literary History*. Vol. 6, no. 2 (1975): 237-272.

Bartis, Peter. *Folklore and Field Work: An Introduction to Field Techniques*. Washington: Library Congers, 2002.

Bascom, William R. "Four Functions of Folklore." *Journal of American Folklore*. Vol. 67, no. 266 (1954): 333-349.

______. "The Forms of Folklore: Prose Narrative." *Journal of American Folklore*. Vol.78, no. 307 (1965): 3-20..

______. "Folklore and the Africanist." *Journal of American Folklore*.Vol. 86, no. 341 (1973): 253- 259.

Bauman, Richard "Context" In Richard, Dorson , ed. *Hand book of American Folklore*. Indiana: Indian University Press, 1986.

Ben Amos, Dan. "Context in Context." *Western Folklore*. Vol. 52, no. 2/4 (1993): 209- 226.

___. "Folklore in African Society." *Research in African Literature*, Vol. 6 no.2 (1975): 165-198.

Barber, Paul. "Reversal" in *An Encyclopedia of Beliefs Customs, Tales, Music and Art*. California: ABC-CLIO. LLC, 2011, 1093- 1094.

BenEzer, G. *The Ethiopian Jewish Exodus: Narratives of the Migration Journey to Israel 1977–1985*. London and New York: Taylor & Francis e-Library, 2005.

Cavallaro, Dani. *Critical and Cultural Theory*. London and New Brunswick: The Athlone Press, 2007.

Clark, Mary. "Evil Eye in Southern Italy." *Western Folklore*. Vol. 23, no, 2 (1964): 123- 124.

Dégh, Lind. "Legend" in *An Encyclopedia of Beliefs customs, Tales, Music and Art*. California: ABC-CLIO. LLC, 2011, 772- 781.

______ "Oral Folklore: Oral Narratives." In Richard, Dorson, ed. *Folklore and Folklife: An Introduction*. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Dorson, Richard, ed. *Folklore and Folk Life: An Introduction*. Chicago: The University of Chicago Press, 1972.

_______. ed. *Hand book of American Folklore*. Indiana: Indiana University Press, 1986.

Dundes, Alen, ed. *The Evil Eye*. Wisconsin: University of Wisconsin Press, 1992.

_______."Wet and Dry, the Evil Eye: An Essay in Indo-European and Semitic Worldview." In Dundes, Alen, ed. *The Evil Eye*. Wisconsin: University of Wisconsin Press,1992.

Elworthy, Thomas. *The Evil Eye: An Account of This Ancient and Widespread Superstition*. London, 1895.

Finnera, Naill. "Ethiopian Evil Eye belief and the Magical Symbolism of Iron Working." *Folklore*. Vol. 114, no. 3 (2003): 427- 433.

Freud, Sigmund "The Uncanny" In Simth, Ivan, comp. *Collected Papers*. New York: Basic Books, 1959.

Flad, J.M. The Falashas (Jews) of Abyssinia.Translated by S.P. Goodheart. Londan: William Macintoch, 1869.

Galt, Anthony. "The Evil Eye A synthetic Image and Its Meaning on the Island of Pentelleria, Italy." *Ethnologist*. Vol. 9, no. 4. (1987): 664-668.

Griffiths, J. G. A Protection Against the Evil Eye in Lower Nubia and upper Egypt. *Man*. Vol. 38 (1938): 68- 70)

Goldstein, Kenneth. A Guide For Field Workers in Folklore. USA: Folklore Association Inc, 1964.

Gubbins, J.K. "Some Observation on the Evil Eye in Modern Greece." *Folklore.* Vol. 57, no. (1946): 195- 198.

Honea, K. "Buda in Ethiopia." *Wienner V□lkerkundliche Mitteilugen.* Vol, 4, no. I, (1956): 20- 24.

Hufford, J. David. "Folk Healers" In Richard Dorson, ed. *Hand Book of American Folklore.* Indiana: Indiana University Press, 1986.

Kaplan, S. *The Beta Israel (Falasha) in Ethiopia: From Earliest Times to the Twentieth Century.* New York: New York University Press, 1992.

Leslau, W. *Comparative Dictionary of Geez.* Germen: Wiesbaden, 1991

______. *English – Amharic Dicionary.* Germen: Wiesbaden, 1991.

______ .*Falasha Anthology.* New Haven: Yale University Press, 1951.

Lykiardopoulos, Amica. "The Evil Eye, Towards an Exhaustive Study." *Folklore.* Vol. 92, no. 2 (1981): 221- 230.

Matsuzona, Mario. "Rubbing off the Dirt: Evil Eye Belief Among the Gusii." *Nilo- Ethiopian Studies.* Vol. 1 (1993): 1-13.

McCormick, Kim and Kim, Kennedy, eds. *An Encyclopedia of Beliefs Customs, Tales, Music and Art.* California: ABC-CLIO. LLC, 2011.

Migliore, Sam. "The Sicilian-Canadian Evil Eye Complex". Hamilton, Ontario: McMaster University, 1981.

Mullen, Patrick, "Belief, Folk" In *An Encyclopedia of Beliefs customs, Tales, Music and Art.* California: ABC-CLIO. LLC, 2011, 206- 216).

Mulgoci, A. "The Evil Eye in Romania and Its Antidotes." *Folklore.* Vol. 34, no. 4 (1923): 357- 362.

Oring, Elliot. *Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction.* Logan, Utah: Utah University Press, 1986.

Quirin, James. "The Process of Caste Formation in Ethiopia: A Study of the Beta Israel (Felasha) 1270-1868." *International Journal of African Historical Studies.* Vol. 12, no. 2 (1979): 235- 250.

Reminick, Roland. "The Evil Eye Beliefs among the Amhara of Ethiopia." *Ethnology.* Vol. 13, no. 3 (1974): 279-291.

Ross, Colin. "Hypothesis; The Electrophysiological Basis of Evil Eye Belief." *Anthropology of Consciousness.* vol. 21. Issu. 47-57 (2010): 47- 57.

Salaman, Hagar. *The Hyena People: Ethiopian Jews in Christian Ethiopia.* California: University of California Press, 1999.

Seeman, Don. *One People, One Blood: Ethiopian-Israelis and the return to Judaism.* New Brunswick, New Jersey, and London: Rutgers University press, 2009.

Shelemay, Kay Kaufman. *Music, Ritual, and Falasha History.* East Lansing: Michigan State University Press, 1989.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions.* Utah: Utah State University Press, 2005.

Stahl, Sandra. "The Personal Narrative as Folklore." *Journal of the Folklore Institute.* Vol. 14, no.1/2 (1977): 9-30.

______. "Personal Experience Stories." In Richard Dorson, ed. *Handbook of American Folklore.* Indiana: Indiana University Press, (1986): 306-313

Steven, Samantha. *Psychic Self Defence: Spiritual Prescription for Inner Peace.* Canada: Insomanic press, 2003.

Woodburne, A. Stewart. "The evil eye in south Indian Folklore." In Dundes, Alen, ed. *The Evil Eye.* Wisconsin: University of Wisconsin press,1992.

Vecchiato, N. "Evil Eye, Health Beliefs and Social Tensions Among the Sidama" In New Trends in Ethiopian Studies. Proceedings of the 21[th] International Conference of Ethiopian Studies. Ed. H. Marcus. 1033-43 Asmara, N.J. Red Sea press 1991.

Vansina, Jan. Oral Tradition as History, Madison, Wisconsin: University of Wisconsin Press, 1985.

Young, Allan. "Medical Beliefs and Practices of Begemder Amhara." Dissertation, Philadelphia: University of Pensylvania, 1970.

## አባሪ አንድ የግለሰባዊ ልምድና ገጠመኝ ተረኮች

### ተረክ አንድ

እኔን የገጠመኝ ነገር አለ። በኔ ልጅ ሆኜ አባቴ አውድማ ጥሎ ነበር። ባላንባራስ ሳህሌ ይባላሉ። ሸንብራ ውድማ ጥሎ ሜዳ ላይ ቡዳ እየተባለ የሚጠረጠር ሰው ነበር። ያ የሚጠረጠረው ሰውዬ በዚያን ቀን ከጆቡ ላይ ተሰቅሎ ሲሄድ ታይቷል ማለት ነው። ተሰቅሎ ሲሄድ ከአባቴ ጋር የተኛ አንድ ተኳሽ ያንን ጆብ ሲመታው ሰውየውና ጄቡን በአንድ ጥሎታል። አሁን ወደቀ። ህዝብ ተጠራ እንዲያው ሰውየው አባ ጋገሬ ይባላል። ያ ቡዳ። አሁን አየ ጋገሬማ ከጆብ ጋር ወድቆ ተገኘ ተባለ። ቡዳ ይባል ስለነበረ አሁን ይኸው ተከሰተበት ብሎ ከጆቡ ጋር ያ ሰውየ እግሩን ተመትቶ ጆቡ ሞቶ ይኼ በሚገባ በህይወቴ ያየሁት ጉዳይ ነው። (ደሳለኝ ሳህሌ)

### ተረክ ሁለት

ቡዳ የሆነ ሰው እንዴት ኢጋጥመሀ ብትሉኝ ትልቅ እህቴ የምትኖረው ጭልጋ ጫቆ የሚባል ሀገር ነው። የሷ ልጆች ደግሞ ሁለት ልጆች ወልደው ጥሩ ጥሩ ልጆች ነበሯት። ቡዳ በልቷቸው ነበር። አይለፈልፉም ምንም ሳይሉ ይሞታሉ። እኔ ተወገራ ተነስቼ ለቅሶ ጫቆ እሄዳለሁ። አይናገሩም። አይለፈልፍም። ''ይኼው በዘጠኝ ወራቸው ምንም ሳይሉ በአመታቸው ሞቱ አይ!' ትላለች። እሄ ሳይለፈልፉ ከሞቱ እማ ቡዳ አይደል አልኩ። ምን አይነት ነገር ነው ስል ቡዳማ የምትጠረጥር አንዲት ሴትዮ ከደንቢያ መጥታ የተጋባች ሴትዮ አለች። ያገባት የኔ ዘመድ ነው። ከዚህ ከደንቢያ ነው የወሰዳት እሷ ትሆናለች ብየ ጠረጠርኩ። እንዴት እናድርግ እሷን በሀይል ይዘን መጠቀም አስበን አልንና ተማከርን። እሷን እንያዝና መድሐኒት እንጋታት ተባብለን ተማከርን። መድሐኒት አለ የቡዳ መድሐኒት ብዙ ሰዎች የሚያውቁ አሉ። ያንን መድሃኒት ሰው አሰባስበን ልናጠጣት ባልን ጊዜ ከነባሏ ጠፋች። ጠፋችና አመለጠች። በዚህ ቡዳ መሆኗን አረጋገጥን። (መንገሻ ስዩም)

### ተረክ ሶስት

እኔ በአይኔ ያየሁት ነገር አለ። አንዲት ሰው በቡዳ ተበልታ እዚህ አካባቢ ማለት ነው። እዚህ አካባቢ ነበር ቤቱ አንዲት ልጅ ተበላች። የቀን ሰራተኛ ናት። ልጅቱ እትሁን ትባላለች በቃ በጭሩ። ሰውየው በልቷታል። እንግዲህ አንድ ቡዳ የሚያስለፈልፍ ሰው ነበር። ሲራወጡ እየሁና ሄድኩ በጫው አካባቢ። ምንድነው ብየ በምጠይቅ ጊዜ እረ እትሁንን ቡዳ በልቷት ብለው

በዚህ ወደ ድርማ ወንዝ ወስደው ይህን መድሃኒት ይሰጧታል። በኋላ ድምጿ የሰውየውን የወንድ ነው የምትለፈልፈው። "ከምን አገኙኃት" ሲሉት እንደዚህ ያለ ቦታ ላይ ይላል። "አፈልጋታለሁ ለስራ ትጠቅመኛለች" ይላል። በቃ ድመጿ እሱን [ቡዳውን] በአካል ነው። የሰውየውን ድምፅ ሳይቀር ሰልቦ ይዞ የሚሄድ ነው ቡዳ ማለት። ድምፅ ሁሉ ይሰልባል። አሁን ይሄን መድሐኒት ምናምን ብለው ሲያወጡ፣ ሲያወርዱና ሲያጠጧት ወዲያውኑ መሻሪያ ምስ የሚባል ነገር አለ። ምሴ የአህያ ገጣባ መላስ ነው አለች። አህያ ፈልገው አንድ አለ አያ አስማማው የሚባል ሽቃጭ (ነጋዴ) የሱን አህያ ወስደው እንደዚያ አድርገው ያ አህያ ገጣባ መሻርያ ሆነ፣ ዳነች። አሁን ሴትዮትም አለች የማውቃት ናት። (አጥቢያው አስረስ)

## ተረክ አራት

በአንድ መንግስት ጊዜ ነው አሉ። ያን ግዜ እኔ አልነበርኩም ሲባል ነው የሰማሁት። አንድ ሰው የዚህ ወረዳ አስተዳዳሪ ነበሩ። ቡዳ አትበሉ እያሉ ያወግዛሉ። በመጨረሻ ግዜ ሰራተኛቸው ትበላለች። አሁን ምንድን ነገር ያድርጉ። በቃ ሌላ ነገር ማድረግ አልቻሉም። የበላት ሰውዬ እንዲመጣ አደረጉና አዘዙ። ቡዳ የተባለው ቢሄዱ ሁሉ አጡት። ያው ከቤቱ ሁሉ ጥይት ተኩሰው ሰውየውም አምልጦ ሄደ። ኃላፊዎች ሁሉ ቡዳ አትበሉ ይላሉ። ሲደርስባቸው ግን ይላሉ። ሁሉ አልደረሰበት ሆኖ እንጂ (ሲደርስበት) ቡዳ ይላል። (አጥቢያው አስረስ)

## ተረክ አምስት

እኔ ደግሞ የማምንበትን ልንገርህ ስምንት ልጆች አሉኝ። ከወገራ ተነስቼ በስራ ምክንያት ተዛውሬ ስመጣ ቤቴም እዚች ነው ተከራዮቼ የገባሁ። ያ ቡዳ ነው ተብሎ የሚጠረጠር ሰውዬ ሰራተኛ ነው፣ ተሚጋች ነው። ከኔ ቤተሰብ ጋር በጣም ወዳጅ ሆነ። ወተት ጠዋት ጠዋት ይዞ መምጣት። ተጠራጠርኩና ይሄ ሰውዬ ቀርቦ እንግዲህ እነዚህን ውጫጮች [እንቦቀቅላ ህጻናት ] ሊፈጃቸው አይደል አልኩ። ቡዳ መድሐኒት ከሚያውቅ ሰው ሄድኩ፣ የቡዳ መድሐኒት የሚያውቅ ሰው ምን አድርግ አለ። "አሁን እንግዲህ ጥሩ ጠላ አዘጋጅና በዋንጫ ውስጥ በማር አድርገህ ከነኑ አስቀምጠው። ለአንተም ለሱም ጠላውን በተመሳሳይ ዋንጫ አስቀምጠው። ከጠጣ (ቡዳ) አይደለም ካልጠጣ ግን ቡዳ ነው አታቅርበው" አለኝ። አመጣሁ ያንን [የቡዳ] መድሐኒት። አፈር ይቅለለው ፈንታሁን ለማስረጃ ነበሩ። ተገኝ የሚባል ጓደኛም ነበረኝ። ለማስረጃነት እነሱን ቁጭ አድርጌ ጠላ መጣ። ለነሱም ከነሱ ዋንጫ ሁሉ ያንን መድሐኒት አደረኩበት። እነሱ አያነሱ ጠጡ። እሱግን ሊጠጣልህ ነው፣ በቃ መልስም የለም ዝም።

አልጠጣም። ተቅበዘበዘ። ከዛ ሮጠ። ወጣና ሮጠ። እየተበሳጨ ሮጦ ሄደ። ከዚያ ወዲያ ወዳጅነቱም ቀረ ሰውየውም አሁን እስ ዛሬ። ይንን በአይኔ አይቻለሁ። (መንገሻ ስዩም)

## ተረክ አምስት

የባላባት ልጅ ነው። የትልቅ ሰው። ቤተሰቡን በሙሉ በላ ከአባታችን ቅድም እንደተባለው የሚበላው ከብቶችንና ህፃናትን ነበር። አይታወቅበትም በዛን ሰዓት። አሁን ግን ከዕለታት አንድ ቀን አራሷን መገጭ ወንዝ ውሃ ቀድታ ስትሄድ አግኝቶ በልቷት በዛች ተከሰተበት። ከዛች ቀን ጀምሮ ብዙ ሰው እየበላ ተሰፈሰፈበት። ጉራንምባ ሚካኤል ላይ እንደነዚህ ያሉ አባቶች ተመረጡና የራሱ ቤተሰቦች የን ተባባል ይርዳው የእህት ልጅ ነው። የቀኑብሽ እምሩ ልጅ ነው። እሱ ውዛባ ሚካኤል ላይ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተወግዞ ተባለና ተያዘ። በራሳቸው በባህላቸው ቤተሰቡም ጋር ሁነው ይህን ነገር [እፅ] ጣል ሳትጥል ግን ልጆችህ ካልተማሩ ሚስትህ ካላስተማርካት ከሀገር ይቀመጣሉ አንተ ግን ሀገር ትለቃለህ። ትሰደዳለህ ተብሎ አሁን ያ ሰው ተሰናበተ። ተባረረ። የለም አሁን ከቀበሌዎችን ልጁና ሚስቱ ግን አለች። ይህን ሰውየ በጨለማ ብታስወጭ ብታስገቢ ከዕለታት አንድ ቀንም ብትያዥ ግን አንቺም ከሀገር ትሰናበቻለሽ ተባለች። የቀበሌ አስተዳዳሪ ስራ አስኪያጅ ባለችበት አገሩ ሁሉ ሽማግሌዎች ተፈራርመው ከአገሩ አሰናበቱት። ለቀቀ። አሁን የለም። አሁን አገሩ ሰው ሁሉ ጤነኛ ነው።

## ተረክ ስድስት

እኔ ወደገበያ እሄዳለሁ ሚስቴ አብራኝ ትሄዳለች። ወደ ገበያ እየሄድን እህያ ጭኖ አንድ ሰው በዚያ በመኪናው መንገድ ሽቅብ ይሄዳል። ታድያ እንዲህ እንዲህ (ጭንቅላታቸው ግራና ቀኝ እያዞሩ) እያለ ያያል። ደሞ ወደኛ ያያል። ሚስቴ ጠጉሯን እየፈታች ትሄዳለች። ዘወር ብየ አይቼ አንቺ ለምንድነው መንገድ ላይ ፀጉርሽን የምትፈች እላታለሁ። ስቆጣት እንደገና ትተዋለች። 'በኋላ እውነቱን እኮ ነው' ብለው እናቲቱ ይቆጣሉ። አሁን ያ ሰውየ አልፎ ሄዴ። ጎለቻ [ጥምጣም] አዲስ ጎልቻ እዚች (ጭንቅላቱ) ላይ አድርጓል። በልብሱ እንዲህ አድርጎ (ወደ ብብታቸው እያመላከቱ) አኮፋዳ ይዟል። ሱሪው ሞዳ [አዲስ] ናት። አስተውየዋለሁ። ራሱን በጫሽ ጠምጥሟል። በኋላ ሄደን ውለን ገበያ ተመልሰን እንመጣለን። መጥተን ሚስቴ ከቤት ስትደርስ እንዲሁ ተበሳጨች። ምን ሆንሽ ስላት አንዱን ጭብጥ! አንዱን ለቀቅ አንዱን ጭብጥ አንዱን ለቀቅ ታደርጋለች። ስታደርግ እሃ ይሄ ነገር ምንድር ነገር ነው አልኩና አንስቼ ባህል እስ ይሄማ ቡዳ ነው አልኩ። ያን ሰውዬ ጠረጠርኩት። ቡዳ ነው አልኩና ጣሪያ ላይ

ያለውን [መድሐኒቱን] አምጥቼ አሽተትኳት። ሳሽታት 'እኔ ነኝ አለ። ያ ሰው። ምንድን ይዘህ ነበር እስቲ ምልክቱን ተናገር? አልኩ። 'ሞዳ ነው ሱሪዬ፣ ጎልቻየን [ምንጣፌን ] እዚህ አድርጌ ነበር'። ከምን ኖረህ ነው? 'ጎርጎራ ዘመድ ጥየቃ ሄጀ አሁን ወደ ሀገሬ እሄድኩ ነው'። ወዴት ነው ሀገርህ? 'ወገራ'። አይ የዛን ጊዜ ፀጉሯን እየፈታች አየኋት የዛን ጊዜ ቀሰምኳት። ይህን ሲል እንገዲህ ይህን ሰውዬ አይቼዋለሁ። እሷም በዚህ ለፈለፈች። ምስህ ምንድን ነው ተብላ እንዲህ ያለ ነው ምሴ አለ። ካለ በኋላ ጤናዋ ተመለሰላት።(መስፍን ከበደ)

## ተረክ ሰባት

ቡዳ የሚለውን የኛ መፅሐፋችን ርኩስ መንፈስ ነው የሚለው። ርኩስ መንፈስ ማለት አዳምና ሄዋንን አሳስቶ እፀ በለስ አስበልቶ እኔ አምላክ ነኝ እንደ አምላክ አመስግኑኝ ቢል ዳቢሎስ ከሱ ጋራ አምላክ ነው ያሉት እግዚአብሔር ተቃወማቸው። እናንተ እንግዲህ የኔ ጓደኛ ከሆናችሁ ከዚህ መኖር የለባችሁም ብሎ ወደ ምድር ጣላቸው ይላል። ወደዚህ ምድር። እነሱ የአየር ጋኔል ነው የሚባሉት። ተፈጥሮአቸው ግን መላይክት ናቸው፤ እንደ ሚካኤል እንደ ገብርኤል ከነፍስና ከአየር ነው ተፈጥሮአቸው። እነዚህ ከዚህ ምድር የመጡት ለኛ ለአዳም ልጆች ተቃራኒ ሆነው። ቡዳ ይሆናሉ። ወባም ይሆናሉ። በብዙ የአዳም ልጅ የሚበክሉ አጋንንት መንፈስ ርኩስ ይባላል። ርኩስ መናፍስት ይላቸዋል- መጽሐፋችን። እነሱ ሰውን ቡዳም በአይናቸው ሰውን ይበላሉ። (ቄስ መላእክ ሰላም ተውህቦ ማሩ)

## ተረክ ስምንት

እኔንም በልቶኝ ነበር። በተለይ፣ በተለይ ዲያቆን ሳለሁ የአባቴ ቤት ሰባት ወጋግራ የሳር ቤት ነው። አሁን ታመምኩ። ታምሜ በሰባቱ ወጋግራ የሚጠረጠሩት ቡዳ የሚባሉት ሰዎች በሰባቱ ወጋግራ ቆመዋል። ቆመው ይታዩኛል። ኋላ መጨረሻ አንዱ እንዲያው በጦር ጫንቃዬን ወጋኝ። ወግቶኝ ድኘ ቄስሉ መንፈት ቆየ በግልፅ በእውነት አም ሰውዬውን በአየሁት ቁጥር ስፈራው እኖር ነበር አሁን ሙቷል። እንደገና ደግሞ አንዲት ካይላ የምትባል ካይላ እንለው ነበር ይህን ቤት እስራኤል። እነሱ ይባላሉ ነው የሚባል። አንዲቱ ደግሞ ሴት ናት እሷ ደግሞ ከአንዱ ወጋግራ ቆጭ ብላ ጥርሷን ሃም ሃም ትለኛለች። እመመኝ። አንዱ ደግሞ ጥቁር ሰውዬ በአንዱ ወጋግራ ቆሞ ደግሞ ጥርሱን ግጥጥ ግጥጥ ሲያደርግብኝ ያመኛል። ሃም ሃም ሃም እያለ በጦር ወግቶኝ ሄደ። በጦር የወጋኝም ድኚ እነዚህ ወንድሞቼ ሁሉ እስተ መንፈቅ እዚህ

ጫንቃዬ ላይ ቆስሉ ዳነ። ይህን የመሰለ ነው። እርግጥ [ቡዳ] አሉ አጋንንት ናቸው። (ቄስ መላእክ ሰላም ተውህቦ ማሩ)

## ተረክ ዘጠኝ

በልጅነቴ አንድ የበኩር ልጅ ነበረኝ። የቡዳ ታሪክ ነው እንግዲህ። ታዲያ ማለዳ እኔ የለሁም። ማሽላ ጥበቃ ከሄድኩት ያች ቡዳ የምትባል የምትጠረጠር ሴት ባለቤቴ እሷ እሚታዋ [አያትዋ] ቤት እሳት ልትጭር ሄዳለች። እሱ ተኝቶ ኖሯል። ኋላ ተኝቶ ቆይቶ ብድግ ቢል እናቱ የለችም። እራቂቱን መሰስ ሲል ያች [ቡዳ] ጤፍ አበድሩኝ እያለች መጥታ ገጥመዋለች፤ አይታዋለች። ወዲያው በልታዋለች። ኋላ ከዋልኩት ውዬ ካደርኩት አድሬ ብመጣ ማልዳ ቁልምም ብሉ ተኝቶ። ወትሮ ድምጼን ሲሰማ ብድግ የሚለው ቁልምም ብሎ ተኝቶ። አንቺ ምን ሆኖ ነው ስላት 'እረ መጣችብኝ አይጢቱ' እያለ ሲባባ ነው ያደረ ትለኛለች። ማን መጥቶ ኑሯል? እገሌ መጥታ ነበር። ወት [የት] ሄደሽ? አንቺ ከነ አባ ቤት እሳት ልጭር ሄጄ እሷ ጤፍ አበድሩኝ ብላ መጥታ ራቂቱን ቁሞ እሷም ቁማ አገኘኋቸው። ሲባባ አደረ። ኋላ አዬ አዬ ብዬ ተነስቼ እንዲያው መድሐኒት ፍለጋ ስሄድ አንድ ሽማግሌ እንዲያው እርር ብዬ ደንግጫለሁ። አዲያ አልጠረጠርኳቸውም። 'አንተ ልጄ ምን ሆነህ ነው?' አሉኝ እረ ልጄ ታሞብኝ ነው አልኳቸው። 'ምን ሆነ?' አሉኝ እንዲያው አይጢቱ በላችኝ እያለ ሲባባ አደረ በዚህ ታሞብኝ እላቸዋለሁ። እረግ እረግ አሉና እስቲ ብለው እንዲያው አኮፋዳይቱን አውጥተው ከዚያ ከአኮፋዳው ቅጠል የሚመስል ነገር አወጡ። ያችን ቅጠል እሽትሽት አደረጉና ከአፍንጫቸው አሽትተው 'ይህችን ይዘህ ሂድና አሽትተህ አስረለት እና እስተ እድሜ [እስከ እለተ ሞቱ] በጠንካራ ማሰሪያ አስረህ ጠብቀው' ብለው ይሰጡኛል። ወስጄ ያችን አሽተዋለሁ። ወዲያው ቀጥ አለ። ወዲያው ቀጥ! ዳነ። ከዳነ በኋላ ጎበዝ ሆኖ ትልቅ ሆኖ እየተራወጠ እያለ ከጓደኛው ጋር በቀለሃ አግብቼ በአረብ [ቀይ ቀለም ባለው ቆዳ] ሰፍቼ ከአንገቱ ላይ አስርለታለሁ። እንዲያ ደህና ሆኖ ያደገው ልጅ አንድ ቀን ከጓደኛው ጋር ሲሯሯጥ ያች የቡዳ መድሐኒቷ ተቆርጣ ትጠፍለች። ያች የቡዳ መድሐኒት መጠበቂያው ጠፋች። ወዲያው ለቀም። ወዲያም ታመመ ሌላ መድሐኒት ቢፈለግ ቢለፋ ቢባል ሳያድነው ቀረ። እንዲያ ብሎ ሞተ። ገደለችው ያች ቡዳ። (አቶ አስናቀው ዘሪሁን)

## ተረክ አስር

እነዚህ ቡዳዎች ስራቸው ብዙ ነው። እኔ ደግሞ አንድ አባትዬው በላኝ ብየ ቅድም ነግሬሃለሁ። አሁን ልጆዬው እለ ልጆዬው ኣመት በእል ሲጠራኝ ከቤቴ ይመጣል። መጥቶ ጥሩ የእንቦሳ እናት ላም አለችኝ። እሷን እያሰብኩ ትክ ብሉ አይቷት ሄደ። ማታ ደም ታሰበች! ማታ ደም

ታሰበች። ያ ሰውዬ አሁንም አለ ቡዳ ነው የሚባል። እኔም ምንም አላረኩም የላሚቱ ጡት ወተቷም ደርቆ ቀረች። እንዲያው ወተታም የነበረችው ድርቅ ብላ ቀንሳ ቀረች። ሰልቧት፤ ያ ቡዳ በልቷት። (ቄስ መላእክ ሰላም ተውህቦ ማሩ)

### ተረክ አስራ አንድ

አሁን ለኔ ደርሶኛል። አንዲት ሴት የኔ ባለቤት ዶሮ ትሰራለች። ዶሮ እስከ እንቁላሉ ስትሰራ አንዲት ሴት ትክ ብላ አይታት ሄደች። እንዳታቀምሳት ገና ወጡ አልወጣም። አሁን ያችን ዶሮ በላን። አስጠላኝ! አስጠላኝ! እንዲው የዶሮ መረቅ ሲሸተኝ ያመኛል። ያመኛል። ከሰው ስለዚህ ነገር መጠየቅ ማጠያየቅ። አሁን አንድ ሰው ያችን ሴትዮ የምታውቃት ከሆነ የዛችን ሴትዮ ጨርቅ ፈልገህ በእሳት አቃጥለህ ታጠናት አለኝ። ፈልጌ ጨርቋን አምጥቼ ብታጠነው ለቀቀኝ። ዶሮየን በላሁ። ያች ያየችኝ ሴትዮ አይኗ ባርጤዛ ነው።

### ተረክ አስራ ሁለት

እናቴ ትንሽ እህቴ ገበያ ሄዱ። ታድያ ከዚያ ጠዳ ገበያ እናቷና ልጅቱ ሄደዋል። ያን ጊዜ እስራኤሉ ነበር ቡዳ የሚባል። ከዚያ ገበያ ውላ መጥታ። እናቷ ትታመማለች። እናቷ ታማ በሦስተኛው ነው በአራተኛው ቀን ሞተች። የዛን ጊዜ አብራ የነበረችውን ልጅ ያማታል። እንዲህ እንደ ወባ ክፍት ክድን [ድርስ ምልስ] እያደረገ ያማታል። ቀን ቀን እያነዛነዛትና እያስጣለባት አንድ ወር ቆየች። ሰላሳዋ የእናታችን ሰላሳ ደርሶ ሰላሳዋን ስናሳልፍ ልጅቱ ገቢያ ሄዳ ገብይታ ትመጣለች። ገበያ መጥታ አገኛታለሁ። ከከተማው ጠላ አማረኝ ትላለች። አይ ከቤት ጠላ አለ አይሆንም አልኩና ዝም በይ ነይ ከቤት አልኩና ይገርት መጣሁ። ከቤት ደረስን። ኩርምት ብላ ተኛች። ጥቅልል ብላ ተኛች። ጠላ ስጧት ብዬ ያችን ጠላ ቅምስ ስታደርግ ሳብ ሳብ አድርጋ ጠጣችው። ደርሳ ክርትም ስትል እንዲያው የዛን ጊዜ እናቲቱን ስንቀብር ከእናቷ እጅ ላይ የቡዳ መድሐኒት ታስሯል። ያን ፈትቼ በኪሴ አኑሬ አንድ ወር ተቀምጧል። ያን ምዝዝ አደረኩና ወስጄ ሳሸታት ባባች። አይኗ ሌላ ሆነ። እስቲ ትክክል እዩ ስላት እዛም ማየት እዚህም ማየት። እሄ! ይሄማ ቡዳ አይደል አልኩና ስር ከሚምሱት ሰዎች ሮጬ ሄጄ አምጥቼ ሳሸታት አይ ወይኔ አለ። ለፈለፈ። ኋላ ከምን አገኝኃት ስለው ማክሰኞት ገበያ ካይላይቱን ሸክላ ገዝታ ከእናቷ ጋር ውሃ ቀድታ ስትመጣ ነው ያያዝኳት። አሁን ሸክላይቱ አለች ሳላይህ አልኩት። አልተሟሸችም። ያች ሸክላ ኬሻ ለብሳ በዚያ አለች። አሁን ጨለማ ነው ማን ነህ? ስለው ጊዜ ንጉሴ ነኝ አለ። በል ተናገር ምስህን አልኩት 'እህያ ገጣባ

ነው' አለ። ከምን ይገኛል አልነው? 'ልቀቀኝ እኔ አገኘዋለሁ' አለ። ሮጣ ታመልጣለች አልንና ይኸው ከሱ ጋር [አጠገባቸው ያለን ሰው እየጠቆሙ] ወንድሜ ነው በመጫኛ (በገመድ) አስረንና ሂድ አልነው። እህ ከምን ሊገኝ ነው ብዬ እንዲያው ጨንቆኝ (ሳቅ) ኋላ ግማሽ ስንደርስ እሬ ልቀቁኝ። አይ ወይኔ! አይ ወይኔ! እያለች ዝል ዝል ትላለች። አቸፈሬው ወንዝ አጠገብ ነጋዴዎች አህያቸውን ይዘው ኑግና ተልባ ይዘው ያድራሉ። የዛን ቀን አላየሁትም ለካ ከመሸ መጥተው ሰፍረዋል። እዛ በቅሉዎች አሉ አህዮችም አሉ። እዚያ አጠገብ ስትደርስማ እንዲያው እንደ ጆብ ዝል ብላ ሄዳ አህያውን ለቀም። አህያውን ብናይስ ገጣባ አህያ። ያን ገጣባ ሳስ ሳስ አድርጋ ውህ ውህ አለች (በረጅሙ ተነፈሰች)። በኋላ እኔ ማን ነኝ ስላት 'ወንድማለም' አለች። ይሄ እሳ? 'ጥላዬ'። ይሄሳ? 'ሽሜ' ያዝናት ምንሽን ያምሻል? 'እንዲያው ምንም አይታወቀኝም ልቤን ድው ይልብኛል።' አለች። እንዲያ ብላ ያውላችሁ፣ በወሩ ታወቀ። እናቷ በሞተች በወሩ። እናቷንም የበላሁ እኔ ነኝ፣ የገደልኳት አለ። እንዲያውም የቀበርን እለት ጆቡ እዚያ ከበሩ ላይ እንደ ጮኸ አደረ ጆቡ። አዲያ አባ አርአያ ፍርንስን ቡዳ ነው በልቷት ያለ እለ።

## ተረክ አስራ ሦስት

እንዲት ጨቅላ የልጅ ልጅ ናት። ሳልጅ ነው የተወለደችው። እናቷን ከድታ እናንዬ [እናቴ] ብላ ተጠግታ ትመጣለች። አበባ ነው 'ምትመስል። ያችን አሽከር ጀሪካይቱን ገዝቼ፣ ልብሲቱን አልብሼ በይ እንግዲህ አሳድጌ ሳስተምርሽ ነው ብየ አምጥቼ ብር ብር ያለች ናት። ለካስ ስትሄድ ከመንገድ አግኝቷታል። ውሃ ቀድታ ስትመጣ። ያው የመንደራችን ሰው ነው። ኋላ የዛን ጊዜ ሰውነቱ ሽብር ሽብር አለብኝ አለች ያች አሽከር ያን ውሃ ቀድታ ስትመጣ። አሁን ታመመች። ተያዘች። ይህን ቅጠሉን ምናምን ስናሽታት አልቀበልም ትላለች። ኋላ ደህና መድሐኒት ፈልገን ብናሽታትስ እሬ። እገሌ ነው የበላኝ አለች። ከምን አገኝታት "እጨየ ስትሄድ እሷ ውሃ ስትሄድ እዚያ ነው ያገኘኋት" አለ። የመድሐኒያለም ያለህ እረ ምን አደረኩህ እናቱ አንተ አሁን ብየ እኔም ዳገም ሳይደርስ ምሉ ሄደ። አሁን ለካ ቅሬታ አለው ምስ ኖሮት፣ ምስ ስናደርግ ወዲያው ማታ ከች፣ ማስለቀስ፣ ማስፋሸግ ወጥቼ ልሄድ ማለት። እንዲያው ፊሷን ዋገ ዋገ ማድረግ። ደግሞ (ሳቅ) አወይ አፈር ያብላው ያማ ቡዳማ ወራዳ እኮ ነው። ኋላ ደረጀ ታከለ የለም ነበረና ማታ መጣና ማረሻ አግሉ፣ እሳት አንድዱ አለ። ማረሻ ተጋለ፣ መድሐኒት ተያዘ፣ ወግዱ እናንተ ይዣት ነው የምወጣው አለ። ይዞት ወጣ እንዲው እርም ነው የምታህል አይ እናቴ አይ ግሩም። ዛሬ ይሰብክኛል የዛች አሽከር ነገር፣ አሁን ያችን ያዙና እንጠልጥለው

ፍዳ አሳዩኣት። ልፍልፍ፤ ልፍልፍ፤ ንግር፤ ንግር። ከምን አመጣኸው? 'ከእንዲህ ያለ አገር ድርማ እምጥቼ ነው የጠጣሁት። አጠጥተውኝ ነው' አለ። 'እረ ጓደኛም ነበረኝ። አንድ ነበር ሞቷል። አሁን እሱ እምጥቶ ነው እኔ የጠጣሁኝ አለ። አሁንስ አትለቃትም? አሉት። አለቃለሁኝ። ምስህ ባእህያ ፋንድያ ያቺ አሽከር ተደብቃ ተቀበረ። በይ ሂጅ ሲላት ሄደች። ከዚያ ገድም ሄዳ ያን ፋግር ፋግር [ቆፈር] አድርጋ ቃም ቃም አደረገች። መልሰህ ትፋው ተባለ። እኔ አለቀስኩ። አባቷ ጠንካራ ነበር። የግድ ወዲያው አንጠልጥሎ ይዟት ሄደ። ቸንከር ተከለ ሃይማኖት ጠበል ይዟት ሄደ። አምስት ቀን አስጠምቆ ሙታል እንጂ አሁን። ያች አሽከር አሁን ታማሚ ሆነች። ልቧንም ሰልቧት ሌላ ሌላውን ተጨምሮባት ታማሚ ሆና ቀረች አሁን ሳልጆ ነው ያለች። አለች መቼም መኖር አይደልም። አይ ዛሬ ልቧን ደግፉ ውህ ትላላች። አወይ ዛሬ እንኳ የማይተውኝ ትላለች።

### ተረክ አስራ አራት

[ቡዳ በልቶሽ ያውቃል አንቺን?] አዎ ]መቼ በቅርቡ ወይስ?] እረ ቆይቷል። መጀመሪያ ልቤን ካድ ካድ አደረገኝ። ወደ ታች ይዞ ጭልጥ ጭልጥ ነው የሚለው። ልብህ ያመልጥሀል። ጭራሽ ድከም ይላል። ከዛ ሰው ማየት አልፈልግም። ሰው እንዲያየኝ አልፈልግም። እ..እ ጫማ አናጢስ ምና ምን ሲሉ ልቤ ፍርት ፍርት ይላል። እፈራለሁ። እና ጫማ ሊያጨሱ ሲሉ ወጥተሽ ሩጭ ወጥተሽ ሩጭ፤ አትያቸው አትያቸው የሚለኝ ነው የሚመጣው- ጫማ ወይም አንትን ሊያጨሱ ሲሉ። እና እነሱ ሲነግሩኝ እንደዚህ እንዲዚህ ብለሽ ነው የለፈለፍሽ ምናምን አሉኝ። እኔ ግን አይታወቀኝም። ስለፈልፍ ትዝ አይለኝም። ምንም አይታወቅህም። ምን እንደበላኝ፤ ምን እንዳልህ፤ እንደታመምክ አይታወቅህም።

### ተረክ አስራ አምስት

ጥቅምት ላይ የኔ ሁለቱ ላሞች ወለዱ። ወልደዋል። ይመገባሉ። ይሄ ጡታቸው ጋታቸው በደንብ አምሯል። ይዟል። አሁን እየተነዱ ወደ ምግብ ሲሄዱ አገኛቸው አጋጣሚ። ያ የሚጠረጠረው ሰውዬ "ወልደውላችሁ እነው?" አለን። አዎ አልነው። ከዚያ "ደህና ደህና ሆነውላችኋል" አለ። ያው ማታ አንዷቷ ላም ሁለቱ የመኸር ጡቷ እንዳለ ቅትት ብሎ ነው የመጣው። ማታ እንዲህ ሳልብ ስል ደም ነው የፈሰሳት። ደም ፈሰሳት። ጥዋትም ማታም ብል ያው ደም ብቻ ነው። ያው ሀኪም ቤት አመጣኋት። የሚቀባ ነገር ሰጣት። ምንም ግልፅ

አልሆነልኝም አለ ሀኪሙ። ያ ደም ሲፈስ ውሎ ሲፈስ አደረ። ከሦስተኛው ቀን በኋላ ደምና ወተት እየተቀላቀለ መጣ ከዛ በኋላ ኖርማል ሆነ።

### ተረክ አስራ ስድስት

ተረት ተረት። በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሁለት ልጆች ነበሩ። የአንዷ ልጅ እናት ቡዳ በልቷት ሞታለችና ተቀበረች። ነገር ግን በተቀበረች በሦስት ቀኑ ቡዳው ወሰዳት ከቤቱ ከዚያ የተደገመባት ለበቅ [አለንጋ] አለች አሉ። ያችን ለበቂቱን በለበቁ ሄዶ ጋኑን ሾጥ ሲያደርጋት ሴትዮዋ ትቆማለች። አዙሮ ደግሞ ሴትዮቱን በለበቅ ሲላት ጋን ትሆናለች። ቡዳው ይሄን ሲያረግ ልጁ ታያለች። ደሞ እናቷ በቡዳ ተበልታ የሞተችባት ታያለች። ኋላ ሲኖሩ ሲኖሩ ከዛ እንደ አጋጣሚ ልጅቱ ጎረቤት ስለሆኑ እስቲ ጋንህን ስጠኝ ትለዋለች። እረ ምን ጋን አለኝ ሲላት ያችን እናቲቱ የምትሆነን ጋን ሰጣት። ከዛ ቀስ ታደርግና ትወስድና የተደገመበትን ለበቅ ወስዳ ከቤቷ ላጥ ብታደርጋት እናቷ ቀጥ አለች ነው

### ተረክ አስራ ሰባት

እዚህ [ፀበል] በቡድንት ተጠርጠርኩ መጣሁ። ይለፍለፍ አይለፍለፍ አላውቅም ተጠርጠርኩ መጣሁ። የሀገር ሽማግሌዎች ናቸው ያመጡኝ። ከዚህ ከመጣሁ ሁለተኛ ወሬ ነው። ማውቀው ነገር የለኝም። የሰማሁትም ነገር የለኝም። ብቻ ታማህ [ቡዳ ሲሉኝ] ሲሉኝ ተናድጄ መጥቻለሁ። ቡዳ መባሌን ስሰማ አንቀጠቀጠኝ፣ ሰውነቴን ሰበከኝ። ይህ ነገር ጥቅም አለው ብየ ፀበል መጣሁ። ከእኔም ውጭ ከሌላ ቀበሌ አስራ ስድስት ሰው እው እረ እያሉ ተበላሁ ብለው መጥተው ከአባ ተፈውሰው ሄደዋል። የተበሉ ሰዎችን ፈውሰዋል። እገሌ በላን እያሉ የበላቸው ሰውዬም መጥቶ ተፈውሷል። እኔ የኔመጣሁት ጭልጋ ወረዳ ነው። ከአጨዳ፣ ከገበያ ሆነ ከሰለቅሶ ተለይቼም አላውቅም። በቃ እራሴ ይህንን ነገር ስሰማ ነው ተናድጄ የመጣሁ። [ማን ነበር የነገረዎ?] እንዲህ ሰው ሲከናነብ አየሁ። ኩታውን ክውን ሲያደርግ። እ.. ምንድን ነው ይሄ ነገር ብየ መጣሁ። እንዲያው ሰው ልብሱን ክድን ሲያደርግ ተናደድኩ መጣሁ።

### ተረክ አስራ ስምንት

እኔ አሁን ቡዳ ተብየ (በቡድንት ተጠርጥሬ) መጣሁ። ምንድን ነው እንዴት ሰውን ሰው ይበላዋል እንዴት ቡዳ አላችሁኝ ስል እንዴት ሰውን ሰው ይበላዋል እኔ በሰውነቴ የሚታወቀኝ ነገር የለም። ስኖር ይሄ ቡድንት አይታወቀኝም። ይሄ ቡድንት ምንድን ነው ስል እስቲ እንደዚህ

ያለ ጠበል አለ አሉኝ መጣሁ። ከጭልጋ ወረዳ ነው መጣሁ። አይታወቀኝም ይሄ ቡዳ። ህዝቡ ግን ያማኛል። ስታማ ደግሞ ይህንን ልጅ እንደዚህ ታለ ጠበል እንውሰደው ተባለ። ከዛ በአሜን [ፈቃደኛ] ሆኜ መጣሁ። ከመጣሁ በኋላ ደግሞ ይሄ አጋንንት እኔ ላይ እንዳለ አወኩት። ስጠመቅ አጋንንት መሆኑን አወኩት። ስለዚህ ተጠመኩ አሁን ተፈውሼ ይህንን አጋንንት አስለቅቄ በሰላም ወደ አገሬ ስሄድ ማህተም ያስፈልጋል። ይሄ አጋንንት መልቀቁን የሚያሳይ ደብዳቤ ይገኛ እሄዳለሁ። [አንተን ቡዳነት በምን መንገድ አገኘህ?] ይህንን እፅ እኮ ቅድም ሲነገር ስምተህል ሳላስበው ማለት ነው። ወይ በሚበላ ነገር ወይ በሚጠጣ ነገር እነዛ ቡዳ በፀበል አይለቅም የሚሉት ሰዎች (ጠንቋዮች) ያንን ዕፅ እኔ ለምሳሌ ለስራ፣ ለምን እንቀሳቀሳለሁ ለማደግ ማለት ነው። ግን እንዳላድግ ይጸረሩኛል። ምን ያደርጋሉ መሰለህ ወይ ከምበላው ወይ ከምጠጣው ነገር አምጥተው [ቡዳ የማድረጊያ መድሃኒት(እጽ)] ይሰጡኛል። ይሄ ቅናት ነው። እንዳላድግ ወይም አገሩ እንዲጠላኝ፣ አገር ጥየ እንድመንን ወይም ስሜ እንዲጠፋ በሚል ከምበላው፣ ከምጠጣው ወይ ከጠላው፣ ወይ ከቡናው፣ ወይ ከእንጀራው ወይ ከእርጎው ጠብ አርገው ይሰጡኛል። ያ ምን ይሆናል? አጋንንት ከዛ ሰዉ ቡዳ ይሉኛል። ቡዳ ነው ይባላል።

## ተረክ አስራ ዘጠኝ

ለምሳሌ ያህል እነ ዶክተር ደረጀ እነ ወርቁ እየሁ ሲያዋልዱ ብለው ለካ የሌላትን እርጉዝ ናትና ልትወልድ ነው ብለው የሞተች ነገር ናት። አሁን ተጠራሁ። እኔን ይዘውኝ ሄዱ። ሄድኩና ዶክተር ደረጀ ፈቀዱልኝ ገባሁ ከማዋለጃ ቤት። ወርቁም እዚያ አለ። ገባሁና ቀስ ብላ ሙታ ያበቃች ናት። መድሃኒቱን ጠጋ አድረኩባት። እነሱ ቢነሱ ቢወድቁ፣ ቢመራመሩ እንቢ አላቸው እነ ዶክተርን። ተጠቅታለች። ወስዷታል። ቀስ አድርጌ [መድሃኒቱን] በአፍንጫዋ ጠጋ አደረኩላት። ጠጋ ሳደርግለት ያን ጊዜ ብድግ አለችና ው. . ው...ው አለች። ጤና ጣቢያ ከዶክተሩ ውስጥ። አሁን ያንን አስለቀቅኩና ሳበቃ ወደ ቤቷ ሰደድናት። አሁን ዶክተር ደረጀ "ጥቁር አንበሳ ነው" የሚለኝ። አሁን ዛሬ ወርቃየ ሲጠራኝ "ጥቁር አንበሳ" ብሎ ነው ስሜን የሚጠራው።

## ተረክ ሀያ

ነገሬህለሁ እኮ መድሐኒቱን ጠጋ ሳደርግበት ብድግ ብድግ ነው የሚለው። በአልጋ መጥተው በእግራቸው ነው የሚሄዱት። እንኳን በህይወት ያሉ የሞቱ ሰዎች ሞተዋል ተብለው ሰሌን (ከፈን) ተገዝቶላቸው ጃንን.. ጃንን በፈረስ መጥቶ ሰውየው መድሐኒት ሊወስድ መጥቶ ሲነገረኝ ለሰውየው ሰሌን ተገዝቷል። ተመንደር ሁላ መርዶ ተልኳል። በየሀገሩ ተልኳል። ኋላ እስቲ እንሂድ ብለው ተጠራጥረው መጡ። በቃ ሞቷል ተብሎ እየተለቀሰ ነው። መርዶ ለለቅሶ እየተላከ ነው። ከዛ በኋላ መጡ። በዘመድ ተልከው እየበረሩ ከእኔ መጡ። እንዲያው ትረፍ ብሉት ነው መሠለኝ ያን መድሃኒት ወስደው ጠጋ ቢያደርጉለት ያ የሞተ ሰውዬ ብድግ አለ። እኔ የለሁም እዚያው ነው በሰጠኋቸው መድሃኒት የጨረሱት። ያ እንዲያ ሆነ ዳነ። አልቃሽ በየሀገሩ ተልኳል። ግን እንዲያ ሆኖ ዳነ።

## አባሪ ሁለት የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | የአቀባይ ስም | እድሜ | ፆታ | ሙያ | መረጃ የተሰጠበት መቼት | የመኖሪያ ቀበሌ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ መንገሻ ስዩም | 86 | ወ | ነጋዴና የሀገር ሽምግሌ ተወካይ | ደንቢያ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት | ቆላድባ ከተማ |
| 2 | መርጌታ አዳነ አሰፋ | 53 | ወ | የባህል ህክምና ባለሙያ | ጎንደር ዙሪያ ወረዳ እንፍራንዝ ከተማ | ስሁር ሳር ጨሀ ቀ/ገ/ማህበር |
| 3 | አቶ ታረቀኝ እምሩ | 52 | ወ | ነጋዴና የቡዳ ጥቃት አስለፍላፊ (ፈዋሽ) | በመኖሪያ ቤታቸው | ቆላድባ ከተማ |
| 4 | አቶ ወርቁ ታደሰ | 46 | ወ | የባህል ህክምና ባለሙያ | በመኖሪያ ቤታቸው | ቆላድባ ከተማ |
| 5 | ቄስ መልአከ ገነት ካሴ አለሙ | 70 | ወ | የቤተ ክርስቲያ አስተዳዳሪና አርሶ አደር | ጣቁሳ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት | ደልጊ ከተማ |
| 6 | ቄስ መልአከ ሰላም ተውህቦ ማሩ | 72 | ወ | የቤተ ክርስቲያ አስተዳዳሪና አርሶ አደር | ጭሉ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን | ጭሉ ቀ/ገ/ማህበር |
| 7 | ዘመነ ባይህ | 19 | ወ | የ 11ኛ ክፍል ተማሪ | ደልጊ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | ደልጊ ከተማ |
| 8 | እሙሀይ ፈለጉ በለጠ | 63 | ሴ | የቤተ ክርስቲያ አገልጋይ | ጭሉ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን | ጭሉ ቀ/ገ/ማህበር |
| 9 | ወ/ሮ ዘርትሁን እሸቱ | 38 | ሴ | የቤት እመቤት | ጭሉ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን | ጭሉ ቀ/ገ/ማህበር |
| 10 | አቶ ተገኝ አየለ | 52 | ወ | አርሶ አደር | ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ፀበል ቦታ | ጭልጋ ወረዳ |
| 11 | አባ ፍስሀ አባተ | 65 | ወ | ፀበል አጥማቂ | ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ፀበል ቦታ | ቆላድባ ከተማ |
| 12 | አቶ ዘመነ አስማረ | 32 | ወ | ነጋዴ | ቅ/ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ፀበል ቦታ | ቆላድባ ከተማ |
| 13 | ታድሉ አለሙ | 18 | ወ | የ 10ኛ ክፍል ተማሪ | ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ጉዛራ 2ኛ ደ/ ት/ቤት | እንፍራንዝ ከተማ |
| 14 | መኳንንት ሙላት | 18 | ወ | የ 10ኛ ክፍል ተማሪ | ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ጉዛራ 2ኛ ደ/ት/ቤት | እንፍራንዝ ከተማ |
| 15 | መዲና ሰይድ | 16 | ሴ | የ 9ኛ ክፍል ተማሪ | ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ጉዛራ 2ኛ ደ/ት/ቤት | እንፍራንዝ ከተማ |
| 16 | ገቢያሽ ማንደፍሮ | 18 | ሴ | የ 10ኛ ክፍል ተማሪ | ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ጉዛራ 2ኛ ደ/ት/ቤት | እንፍራንዝ ከተማ |
| 17 | ሰላም ጌጡ | 16 | ሴ | የ 9ኛ ክፍል ተማሪ | ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ጉዛራ 2ኛ ደ/ት/ቤት | እንፍራንዝ ከተማ |
| 18 | አቶ ደሳለኝ ሳህሌ | 51 | ወ | ማመልከቻ ፀሀፊ | ደንቢያ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት | ቆላድባ ከተማ |
| 19 | አቶ መስፍን ከበደ | 61 | ወ | አርሶ አደር | ጭሎ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን | ጭሎ ቀ/ገ/ማህበር |
| 20 | አቶ አስናቀ ዘሪሁን | 67 | ወ | አርሶ አደር | ጭሎ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን | ጭሎ ቀ/ገ/ማህበር |
| 21 | አቶ መልሴ ማሩ | 62 | ወ | አርሶ አደር | ጭሎ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን | ጭሎ ቀ/ገ/ማህበር |
| 22 | አቶ ሙሌ ፍስሀ | 34 | ወ | መምህር | ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ማክሰኝት 2ኛ ደ/መ/ት/ቤት | ማክሰኝት ከተማ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 23 | አቶ አደራጀው ዓዬ | 32 | ወ | የቪዲዮ ባለሙያ | እንፍራንዝ ከተማ | ማክሰኝት ከተማ |
| 24 | አቶ ወርቁ መልኬ | 54 | ወ | ነጋዴ | አዲስ አበባ ከተማ በመኖሪያ ቤታቸው | አዲስ አበባ |
| 25 | አቶ ናሁሰናይ አየለ | 83 | ወ | ጡረተኛ | አዲስ አበባ ከተማ አቶ ወርቁ መልኬ ቤት | እስራኤል |
| 26 | አቶ ዲበኩሉ አየለ | 60 | ወ | አልተጠቀሰም | አዲስ አበባ ከተማ አቶ ወርቁ መልኬ ቤት | እስራኤል |
| 27 | አቶ ያለው አዲስ | 35 | ወ | የመንግስት ሰራተኛ | ጎንደር ከተማ በዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ | ጎንደር ከተማ |
| 28 | ወ/ሮ የሺ መኮንን | 33 | ሴ | መምህር | ጎንደር ዙሪያ ወረዳ ጉዛራ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | እንፍራንዝ ከተማ |
| 29 | መርጌታ ንብሬ ወንዴ | 38 | ወ | የአብነት ት/ቤት መምህር | ጣቁሳ ወረዳ መኮንታ ቀበሌ ገ/ማህበር | መኮንታ ቀ/ገ/ማህበር |
| 30 | ወ/ሮ በሰጠች ነጋሽ | 42 | ሴ | የቤት እመቤት | ጣቁሳ ወረዳ መኮንታ ቀበሌ ገ/ማህበር | መኮንታ ቀ/ገ/ማህበር |
| 31 | አቶ ሰለሞን በቀለ | 29 | ወ | የጣቁሳ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሀላፊ | በቢሯቸው | ደልጊ ከተማ |
| 32 | ወ/ሮ ላሁሽ ጓዴ | 38 | ሴ | የቤት እመቤት | ጣቁሳ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት | ደልጊ ከተማ |
| 33 | ወ/ሮ ሻሼ ታዬ | 36 | ሴ | የቤት እመቤት | ደንቢያ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት | ቆላድባ ከተማ |
| 34 | ያለምርቅ ፍስሀ | 19 | ሴ | የ 11ኛ ክፍል ተማሪ | ደልጊ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት | ደልጊ ከተማ |
| 35 | መልአከ ሰላም ጌታሰው በላይ | 42 | ወ | የደንቢያ ወረዳ ቤተ ክህነት ሊቀ ካህናት | ቆላድባ ከተማ በቢሯቸው | ቆላድባ ከተማ |

## አባሪ ሶስት የፎቶ ግራፎች ዝርዝር

### 3.1 የመረጃ አቀባዮች ፎቶዎች



መርጌታ አዳነ አሰፋ የባህል ህክምና ባለሙያ



አቶ ወርቁ ታደሰ ልማዳዊ የቡዳ ጥቃት ፈዋሽ



ቄስ መልአከ ሰላም ተውህቦ ማሩ



አቶ ታረቀኝ እምሩ፤ ቡዳ አስለፍላፊ



ወይዘሮ ላሁሽ ጓዴ



አቶ መንገሻ ስዩም

3.2 የቡዳ ጥቃት መከላከያ መንገዶች የሚያሳይ



ክታብ



ቁንጮ



የቡዳ መድሃኒት



ንቅሳት፣ ብረትና የቡዳ መድሃኒት

3.3 የቡዳ ጥቃት የፈውስ ዘዴ ስርዓተ ክዋኔ



የጸበል እርጭት ስርዓት በቆላድባ ከተማ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን



ሐይማኖታዊ የቡዳ ጥቃት (ልቦናን የመመለስ) ስርዓት

ልማዳዊ የቡዳ ጥቃት የፈውስ ዘዴ ስርዓተ ክዋኔ በአቶ ወርቁ ታደሰ ፈዋሽነት



መድሃኒት ማጠጣትና የቡዳውን ማንነት መለየት



ማስለፍለፍ



ልቦናን መመለስ